የምታቀርቡት ፣ መባ ፣ ርዝመቱ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ወርዱም ፡ ሀያ ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ።
፲፫ ለእነዚህም ፡ ለክህናቱ ፡ የተቀደሰ ፡ መባ ፡ ይሆናል ፣ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ርዝመቱ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ÷ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ወርዱ ፡ አሥር ፡ ሺህ ÷ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ወርዱ ፡ አሥር ፡ ሺህ ÷ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ርዝመቱ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ። የእግዚአብሔርም ፡ መቅደስ ፡ በመካከሉ ፡ ይሆናል ።
፲፩ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በሳቱ ፡ ጊዜ ÷ ሌዋውያን ፡ እንደ ፡ ሳቱ ፡ ላልሳቱት ፡ ሥርዓቴን ፡ ለጠበቁት ፡ ከሳዶቅ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ለተቀደሱት ፡ ካህናት ፡ ይሆናል ። ከምድርም ፡ መባ ፡ የተለየ ፡ መባ ፡ ይሆንላቸዋል ÷ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የተቀደሰ ፡ ይሆናል ፡ በሌዋውያን ፡ ድንበር ፡ አጠገብ ፡ ይሆናል ።
፲፪ በካህናቱም ፡ ድንበር ፡ አንጻር ፡ ርዝመቱ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ወርዱም ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ የሆነ ፡ ዕጣ ፡ ለሴዋውያን ፡ ይሆናል ፡ ርዝመቱ ፡ ሁሉ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ወርዱም ፡ ሀያ ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ። ለእግዚአብሔርም ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፡ ከእርሱ ፡ ምንም ፡ አይሸጡም ፡ አይለውጡምም ÷ የምድሩም ፡ በኵራት ፡ አይፋለስም ።
፲፫ በሀያ ፡ አምስቱም ፡ ሺህ ፡ አንጻር ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ወርድ ፡ ያለው ፡ የቀረ ፡ ስፍራ ፡ ለከተማይቱ ፡ ለጋራ ፡ ጉዳይዋ ÷ ለመኖሪያ ፡ ለማሰማርያም ፡ ይሆናል ፡ ከተማይቱም ፡ በመካከሉ ፡ ትሆናለች ። ልክዋም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ÷ በደቡብም ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ÷ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ÷ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ። ለከተማይቱም ፡ ማሰማርያ ፡ ይኖራታል ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ÷ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ÷ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ÷ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ።
፲፰ በተቀደሰው ፡ መባ ፡ አንጻር ፡ የተረፈው ፡ ርዝመቱ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ወደ ፡ ምዕራብም ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ። በተቀደሰው ፡ መባ ፡ አንጻር ፡ ይሆናል ። ፍሬውም ፡ ከተማይቱን ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ለመብል ፡ ይሆናል ። ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ ይቱን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ያርሱታል ። መሬው ፡ ሁሉ ፡ ርዝመቱ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ወርዱም ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ፡ የተቀደሰውን ፡ መባ ፡ ከከተማይቱ ፡ ይዘታ ፡ ጋር ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ አድርጋችሁ ፡ ትሰጣላችሁ ።
፳፩ በተቀደሰው ፡ መባና ፡ በከተማይቱ ፡ ይዞታ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ የቀረው ፡ ለአለቃው ፡ ይሆናል ፡ በመባው ፡ በዚያ ፡ አምስቱ ፡ ሺህ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ድንበር ÷ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ በዚያ ፡ አምስቱ ፡ ሺህ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምዕራቡ ፡ ድንበር ÷ እንደ ፡ ዕጣ ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ፡ መጠን ÷ ለአለቃው ፡ ይሆናል ፤ የተቀደሰውም ፡ መባና ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ በመካከሉ ፡ ይሆናል ። የሌዋውያንም ፡ ርስት ፡ የከተማይቱም ፡ ይዞታ ፡ ለአለቃው ፡ በሆነው ፡ መካከል ፡ ይሆናል ፡ በይሁዳ ፡ ድንበርና ፡ በብንያም ፡ ድንበር ፡ መካከል ፡ የአለቃ ፡ ዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፳፪ ለቀሩትም ፡ ነገዶች ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለብንያም ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፳፫ ከብንያምም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለስምዖን ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፳፬ ከስምዖንም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለይሳኮር ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፳፭ ከይሳኮርም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለዛብሎን ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፳፮ ከዛብሎንም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለጋድ ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፳፯ ከጋድም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ድንበሩ ፡ ከታማር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሜሪባ ፡ ቃዴስ ፡ ውኃ ፡ እስከ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ይሆናል ።
፳፰ ርስት ፡ አድርጋችሁ ፡ ለእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ በዕጣ ፡ የምታካፍሉአት ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፥ የእያንዳንዱም ፡ ዕጣ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ÷ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።
፳፱ የከተማይቱም ፡ መውጫዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። በሰሜን ፡ ወገን ፡ ልኩ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ነው ። የከተማይቱ ፡ በሮች ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ስም ፡ ይሆናሉ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አንዱ ፡ የሮቤል ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የይሁዳ ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የሌዊ ፡ በር ÷ ሦስት ፡ በሮች ፡ ይሆናሉ ። በምሥራቁም ፡ ወገን ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ÷ ሦስትም ፡ በሮች ፡ አሉ ፡ አንዱ ፡ የዮሴፍ ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የብንያም ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የዳን ፡ በር ፡ ነው ። በደቡብም ፡ ወገን ፡ ልኩ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ÷ ሦስትም ፡ በሮች ፡ አሉ ፡ አንዱ ፡ የስምዖን ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የይሳኮር ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የዛብሎን ፡ በር ፡ ነው ። በምዕራቡም ፡ ወገን ፡ ልኩ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ÷ ሦስትም ፡ በሮች ፡ አሉ ፡ አንዱ ፡ የጋድ ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የአሴር ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የንፍታሌም ፡ በር ፡ ነው ። ዙሪያዋም ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ÷ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የከተማይቱ ፡ ስም ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ ከበባት ።
፪ ጌታም ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄምን ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ከፍሎ ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ሰናዖር ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ቤት ፡ ወሰደው ÷ ዕቃውንም ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አገባው ።
፫ ንጉሡም ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውንና ፡ መልከ ፡ መልካሞቹን ÷ በጥበብ ፡ ሁሉ ፡ የሚያስተውሉትን ፡ እውቀትም ፡ የሞላባቸውን ፡ ብልሃተኞችና ፡ አስተዋዮች ፡ የሆኑትን ÷ በንጉሡም ፡ ቤት ፡ መቆም ፡ የሚችሉትን ፡ ብላቴኖች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከነገሥታቱና ፡ ከመሳፍንቱ ፡ ዘር ፡ የመጣ ፡ ዘንድ ፡ የከለዳውያንንም ፡ ትም ህርትና ፡ ቋንቋ ፡ ያስተምሩአቸው ፡ ዘንድ ፡ ለጃንደረቦች ፡ አለቃ ፡ ለአስፋኔዝ ፡ ነገረ ።
፬ ንጉሡም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያሳድጉአቸው ፡ ዘንድ ÷ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ይቆሙ ፡ ዘንድ ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ ከሚጠጣውም ፡ ጠጅ ፡ በየዕለቱ ፡ ድርጎአቸውን ፡ አዘዘላቸው ። በእነዚህም ፡ መካከል ፡ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዳንኤልና ፡ አናንያ ፡ ሚሳኤልና ፡ አዛርያ ፡ ነበሩ ።
፭ የጃንደረቦቹም ፡ አለቃ ፡ ስም ፡ አወጣላቸው ፡ ዳንኤልን ፡ ብልጣሶር ፡ አናንያንም ፡ ሲድራቅ ፡ ሚሳኤልንም ፡ ሚሳቅ ÷ አዛርያንም ፡ አብደናጎ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።
፮ ዳንኤልም ፡ በንጉሡ ፡ መብልና ፡ በሚጠጣው ፡ ጠጅ ፡ እንዳይረክስ ፡ በልቡ ፡ አሰበ ፡ እንዳይረክስም ፡ የጃንደረቦቹን ፡ አለቃ ፡ ለመነ ።
፰ እግዚአብሔርም ፡ በጃንደረቦቹ ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡ ለዳንኤል ፡ ሞገስንና ፡ ምሕረትን ፡ ሰጠው ።
፱ የጃንደረቦቹም ፡ አለቃ ፡ ዳንኤልን ፡ መብሉንና ፡ መጠጡን ፡ ያዘዘላቸውን ፡ ጌታዬን ፡ ንጉሡን ፡ እፈራለሁ ፡ በዕድሜ ፡ እንደ ፡ እናንተ ፡ ካሉ ፡ ብላቴኖች ፡ ይልቅ ፡ ፈታችሁ ፡ ከስቶ ፡ ያየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ በራሴ ፡ ታስፈርዱብኛላችሁ ፡ አለው ።
፲ ዳንኤልም ፡ የጃንደረቦቹ ፡ አለቃ ፡ በዳንኤልና ፡ በአናንያ ፡ በሚሳኤልና ፡ በአዛርያ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ ሚልዳርን ፦ — እኛን ፡ ባሪያዎችህን ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ትፈትነን ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ የምንበላውንም ፡ ጥራጥሬ ፡ የምንጠጣውንም ፡ ውኃ ፡ ይስጡን ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእኛን ፡ ፊትና ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ የሚበሉትን ፡ የብላቴኖችን ፡ ፊት ፡ ተመልከት ፡ እንዳየኸውም ፡ ሁሉ ፡ ከባሪያዎችህ ፡ ጋር ፡ የወደድኸውን ፡ አድርግ ፡ አለው ።
፲፩ ይህንም ፡ ነገራቸውን ፡ ሰምቶ ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ፈተናቸው ።
፲፪ ከአሥር ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ ከበሉ ፡ ብላቴኖች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ፈታችው ፡ አምሮ ፡ ሥጋቸውም ፡ ወፍሮ ፡ ታዩ ።
፲፫ ሚልዳርም ፡ መብላቸውንና ፡ የሚጠጡትን ፡ ጠጅ ፡ አስቀርቶ ፡ ጥራጥሬውን ፡ ሰጣቸው ።
፲፬ ለእነዚህም ፡ ለአራቱ ፡ ብላቴኖች ፡ እግዚአብሔር ፡ በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ ሁሉ ፡ እውቀትንና ፡ ማስተዋልን ፡ ሰጣቸው ፡ ዳንኤልም ፡ በራእይና ፡ በሕልም ፡ ሁሉ ፡ አስተዋየ ፡ ነበረ ።
፲፭ እነርሱም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ ያዘዘው ፡ ቀን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ÷ የጃንደረቦቹ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሡ ፡ አገባቸው ።
፲፮ ንጉሡም ፡ በተነጋገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ከብላቴኖቹ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ዳንኤልና ፡ እንደ ፡ አናንያ ፡ እንደ ፡ ሚሳኤልና ፡ እንደ ፡ አዛርያ ፡ ያለ ፡ አልተገኘም ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።
፲፯ ንጉሡም ፡ በጠየቃቸው ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በግዛቱ ፡ ሁሉ ፡ ከሚኖሩ ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ አስማተኞች ፡ ሁሉ ፡ እነርሱ ፡ አሥር ፡ እጅ ፡ የበለጡ ፡ ሆነው ፡ አገኘቸው ።
፲፰ ዳንኤልም ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ቂሮስ ፡ መጀመርያ ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ናቡከደነፆርም ፡ በነገሠ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ናቡከደነፆር ፡ ሕልም ፡ አለመ ፤ መንፈሱም ፡ ታወከ ፡ እንቅልፉም ፡ ከእርሱ ፡ ራቀ ።
፪ ለንጉሡም ፡ ሕልሙን ፡ እንዲነግሩት ፡ ንጉሡ ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎቹንና ፡ አስማተኞቹን ፡ መተተኞቹንና ፡ ከለዳውያኑንም ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ እነርሱም ፡ ገብተው ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።
፫ ንጉሡም ፡— ሕልም ፡ አልሜአለሁ ÷ ሕልሙንም ፡ ለማወቅ ፡ መንፈሴ ፡ ታውኮአል ፡ አላቸው ።
፬ ከለዳውያኑም ፡ ንጉሡን ፡ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፡— ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ፤ ለባሪያዎችህ ፡ ሕልሙን ፡ ንገር ÷ እኛም ፡ ፍቺውን ፡ እናሳይሃለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።
፭ ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ከለዳውያኑንም ፡— ነገሩ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ርቆአል ፡ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ ባታስታውቁኝ ÷ ትቈረጣላችሁ ፡ ቤቶቻችሁም ፡ የጉድፍ ፡ መጣያ ፡ ይደረጋሉ ።
፮ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ ግን ፡ ብታሳዩ ÷ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ስጦታና ፡ ዋጋ ፡ ብዙ ፡ ክብርም ፡ ትቀበላላችሁ ፤ ስለዚህም ፡ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ አሳዩኝ ፡ አላቸው ።
፯ ሁለተኛም ፡ ጊዜ ፡ መልሰው ፡— ንጉሡ ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ሕልሙን ፡ ይንገር ÷ እኛም ፡ ፍቺውን ፡ እናሳያለን ፡ አሉት ።
፰ ንጉሡ ፡ መልሶ ፡— ነገሩ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ታውቃላችሁና ፡ ጊዜውን ፡ እንድታስረዝሙ ፡ እኔ ፡ አው

፴፩ ቃለሁ ። ሕልሙንም ፡ በታስታውቀኝ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ አለባችሁ ፡ ጊዜውን ፡ ለማሳለፍ ፡ የሐሰ ትንና ፡ የተንኰልን ፡ ቃል ፡ ልትነግሩኝ ፡ አዘጋ ጅታችኋል ፡ ስለዚህ ፡ ሕልሙን ፡ ንገሩኝ ፡ ፍቺ ውንም ፡ ማሳየት ፡ እንድትችሉ ፡ አውቃለሁ ፡ ፲ አለ ። ከለዳውያኑም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መል ሰው ፡— የንጉሡን ፡ ነገር ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ የሚ ችል ፡ ሰው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የለም ፡ ከነገሥታ ትም ፡ ታላቅና ፡ ኃይለኛ ፡ የሆነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚንና ፡ አስማተ ፲፩ ኛን ፡ ከለዳዊንም ፡ አልጠየቀም ። ንጉሡም ፡ የሚጠይቀው ፡ ነገር ፡ የቸገረ ፡ ነው ፡ መኖሪያ ቸው ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ከልሆነ ፡ ከአማልክት ፡ በቀር ፤ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ የሚያሳየው ፡ ማንም ፡ ፲፪ የለም ፡ አሉ ። ስለዚህም ፡ ንጉሡ ፡ ተበሳጨ ፡ እጅግም ፡ ተቈጣ ፡ የባቢሎንንም ፡ ጠቢባን ፡ ፲፫ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ትእዛዝም ፡ ወጣ ፡ ጠቢባንንም ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡ ዳንኤ ልንና ፡ ባልንጀሮቹንም ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ፈለ ጉአቸው ።

፲፬ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ የወጣውን ፡ የንጉ ሡን ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ አርዮክን ፡ በፈሊጥና ፲፭ በማስተዋል ፡ ተናገረው ፡ ለንጉሡም ፡ አለቃ ፡ ለአርዮክ ፡ መልሶ ፡— የንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቸኰለ ? አለው ። አርዮክም ፡ ነገሩን ፡ ፲፮ ለዳንኤል ፡ አስታወቀው ። ዳንኤልም ፡ ገብቶ ፡ ፍቺውን ፡ ለንጉሡ ፡ የሚያስታውቅበት ፡ ጊዜ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡን ፡ ለመነ ።

፲፯፤፲፰ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። ዳንኤልም ፡ ባልንጀሮቹም ፡ ከቀሩት ፡ ከባቢ ሎን ፡ ጠቢባን ፡ ጋር ፡ እንዳይሞቱ ፡ ስለዚህ ፡ ምሥጢር ፡ ምሕረትን ፡ ከሰማይ ፡ አምላክ ፡ ይለ ምኑ ፡ ዘንድ ፡ ነገሩን ፡ ለባልንጀሮቹ ፡ ለአናን ያና ፡ ለሚሳኤል ፡ ለአዛርያ ፡ አስታወቃቸው ። ፲፱ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ምሥጢሩ ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ ለዳንኤል ፡ ተገለጠለት ፡ ዳንኤልም ፡ ፳ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ አመሰገነ ። ዳንኤልም ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡— ጥበብና ፡ ኃይል ፡ ለእርሱ ፡ ነውና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከዘላ ፳፩ ለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ይባረክ ። ጊዜያትንና ፡ ዘመናትን ፡ ይለውጣል ፡ ነገሥታትን ፡ ያፈል ሳል ፡ ነገሥታትንም ፡ ያስነሣል ፡ ጥበብን ፡ ለጠ ቢባን ፡ እውቀትንም ፡ ለአስተዋዮች ፡ ይሰጣል ። ፳፪ የጠለቀውንና ፡ የተሠወረውን ፡ ይገልጣል ፤ በጨለማ ፡ ያለውን ፡ ያውቃል ፥ ብርሃንም ፡ ከእ ፳፫ ርሱ ፡ ጋር ፡ ነው ። ጥበብንና ፡ ኃይልን ፡ የሰጠ ኸኝ ፡ አኖም ፡ የለመንንህን ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ያስ ታወቅኸኝ ፥ አንተ ፡ የአባቶቼ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የንጉሡን ፡ ነገር ፡ አስታውቀኸኛልና ፡ እገዛል ፳፬ ሃለሁ ፡ አመሰግንህማለሁ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዳንኤል ፡ ንጉሡ ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወዳዘዘው ፡ ወደ ፡ አርዮክ ፡ ገባ ፡ በገባም ፡ ጊዜ ፡— የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ አታጥፋ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስገባኝ ፥ እኔም ፡ ፍቺውን ፡ ለንጉሡ ፡ እሳያለሁ ፡ አለው ።

፳፭ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አርዮክ ፡ ዳንኤልን ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስገበውና ፡— ከይሁዳ ፡ ምርኮ ኞች ፡ ያለውን ፡ ለንጉሡ ፡ ፍቺውን ፡ የሚያስ ታውቀውን ፡ ሰው ፡ አግኝቼአለሁ ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ብልጣሶርም ፡ የሚባለውን ፡ ፳፮ ዳንኤልን ፡— ያየኩትን ፡ ሕልምና ፡ ፍቺውን ፡ ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለህን ? አለው ። ዳንኤልም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ፳፯ አለ ፡— ንጉሡ ፡ የጠየቀውን ፡ ምሥጢር ፡ ጠቢ ባንና ፡ አስማተኞች ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ ቃላተኞች ፡ ለንጉሡ ፡ ያሳዩ ፡ ዘንድ ፡ አይች ሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምሥጢር ፡ የሚገልጥ ፡ ፳፰ አምላክ ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፥ እርሱም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሚሆነውን ፡ ለንጉሡ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ አስታውቆታል ። በአልጋህ ፡ ላይ ፡ የሆነው ፡ ሕልምና ፡ የራስህ ፡ ራእይ ፡ ይህ ፳፱ ነው ። አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ የሚሆነው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአልጋህ ፡ ላይ ፡ ታስብ ፡ ነበር ፤ ምሥጢርንም ፡ የሚገልጠው ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ አስታውቆሃል ። ነገር ፡ ግን ፴ ፡ ይህ ፡ ምሥጢር ፡ ለእኔ ፡ መገለጡ ፡ ፍቺው ፡ ለንጉሡ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፥ አንተም ፡ የልብህን ፡ አሳብ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሉ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ በጥበብ ፡ ስለ ፡ በለጥሁ ፡ አይደለም ።

፴፩ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ታላቅ ፡ ምስል ፡ አየህ ፤ ይህም ፡ ምስል ፡ ታላቅና ፡ ብልጭልጭ ታው ፡ የበዛ ፡ ነበረ ፥ በፊትህም ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ ፴፪ መልኩም ፡ ግሩም ፡ ነበረ ። የዚህም ፡ ምስል ፡ ራስ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፥ ደረቱና ፡ ክንዶቹም ፡ ብር ፥ ፴፫ ሆዱና ፡ ወገቡም ፡ ናስ ፥ ጭኖቹም ፡ ብረት ፥ አግሮቹም ፡ እኩሉ ፡ ብረት ፡ እኩሉም ፡ ሸክላ ፡ ነበረ ። ፴፬ እጅም ፡ ሰይነካው ፡ ድንጋይ ፡ ከተራ ራው ፡ ተፈንቅሎ ፡ ከብረትና ፡ ከሸክላ ፡ የሆነ ውን ፡ የምስሉን ፡ እግሮች ፡ ሲመታና ፡ ሲፈጭ ፡ አየህ ። ፴፭ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብረቱና ፡ ሸክላው ፥ ናሱና ፡ ብሩ ፡ ወርቁም ፡ በአንድነት ፡ ተፈጩ ፥ በመከርም ፡ ጊዜ ፡ በአውድማ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ እብቅ ፡ ሆነ ፡ ነፋስም ፡ ወሰደው ፥ ቦታውም ፡ አልታወቀም ፤ ምስሉንም ፡ የመታ ፡ ድንጋይ ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ሆነ ፡ ምድርንም ፡ ፈጽሞ ፡ ሞላ ።

፴፮ ሕልሙ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ ፍቺውን ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ እንናገራለን ። ፴፯ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ መንግሥትንና ፡ ኃይልን ፥ ብርታትንና ፡ ክብርን ፡ የሰጠህ ፡ የንጉሥ ፴፰ ታት ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህ ። በሚቀመጡበ ትም ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ልጆችንና ፡ የም ድር ፡ አራዊትን ፡ የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ በእጅህ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶሃል ፥ ለሁሉም ፡ ገዥ ፡ አድርጎ ፡ ሃል ፡ አንተ ፡ የወርቁ ፡ ራስ ፡ ነህ ። ከአንተም ፡ ፴፱ በኋላ ፡ ከአንተ ፡ የሚያንስ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ ይነሣል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ የናስ ፡ መንግ ፵ ሥት ፡ ይነሣል ። አራተኛውም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉን ፡ እንደሚቀጠቅጥና ፡ እንደሚያደቅቅ ፡ ብረት ፡ ይበረታል ፡ እነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ሚፈጭ ፡ ብረት ፡ ይቀጠቅጣል ፡ ያፈጭማል ። ፵፩ እግሮቹና ፡ ጣቶቹም ፡ አኩሉ ፡ ሸክላ ፡ አኩሉም ፡ ብረት ፡ ሆኖ ፡ እንዳየህ ፡ እንዲሁ ፡ የተከፋፈለ ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ፡ ብረቱም ፡ ከሸክላው ፡ ጋር ፡ ተደበልቆ ፡ እንዳየሁ ፥ የብረት ፡ ብርታት ፡ ፵፪ ለእርሱ ፡ ይሆናል ። የእግሮቹም ፡ ጣቶች ፡ እኩሉ ፡ ብረት ፡ እኩሉም ፡ ሸክላ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፥ እንዲሁ ፡ መንግሥቱ ፡ እኩሉ ፡ ብርቱ ፡ እኩሉ ፡ ፵፫ ደካማ ፡ ይሆናል ። ብረቱም ፡ ከሸክላው ፡ ጋር ፡ ተደበልቆ ፡ እንዳየህ ፥ እንዲሁ ፡ ከሰው ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ ይደበለቃሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብረት ፡ ከሸ ክላ ፡ ጋር ፡ እንደማይጣበቅ ፥ እንዲሁ ፡ እርስ ፡ ፵፬ በርሳቸው ፡ አይጣበቁም ። በእነዚያም ፡ ነገሥ ታት ፡ ዘመን ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ለዘላለም ፡ የማይፈርስ ፡ መንግሥት ፡ ያስነሣል ፡ ለሌላ ፡ ሕዝብም ፡ የማይሰጥ ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ፤ እነዚያንም ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ትፈጫቸ ዋለች ፡ ታጠፋቸውማለች ፥ ለዘላለምም ፡ ትቆ ፵፭ ማለች ። ድንጋዩም ፡ እጅ ፡ ሳይነካው ፡ ከታ ራሙ ፡ ተፈንቅሎ ፡ ብረቱንና ፡ ናሱን ፡ ሸክላው ንና ፡ ብሩን ፡ ወርቁንም ፡ ሲፈጨው ፡ እንዳ የህ ፥ እንዲሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚሆነውን ፡ ታላቁ ፡ አምላክ ፡ ለንጉሡ ፡ አስታውቆታል ፡ ሕልሙም ፡ እውነተኛ ፡ ፍቺውም ፡ የታመነ ፡ ነው ።

፵፮ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነፆር ፡ በግ ምባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ለዳንኤል ፡ ሰገደለት ፥ የእህ ሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ ያቀርቡለት ፡ ፵፯ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ንጉሡም ፡ ዳንኤልን ፡— ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ተችሎሃልና ፡ በእ ውነት ፡ አምላካችሁ ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፥ የነገሥታትም ፡ ጌታ ፥ ምሥጢርም ፡ ገላጭ ፡ ፵፰ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። ንጉሡም ፡ ዳንኤልን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፥ ብዙም ፡ ታላቅ ፡ ስጦታ ፡ ሰጠው ። ፵፱ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ፥ በባቢሎንም ፡ ጠቢባን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ዋነኛ ፡ አለቃ ፡ አደረገው ። ዳንኤልም ፡ ንጉ ሡን ፡ ለመነ ፥ እርሱም ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳ ቅን ፡ አብደናጎንም ፡ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሾማቸው ፡ ዳንኤል ፡ ግን ፡ በን ጉሡ ፡ በር ፡ ነበረ ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ ንጉሡ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ቁመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ የሆነውን ፡ የወር ቁን ፡ ምስል ፡ አሠራ ፡ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ ፪ በዱራ ፡ ሜዳ ፡ አቆመው ። ንጉሡም ፡ ናቡከደ ነፆር ፡ መኳንንትንና ፡ ሹማምቶችን ፥ አዛዦች ንና ፡ አዛውንቶችን ፥ በጅሮንዶችንና ፡ አማካ

ሪዎችን ፥ መጋቢዎችንም ፥ አውራጃ ፡ ገዦ ችንም ፡ ሁሉ ፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡም ፡ ናቡከደነፆር ፡ ላቆመው ፡ ምስል ፡ ምረቃ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ላከ ። ፫ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ መኳ ንንቱና ፡ ሹማምቶቹ ፥ አዛገሮቹና ፡ አዛውንቶቹ ፥ በጅሮንዶቹና ፡ አማካሪዎቹ ፥ መጋቢዎቹና ፡ አው ራጃ ፡ ገዦቹ ፡ ሁሉ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ላቆመው ፡ ምስል ፡ ምረቃ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ናቡከ ደነፆርም ፡ በቆመው ፡ ምስል ፡ ፊት ፡ ቆሙ ። ፬ አዋጅ ፡ ነጋሪውም ፡ እየጮኸ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፭ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የምትናገሩ ፡ ሆይ ፥ የመለከትንና ፡ የእንቢል ፮ ታን ፥ የመሰንቆንና ፡ የክራርን ፥ የበገናንና ፡ የዋሽንትን ፥ የዘፈንንም ፡ ሁሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ችሁ ፡ ጊዜ ፥ ተደፍታችሁ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነ ፆር ፡ ላቆመው ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንድትሰ ግዱ ፡ ታዝዛችኋል ፡ ተደፍቶም ፡ የማይሰግድ ፯ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሚነድድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ይጣላል ። ፰ ስለዚህ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አሕ ዛብ ፡ ሁሉ ፡ የመለከቱንና ፡ የእንቢልታውን ፥ የመሰንቆውንና ፡ የክራሩን ፥ የበገናውንና ፡ የዘ ፈኑንም ፡ ሁሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ ወገኖ ችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የተና ገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተደፉ ፥ ንጉሡም ፡ ናቡከደነፆር ፡ ላቆመው ፡ ለወርቅ ፡ ምስል ፡ ሰገዱ ።

፲ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከለዳውያን ፡ ቀርበው ፡ ፲፩ አይሁድን ፡ ከሰሱ ። ለንጉሡም ፡ ለናቡከደነ ፆር ፡ ተናገሩ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ፡— ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ። ፲፪ ሆይ ፥— ላከትንና ፡ የእንቢልታን ፥ የመሰ ንቆንና ፡ ነዘራርን ፥ የበገናንና ፡ የዋሽንትን ፥ የዘፈንንም ፡ ሁሉ ፡ ድምፅ ፡ የሚሰማ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተደፍቶ ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ ይሰገድ ፡ ተደፍቶም ፡ የማይሰግድ ፡ በሚነድድ ፡ እሳት ፲፫ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ይጣላል ፡ ብለህ ፡ አዘዝህ ። በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሾምሃቸው ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ አብደናጎም ፡ የሚ ባሉ ፡ አይሁድ ፡ አሉ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝህን ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ፡ አማልክ ትህን ፡ አያመልኩም ፥ ላቆምኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ አይሰግዱም ። ፲፭ ናቡከደነፆርም ፡ በብስጭትና ፡ በቍጣ ፡ ሲድ ራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ አብደናጎንም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ እነዚህንም ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ አመጡአቸው ። ፲፮ ናቡከደነፆ ርም ፡— ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ አብደናጎም ፡ ሆይ ፥ አምላኬን ፡ አለማምለካችሁ ፡ ላቆምሁ ትም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ አለመስገዳችሁ ፡ እው ነት ፡ ነውን ? አሁንም ፡ የመለከቱንና ፡ የእንቢ ፲፯ ልታውን ፡ የመሰንቆውንና ፡ የክራሩን ፡ የበገና ውንና ፡ የዋሽንቱን ፡ የዘፈኑንም ፡ ሁሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ተደፍታችሁ ፡ ላሠራሁት ፡ ምስል ፡ ብትሰግዱ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በትሰ ግዱ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በሚነድድ ፡ እሳት ፡

እቶን ፡ ውስጥ ፡ ትጣላላችሁ ፡ ከእጁስ ፡ የሚያ
ድናችሁ ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡ ተናገራ
፲፭፡ ቸው ። ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ አብደናጎም ፡
መለሱ ፡ ንጉሡንም ፦ ናቡከደነፆር ፡ ሆይ ፡
በዚህ ፡ ነገር ፡ እንመልስልህ ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ
፲፮፡ ያችን ፡ አይደለም ። የምናመልከው ፡ አምላክ
ችን ፡ ከሚነድደው ፡ ከእሳቱ ፡ እቶን ፡ ያድነን ፡
ዘንድ ፡ ይችላል ፡ ከእጅህም ፡ ያድነናል ። ንጉሥ ፡
፲፯፡ ሆይ ! ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እርሱ ፡ ባያ
ድነን ፡ አማልክትህን ፡ እንዳናመልክ ፡ ላቆም
ኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንዳንሰግድለት ፡
እወቅ ፡ አሉት ።

፲፰፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ናቡከደነፆር ፡ በሲድራቅና ፡
በሚሳቅ ፡ በአብደናጎም ፡ ላይ ፡ ቊጣ ፡ ሞላ
በት ፡ የፊቱም ፡ መልክ ፡ ተለወጠባቸው ፡ እር
ሱም ፡ ተናገረ ፡ የእቶንም ፡ እሳት ፡ ይነድድ ፡
ከነበረው ፡ ይልቅ ፡ ሰባት ፡ እጥፍ ፡ አድርገው ፡
፲፱፡ እንዲያነድዱት ፡ አዘዘ ። ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅ
ንም ፡ አብደናጎንም ፡ ያስሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደሚነ
ድድም ፡ ወደ ፡ እቶን ፡ እሳት ፡ ይጥሉአቸው ፡
ዘንድ ፡ በሠራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ ከነበሩት ፡ ኃያላን ፡
፳፩፡ አዘዘ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከሰ
ናፈላቸውና ፡ ከቀሚሳቸው ፡ ከመጐናጸፊያቸ
ውም ፡ ከቀረውም ፡ ልብሳቸው ፡ ጋር ፡ ታስ
ረው ፡ በሚነድድ ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡
፳፪፡ ተጣሉ ። የንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ አስቸኳይ ፡ ስለ ፡
ሆነ ፡ የእቶኑም ፡ እሳት ፡ እጅግ ፡ ስለሚነድድ ፡
ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ አብደናጎንም ፡ የጣሉ
አቸውን ፡ ሰዎች ፡ የእሳቱ ፡ ወላፈን ፡ ገደላቸው ።
፳፫፡ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡
አብደናጎም ፡ ታስረው ፡ በሚነድድው ፡ በእቶኑ ፡
እሳት ፡ ውስጥ ፡ ወደቁ ።

፳፬፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ተደ
ነቀ ፡ ፈጥኖም ፡ ተነሣ ፡ አማካሪዎቹንም ፦ ሦስት ፡
ሰዎች ፡ አስረን ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ጥለን ፡ አል
ነበረምን ? ብለው ፡ ተናገራቸው ። እነርሱም ፦
ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለን
፳፭፡ ጉሡ ፡ መለሱለት ። እርሱም ፦ እነሆ ፡ እኔ ፡ የተ
ፈቱ ፡ በእሳቱም ፡ መካከል ፡ የሚመላለሱ ፡
አራት ፡ ሰዎች ፡ አያለሁ ፡ ምንም ፡ አላቈሰሳቸ
ውም ፡ የአራተኛውም ፡ መልክ ፡ የአማልክትን ፡
፳፮፡ ልጅ ፡ ይመስላል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። የዚያን ፡
ጊዜም ፡ ናቡከደነፆር ፡ ወደሚነድደው ፡ ወደ ፡
እሳቱ ፡ እቶን ፡ በር ፡ ቀርቦ ፦ እናንተ ፡ የል
ውል ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡
አብደናጎም ፡ ኑ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።
ሲድራቅና ፡ ሚሳቅም ፡ አብደናጎም ፡ ከእሳቱ ፡
፳፯፡ መካከል ፡ ወጡ ። መሳፍንቱና ፡ ሹማምቶቹም ፡
አዛዦቹና ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪዎች ፡ ተሰብስ
በው ፡ እሳቱ ፡ በእነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ኀከል ፡ ላይ ፡
ኃይል ፡ እንዳልነበረው ፡ የራሳቸውም ፡ ጠጕር ፡
እንዳልተቃጠለች ፡ ሰናፈላቸውም ፡ እንዳልተ
ለወጠ ፡ የእሳቱም ፡ ሽታ ፡ እንዳልደረሰባቸው ፡
አዩ ።

ናቡከደነፆርም ፡ መልሶ ፦ መልአኩን ፡ የላከ ፡ ፳፰፡
ከአምላካቸውም ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ አምላክ ፡
እንዳያመልኩ ፡ ለእርሱም ፡ እንዳይሰግዱ ፡ ሰው
ነታቸውን ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡትን ፡ የንጉሡ
ንም ፡ ቃል ፡ የተላለፉትን ፡ በእርሱ ፡ የታመኑ
ትን ፡ በሪያዎቹን ፡ ያዳነ ፡ የሲድራቅና ፡ የሚ
ሳቅ ፡ የአብደናጎም ፡ አምላክ ፡ ይባረክ ። እኔም ፡ ፳፱፡
እንደዚህ ፡ የሚያድን ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡
በሲድራቅና ፡ በሚሳቅ ፡ በአብደናጎም ፡ አም
ላክ ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ ወገንና ፡
ሕዝብ ፡ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡
ይቈረጣሉ ፡ ቤቶቻቸውም ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፡
ይደረጋሉ ፡ ብዬ ፡ አዝዣለሁ ፡ አለ ። የዚያን ፡ ፴፡
ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ አብ
ደናጎንም ፡ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋቸው ።

ምዕራፍ ፬ ።

ከንጉሡ ፡ ከናቡከደነፆር ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ፩፡
ወደሚቀመጡ ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡
ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ ወደሚናገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡
ይብዛላችሁ ። ፪፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ በፊቴ ፡ ያደ ፪፡
ረገውን ፡ ተአምራቱንና ፡ ድንቁን ፡ አሳያችሁ ፡
ዘንድ ፡ ወድኃለሁ ። ፫፡ ተአም ፡ ራቱ ፡ እንዴት ፡ ፫፡
ታላቅ ፡ ነው ! ድንቁም ፡ እንዴት ፡ ጽኑ ፡ ነው ! ፡
መንግሥቱም ፡ የዘላለም ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ ፡
ግዛቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

እኔ ፡ ናቡከደነፆር ፡ በቤቴ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ፬፡
በአዳራሽም ፡ ተመችቶኝ ፡ ነበር ። ሕልም ፡ ፭፡
አለምሁ ፡ እርስዋም ፡ አስፈራችኝ ፡ በአልጋ
ዬም ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ አሳቤና ፡ የራሴ ፡ ራእይ ፡
አስፈሩኝቱ ። ፮፡ ስለዚህ ፡ የሕልሙን ፡ ፍቺ ፡ ፮፡
እንዲያስታውቁኝ ፡ የባቢሎን ፡ ጠቢባን ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ እኔ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝሁ ። ፯፡ የዚያን ፡ ፯፡
ጊዜም ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎቹና ፡ አስማተ
ኞቹ ፡ ከለዳውያኑና ፡ ቃላተኞቹ ፡ ገቡ ፡ ሕልሙ
ንም ፡ በፊታቸው ፡ ተናገርሁ ። ፍቺውን ፡ ግን ፡
አላስታወቁኝም ። ፰፡ በመጨረሻም ፡ የቅዱሳን ፡ ፰፡
አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ አምላኬ ፡
ስም ፡ ብልጣሶር ፡ የሚባለው ፡ ዳንኤል ፡ በፊቴ ፡
ገባ ፡ እኔም ፡ ሕልሙን ፡ ነገርሁት ፡ እንዲህም ፡
አልሁት ፦ ፱፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎች ፡ አለቃ ፡ ፱፡
ብልጣሶር ፡ ሆይ ፡ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መን
ፈስ ፡ በአንተ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ከምሥጢ
ርም ፡ ሁሉ ፡ የሚያስቸግርህ ፡ እንደሌለ ፡ አው
ቄአለሁና ፡ ያለምሁትን ፡ የሕልሜን ፡ ራእይ ፡
ፍቺውንም ፡ ንገረኝ ። ፲፡ የራሴ ፡ ራእይ ፡ በአል ፲፡
ጋዬ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ እነሆ ፡ በምድር ፡ መካ
ከል ፡ ዛፍ ፡ አየሁ ፡ ቁመቱም ፡ እጅግ ፡ ረጅም ፡
ነበረ ። ፲፩፡ ዛፉም ፡ ትልቅ ፡ ሆነ ፡ በረታም ፡ ቁመ ፲፩፡
ቱም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ፡ መልኩም ፡ እስከ ፡
ምድር ፡ ሁሉ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ታየ ። ፲፪፡ ቅጠሉም ፡ ፲፪፡
የተዋበ ፡ ነበረ ፡ ፍሬውም ፡ ብዙ ፡ ነበረ ፡ ለሁ
ሉም ፡ መብል ፡ ነበረበት ፡ ከጥላውም ፡ በታች ፡

የምድር ፡ አራዊት ፡ ያርፉበት ፡ ነበር ፡ በቅርን ፲፫፡
ጫፎቹም ፡ ውስጥ ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይቀ
መጡ ፡ ነበር ፡ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡
፲፬፡ ይበላ ፡ ነበር ። በአልጋዬም ፡ ላይ ፡ በራሴ ፡
ራእይ ፡ አየሁ ፡ እነሆም ፡ አንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጠባቂ ፡
፲፭፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ። በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየ
ጮኸ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ዛፉን ፡ ቍረጡ ፡ ቅር
ንጫፎቹንም ፡ ጨፍጭፉ ፡ ቅጠሎቹንም ፡ አራ
ግፉ ፡ ፍሬውንም ፡ በትኑ ፡ አራዊትም ፡ ከበ
፲፮፡ ታቹ ፡ ወፎቹም ፡ ከቅርንጫፉ ፡ ይሸሹ ። ነገር ፡
ግን ፡ ጉቶውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ተዉት ፡
በመስክም ፡ ውስጥ ፡ በብረትና ፡ በናስ ፡ ማሰሪያ ፡
ታስሮ ፡ ይቈይ ፡ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ይረስርስ ፡
እድል ፡ ፈንታውም ፡ በምድር ፡ ሣር ፡ ውስጥ ፡
፲፯፡ ከአራዊት ፡ ጋር ፡ ይሁን ። ልቡም ፡ ከሰው ፡
ልብ ፡ ይለወጥ ፡ የአውሬም ፡ ልብ ፡ ይሰጠው ፡
፲፯፡ ሰባት ፡ ዘመንም ፡ ይለፋበት ። ልዑሉ ፡ በሰ
ዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፡ ለወደ
ደውም ፡ እንዲሰጠው ፡ ከሰውም ፡ የተዋረደ
ውን ፡ እንዲሾምበት ፡ ሕያዋን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡
ይህ ፡ ነገር ፡ የጠባቂዎች ፡ ትእዛዝ ፡ ይህም ፡
፲፰፡ ፍርድ ፡ የቅዱሳን ፡ ቃል ፡ ነው ። እኔ ፡ ንጉሡ ፡
ናቡከደነፆር ፡ ይህን ፡ ሕልም ፡ አልሜአለሁ ፡
አንተም ፡ ብልጣሶር ፡ ፍቺውን ፡ አስታውቀኝ ፡
የመንግሥቴ ፡ ጠቢባን ፡ ሁሉ ፡ ፍቺውን ፡ ያስታ
ውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉምና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቅ
ዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ በአንተ ፡ ውስጥ ፡
አለና ፡ አንተ ፡ ትችላለህ ።

፲፱፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብልጣሶር ፡ የተባለው ፡ ዳን
ኤል ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ አሰበ ። ልቡም ፡
ታወከ ። ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፡
ሕልሙና ፡ ፍቺው ፡ አያስቸግርህ ፡ አለው ።
ብልጣሶርም ፡ መልሶ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡
ሕልሙ ፡ ለሚጠሉህ ፡ ፍቺውም ፡ ለጠላቶችህ ፡
፳፡ ይሁን ። ትልቅ ፡ የነበረው ፡ የበረታውም ፡ ቁመ
ቱም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ የደረሰው ፡ መልኩም ፡
፳፩፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ድረስ ፡ የታየው ፡ ቅጠ
ሉም ፡ አምሮ ፡ የነበረው ፡ ፍሬውም ፡ የበዛው ፡
ለሁሉም ፡ መብል ፡ የነበረበት ፡ በበታቹም ፡
የምድር ፡ አራዊት ፡ የተቀመጡ ፡ በቅርንጫፎ
ቹም ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ያደሩበት ፡ ያየኸው ፡
፳፪፡ ዛፍ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እርሱ ፡ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡
የሆንህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ታላቅነትህ ፡ በገዛዳል ፡
እስከ ፡ ሰማይም ፡ ደርሶአል ፡ ግዛትህም ፡ እስከ ፡
፳፫፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ነው ። ንጉሡም ፡ ከሰ
ማይ ፡ የመረደውንና ፡ — ዛፉን ፡ ቍረጡ ፡ አጥ
ፉትም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጉቶውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ተዉት ፡ በብረትና ፡ በናስ ፡ ማሰሪያ ፡ ታስሮ ፡
በመስክ ፡ ውስጥ ፡ ይቈይ ፡ በሰማይም ፡ ጠል ፡
ይረስርስ ፡ ዕድል ፡ ፈንታውም ፡ እስከ ፡ ያልፉበት ፡
ድረስ ፡ እድል ፡ ፈንታው ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡
ጋር ፡ ይሁን ፡ ያለውን ፡ ቅዱስ ፡ ጠባቂ ፡ ማየቴ ፡
፳፬፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ፍቺው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በጌታዬ ፡
በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የወረደው ፡ የኤውሉ ፡ ትእዛዝ ፡
ነው ፡ ልዑሉም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡
፳፭፡ እንዲሠለጥን ፡ ለሚወድደውም ፡ እንዲሰጠው ፡
እስክታውቅ ፡ ድረስ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይተህ ፡
ትሰደዳለህ ፡ መኖሪያህም ፡ ከምድር ፡ አራ
ዊት ፡ ጋር ፡ ይሆናል ፡ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡
ትበላ ፡ ዘንድ ፡ ትገደዳለህ ፡ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡
፳፮፡ ያልፉብሃል ፡ አለው ። በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ነገሩ ፡
ፈጸመ ፡ በናቡከደነፆር ፡ ላይ ፡ ፳፫፡
ደረሰ ፡ ጠቦሩም ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ጥፍሩም ፡
እንደ ፡ ወፎች ፡ እስኪረዝም ፡ ድረስ ፡ ከሰዎች ፡
ተለይቶ ፡ ተሰደደ ፡ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ በላ ፡
አካሉም ፡ በሰማይ ፡ ጠል ፡ ረሰረሰ ።

ዘመኑም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ናቡከደ ፴፬፡
ነፆር ፡ ዓይኔን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አነሣሁ ፡ አእም
ሮዬም ፡ ተመለሰልኝ ፡ ልዑሉንም ፡ ባረክሁ ፡
ለዘላለምም ፡ የሚኖረውን ፡ አመሰገንሁ ፡ አከበር
ሁትም ፡ ግዛቱ ፡ የዘላለም ፡ ግዛት ፡ ነውና ፡ መን
ግሥቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነውና ። ፴፭፡ በምድርም ፡ ፴፭፡
የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ይቈጠሩ ፡
በሰማይም ፡ ሠራዊት ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ በሚ
ኖሩ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፡
እጁንም ፡ የሚከለክላት ፡ ወይም ፡ — ምን ፡ ታደ
ርጋለህ ? የሚለው ፡ የለም ። ፴፮፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ፴፮፡
አእምሮዬ ፡ ተመለሰልኝ ፡ ለመንግሥቴም ፡
ክብር ፡ ግርማዬና ፡ ውበቴ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመ
ለሰ ፡ አማካሪዎቼና ፡ መኳንንቶቼም ፡ ፈለጉኝ ፡
በመንግሥቴም ፡ ውስጥ ፡ ጸናሁ ፡ ብዙም ፡
ክብር ፡ ተጨመረልኝ ። ፴፯፡ አሁንም ፡ እኔ ፡ ናቡከ ፴፯፡
ደነፆር ፡ የሰማዩን ፡ ንጉሥ ፡ አመሰግናለሁ ፡
ታላቅም ፡ አደርገዋለሁ ፡ አከብረውማለሁ ።

ሥራው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ÷ መንገዱም ፡ ፍርድ ፡ ነውና ÷ በትዕቢትም ፡ የሚሄዱትን ፡ ያዋርድ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልና ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ንጉሡ ፡ ብልጣሶር ፡ ለሺህ ፡ መኳንንቶቹ ፡ ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ÷ በሺሁም ፡ ፊት ፡ የወ
፪ ይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ። ብልጣሶርም ፡ የወ ይን ፡ ጠጅ ፡ በቀመሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡና ፡ መኳንን ቶቹ ፡ ሚስቶቹና ፡ ቁባቶቹ ፡ ይጠጡበቸው ፡ ዘንድ ፡ — አባቴ ፡ ናቡከደነፆር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ መቅደስ ፡ ያመጣቸውን ፡ የወርቁ ንና ፡ የብሩን ፡ ዕቃዎች ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።
፫ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የመጡትን ፡ የወርቁን ፡ ዕቃዎች ፡ አመጡ ፤ ንጉሡና ፡ መኳ ንንቶቹም ፡ ሚስቶቹና ፡ ቁባቶቹም ፡ ጠጡባ
፬ ቸው ። የወይን ፡ ጠጅም ፡ እየጠጡ ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ከናስና ፡ ከብረት ፡ ከእንጨትና ፡ ከድን ጋይ ፡ የተሠሩትን ፡ አማልክት ፡ አመሰገኑ ።
፭ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ጣቶች ፡ ወጥ ተው ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ በተለሰነው ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ በመቅረዙ ፡ አንጻር ፡ ጻፉ ፤ ንጉሡም ፡ የሚ
፮ ጽፉትን ፡ ጣቶች ፡ አየ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የን ጉሡ ፡ ፊት ፡ ተለወጠበት ÷ አሳቡም ፡ አስቸገ ረው ÷ የወገቡም ፡ ጅማቶች ፡ ተፈቱ ÷ ጕልበ
፯ ቶቹም ፡ ተብረከረኩ ። ንጉሡም ፡ አስማተኞ ቹንና ፡ ከለዳውያኑን ፡ ቃላተኞቹንም ፡ ያገቡ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። ንጉሡም ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ — ይህን ፡ ጽሕፈት ፡ ያነ በብ ፡ ፍቺውንም ፡ ያሳየኝ ፡ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ ይለብሳል ÷ የወርቅም ፡ ማርዳ ፡ በአንገቱ ፡ ይሆንለታል ÷ በመንግሥትም ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዥ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንጉሡ ፡ ጠቢባን ፡ ሁሉ ፡ ገቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጽሕ ፈቱን ፡ ያነብቡ ÷ ፍቺውንም ፡ ለንጉሡ ፡ ያስ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።
፰ ንጉሡም ፡ ብልጣሶር ፡ እጅግ ፡ ደነገጠ ÷ ፊቱም ፡ ተለወጠበት ÷ መኳንንቶቹም ፡ ተደናገጡ ።
፱ ንግሥቲቱም ፡ ስለ ፡ ንጉሡና ፡ ስለ ፡ መኳን ንቱ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ግብዣ ፡ ቤት ፡ ገባች ፤ ንግ ሥቲቱም ፡ ተናገረች ፡ እንዲህም ፡ አለች ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ፤ አሳብህ
፲፩ አያስቸግርህ ÷ ፊትህም ፡ አይለወጥ ። የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በመንግ ሥትህ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፤ በአባትህም ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ አማልክት ፡ ጥበብ ፡ ያለ ፡ ጥበብና ፡ ማስ ተዋል ፡ እውቀትም ፡ ተገኝበት ፤ አባትህ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነፆር ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎ ችና ፡ የእስማተኞች ፡ የከለዳውያንና ፡ የቃላ
፲፪ ተኞች ፡ አለቃ ፡ አደረገው ። መልካም ፡ መን ፈስ ÷ እውቀትም ÷ ማስተዋልም ÷ ሕልምንም ፡ መተርጐም ÷ እንቈቅልሽንም ፡ መግለጥ ÷ የተ ቋጠረውንም ፡ መፍታት ፡ ንጉሡ ፡ ስሙን ፡ ብል ጣሶር ፡ ብሎ ፡ በሰየመው ፡ በዳንኤል ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቶአልና ። አሁንም ፡ ዳንኤል ፡ ይጠራ ÷ እርሱም ፡ ፍቺውን ፡ ያሳያል ።
፲፫ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገባ ። ንጉሡም ፡ ተናገረው ፡ ዳንኤልም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ — ንጉሡ ፡ አባቴ ፡ ከይሁዳ ፡ ከማረካቸው ፡ ከይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ የሆንህ ፡
፲፬ ዳንኤል ፡ አንተ ፡ ነህን ? የአማልክት ፡ መን ፈስ ፡ እንዳለብህ ÷ እውቀትና ፡ ማስተዋልም ፡ መልካምም ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ ተገኘብህ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ሰምቻለሁ ። አሁንም ፡ ይህን ፡ ጽሕ
፲፭ ፈት ፡ ያነብቡ ፡ ዘንድ ÷ ፍቺውንም ፡ ያስታው ቁኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠቢባንና ፡ አስማተኞች ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ገብተው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የነገሩን ፡ ፍቺ ፡ ያሳየ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ። አንተ ፡ ግን ፡
፲፮ ፍቺን ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ÷ የተቋጠረንም ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ እንድትችል ፡ ሰምቻለሁ ፤ አሁንም ፡ ጽሕፈቱን ፡ ታነብብ ፡ ዘንድ ÷ ፍቺውንም ፡ ታስ ታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ብትችል ÷ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ ትለብሳለህ ÷ የወርቅም ፡ ማርዳ ፡ በአንገትህ ፡ ዙሪያ ፡ ይሆንልሃል ÷ አንተም ፡ በመንግሥት ፡
፲፯ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዥ ፡ ትሆናለህ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ መለሰ ፡ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ — ስጦታህ ፡ ለአንተ ፡ ይሁን ÷ በረከትህንም ፡ ለሌላ ፡ ስጥ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጽሕፈ ቱን ፡ ለንጉሡ ፡ አነብባለሁ ፡ ፍቺውንም ፡ አስ ታውቃለሁ ። ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ልዑል ፡ አምላክ ፡
፲፰ ለአባትህ ፡ ለናቡከደነፆር ፡ መንግሥትንና ፡ ታላ ቅነትን ፡ ክብርንና ፡ ግርማን ፡ ሰጠው ። ስለ ፡ ሰጠው ፡ ታላቅነት ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ይን ቀጠቀጡና ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ፤ የፈቀደውን ፡ ይገ
፲፱ ድል ÷ የፈቀደውንም ፡ በሕይወት ፡ ያኖር ፡ ነበር ፤ የፈቀደውንም ፡ ያነሣ ÷ የፈቀደውንም ፡ ያዋ ርድ ፡ ነበር ። ልቡ ፡ ግን ፡ በታበየ ፡ በሠራትም ፡
፳ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ መንፈሱ ፡ በጠነከረ ፡ ጊዜ ÷ ከመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ተዋረደ ÷ ክብሩም ፡ ተለ የው ። ልዑል ፡ አምላክም ፡ በሰዎች ፡ መንግ
፳፩ ሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ÷ የሚወድደውንም ፡ እንዲሾምበት ፡ እስኪያውቅ ፡ ድረስ ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ተይለቶ ፡ ተሰደደ ÷ ልቡም ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ ልብ ፡ ሆነ ÷ መኖሪያውም ፡ ከምድረ
፳፪ በዳ ፡ አህዮች ፡ ጋር ፡ ነበረ ፤ እንደ ፡ በሬ ፡ ሣር ፡ በላ ÷ አካሉም ፡ በሰማይ ፡ ጠል ፡ ረሰረሰ ። ብልጣ
፳፫ ሶር ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡ ልጁ ፡ ስትሆን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እያወቅህ ፡ በሰማይ ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ ኰራህ ፡ እንጂ ፡ ልብህን ፡ አላዋረድህም ። የመቅደሱንም ፡ ዕቃ ዎች ፡ በፊትህ ፡ አመጡ ÷ አንተም ፡ መኳን ንትህም ፡ ሚስቶችህም ፡ ቁባቶችህም ፡ የወ ይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣችሁበቸው ፤ ከብርና ፡ ከወር ቅም ፡ ከናስና ፡ ከብረትም ፡ ከእንጨትና ፡ ከድ ንጋይም ፡ የተሠሩትን ፡ የማያዩትንም ፡ የማይ ሰሙትንም ፡ የማያውቁትንም ፡ አማልክት ፡ አመሰገንህ ፤ ትንፋሽህንና ÷ መንገድህን ፡ ሁሉ ፡

በእጁ ፡ የያዘውን ፡ አምላክ ፡ አላከበርኸውም ።
፳፬ ስለዚህም ፡ እኒህ ፡ የእጅ ፡ ጣቶች ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተልከዋል ፡ ይህም ፡ ጽሕፈት ፡ ተጽፎአል ።
፳፭ የተጻፈውም ፡ ጽሕፈት ፡ — ሜኔ ፡ ቴቄል ፡ ፋሬስ ፡ ይላል ። የነገሩም ፡ ፍቺ ፡ ይህ ፡ ነው ፡
፳፮ ሜኔ ፡ ማለት ÷ እግዚአብሔር ፡ መንግሥትህን ፡ ቈጠረው ፡ ፈጸመውም ፡ ማለት ፡ ነው ። ቴቄል ፡ ማለት ÷ በሚዛን ፡ ተመዘንህ ÷ ቀልለህም ፡ ተገ
፳፯ ኘህ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፋሬስ ፡ ማለት ÷ መንግ ሥትህ ፡ ተከፈለ ÷ ለሚዶንና ፡ ለፋርስ ፡ ሰዎ ችም ፡ ተሰጠ ፡ ማለት ፡ ነው ።
፳፱ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብልጣሶር ፡ ለዳንኤል ፡ ሐም ራዊ ፡ ግምጃ ፡ እንዲያለብሱት ÷ የወርቅ ፡ ማር ዳም ፡ በአንገቱ ፡ ዙሪያ ፡ እንዲያደርጉለት ፡ አዘዘ ፡ በመንግሥትም ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዥ ፡ እንዲ ሆን ፡ አዋጅ ፡ አስነገረ ።
፴ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ የከለዳውያን ፡ ንጉሥ ፡ ብልጣ ሶር ፡ ተገደለ ።
፴፩ ሜዶናዊውም ፡ ዳርዮስ ፡ መን ግሥቱን ፡ ወሰደ ፤ ዕድሜውም ፡ ስድሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ ዳርዮስም ፡ በመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ እን ዲሆኑ ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ መሳፍንት ፡ በመንግሥቱ ፡
፪ ላይ ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ። መሳፍንቱም ፡ ሒሳቡን ፡ ያመጡላቸው ፡ ዘንድ ÷ ንጉሡም ፡ እንዳይጐዳ ፡ ሦስት ፡ አለቆች ፡ በላያቸው ፡ አደ ረገ ፤ ከእነርሱም ፡ አንደኛው ፡ ዳንኤል ፡ ነበረ ።
፫ ዳንኤልም ፡ መልካም ፡ መንፈስ ፡ ስላለው ፡ ከአ ለቆችና ፡ ከመሳፍንት ፡ በለጠ ፡ ንጉሡም ፡ በመ ንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይሾመው ፡ ዘንድ ፡ አሰበ ።
፬ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አለቆችና ፡ መሳፍንቱ ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ ሰበብ ፡ ይፈ ልጉ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የታመነ ፡ ነበረና ÷ ስሕ ተትና ፡ በደልም ፡ አልተገኘበትምና ፡ በእርሱ ፡
፭ ላይ ፡ ሰበብና ፡ በደል ፡ ያገኙበት ፡ ዘንድ ፡ አል ቻሉም ። እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ — ከአምላኩ ፡ ሕግ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰበብ ፡ እናገኝበትም ፡ አሉ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡
፮ አለቆቹና ፡ መሳፍንቱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተሰ ብስበው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ — ንጉሥ ፡ ዳር ዮስ ፡ ሆይ ÷ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ። የመንግ ሥቱ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ሹማምቶችና ፡ መሳፍ ንት ፡ አማካሪዎችና ፡ አዛዦች ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልመና ፡ ከአምላክ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ ቢለምን ÷ በአንበሶች ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይጣል ፡ የሚል ፡ የንጉሥ ፡ ሕግና ፡ ብርቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ።
፰ አሁንም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ እንደማይለወጠው ፡ እንደ ፡ ሜዶንና ፡ እንደ ፡ ፋርስ ፡ ሕግ ÷ እንዳይ ለወጥ ፡ ትእዛዙን ፡ አጽና ÷ ጽሕፈቱንም ፡ ጻፍ ።
፱ ንጉሡም ፡ ዳርዮስ ፡ ጽሕፈቱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ባወቀ ፡
፲ ዳንኤልም ፡ ጽሕፈቱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፤ የአልፍኙም ፡ መስኮ ቶች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አንጻር ፡ ተከፍተው ፡ ነበር ፤ ቀድሞም ፡ ያደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በየ ዕለቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡
፲፩ በእምላኩ ፡ ፊት ፡ ጸለየ ፡ አመሰገነም ። እኒህ ያም ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ዳንኤል ፡ በእም ላኩ ፡ ፊት ፡ ሲጸልይና ፡ ሲለምን ፡ አገኙት ።
፲፪ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ቀርበው ፡ ስለ ፡ ንጉሡ ፡ ትእ ዛዝ ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ከአንተ ፡ በቀር ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከአምላክ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ የሚለምን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በአንበሶች ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጣል ፡ ትእዛዝ ፡ አልጻፍህምን ? አሉት ። ንጉሡም ፡ መልሶ ፡ — ነገሩ ፡ እንደማ ይለወጠው ፡ እንደ ፡ ሜዶንና ፡ እንደ ፡ ፋርስ ፡ ሕግ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አላቸው ።
፲፫ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሰው ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ከይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ የሆነው ፡ ዳንኤል ፡ በየዕለቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ልመናውን ፡ ይለም ናል ፡ እንጂ ፡ እንተንና ፡ የጻፍኸውን ፡ ትእዛዝ ፡ አይቀበልም ፡ አሉት ።
፲፬ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አዘነ ÷ ያድነው ም ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ ወደ ፡ ዳንኤል ፡ አደረገ ። ሊያድነውም ፡ ፀሐይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ደከመ ።
፲፭ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተሰብ ስበው ፡ ንጉሡን ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ ንጉሡ ፡ ያጸናው ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ሥርዓት ፡ ይለወጥ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገባ ፡ የሜዶንና ፡ የፋርስ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እወቅ ፡ አሉት ።
፲፮ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ አዘዘ ÷ ዳንኤል ፡ ንም ፡ አምጥተው ፡ በአንበሶች ፡ ጕድጓድ ፡ ጣሉት ። ንጉሡም ፡ ተናገረ ፡ ዳንኤልንም ፡ — ሁልጊዜ ፡ የምታመልከው ፡ አምላክህ ፡ እርሱ ፡ ያድንህ ፡ አለው ። ድንጋይም ፡ አምጥተው ፡
፲፯ በጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ገጠሙበት ። ንጉሡም ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ እንዳይለወጥ ፡ በቀለበቱና ፡ በመኳንንቱ ፡ ቀለበት ፡ አተመው ።
፲፰ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ፡ ሳይበላም ፡ አደረ ፡ መብልም ፡ አላመጡለትም ÷ እንቅልፉም ፡ ከእ ርሱ ፡ ራቀ ።
፲፱ በነጋውም ፡ ንጉሡ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ÷ ፈጥ
፳ ኖም ፡ ወደ ፡ አንበሶች ፡ ጕድጓድ ፡ ሄደ ። ወደ ፡ ጕድጓዱም ፡ ወደ ፡ ዳንኤል ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በኀዘን ፡ ቃል ፡ ጠራው ። ንጉሡም ፡ ተናገረ ፡ ዳንኤልንም ፡ — የሕያው ፡ አምላክ ፡ የሆንህ ፡ ዳን ኤል ፡ ሆይ ÷ ውልጊዜ ፡ የምታመልከው ፡ አምላ ክህ ፡ ከአንበሶች ፡ ያድንህ ፡ ዘንድ ፡ ችሎአልን ?
፳፩ አለው ። ዳንኤልም ፡ ንጉሡን ፡ — ንጉሥ ፡ ሆይ ÷
፳፪ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ። በፊቱ ፡ ቅንነት ፡ ተገኘ
፳፫ ቶብኛልና ÷ በእንተም ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ አልበደልሁምና ፡ አምላኬ ፡ መልአኩን ፡ ልኮ ፡ የአንበሶችን ፡ አፍ ፡ ዘጋ ÷ እነርሱም ፡ አል ጕዱኝም ፡ አለው ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡
፳፬ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ÷ ዳንኤልንም ፡ ከጉድ ጓዱ ፡ ያወጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ዳንኤልም ፡

ከጕድጓድ ፣ ወጣ ÷ በእምላኩም ፣ ታምኖ ፣ ነበ
ርና ፣ አንዳች ፣ ጕዳት ፣ አልተገኘበትም ።
፳፫ ንጉሡም ፣ እዘዘ ÷ ዳንኤልንም ፣ የከሰሱ ፣
እነዚያን ፣ ሰዎች ፣ አመጡአቸው ÷ እነርሱንና ፣
ልጆቻቸውንም ፣ ሚስቶቻቸውንም ፣ በአንበ
ሶች ፣ ጕድጓድ ፣ ጣሉአቸው ፤ ወደ ፣ ጕድጓ
ዱም ፣ መጨረሻ ፣ ሳይደርሱ ፣ አንበሶች ፣ ያዙአ
ቸው ፣ አጥንታቸውንም ፣ ሁሉ ፣ ሰባበሩ ።
፳፬ የዚያን ፣ ጊዜም ፣ ንጉሥ ፣ ዳርዮስ ፣ በም
ድር ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣ ወደሚኖሩ ፣ ወገኖችና ፣ አሕ
ዛብ ፣ በልዩ ፣ ልዩም ፣ ቋንቋ ፣ ወደሚናገሩ ፣
ሁሉ ፣ ጻፈ ÷ እንዲህም ፣ አለ ፦— ሰላም ፣ ይብ
ዛላችሁ ። በመንግሥቴ ፣ ግዛት ፣ ሁሉ ፣ ያሉ ፣
ሰዎች ፣ በዳንኤል ፣ አምላክ ፣ ፊት ፣ እንዲፈ
ሩና ፣ እንዲንቀጠቀጡ ፣ አዝዣለሁ ፤ እርሱ ፣
ሕያው ፣ አምላክ ፣ ለዘላለም ፣ የሚኖር ፣ ነውና ፤
መንግሥቱም ፣ የማይጠፋ ፣ ነው ÷ ግዛቱም ፣
እስከ ፣ መጨረሻ ፣ ድረስ ፣ ይኖራል ። ያድናል ፣
ይታደግማል ÷ በሰማይና ፣ በምድርም ፣ ተአ
ምራትንና ፣ ድንቅን ፣ ይሠራል ÷ ዳንኤልንም ፣
ከአንበሶች ፣ አፍ ፣ አድኖታል ።
፳፰ ይህም ፣ ዳንኤል ፣ በዳርዮስ ፣ መንግሥትና ፣
በፋርሳዊው ፣ በቂሮስ ፣ መንግሥት ፣ ኑሮው ፣
ተቃናለት ።

ምዕራፍ ፣ ፯ ።

፩ በባቢሎን ፣ ንጉሥ ፣ በብልጣሶር ፣ በመጀመ
ሪያው ፣ ዓመት ፣ ዳንኤል ፣ በአልጋው ፣ ላይ ፣
ሕልምንና ፣ የራሱን ፣ ራእይ ፣ አየ ፤ ከዚያም ፣
በኋላ ፣ ሕልሙን ፣ ጻፈ ÷ ዋነኛውንም ፣ ነገር ፣
፪ ተናገረ ። ዳንኤልም ፣ ተናገረ ፣ እንዲህም ፣
አለ ፦— በሌሊት ፣ በራእይ ፣ አየሁ ፤ እነሆም ÷
አራቱ ፣ የሰማይ ፣ ነፋሳት ፣ በታላቁ ፣ ባሕር ፣
፫ ላይ ፣ ይጋጩ ፣ ነበር ። አራትም ፣ ታላላቅ ፣ አራ
ዊት ፣ ከባሕር ፣ ወጡ ÷ እያንዳንዳቸውም ፣ ልዩ ፣
፬ ልዩ ፣ ነበረች ። መጀመሪያይቱ ፣ አንበሳ ፣
ትመስል ፣ ነበር ÷ የንስርም ፣ ክንፍ ፣ ነበራት ፣
ክንፎችዋም ፣ ከእርስዋ ፣ እስኪነቀሉ ፣ ድረስ ፣
አያ ፣ ነበር ÷ ከምድርም ፣ ከፍ ፣ ከፍ ፣ ተደረ
ገች ÷ እንደ ፣ ሰውም ፣ በሁለት ፣ እግር ፣ እንድ
ትቆም ፣ ተደረገች ÷ የሰውም ፣ ልብ ፣ ተሰጣት ።
፭ እነሆም ÷ ሁለተኛይቱ ፣ ድብ ፣ የምትመስል ፣
ሌላ ፣ አውሬ ፣ ነበረች ÷ በአንድ ፣ ወገንም ፣
ቆመች ÷ ሦስትም ፣ የጕድን ፣ አጥንቶች ፣ በአ
ፍዋ ፣ ውስጥ ፣ በጥርስዋ ፣ መካከል ፣ ነበሩ ፣ እን
ደዚህም ፦— ተነሥተሽ ፣ እጅግ ፣ ሥጋ ፣ ብዪ ፣
፮ ተባሉላት ። ከዚህም ፣ በኋላ ÷ እነሆ ÷ ነብር ፣ የምት
መስል ፣ በጀርባዋም ፣ ላይ ፣ አራት ፣ የወፍ ፣ ክን
ፎች ፣ የነበሩአት ፣ ሌላ ፣ አውሬ ፣ አየሁ ፤ ለአ
ውሬይቱም ፣ አራት ፣ ራሶች ፣ ነበሩአት ÷ ግዛ
፯ ትም ፣ ተሰጣት ። ከዚህም ፣ በኋላ ፣ በሌሊት ፣
ራእይ ፣ አየሁ ፣ እነሆም ÷ የምታስፈራና ፣ የምታ
ስደነግጥ ፣ እጅግም ፣ የበረታች ÷ ታላላቅም ፣
የብረት ፣ ጥርሶች ፣ የነበሩአት ፣ አራተኛ ፣ አውሬ ፣
ነበረች ፤ ትበላና ፣ ታደቅቅ ፣ ነበር ÷ የቀረው
ንም ፣ በእግርዋ ፣ ትረግጥ ፣ ነበር ፤ ከእርስዋም ፣
በፊት ፣ ከነበሩት ፣ አራዊት ፣ ሁሉ ፣ የተለየች ፣
ነበረች ፤ አሥር ፣ ቀንዶችም ፣ ነበሩአት ። ፰ ቀንዶ
ችንም ፣ ተመለከትሁ ፣ እነሆም ÷ በመካከላቸው ፣
ሌላ ፣ ትንሽ ፣ ቀንድ ፣ ወጣ ÷ በፊቱም ፣ ከቀደ
ሙት ፣ ቀንዶች ፣ ሦስት ፣ ተነቃቀሉ ፤ እነሆም ÷
በዚያ ፣ ቀንድ ፣ እንደ ፣ ሰው ፣ ዓይኖች ፣ የነበሩ ፣
ዓይኖች ፣ በትዕቢትም ፣ የሚናገር ፣ አፍ ፣ ነበ
ሩበት ።
፱ ዙፋኖችም ፣ እስኪዘረጉ ፣ ድረስ ፣ አየሁ ÷
በዘመናት ፣ የሸመገለውም ፣ ተቀመጠ ፤ ልብ
ሱም ፣ እንደ ፣ በረዶ ፣ ነጭ ÷ የራሱም ፣ ጠጕር ፣
እንደ ፣ ጥሩ ፣ ጥጥ ፣ ነበረ ፤ ዙፋኑም ፣ የእሳት ፣
ነበልባል ፣ ነበረ ÷ መንኰራኵሮቹም ፣ የሚነ
ድድ ፣ እሳት ፣ ነበሩ ። ፲ የእሳትም ፣ ፈሳሽ ፣ ከፊቱ ፣
ይፈልቅና ፣ ይወጣ ፣ ነበር ፤ ሺህ ፣ ጊዜ ፣ ሺህ ፣
ያገለግሉት ፣ ነበር ÷ እልፍ ፣ አእላፋትም ፣ በፊቱ ፣
ቆመው ፣ ነበር ፤ ፍርድም ፣ ሆነ ÷ መጻሕፍትም ፣
ተገለጡ ። ፲፩ የዚያን ፣ ጊዜም ፣ ቀንዱ ፣ ይናገ
ረው ፣ ከነበረው ፣ ከታላቁ ፣ ቃል ፣ ድምፅ ፣ የተ
ነሣ ፣ አየሁ ፤ አውሬይቱም ፣ እስክትገደል ÷
አካልዋም ፣ እስኪጠፋ ፣ ድረስ ÷ በእሳትም ፣
ለመቃጠል ፣ እስክትሰጥ ፣ ድረስ ፣ አየሁ ።
፲፪ ከቀሩትም ፣ አራዊት ፣ ግዛታቸው ፣ ተወሰደ ፤
የሕይወታቸው ፣ ዕድሜ ፣ ግን ፣ እስከ ፣ ዘመንና ፣
እስከ ፣ ጊዜ ፣ ድረስ ፣ ረዘመ ።
፲፫ በሌሊት ፣ ራእይ ፣ አየሁ ፤ እነሆም ÷ የሰው ፣
ልጅ ፣ የሚመስል ፣ ከሰማይ ፣ ደመናት ፣ ጋር ፣
መጣ ፣ በዘመናት ፣ ወደ ፣ ሸመገለውም ፣ ደረሰ ፤
ወደ ፣ ፊቱም ፣ አቀረቡት ። ፲፬ ወገኖችና ፣ አሕ
ዛብ ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ቋንቋም ፣ የሚናገሩ ፣ ሁሉ ፣
ይገዙለት ፣ ዘንድ ፣ ግዛትና ፣ ክብር ፣ መንግሥ
ትም ፣ ተሰጠው ። ግዛቱም ፣ የማያልፍ ፣ የዘላ
ለም ፣ ግዛት ፣ ነው ÷ መንግሥቱም ፣ የማይጠፋ ፣
ነው ።
፲፭ በእኔም ፣ በዳንኤል ፣ በሥጋዬ ፣ ውስጥ ፣ መን
ፈሴ ፣ ደነገጠች ÷ የራሴም ፣ ራእይ ፣ አስቸገረኝ ።
፲፮ በዚያም ፣ ከቆሙት ፣ ወደ ፣ አንዱ ፣ ቀርቤ ፣ ስለ
ዚህ ፣ ሁሉ ፣ እውነቱን ፣ ጠየቅሁት ፤ እርሱም ፣
ነገረኝ ÷ የነገሩንም ፣ ፍቺ ፣ አስታወቀኝ ። ፲፯ እነ
ዚህ ፣ አራቱ ፣ ታላላቅ ፣ አራዊት ፣ ከምድር ፣
የሚነሡ ፣ አራት ፣ ነገሥታት ፣ ናቸው ። ፲፰ ነገር ፣
ግን ፣ የልዑሉ ፣ ቅዱሳን ፣ መንግሥቱን ፣ ይወስ
ዳሉ ÷ እስከ ፣ ዘላለም ፣ ዓለምም ፣ መንግሥቱን ፣
ይወርሳሉ ። ከዚህም ፣ በኋላ ፣ ከቀሩት ፣ ሁሉ ፣
ተለይታ ፣ እጅግ ፣ ስለምታስፈራው ÷ ጥርሶች
ዋም ፣ የብረት ፣ ጥፍሮችዋም ፣ የናስ ፣ ስለሆኑት ÷
ስለምትረ፡ላውና ፣ ስለምታደቅቀው ፣ የቀረው
ንም ፣ በእግርዋ ፣ ስለምትረግጠው ፣ ስለ ፣ አራተኛ
ይቱ ፣ አውሬ ÷ በራስዋም ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ነበሩ ፣
ስለ ፣ አሥር ፣ ቀንዶች ÷ በኋላም ፣ ስለ ፣ ወጣው ÷
በፊቱም ፣ ሦስቱ ፣ ስለ ፣ ወደቁ ÷ ዓይኖችና ፣ ትዕ
ቢት ፣ የተናገረ ፣ አፍ ፣ ስለ ፣ ነበሩት ÷ መልኩም ፣

ከሌሎች ፣ ሁሉ ፣ በለጠ ፣ ስለ ፣ ሌላው ፣ ቀንድ ፣
፳፩ እውነቱን ፣ ለማወቅ ፣ ፈቀድሁ ። እነሆም ÷ ያ ፣
፳፪ ቀንድ ፣ ከቅዱሳን ፣ ጋር ፣ ሲዋጋ ፣ አየሁ ÷ በዘ
መናት ፣ የሸመገለው ፣ እስኪመጣ ፣ ድረስ ÷ ፍር
ድም ፣ ለልዑሉ ፣ ቅዱሳን ፣ እስኪሰጥ ፣ ድረስ ÷
ቅዱሳኑም ፣ መንግሥቱን ፣ የሚወስዱበት ፣
ዘመን ፣ እስኪመጣ ፣ ድረስ ፣ እሸነፋቸውም ።
፳፫ እንዲህም ፣ አለ ፦— አራተኛይቱ ፣ አውሬ ፣
በምድር ፣ ላይ ፣ አራተኛ ፣ መንግሥት ፣ ትሆና
ለች ፤ እርሱም ፣ ከመንግሥታት ፣ ሁሉ ፣ የተ
ለየ ፣ ይሆናል ÷ ምድሪቱንም ፣ ሁሉ ፣ ይበላል ፣
፳፬ ይረግጣታል ፣ ያደቅቃትማል ። አሥሩም ፣ ቀን
ዶች ፣ ከዚያ ፣ መንግሥት ፣ የሚነሡ ፣ አሥር ፣ ነገ
ሥታት ፣ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፣ በኋላ ፣ ሌላ ፣ ይነ
ሣል ÷ እርሱም ፣ ከፊተኞች ፣ የተለየ ፣ ይሆ
ናል ÷ ሦስቱንም ፣ ነገሥታት ፣ ያዋርዳል ።
፳፭ በልዑሉም ፣ ላይ ፣ ቃልን ፣ ይናገራል ÷ የልዑ
ልንም ፣ ቅዱሳን ፣ ይሰባብራል ÷ ዘመናትንና ፣
ሕግን ፣ ይለውጥ ፣ ዘንድ ፣ ያስባል ፤ እስከ ፣ ዘመ
ንና ፣ እስከ ፣ ዘመናት ፣ እስከ ፣ እኵሌታ ፣ ዘመ
፳፮ ንም ፣ በእጁ ፣ ይሰጣሉ ። ነገር ፣ ግን ፣ ፍርድ ፣
ይሆናል ÷ እስከ ፣ ፍጻሜም ፣ ድረስ ፣ ያፈርሱ
ትና ፣ ያጠፉት ፣ ዘንድ ፣ ግዛቱን ፣ ያስወግዱታል ።
፳፯ መንግሥትም ፣ ግዛትም ፣ ከሰማይም ፣ ሁሉ ፣
በታች ፣ ያሉ ፣ የመንግሥታት ፣ ታላቅነት ፣ ለል
ዑሉ ፣ ቅዱሳን ፣ ሕዝብ ፣ ይሰጣል ፤ መንግሥቱ ፣
የዘላለም ፣ መንግሥት ፣ ነው ÷ ግዛቶችም ፣ ሁሉ ፣
፳፰ ይገዙለታል ፣ ይታዘዙለትማል ። የነገሩም ፣
ፍጻሜ ፣ እስከዚህ ፣ ድረስ ፣ ነው ። እኔም ፣ ዳን
ኤል ፣ በአሳቤ ፣ እጅግ ፣ ተቸገርሁ ÷ ፊቴም ፣
ተለወጠብኝ ፤ ዳሩ ፣ ግን ፣ ነገሩን ፣ በልቤ ፣ ጠብ
ቂአለሁ ።

ምዕራፍ ፣ ፰ ።

፩ በመጀመሪያ ፣ ከተገለጠልኝ ፣ ራእይ ፣ በኋላ ÷
ንጉሡ ፣ ብልጣሶር ፣ በነገሠ ፣ በሦስተኛው ፣
ዓመት ÷ ለእኔ ፣ ለዳንኤል ፣ ራእይ ፣ ተገለጠ
፪ ልኝ ። በራእዩም ፣ አየሁ ፣ በየሁም ፣ ጊዜ ፣ በኤ
ላም ፣ አውራጃ ፣ ባለው ፣ በሹሳ ፣ ግንብ ፣ ነበርሁ ፤
በራእዩም ፣ አየሁ ፣ በኡባል ፣ ወንዝም ፣ አጠ
፫ ገብ ፣ ነበርሁ ። ዓይኔን ፣ አንሥቼ ፣ አየሁ ፤ እነ
ሆም ÷ ሁለት ፣ ቀንዶች ፣ የነበሩት ፣ አንድ ፣
አውራ ፣ በግ ፣ በወንዙ ፣ ፊት ፣ ቆሞ ፣ ነበር ÷
ሁለቱም ፣ ቀንዶቹ ፣ ከፍ ፣ ከፍ ፣ ይሉ ፣ ነበር ፤
፬ አንዱ ፣ ግን ፣ ከሁለተኛው ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ነበረ ÷
ታላቁም ፣ ወደ ፣ ኋላው ፣ ወጥቶ ፣ ነበር ። አው
ራውም ፣ በግ ፣ ወደ ፣ ምዕራብ ፣ ወደ ፣ ሰሜንም ፣
ወደ ፣ ደቡብም ፣ በቀንዱ ፣ ሲጐሽም ፣ አየሁ ፤
አራዊትም ፣ ሁሉ ፣ ይቋቋሙት ፣ ዘንድ ፣ አልቻ
ሉም ÷ ከእጁም ፣ የሚያድን ፣ አልነበረም ፤
እንደ ፣ ፈቃዱም ፣ አደረገ ÷ ራሱንም ፣ ታላቅ ፣
አደረገ ።
፭ እኔም ፣ ስመለከት ÷ እነሆ ÷ ከምዕራብ ፣ ወገን ፣
አንድ ፣ አውራ ፣ ፍየል ፣ በምድር ፣ ሁሉ ፣ ፊት ፣
ላይ ፣ ወጣ ÷ ምድርንም ፣ አልነካም ፣ ለፍየ
ሉም ፣ በዓይኖቹ ፣ መካከል ፣ አንድ ፣ ታላቅ ፣
፮ ቀንድ ፣ ነበረው ። ሁለትም ፣ ቀንድ ፣ ወዳለው ፣
በወንዝም ፣ ፊት ፣ ቆሞ ፣ ወዳየሁት ፣ አውራ ፣
በግ ፣ መጣ ÷ በኃይሉም ፣ ቊጣ ፣ ፈጥኖ ፣ ወደ ፣
እርሱ ፣ ሮጠ ። ወደ ፣ አውራውም ፣ በግ ፣ ሲቀርብ ፣
፯ አየሁት ፣ እርሱም ፣ ተመረረበት ÷ አውራው
ንም ፣ በግ ፣ መታ ÷ ሁለቱንም ፣ ቀንዶች ፣ ሰበረ ፤
አውራውም ፣ በግ ፣ ሊቋቋመው ፣ ኃይል ፣ አል
ነበረውም ÷ እርሱም ፣ በምድር ፣ ላይ ፣ ጥሎ ፣
ረገጠው ፤ አውራውንም ፣ በግ ፣ ከእጁ ፣ ያድነው ፣
፰ ዘንድ ፣ የሚችል ፣ አልነበረም ። አውራውም ፣
ፍየል ፣ ራሱን ፣ እጅግ ፣ ታላቅ ፣ አደረገ ፤ በበረ
ታም ፣ ጊዜ ፣ ታላቁ ፣ ቀንዱ ፣ ተሰበረ ÷ ወደ ፣
አራቱም ፣ የሰማይ ፣ ነፋሳት ፣ የሚመለከቱ ፣
አራት ፣ ቀንዶች ፣ ከበታቹ ፣ ወጡ ።
፱ ከአነርሱም ፣ ከአንዳቸው ፣ አንድ ፣ ታናሽ ፣
ቀንድ ፣ ወጣ ÷ ወደ ፣ ደቡብም ፣ ወደ ፣ ምሥራ
ቅም ፣ ወደ ፣ መልከሚቱም ፣ ምድር ፣ እጅግ ፣
ከፍ ፣ አለ ። ፲ እስከ ፣ ሰማይም ፣ ሠራዊት ፣ ድረስ ፣
ከፍ ፣ አለ ! ከሠራዊትና ፣ ከከዋክብትም ፣ አያ
ሌዎችን ፣ ወደ ፣ ምድር ፣ ጣለ ÷ ረገጣቸውም ።
፲፩ እስከ ፣ ሠራዊትም ፣ አለቃ ፣ ድረስ ፣ ራሱን ፣
ታላቅ ፣ አደረገ ፤ ከእርሱም ፣ የተነሣ ፣ የዘወ
ትሩ ፣ መሥዋዕት ፣ ተሻረ ÷ የመቅደሱም ፣
ስፍራ ፣ ፈረሰ ። ፲፪ ሠራዊቱም ፣ ከኃጢአት ፣ የተ
ነሣ ፣ ከዘወትሩ ፣ መሥዋዕት ፣ ጋር ፣ ተሰጠው ፤
እርሱም ፣ እውነትን ፣ ወደ ፣ ምድሩ ፣ ጣለ ÷
አደረገም ፣ ተከናወነም ። ፲፫ ከቅዱሳኑም ፣ አንዱ ፣
ሲናገር ፣ ሰማሁ ፤ ለተናገረው ፣ ለቅዱሱም ፣
ሁለተኛው ፣ ቅዱስ ፦— ስለ ፣ ዘወትሩ ፣ መሥዋ
ዕት ÷ መቅደሱና ፣ ሠራዊቱም ፣ ይረገጡ ፣ ዘንድ ፣
ስለሚሰጥና ፣ ስለሚያጠፋ ፣ ኃጢአት ፣ የሆነው ፣
ራእይ ፣ እስከ ፣ መቼ ፣ ይሆናል ? አለው ። ፲፬ እር
ሱም ፦— እስከ ፣ ሁለት ፣ ሺህ ፣ ሦስት ፣ መቶ ፣
ማታና ፣ ጥዋት ፣ ድረስ ፣ ነው ፤ ከዚያም ፣ በኋላ ፣
መቅደሱ ፣ ይነጻል ፣ አለኝ ።
፲፭ እኔም ፣ ዳንኤል ፣ ራእዩን ፣ በየሁ ፣ ጊዜ ፣ ማስ
ተዋሉን ፣ ፈለግሁ ፤ እነሆም ÷ የሰው ፣ ምስያ ፣
በፊቴ ፣ ቆሞ ፣ ነበር ። ፲፮ በኡባልም ፣ ወንዝ ፣ መካ
ከል ፦— ገብርኤል ፣ ሆይ ÷ ራእዩን ፣ ለዚህ ፣
ሰው ፣ አስታውቀው ፣ ብሎ ፣ የሚጮኽውን ፣
የሰውን ፣ ድምፅ ፣ ሰማሁ ። ፲፯ እኔም ፣ ወደ ፣ ቆም
ሁበት ፣ ቀረበ ፤ በመጣም ፣ ጊዜ ፣ ፈርቼ ፣ በግ
ምባሬ ፣ ተደፋሁ ፤ እርሱም ፦— የሰው ፣ ልጅ ፣
ሆይ ÷ ራእዩ ፣ ለፍጻሜ ፣ ዘመን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣
አስተውል ፣ አለኝ ። ፲፰ ሲናገረኝም ፣ ደንግጬ ፣
በምድር ፣ ላይ ፣ በግምባሬ ፣ ተደፋሁ ፤ እርሱም ፣
ዳሰሰኝ ፣ ቀጥ ፣ አድርጎም ፣ አቆመኝ ። ፲፱ እንዲ
ህም ፣ አለኝ ፦— እነሆ ÷ በመቅሠፍቱ ፣ በመጨ
ረሻ ፣ ዘመን ፣ የሚሆነውን ፣ አስታውቅሃለሁ ፤
ይህ ፣ ለተወሰነው ፣ ለፍጻሜ ፣ ዘመን ፣ ነውና ።
፳ በየኸው ፣ በአውራው ፣ በግ ፣ ላይ ፣ የነበሩ ፣
ሁለቱ ፣ ቀንዶች ፣ እነርሱ ፣ የሜዶንና ፣ የፋርስ ፣ ነገ

ሸሷ፡ ሥታት፡ ናቸው። አሙራውም፡ ፍየል፡ የግሪክ፡ ንጉሥ፡ ነው፡ በዓይኖቹም፡ መካከል፡ ያለው፡ ታላቁ፡ ቀንድ፡ መጀመሪያው፡ ንጉሥ፡ ነው።
ሸሸ፡ እርሱም፡ በተሰበረ፡ ጊዜ፡ በእርሱ፡ ፋንታ፡ አራቱ፡ እንደ፡ ተነሡ፡ እንዲሁ፡ ከመንኩ፡ አራት፡ መንግሥታት፡ ይነሣሉ፡ ነገር፡ ግን፡
ሸሹ፡ በኃይል፡ አይተክሉትም። በመንግሥታቸውም፡ መጨረሻ፡ ኃጢአታቸው፡ በተሞላች፡ ጊዜ፡ እንቋቋልሽን፡ የሚያስተውል፡ ፊተ፡
ሸሼ፡ ጨካኝ፡ ንጉሥ፡ ይነሣል። ኃይሉም፡ ይበረታል፡ ነገር፡ ግን፡ በራሱ፡ ኃይል፡ አይደለም፡ በድንቅም፡ ያጠፋል፡ ያደርግማል፡ ይከናወንማል፡ ኃያላንንና፡ የቅዱሳንን፡ ሕዝብ፡ ያጠፋል።
ሸረ፡ በመታለሉ፡ ተንኰልን፡ በእጁ፡ ያከናውናል፡ በልቡም፡ ይታበያል፡ ታምነውም፡ የሚኖሩትን፡ ብዙዎችን፡ ያጠፋል፡ በአለቆቹም፡ አለቃ፡ ላይ፡ ይቆሟልና፡ ያለ፡ እጅም፡ ይሰበራል።
ሸሽ፡ የተነገረውም፡ የማታውና፡ የጥዋቱ፡ ራእይ፡ እውነተኛ፡ ነው፡ ነገር፡ ግን፡ ከብዙ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ ስለሚሆን፡ ራእዩን፡ ዝጋ።
ሸሸ፡ እኔም፡ ዳንኤል፡ ተኛሁ፡ ታመምሁ፡ ቀን፡ ታመምሁ፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ ተነሥቼ፡ የንጉሡን፡ ሥራ፡ አሠራ፡ ነበር፡ ስለ፡ ራእዩም፡ አደንቅ፡ ነበር፡ የሚያስተውለው፡ ግን፡ አል ነበረም።

ምዕራፍ ፱።

፩፡ በነሰዳውያን፡ መንግሥት፡ ላይ፡ በነገሠ፡ ከሚድን፡ ዘር፡ በነበረ፡ በአሕዛዊነት፡ ልጅ፡ በዳ
፪፡ ርዮስ፡ በመጀመሪያ፡ ዓመት፡ በነገሠ፡ በመጀመሪያው፡ ዓመት፡ እኔ፡ ዳንኤል፡ የኢየሩሳሌም፡ መፍረስ፡ የሚፈጸምበትን፡ ሰባዉን፡ ዓመት፡ እግዚአብሔር፡ በቃሉ፡ ለነቢዩ፡ ለኤርምያስ፡ የተናገረውን፡ የዓመቱን፡ ቍጥር፡ በመጽሐፍ፡ አስተዋልሁ።
፫፡ ማቅ፡ ለብሼ፡ በአመድም፡ ላይ፡ ሆኜ፡ ስጸም፡ አጸልያና፡ አለምን፡ ዘንድ፡ ፊቴን፡ ወደ፡ ጌታ፡
፬፡ ወደ፡ አምላክ፡ አቀናሁ። ወደ፡ አምላኬም፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ጸለይሁ፡ ተናዝዘሥም፡ እንዲህ፡ አልሁ፡— ጌታ፡ ሆይ፡ ከሚወድዱህና፡ ትእዛዝህን፡ ከሚፈጽሙ፡ ጋር፡ ቃል፡ ኪዳንንና፡ ምሕረትን፡ የምትጠብቅ፡ ታላቅና፡
፭፡ የምታስፈራ፡ አምላክ፡ ሆይ፡ ኃጢአትን፡ ሠር ተናል ÷ በደልንማል ÷ ክፋትንም፡ አድርገናል ÷ ዐምፀንማል ÷ ከትእዛዝህና፡ ከፍርድ
፮፡ ሀም፡ ፈቀቅ፡ ብለናል፡ በስምህም፡ ለነገሥታቶቻችንና፡ ለአለቆቻችን፡ ለአባቶቻችንም፡ ለሕዝቡ፡ ሁሉ፡ የተናገሩትን፡ ባሪያ
፯፡ ዎችህን፡ ነቢያትን፡ አልሰማንም። ጌታ፡ ሆይ÷ ጽድቅ፡ ለእንተ፡ ነው፡ እንደ፡ ዛሬም፡ ለእኛ፡ ለይሁዳ፡ ሰዎችና፡ በኢየሩሳሌም፡ ለሚቀመጡ፡ ለአስራኤልም፡ ሁሉ፡ በቅርብና፡ በሩቅም፡ ላሉት፡ አንተን፡ በበደሉበት፡ በበደላቸው፡ ምክንያት፡ በበትንህበት፡ አገር፡ ሁሉ፡ የፈት፡
እፍረት፡ ነው። ጌታ፡ ሆይ÷ በእንተ፡ ላይ፡ ኃጢአት፡ ስለ፡ ሠራን፡ ለእኛና፡ ለነገሥታቶቻችን፡ ለአለቆቻችንና፡ ለአባቶቻችንም፡ የፈት፡
እፍረት፡ ነው። በእርሱ፡ ላይ፡ ምንም፡ እንኳ፡ ያመፅን፡ ብንሆን÷ በባሪያዎቹም፡ በነቢያት፡ እጅ፡ በፈታችን፡ በኖረው፡ በሕጉ፡ እንኄድ፡ ዘንድ፡ የአምላካችንን፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል፡ ምንም፡ እንኳ፡ ባንሰማ÷ ለጌታ፡ ለአምላካችን፡ ምሕረትና፡ ይቅርታ፡ ነው። እስራኤልም፡ ሁሉ፡ ሕግህን፡ ተላልፈዋል÷ ቃልህንም፡ እንዳይሰሙ፡ ፈቀቅ፡ ብለዋል፡ በእርሱ፡ ላይ፡ ኃጢአት፡ ሠርተናልና፡ በእግዚአብሔር፡ ባሪያ፡ በሙሴ፡ ሕግ፡ የተጻፈው፡ መሐላና፡ እርግማን፡ ፈሰሰብን። እጅግ፡ ክፉ፡ ነገርንም፡ በእኛ፡ ላይ፡ በማምጣቱ፡ በላያችንና፡ በእኛ፡ ዘንድ፡ በተሾሙት፡ ፈራጆቻችን፡ ላይ፡ የተና ገረውን፡ ቃል፡ አጸና፡ በኢየሩሳሌምም፡ ላይ፡ እንደ፡ ተደረገው፡ ያለ፡ ነገር፡ ከቶ፡ ከሰማይ፡ ሁሉ፡ በታች፡ አልተደረገም። በሙሴም፡ ሕግ፡ እንደ፡ ተጻፈ፡ ይህ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ መጣብን፡ ከኃጢአታችንም፡ እንመለስ፡ እውነትህንም፡ እናስብ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ አምላካችን፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ፊት፡ አልለመንንም።
ስለዚህም፡ እግዚአብሔር፡ ክፉ፡ ነገሩን፡ ጠብቆ፡ በእኛ፡ ላይ፡ አመጣ፡ አምላካችን፡ እግዚአብሔር፡ በሚሠራው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ጻድቅ፡ ነውና÷ እኛም፡ ቃሉን፡ አልሰማንምና። አሁንም፡ ሕዝብህን፡ ከግብጽ፡ ምድር፡ በበረታች፡ እጅ፡ ያወጣህ፡ እንደ፡ ዛሬም፡ ቀን፡ ገሢ፡ ለአ ንተ፡ ያገኘህ፡ ጌታ፡ አምላካችን፡ ሆይ÷ ኃጢ አትን፡ ሠርተናል÷ ክፋትንም፡ አድርገናል። ጌታ፡ ሆይ÷ ስለ፡ ኃጢአታችንና፡ ስለ፡ አባቶ ቻችን፡ በደል፡ ኢየሩሳሌምና፡ ሕዝብህ፡ በዙ ሪያችን፡ ላሉት፡ ሁሉ፡ መሰደቢያ፡ ሆነዋልና፡ እንደ፡ ጽድቅህ፡ ሁሉ፡ ተመከህና፡ መንትህ፡ ከከተማህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ከቅዱስ፡ ተራራህ፡ እንዲመለስ፡ እለምንሃለሁ። አሁንም÷ አምላካ ችን፡ ሆይ÷ የባሪያህን፡ ጸሎትና፡ ልመናውን፡ ስማ፡ ጌታ፡ ሆይ÷ በፈረሰው፡ በመቅደስህ፡ ላይ፡ ስለ፡ አንተ፡ ስትል፡ ፊትህን፡ አብራ። አምላኬ፡ ሆይ÷ በፊትህ፡ የምንለምን፡ ስለ፡ ብዙ፡ ምሕረትህ፡ ነው፡ እንጂ፡ ስለ፡ ጽድቃ ችን፡ አይደለምና፡ ጆሮህን፡ አዘንብለህ፡ ስማ፡ ዓይንህን፡ ገልጠህ፡ ጥፋታችንና፡ ስምህ፡ የተ ጠራበትን፡ ከተማ፡ ተመልከት። አቤቱ÷ ስማ፡ አቤቱ÷ ይቅር፡ በል፡ አቤቱ÷ አድምጥና፡ አድ ርግ፡ ኤምላኬ፡ ሆይ÷ ስምህ፡ በከተማህና፡ በሕዝብህ፡ ላይ፡ ተጠርቶአልና፡ ስለ፡ ራስህ፡ አትዘግይ።
እኔም፡ ገና፡ ስናገርና፡ ስጸልይ÷ በኃጢአቴና፡ በሕዝቤም፡ በእስራኤል፡ ኃጢአት፡ ስናዝዝ÷ በእምላኬም፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ስለ፡ ተቀደሰው፡ ስለ፡ አምላኬ፡ ተራራ፡ ስለምን÷ ገና፡ በጸሎት፡ ስናገር፡ አስቀድሜ፡ በራእይ፡

አይቼው፡ የነበረው፡ ሰው፡ ገብርኤል፡ እነሆ፡ እየበረረ፡ መጣ፡ በማታም፡ መሥዋዕት፡ ጊዜ፡
ሸየ፡ ዓሰሰኝ። አስተማረኝም÷ ተናገረኝም፡ እንዲህም፡ አለ፡— ዳንኤል፡ ሆይ÷ ጥበብንና፡ ማስ ተዋልን፡ አሰጥህ፡ ዘንድ፡ አሁን፡ መጥቻለሁ።
ሸረ፡ አንተ፡ እጅግ፡ የተወደድህ፡ ነህና፡ በልመናህ፡ መጀመሪያ፡ ላይ፡ ትእዛዝ፡ ወጥቶአል÷ እኔም፡ እነግርህ፡ ዘንድ፡ መጥቻለሁ፡ አሁንም፡ ነገ ሩን፡ መርምር÷ ራእዩንም፡ አስተውል።
ሸፀ፲ ዓመፃን፡ ይሠሩርስ÷ ኃጢአትንም፡ ይፈጽም÷ በደልንም፡ ያስተሰርይ÷ የዘላለምን፡ ጽድቅ፡ ያገባ፡ ራእይንና፡ ትንቢትን፡ ያትም÷ ቅዱሰ፡ ቅዱሳኑንም፡ ይቀባ፡ ዘንድ፡ በሕዝብህና፡ በቅ ድስት፡ ከተማህ፡ ላይ፡ ሰባ፡ ሱባዔ፡ ተቀጥሮ
ሸፀ፩ አል። ስለዚህ፡ እወቅ፡ አስተውልም፤ ኢየሩሳ ሌምን፡ መጠገንና፡ መሥራት፡ ትእዛዙ፡ ከሚ ወጣበት፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ አለቃው፡ እስከ፡ መሢሕ፡ ድረስ፡ ሰባት፡ ሱባዔና፡ ስድሳ፡ ሁለት፡ ሱባዔ፡ ይሆናል፡ እርስዋም፡ በጭንቀት፡ ዘመን፡ ከንዳናና፡ ከቅዮር፡ ጋር፡ ትሠራለች።
ሸሸ፡ ከሰድሳ፡ ሁለት፡ ጊዜ፡ ሰባትም፡ በኋላ፡ መሢሕ፡ ይገደላል ÷ በእርሱም፡ ዘንድ፡ ምንም፡ የለም፤ የሚመጣውም፡ አለቃ፡ ሕዝብ፡ ከተማዪቱንና፡ መቅደሱን፡ ያጠፋሉ፤ ፍጻሜውም፡ በጕርፍ፡ ይሆናል ÷ እስከ፡ መጨረሻም፡ ድረስ፡ ጦርነት፡ ይሆናል፡ ጥፋትም፡ ተቀጥሮአል። እርሱም፡ ከብዙ፡ ሰዎች፡ ጋር፡ ጽኑ፡ ቃል፡ ኪዳን፡ ለአ ንድ፡ ሱባዔ፡ ያደርጋል፡ በሱባዔውም፡ አጥ ሌታ፡ መሥዋዕቱንና፡ ቁሮበኑን፡ ያስቀራል፡ በርኵሰትም፡ ጫፍ፡ ላይ፡ አጥፊው፡ ይመጣል፡ እስከ፡ ተፈረጠውም፡ ፍጻሜ፡ ድረስ፡ መቅሠ ፍት፡ በአጥፊው፡ ላይ፡ ይፈስሰል።

ምዕራፍ ፲።

፩፡ በፋርስ፡ ንጉሥ፡ በቂሮስ፡ በሦስተኛው፡ ዓመት፡ ብልጣሶር፡ ለተባለው፡ ለዳንኤል፡ ነገር፡ ተገለጠለት፡ ነገሩም፡ እውነት፡ ነበረ÷ እርሱም፡ ታላቅ፡ ጦርነት፡ ነው፡ ነገሩንም፡ አስተዋለ÷ በራእዩም፡ ዕውቀ፡ ማስተዋል፡
፪፡ ተሰጠው። በዚያም፡ ወራት፡ እኔ፡ ዳንኤል፡ ሦስት፡ ሳምንት፡ ሙሉ፡ ሳዝን፡ ነበርሁ።
፫፡ ማለፊያ፡ እንጀራም፡ አልበላሁም÷ ሥጋና፡ ጠጅም፡ በአፌ፡ አልገባም÷ ሦስቱም፡ ሳምንት፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፡ ዘይት፡ አልተቀባሁም።
፬፡ ከመጀመሪያውም፡ ወር፡ በዘያ፡ አራተኛው፡ ቀን፡ ጤግሮስ፡ በተባለው፡ በታላቁ፡ ወንዝ፡
፭፡ አጠገብ፡ ሳለሁ÷ ዓይኔን፡ አነሣሁ÷ እነሆም÷ በፍታ፡ የለበሰውን፡ ጥሩም፡ የአፈዝን፡ ወርቅ፡ በወገቡ፡ ላይ፡ የታጠቀውን፡ ሰው፡ አየሁ።
፮፡ አካሉም፡ እንደ፡ ቢረሌ፡ ይመስል፡ ነበር÷ ፊቱም፡ እንደ፡ መብረቅ፡ ምስያ፡ ነበረ÷ ዓይኖቹም፡ እንደሚንበለበል፡ ፋና÷ ክንዶቹና፡ እግሮቹም፡ እንደ፡ ጋለ፡ ናስ÷ የቃሉም፡ ድምፅ፡ እንደ፡ ብዙ፡ ሕዝብ፡ ድምፅ፡ ነበረ። እኔም፡ ዳንኤል፡ ብቻዬን፡ ራእዩን፡ አየሁ÷ ከእኔ፡ ጋር፡ የነበሩ፡ ሰዎች፡ ግን፡ ራእዩን፡ አላዩም፡ ነገር፡ ግን፡ ድኑ፡ መንቀጥቀጥ፡ ወደ፡ ቀበቶቸው፡ ሊሸ ሸጉም፡ ሸሹ። እኔም፡ ብቻዬን፡ ቀረሁ፡ ይህ፡
፰፡ ንም፡ ታላቅ፡ ራእይ፡ አየሁ፡ ኃይልም፡ አልቀ ረልኝም÷ ደም፡ ግቤቴም፡ ወደ፡ ማሽብሸብ፡ ተለወጠብኝ÷ ኃይልም፡ አጣሁ። የቃሉንም፡
፱፡ ድምፅ፡ ሰማሁ፡ የቃሉንም፡ ድምፅ፡ በሰማሁ፡ ጊዜ፡ ደንግጬ፡ በምድር፡ ላይ፡ በግምባሬ፡ ተደፋሁ።
፲፡ እነሆም÷ አንዲት፡ እጅ፡ ዳሰሰችኝ÷ በጕ ልበቴና፡ በእጄም፡ አቆመችኝ። እርሱም፡— እጅግ፡ የተወደድህ፡ ሰው፡ ዳንኤል፡ ሆይ÷ አኔ፡ ዛሬ፡ ወደ፡ አንተ፡ ተልኬአለሁና፡ የምነ ግርህን፡ ቃል፡ አስተውል÷ ቀጥ፡ ብለህም፡ ቁም፡ አለኝ። ይህንም፡ ቃል፡ በለኝ፡ ጊዜ፡ እየተንቀጠቀጥሁ÷ ቆምሁ። እርሱም፡ እንዲህ፡
፲፩፡ አለኝ፡— ዳንኤል፡ ሆይ÷ አትፍራ፤ ልብህ፡ ያስተውል፡ ዘንድ÷ ሰውነትህም፡ በእምላክህ፡ ፊት፡ ይዋረድ፡ ዘንድ፡ ካደረግህበት፡ ከመጀ መሪያው፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ ቃልህ፡ ተሰምቶአል፤ እኔም፡ ስለ፡ ቃልህ፡ መጥቻለሁ። የፋርስ፡
፲፪፡ መንግሥት፡ አለቃ፡ ግን፡ ሀያ፡ አንድ፡ ቀን፡ ተቋቋመኝ፡ እነሆም÷ ከዋኝዎቹ፡ አለቆች፡ አንዱ፡ ሚካኤል፡ ሊረዳኝ፡ መጣ፡ እኔም፡ ከፋ ርስ፡ ነገሥታት፡ ጋር፡ በዚያ፡ ተውጡት። ራእዩም፡ ገና፡ ለብዙ፡ ዘመን፡ ነውና፡ በኋለ
፲፫፡ ኛው፡ ዘመን፡ ለሕዝብህ፡ የሚሆነውን፡ አስታ ውቅህ፡ ዘንድ፡ አሁን፡ መጥቻለሁ። ይህንም፡
፲፬፡ ቃል፡ በተናገረኝ፡ ጊዜ፡ ፊቴን፡ ወደ፡ ምድር፡ አቀረቀርሁ÷ ዲዳም፡ ሆንሁ። እነሆም÷
፲፭፡ የሰው፡ ልጅ፡ የሚመስል፡ ከንፈሬን፡ ዳሰሰኝ፡ የዘ ያን፡ ጊዜም፡ አፈሬ፡ ከፍቼ፡ ተናገርሁ፡ በፊቴም፡ ቆሞ፡ የነበረውን፡— ጌታዬ፡ ሆይ÷ ከራእዩ፡ የተነሣ፡ ሕመሜ፡ መጣብኝ÷ ኃይ
፲፮፡ ልም፡ አጣሁ። ይህ፡ የጌታዬ፡ በሪያ፡ ከዚህ፡ ከጌታዬ፡ ጋር፡ ይናገር፡ ዘንድ፡ እንዴት፡ ይች ላል? አሁንም፡ ኃይል፡ አጣሁ÷ አስትንፋስም፡ አልቀረልኝም፡ አልሁት።
፲፯፡ ደግሞ፡ ሰው፡ የሚመስል፡ ዳሰሰኝ÷ አበረ ታኝም። እርሱም፡— እጅግ፡ የተወደድህ፡ ሰው፡ ሆይ÷ አትፍራ፤ ሰላም፡ ለአንተ፡ ይሁን፤ በርታ÷ ጽና፡ አለኝ። በተናገረኝም፡ ጊዜ፡ በረ ታሁና፡— አበርትተኸኛልና፡ ጌታዬ፡ ይናገር፡ አልሁ። እርሱም፡ እንዲህ፡ አለኝ፡— ወደ፡
፳፡ አንተ፡ የመጣሁት፡ ስለ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ÷ ታውቃለህን? አሁንም፡ ከፋርስ፡ አለቃ፡ ጋር፡ እዋጋ፡ ዘንድ፡ እመለሳለሁ፡ እኔም፡ ስወጣ÷ እነሆ፡ የግሪክ፡ አለቃ፡ ይመጣል። ነገር፡ ግን፡ በእ
፳፩፡ ውነት፡ ጽሑፍ፡ የተጻፈውን፡ እነግርሃለሁ፡ በዚ ህም፡ ነገር፡ ከእስቃችሁ፡ ከሚክኤል፡ በቀር፡ ማንም፡ የሚያጸናኝ፡ የለም።

ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ እኔም ፡ በሜዶናዊው ፡ በዳርዮስ ፡ መጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ አጸናውና ፡ አበረታው ፡ ዘንድ ፡ ቆሜ ፡ ነበር ።

፪ አሁንም ፡ እውነትን ፡ አሳይሃለሁ ። እነሆ ÷ ሦስት ፡ ነገሥታት ፡ ደግሞ ፡ በፋርስ ፡ ይነግሣሉ ፤ አራተኛውም ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ይሆናል ፤ በባለጠግነቱም ፡ በበረታ ፡ ጊዜ ፡ በግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ሁሉን ፡ ያስነሣል ።

፫ ኃያልም ፡ ንጉሥ ፡ ይነሣል ÷ በትልቅ ፡ አገዛዝም ፡ ይገዛል ÷ እንደ ፈቃዱም ፡ ያደርጋል ።

፬ እርሱም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ ይሰበራል ፡ አሰከ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ ይከፋፈላል ። ለዘሩ ፡ ግን ፡ አይከፋፈልም ÷ እንደ ገዛበትም ፡ አገዛዝ ፡ አይሆንም ፤ መንግሥቱ ፡ ይነቀላልና ፤ ከእነዚህም ፡ ለሌሎች ፡ ይሆናልና ።

፭ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ከአለቆቹም ፡ አንዱ ፡ ይበረታሉ ፤ እርሱም ፡ ይበረታበታል ፡ ይሠለጥንግል ፤ ግዛቱም ፡ ታላቅ ፡ ግዛት ፡ ይሆናል ።

፮ ከዘመናትም ፡ በኋላ ፡ ይጋጠማሉ ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ታጋ ፡ ኪዳን ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ትመጣለች ፤ የክንድዋ ፡ ኃይል ፡ ግን ፡ አይጸናም ÷ እርሱና ፡ ክንዱም ፡ አይጸናም ፤ እርስዋና ፡ እርስዋን ፡ ያመጡ ፡ የወለዳትም ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ያጸናት ፡ አልፈው ፡ ይሰጣሉ ።

፯ ነገር ፡ ግን ፡ ከሥርዋ ፡ ቍጥቋጥ ፡ አንዱ ፡ በስፍራው ፡ ይነሣል ፤ ወደ ፡ ሠራዊቱም ፡ ይመጣል ÷ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ አምባ ፡ ይገባል ÷ በላያቸውም ፡ ያደርጋል ÷ ያሸንፋልም ።

፰ አማልክቶቻቸውንና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎቻቸውን ፡ ከብርና ፡ ከወርቅም ፡ የተሠሩትን ፡ የከበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይማርካል ፤ እስከ ፡ ጥቂትም ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ሳይዋጋ ፡ ይቀመጣል ።

፱ ይህ ም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ መንግሥት ፡ ይገባል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ ምድሩ ፡ ይመለሳል ።

፲ ልጆቹም ፡ ይዋጋሉ ፡ ብዙ ፡ ሠራዊትንና ፡ ሕዝብን ፡ ይሰበስባል ፤ እርሱም ፡ ይመጣል ÷ ይጐርፍማል ÷ ያልፍማል ፡ ተመልሶም ፡ እስከ ፡ አምባው ፡ ድረስ ፡ ይዋጋል ። የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ይቈጣል ፡ ወጥቶም ፡ ከሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ይዋጋል ፡ ብዙ ፡ ሕዝብንም ፡ ለሰልፍ ፡ ያቆማል ÷ ሕዝቡም ፡ አልፎ ፡ በእጁ ፡ ይሰጣል ። ሕዝቡም ፡ በተወሰደ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ይታበያል ፤ እልፋትንም ፡ ይጥላል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አያሸንፍም ። የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ይመለሳል ÷ ከቀደመውም ፡ የበለጠ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ለሰልፍ ፡ ያቆማል ፤ በዘመናትና ፡ በዓመታትም ፡ ፍጻሜ ፡ ከታላቅ ፡ ሠራዊትና ፡ ከብዙ ፡ ሀብት ፡ ጋር ፡ ይመጣል ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ፤ ከሕዝብህም ፡ መከከል ፡ የዓመፅ ፡ ልጆች ፡ ራእዩን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ይነሣሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይወድቃሉ ። የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ይመጣል ÷ አፈርንም ፡ ይደለድላል ÷ የተመሸገች ፡ ንም ፡ ከተማ ፡ ይወስዳል ፤ የደቡብም ፡ ሠራዊት ፡ የተመረጡትም ፡ ሕዝቡ ፡ አይቆሙም ፡ ለመቋቋምም ፡ ኃይል ፡ የላቸውም ። በእርሱም ፡ ላይ ፡ የሚመጣው ፡ ግን ፡ እንደ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ÷ በፊቱም ፡ የሚቆም ፡ የለም ፤ በመልካሚቱም ፡ ምድር ፡ ይቆማል ÷ በእጁም ፡ ውስጥ ፡ ጥፋት ፡ ይሆናል ። ከመንግሥቱም ፡ ሁሉ ፡ ኃይል ፡ ጋር ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ፊቱን ፡ ያቀናል ÷ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አንድነትን ፡ ያደርጋል ፤ ያረ ክሳትም ፡ ዘንድ ፡ ሴትን ፡ ልጅ ፡ ይሰጠዋል ፤ እርስዋም ፡ አትጸናም ፡ ለእርሱም ፡ አትሆንም ።

፲፯ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ይሴቶች ፡ ይመልሳል ፡ ብዙዎችንም ፡ ይወስዳል ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ስድቡን ፡ ይሽራል ÷ ስድቡንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ። ፊቱንም ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ ምድሩ ፡ አምባዎች ፡ ይመልሳል ፤ ተሰናክሎም ፡ ይወድቃል ÷ አይገኝምም ።

፲፰ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በመንግሥቱ ፡ ክብር ፡ መከክል ፡ አስገባሪውን ፡ የሚያሳልፍ ፡ በስፍራው ፡ ይነሣል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በቍጣው ፡ ላይሆን ፡ በሰልፍም ፡ ላይሆን ፡ በጥቂት ፡ ቀን ፡ ይሰበራል ።

፲፱ በእርሱም ፡ ስፍራ ፡ የተጠቃ ፡ ሰው ፡ ይነሣል ፤ የመንግሥቱንም ፡ ክብር ፡ አይሰጡትም ፤ በቀስታ ፡ መጥቶ ፡ መንግሥቱን ፡ በማታለል ፡ ይገዛል ። የሚጐርፍም ፡ ሠራዊት ፡ ከፊቱ ፡ ይወሰዳል ÷ እርሱና ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ አለቃም ፡ ይሰበራሉ ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ከተወዳጀ ፡ በኋላ ፡ በተንኰል ፡ ያደርጋል ፤ ከጥቂትም ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ወጥቶ ፡ ይበረታል ። በቀስታም ፡ ከአገር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ለመለመችው ፡ ከፍል ፡ ይገባል ፤ አባቶቹና ፡ የአባቶቹ ፡ አባቶች ፡ ያላደረጉትን ፡ ያደርጋል ፤ ብዝበዛውንና ፡ ምርኮውንም ፡ ሀብቱንም ፡ በመካከላቸው ፡ ይበትናል ፤ በምሽጎችም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ድረስ ፡ አሳቡን ፡ ይፈጥራል ። በታላቅም ፡ ሠራዊት ፡ ሆኖ ፡ ኃይሉንና ፡ ልቡን ፡ በደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ያስነሣል ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ በታላቅና ፡ በብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ሆኖ ፡ በሰልፍ ፡ ይዋጋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሳብ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይፈጥራሉና ፡ አይጸናም ። መብሉንም ፡ የሚበሉ ፡ ሰዎች ፡ ይሰብሩታል ፤ ሠራዊቱም ፡ ይጐርፋል ፤ ብዙዎችም ፡ ተገድለው ፡ ይወድቃሉ ። እነዚህም ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት ፡ ክፋትን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በልባቸው ፡ ያስባሉ ÷ በአንድ ፡ ገበታም ፡ ተቀምጠው ፡ ሐሰት ፡ ይናገራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፍጻሜው ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፡ አይከናወንላቸውም ።

፳፱ ከብዙም ፡ ሀብት ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ይመለሳል ÷ ልቡም ፡ በተቀደሰው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፤ ፈቃዱንም ፡ ያደርጋል ÷ ወደ ፡ ገዛ ፡ ምድሩም ፡ ይመለሳል ። በተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ ይመለሳል ፡ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ይመጣል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኋለኛው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ አይሆንም ። የኪቲም ፡ መርከቦች ፡ ይመጡበታልና ፡ ስለዚህ ፡ አዝኖ ፡ ይመለሳል ÷ በቅዱሱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ÷ ፈቃዱንም ፡ ያደርጋል ፡ ተመልሶም ፡ ቅዱሱን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የተዉትን ፡ ሰዎች ፡ ይመለከታል ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሠራዊቶች ፡ ይቆማሉ ÷ መቅደሱንም ፡ ግንቡንም ፡ ያረክሳሉ ÷ የዘወትሩንም ፡ መሥዋዕት ፡ ያስቀራሉ ÷ የጥፋትንም ፡ ርኵሰት ፡ ያቆማሉ ። ቃል ፡ ኪዳንን ፡ የሚበድሉትንም ፡ በማታለል ፡ ያስታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አምላኩቸውን ፡ የሚያውቁ ፡ ሕዝብ ፡ ይበረታሉ ÷ ያደርጋሉም ። በሕዝቡም ፡ መከከል ፡ ያሉ ፡ ጥበበኞች ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያስተምራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሰይፍና ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ በምርኮና ፡ በመበገዝገዝ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ይወድቃሉ ። በወደቁም ፡ ጊዜ ፡ በጥቂት ፡ እርዳታ ፡ ይረዳሉ ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በግብዝነት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተባብረው ፡ ይሰበሰባሉ ። እስከ ፡ ተወሰነውም ፡ ዘመን ፡ ይሆናልና ፡ ከጥበበኞቹ ፡ አያሌዎቹ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ይነጥሩና ፡ ይበሩ ፡ ይነጡም ፡ ዘንድ ፡ ይወድቃሉ ።

፴፮ ንጉሡም ፡ እንደ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፤ ራሱንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ራሱን ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋል ÷ በአማልክትም ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ በትዕቢት ፡ ይናገራል ፤ ቍጣም ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ይከናወናልና ፤ የተወሰነው ፡ ይደረጋልና ። የአባቶቹንም ፡ አማልክት ፡ የሴቶችንም ፡ ምኞት ፡ አይመለከትም ፤ ራሱንም ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋልና ፡ አማልክትን ፡ ሁሉ ፡ አይመለከትም ። በእነዚህ ፡ ፋንታ ፡ ግን ፡ የአምባዎቹን ፡ አምላክ ፡ ያከብራል ፤ አባቶቹም ፡ ያላወቁትን ፡ አምላክ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ በዕንቍና ፡ በከበረ ፡ ነገር ፡ ያከብረዋል ። በእንግዳም ፡ አምላክ ፡ እርዳታ ፡ በጽኑ ፡ አምባ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፡ ለሚያውቁት ፡ ክብር ፡ ያበዛላቸዋል ÷ በብዙም ፡ ላይ ፡ ያስገዛቸዋል ÷ ምድርንም ፡ በዋጋ ፡ ይከፍላል ።

፴፯ በፍጻሜ ፡ ዘመንም ፡ የደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይዋጋል ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ከሰረገሎችና ፡ ከፈረሰኞች ፡ ከብዙም ፡ መርከቦች ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይመጣበታል ፤ ወደ ፡ አገሮችም ፡ ይገባል ÷ ይጐርፍማል ÷ ያልፍማል ። ወደ ፡ መልካሚቱም ፡ ምድር ፡ ይገባል ÷ ብዙ ፡ አገሮችም ፡ ይወድቃሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኤዶምያስና ፡ ሞዓብ ፡ ከአሞንም ፡ ልጆች ፡ የበለጡት ፡ ከእጁ ፡ ይድናሉ ። እጁን ፡ በአገሮች ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ÷ የግብጽም ፡ ምድር ፡ አታመልጥም ። በወርቅና ፡ በብርም ፡ መዝገብ ፡ ላይ ÷ በከበረችም ፡ በግብጽ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይሠለጥናል ፤ የልብያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎችም ፡ ይከተሉታል ። ከምሥራቅና ፡ ከሰሜን ፡ ግን ፡ ወሬ ፡ ያውከዋል ፡ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ያገድፋል ፡ ዘንድና ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ ቍጣ ፡ ይወጣል ። ንጉሣዊ ፡ ድንኳኑንም ፡ በባሕርና ፡ በከበረው ፡ በቅዱሱ ፡ ተራራ ፡ መከከል ፡ ይተክላል ፤ ወደ ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ይመጣል ÷ ማንም ፡ አይረዳውም ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ሕዝብህ ፡ ልጆች ፡ የሚቆመው ፡ ታላቁ ፡ አለቃ ፡ ሚካኤል ፡ ይነሣል ፤ ሕዝብም ፡ ከሀገኑ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚያ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ ያልሆነ ፡ የመከራ ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ በመጽሐፉ ፡ ተጽፎ ፡ የተገኘው ፡ ሕዝብህ ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ይድናል ። በምድርም ፡ ትቢያ ፡ ውስጥ ፡ ከንቀላፉቱ ፡ ብዙዎች ፡ ይነቃሉ ፤ እነሱም ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሕይወት ÷ እነሱም ፡ ወደ ፡ እፍረትና ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ጕስቍልና ። ጥበበኞቹም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ዐዳል ÷ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ የሚመልሱ ፡ እንደ ፡ ከዋክብት ፡ ለዘላለም ፡ ይደምቃሉ ። ዳንኤል ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ቃሉን ፡ ዝጋ ÷ መጽሐፉንም ፡ አትም ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይመረምራሉ ÷ እውቀትም ፡ ይበዛል ።

፭ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ እየሁ ፤ እነሆም ÷ ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ÷ አንዱ ፡ በዚህ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ÷ ሌላውም ፡ በዚያ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ።

፮ አንዱም ፡ ከወንዙ ፡ ውኃ ፡ በላይ ፡ የነበረውን ፡ በፍታም ፡ የለበሰውን ፦ የዚህ ፡ ድንቅ ፡ ፍጻሜ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? አለው ። ከወንዙም ፡ ውኃ ፡ በላይ ፡ የነበረው ፡ በፍታም ፡ የለበሰው ፡ ሰው ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንሥቶ ፦ ለዘመንና ፡ ለዘመናት ፡ ለዘመንም ፡ እነሱልታ ፡ ነው ፡ የተቀደሰውም ፡ ሕዝብ ፡ ኃይል ፡ መበተን ፡ በተጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸማል ፡ ብሎ ፡ ለዘላለም ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ በሚኖረው ፡ ሰምል ፡ ሰማሁ ። ሰማኑም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አላስተዋልሁም ፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አልሁ ። እርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ÷ ቃሉ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተዘጋና ፡ የታተመ ፡ ነውና ፡ ሂድ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያጠራሉ ፡ ያነጡማል ፡ ይነጥሩማል ፡ ክፉዎች ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡ ያደርጋሉ ፡ ክፉዎችም ፡ ሁሉ ፡ አያስተውሉም ÷ ጥበበኞች ፡ ግን ፡ ያስተውላሉ ። የዘወትሩም ፡ መሥዋዕት ፡ ከቀረ ፡ ጀምሮ ÷ የጥፋትም ፡ ርኵሰት ፡ ከቆመ ፡ ጀምሮ ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ቀን ፡ ይሆናል ። የሚታገሥ ÷ እስከ ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ቀንም ፡ የሚደርስ ፡ ምስጉን ፡ ነው ። አንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ድረስ ፡ ሂድ ፤ አንተም ፡ ታርፋለህ ÷ በቀኑም ፡ መጨረሻ ፡ በዕጣ ፡ ክፍልህ ፡ ትቆማለህ ።

ትንቢተ ሆሴዕ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ በይሁዳ ነገሥታት ፣ በዖዝያንና ፣ በኢዮአታም ፣ በአካዝና ፣ በሕዝቅያስም ፣ ዘመን ፣ በእስራኤልም ፣ ንጉሥ ፣ በዮአስ ፣ ልጅ ፣ በኢዮርብዓም ፣ ዘመን ፣ ወደ ፣ ብኤሪ ፣ ልጅ ፣ ወደ ፣ ሆሴዕ ፣ የመጣ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ቃል ፣ ይህ ፣ ነው ።

፪ እግዚአብሔር ፣ መጀመሪያ ፣ በሆሴዕ ፣ በተናገረ ፣ ጊዜ ፣ እግዚአብሔር ፣ ሆሴዕን ፦— ምድሪቱ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ርቃ ፣ ታላቅ ፣ ግልሙትና ፣ ታደርጋለችና ፣ ሂድ ፣ ጋለሞታን ፣ ሴትና ፣ የግልሙትናን ፣ ልጆች ፣ ለአንተ ፣ ውሰድ፡ አለው።

፫ እርሱም ፣ ሄዶ ፣ የዲቤላይምን ፣ ልጅ ፣ ጎሜርን ፣ አገባ ፤ እርስዋም ፣ ፀነሰች ፣ ወንድ ፣ ልጅንም ፣

፬ ወለደችለት ። እግዚአብሔርም ፡— ከጥቂት ፣ ዘመን ፣ በኋላ ፣ የኢይዝራኤልን ፣ ደም ፣ በኢዩ ፣ ቤተ ፣ ላይ ፣ እበቀላለሁና ፥ ከእስራኤልም ፣ ቤት ፣ መንግሥትን ፣ እሽራለሁና ፣ ስሙን ፣ ኢይዝራኤል ፣ ብለህ ፣ ጥራው ፤

፭ በዚያም ፣ ቀን ፣ በኢይዝራኤል ፣ ሸለቆ ፣ ውስጥ ፣ የእስራኤልን ፣ ቀስት ፣ እሰብራለሁ ፣ አለው ።

፮ ደግሞ ፣ ፀነሰች ፣ ሴት ፣ ልጅንም ፣ ወለደች ። እግዚአብሔርም ፡— ይቅር ፣ እላቸው ፣ ዘንድ ፣ የእስራኤልን ፣ ቤት ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ አልምርምና ፣ ስምዋን ፣ ሎሩሃማ ፣

፯ ብለህ ፣ ጥራት ፤ ነገር ፣ ግን ፣ የይሁዳን ፣ ቤት ፣ እምራለሁ ፣ በአምላካቸውም ፣ በእግዚአብሔር ፣ አድናቸዋለሁ ፣ እንጂ ፣ በቀስት ፣ ወይም ፣ በሰይፍ ፣ ወይም ፣ በሰልፍ ፣ ወይም ፣ በፈረሶች ፣ ወይም ፣ በፈረሰኞች ፣ አላድናቸውም ፡ አለው ።

፰ ሎሩሃማም ፣ ጡት ፣ ባስጣለች ፣ ጊዜ ፥ ደግሞ ፣ ፀነሰች ፣ ወንድ ፣ ልጅንም ፣ ወለደች ።

፱ እግዚአብሔርም ፡— ሕዝቤ ፣ አይደላችሁምና ፥ እኔም ፡ አምላክ ፣ አልሆንላችሁምና ፣ ስሙን ፣ ሎዓሚ ፣ ብለህ ፡ ጥራው ፡ አለው ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ የእስራኤልም ፣ ልጆች ፣ ቍጥር ፣ እንደማይሰፈርና ፣ እንደማይቈጠር ፣ እንደ ፣ ባሕር ፣ አሸዋ ፣ ይሆናል ፣ እንጂ ፡ ያም ፣ ይሆናል ፣ እናንተ ፣ ሕዝቤ ፣ አይደላችሁም ፣ ተብሎ ፣ በተነገረበት ፣ በዚያ ፣ ስፍራ ፣ የሕያው ፣ አምላክ ፣ ልጆች ፣ ይባላሉ ።

፪ የይሁዳ ፣ ልጆችና ፣ የእስራኤል ፣ ልጆች ፣ በአንድነት ፣ ይሰበሰባሉ ፥ ለእነርሱም ፣ አንድ ፡ አለቃ ፣ ይሾማሉ ፥ ከምድሪቱም ፣ ይወጣሉ ፣ የኢይዝራኤል ፣ ቀን ፣ ታላቅ ፣ ይሆናልና ።

፫ ወንድሞቻችሁን ፡— ዓሚ ፥ እኅቶቻችሁንም ፡— ሩሃማ ፣ በሉአቸው ።

፬ እናታችሁ ፣ ሚስቴ ፡ አይደለችምና ፥ እኔም ፣ ባልዋ ፡ አይደለሁምና ፣ ተምዋገቱ ፡ ከእናታችሁ ፣ ጋር ፣ ተምዋገቱ ። ግልሙትናዋን ፣ ከፊትዋ ፥ ምንገዘርናዋንም ፣ ከጡቶችዋ ፣ መካከል ፣ ታስ

፭ ወግድ ፣ ዕራቁትዋን ፣ እንዳልገፍፋት ፡ እንደ ፣ ተወለደችበትም ፣ ቀን ፣ እንዳላደርጋት ፥ እንደ ፣ ምድረ ፣ በዳና ፡ እንደ ፣ ደረቅ ፣ ምድር ፣ እንዳላ

፮ ደርጋት ፥ በጥማትም ፣ እንዳልገድላት ፣ የግል ሙትናዋ ፣ ልጆች ፣ ናቸውና ፣ ልጆችዋን ፡ አል

፯ ምርም ። እናታቸው ፣ አመንዝራለች ፣ የፀነሰቻቸውም ፣ እንጀራዩንና ፣ ውኃዬን ፥ ጥጠ ንና ፣ የተልባ ፣ እግሬን ፥ ዘይቴንና ፣ መጠጠን ፣ ከሚሰጡኝ ፣ ከውሽሞቼ ፣ በኋላ ፣ እሄዳለሁ ፣

፰ ብላ ፡ አስነወረቻቸው ። ስለዚህ ፥ እነሆ ፥ መንገድሽን ፣ በእሾህ ፣ እዘጋለሁ ፥ መንገድዋንም ፡

፱ እንዳታገኝ ፣ ቅጥርን ፣ እቀጥርበታለሁ ። ውሽሞችዋንም ፣ ትከተላለች ፥ ነገር ፣ ግን ፣ እት ደርስባቸውም ፡ ትፈልጋቸውማለች ፥ ነገር ፣ ግን ፣ አታገኛቸውም ፡ እርስዋም ፡— ከባሬ ፣ ይልቅ ፣ የዚያን ፣ ጊዜ ፣ ይሻለኝ ፡ ነበርና ፣ ተመልሺ ፣ ወደ ፣ ቀደመው ፣ ባሴ ፡ እሄዳለሁ ፡ ትላለች ።

፲ እርስዋም ፡ አህልንና ፣ ወይንን ፡ ጠጅ ፡ ዘይትንም ፣ የሰጠኋት ፡ ለበአልም ፡ የተሠራውን ፣ ብርና ፣ ወርቅ ፡ያበዛሁላት ፣ እኔ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡

፲፩ አላወቀችም ። ስለዚህ ፡ እነሴን ፣ በጊዜዋ ፥ ወይን ፡ ጠጄንም ፣ በወረትዋ ፡ እወስዳለሁ ፥ ዕራ ቁትነትዋንም ፣ እንዳትሸፍን ፡ ጥጠንና ፣ የተ

፲፪ ልባ ፡ አግሬን ፡ እንፍታለሁ ። አሁንም ፡ ውሽሞችዋ ፡ እያዩ ፡ ነውርዋን ፡ እገልጣለሁ ፡ ከእጄም ፡

፲፫ ማንም ፡ አያድናትም ። ደስታዋንም ፡ ሁሉ ፥ በዓላቶችዋንም ፡ መጋቻዎችዋንም ፥ ሰንበቶች ዋንም ፥ የተቀደሱትንም ፡ ጉባኤዎችን ፡ ሁሉ ፡

፲፬ አስቀራለሁ ። እርስዋም ፡— ውሽሞቼ ፡ የሰጡኝ ፡ ዋጋዬ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ያሉትን ፡ ወሮበ ዋንና ፡ በለስዋን ፡ አጠፋለሁ ፡ ዱርም ፡ አደርገ ዋለሁ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ይበሉታል ።

፲፭ እኔን ፡ረስታ ፡ ውሽሞችዋን ፡ እየተከተለች ፥ በጉትጆችዋና ፣ በጌጥዋም ፡ እያጌጠች ፡ ለበአ ሊም ፡ ያጠነችበትን ፡ ወራት ፡ እበቀልባታለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

፲፮ ስለዚህ ፥ እነሆ ፥ አባብላታለሁ ፥ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ አመጣታለሁ ፥ ለልብዋም ፡

፲፯ እናገራለሁ ። ከዚያም ፡ የወይን ፡ ቦታዋን ፥ የተስፋ ፡ በርም ፡ እንዲሆንላት ፡የአኮርን ፡ሸለቆ ፡ አሰጣታለሁ ፡ በዚያም ፡ከግብጽ ፡ምድር ፡እንደ ፡ ወጣችበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሕፃንነትዋ ፡ ወራት ፡

፲፰ ትዘምራለች ። በዚያ ፡ ቀን ፡ ባል ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪኛለሽ ፡ እንጂ ፡ ዳግመኛ ፡ በእሌ ፡ ብለሽ ፡ አትጠሪኝም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ የበአሊምን ፡

፲፱ ስም ፡ ከአፍዋ ፡ አስወግደዋለሁና ፥ በስማቸው ም ፡ እንግዲህ ፡ አያታስቡምና ።

፳ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከምድር ፡ አራዊትና ፡ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ከመሬትም ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርግላቸዋለሁ ፡ ቀስትንና ፡ ሰይፍን ፡ ሰልፍ ፡ እንም ፡ ከምድሩ ፡ እሰብራለሁ ፡ ተኝልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አስተኛቸዋለሁ ። ለዘላለምም ፡ለእኔ ፡ ፳፩ እንድትሆኚ ፡ አጭሻለሁ ፡ በጽድቅና ፡ በፍርድ ፡ በምሕረትና ፡ በርኅራኄ ፡ አጭሻለሁ ። ለእኔም ፡ ፳፪ እንድትሆኚ ፡ በመታመን ፡ አጭሻለሁ ፡ አንቺም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታውቂአለሽ ።

፳፫ በዚያንም ፡ ቀን ፡ እመልሳለሁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰማይ ፡ እመልሳለሁ ፡ ሰማይም ፡ ለምድር ፡ ይመልሳል ፡ ምድርም ፡ ለእህልና ፡ ፳፬ ለወይን ፡ ጠጅ ፡ ለዘይትም ፡ ትመልሳለች ፡ እነርሱም ፡ ለኢይዝራኤል ፡ ይመልሳሉ ። በምድርም ፡ላይ ፡ ለእኔ ፡ እዘራታለሁ ፡ ምሕረትም ፡ የሌላትን ፡ እምራለሁ ፥ ሕዝቤም ፡ ያልሆነውን ፡— አንተ ፡ ሕዝቤ ፡ ነህ ፡ እለዋለሁ ፡ እርሱም ፡— አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነህ ፡ ይለኛል ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡— የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ አማልክት ፡ ቢመለሱና ፡ የዘቢብ ፡ ጥፍጥፍን ፡ ቢወድዱ ፡ እንኳ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደሚወድዳቸው ፡ አንተም ፡ ውሽማዋን ፡ የምትወድደውን ፡ አመንዝራይትን ፡ ሴት ፡ ውደድ ፡ አለኝ ። እኔም ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ፪ ብርና ፡ በአንድ ፡ ቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ተኩል ፡ ገብስ ፡ ገዛኋት ። ከእኔ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ፫ ተቀመጪ ፥ አታመንዝሪም ፥ ለሌላ ፡ ሰውም ፡ አትሁኚ ፡ እኔም ፡ እንዲሁ ፡ እሆንልሻለሁ ፡ አልኋት ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያለ ፡ ንጉሥና ፡ ፬ ያለ ፡ አሰቃ ፥ ያለ ፡ መሥዋዕትና ፡ ያለ ፡ ዓምድ ፥ ያለ ፡ ኤፉድና ፡ ያለ ፡ ተራፊም ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ይቀመጣሉና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ፭ ልጆች ፡ ተመልሰው ፡ እግሳላቸውን ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሣቸውን ፡ ዳዊትን ፡ ይፈልጋሉ ፡ በኋለኛውም ፡ ዘመን ፡ ፈርተው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ወደ ፡ በረከቱ ፡ ይመጣሉ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እውነትና ፡ ምሕረት ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ማወቅ ፡ በምድር ፡ ስለሌለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩ ፡ ጋር ፡ ክርክር ፡ አለውና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ስሙ ። እርግማንና ፡ ሐሰት ፡ ፪ ግዳይና ፡ ስርቆት ፡ ምንዝርናም ፡ ወጥተዋል ፡ ደምም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ደርሶአል ። ስለዚህ ፡ ምድ ፫ ሪቱ ፡ ታለቅሳለች ፥ በእርስዋም ፡ የሚቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ ከምድር ፡ አራዊትና ፡ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ጋር ፡ ይደክማሉ ፡ የባሕሩም ፡ ዓሦች ፡ ያልቃሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝብህ ፡ ከክህን ፡ ጋር ፡ እንደሚከራከሩ ፡ ናቸውና ፡ ማንም ፡ አይከራከር ፥ ማንም ፡ አይገለጥ ። በቀንም ፡ ትሰናከላለህ ፥ ነቢይም ፡ ፭ ከአንተ ፡ ጋር ፡ በሌሊት ፡ ይሰናከላል ፡ እናትህንም ፡ አጠፋታለሁ ።

፮ ሕዝቤ ፡ እውቀት ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሣ ፡ ጠፍቶአል ፡ አንተም ፡ እውቀትን ፡ ጠልተሃልና ፡

እኔ ፥ ካህን ፥ እንዳትሆንኝ ፥ አጠላሃለሁ ፥ የአምላክህንም ፥ ሕግ ፥ ረስተሃልና ፥ እኔ ፥ ደግሞ ፥ ልጆችህን ፥ እረሳለሁ ። እንደ ፥ ብዛታቸው ፥ መጠን ፥ ኃጢአት ፥ ሠሩብኝ ፥ እኔም ፥ ክብራቸውን ፥ ወደ ፥ ነውር ፥ እለውጣለሁ ። የሕዝቤም ፥ ኃጢአት ፥ መብል ፥ ሆኖላቸዋል ÷ ልባቸውንም ፥ ወደ ፥ በደላቸው ፥ አድርገዋል ። እንደ ፥ ሕዝቡም ፥ እንዲሁ ፥ ካህኑ ፥ ይሆናል ፤ በመንገዳቸውም ፥ እበቀላቸዋለሁ ÷ ሥራቸውንም ፥ እመልስባቸዋለሁ ። እግዚአብሔርንም ፥ መጠበቅ ፥ ትተዋልና ፥ ሲበሉ ፥ አይጠግቡም ÷ ሲያመነዝሩም ፥ አይበዙም ።

ግልሙትናና ፥ የወይን ፥ ጠጅ ፥ ስካርም ፥ አእምሮን ፥ ያጠፋል ። የግልሙትና ፥ መንፈስ ፥ ሕዝቤን ፥ አስቶአቸዋልና ÷ እነርሱም ፥ ከእም ላክቸው ፥ ርቀው ፥ አመንዝረዋልና ፥ በትራቸውን ፥ ይጠይቃሉ ÷ ዘንጋቸውም ፥ ይመልስላቸዋል ። በተራሮችም ፥ ራስ ፥ ላይ ፥ ይሠዋሉ ፥ ጥላውም ፥ መልካም ፥ ነውና ፥ ከከምበልና ፥ ከልብን ፥ ከእሆማም ፥ ዛፍ ፥ በታች ፥ በኮረብቶች ፥ ላይ ፥ ያጥናሉ ፥ ስለዚህ ፥ ሴቶች ፥ ልጆቻችሁ ፥ ይገለመጫሉ ÷ ሙሽሮቻችሁም ፥ ያመነዝራሉ ።

ወንዶችም ፥ ደግሞ ፥ ከጋለሞቶች ፥ ጋር ፥ ይጫወታሉና ÷ ከጋለሞቶችም ፥ ጋር ፥ ይሠዋሉና ፥ ሴቶች ፥ ልጆቻችሁ ፥ በገለሞቱ ፥ ጊዜ ÷ ሙሽሮቻችሁም ፥ ባመነዘሩ ፥ ጊዜ ፥ አልቀጣቸውም ፥ የማያስተውልም ፥ ሕዝብ ፥ ይገለበጣል ።

አስራኤል ፥ ሆይ ÷ አንተ ፥ ብታመነዝር ፥ ይሁዳ ፥ አይበድል ፤ እናንተም ፥ ወደ ፥ ጌልገላ ፥ አትግቡ ÷ ወደ ፥ ቤትአዌንም ፥ አትውጡ ÷ ወደም ፥ — ሕያው ፥ እግዚአብሔርን ! ብላችሁ ፥ አትማሉ ።

አስራኤል ፥ እንደ ፥ እልከኛ ፥ ጊደር ፥ እንቢ ፥ ብሎአል ፤ እግዚአብሔርስ ፥ በሰፊው ፥ ቦታ ፥ እንደ ፥ ጠቦት ፥ ያሰማራዋልን ? ኤፍሬም ፥ ከጣዖታት ፥ ጋር ፥ ተጋብሮ ፥ ተወው ። ስካርን ፥ ፈጽመዋል ÷ ግልሙትናንም ፥ አዛዝተዋል ።

አለቆችዋም ፥ ነውርን ፥ እጅግ ፥ ወደዱ ። ነፋስ ፥ በክንፍዋ ፥ አስሮአታል ፥ ከመሥዋዕታቸውም ፥ የተነሣ ፥ ያፍራሉ ።

ምዕራፍ ፭ ።

ካህናት ፥ ሆይ ÷ ይህን ፥ ስሙ ፥ የእስራኤል ፥ ቤት ፥ ሆይ ÷ አድምጡ ፥ የንጉሥ ፥ ቤት ፥ ሆይ ÷ ልብ ፥ አድርጉ ፥ በምጽጳ ፥ ላይ ፥ ወጥመድ ÷ በታቦርም ፥ ላይ ፥ የተዘረጋ ፥ አሽክላ ፥ ሠርችኋልና ፥ ፍርድ ፥ በእናንተ ፥ ላይ ፥ ነው ። ዓመፀኞችም ፥ እርድ ፥ አብዝተዋል ፥ እኔ ፥ ግን ፥ እነዘያን ፥ ሁሉ ፥ እዘልፋለሁ ። ኤፍሬምን ፥ አውቀዋለሁ ÷ እስራኤልም ፥ ከእኔ ፥ አልተሰወረም ፥ ኤፍሬም ፥ ሆይ ÷ ዛሬ ፥ አመንዝረሃል ÷ እስራኤልም ፥ ረከሰአል ። ወደ ፥ አምላካቸው ፥ ይመለሱ ፥ ዘንድ ፥ ሥራቸውን ፥ አላቀኑም ፥ የግልሙትና ፥ መንፈስ ፥ በውስጣቸው ፥ አለና ፥ እግዚአብሔርንም ፥ አላወቁምና ። የእስራኤልም ፥ ትዕቢት ፥ በፊቱ ፥ ይመሰክራል ፥ ስለዚህ ፥ እስራኤልና ፥ ኤፍሬም ፥ በኃጢአታቸው ፥ ይሰናከላሉ ፥ ይሁዳም ፥ ደግሞ ፥ ከእነርሱ ፥ ጋር ፥ ይሰናከላል ። እግዚአብሔርንም ፥ ለመሻት ፥ በጎቻቸውንና ፥ ላሞቻቸውን ፥ ነድተው ፥ ይሄዳሉ ፥ ነገር ፥ ግን ፥ እርሱ ፥ ከእነርሱ ፥ ተመልሶአልና ፥ አያገኙትም ። ዲቃሎችን ፥ ልጆች ፥ ወልደዋልና ፥ እግዚአብሔርን ፥ ወንጅለዋል ፥ አሁንም ፥ እንድ ፥ ወር ፥ እነርሱንና ፥ ርስታቸውን ፥ ይበላቸዋል ።

በጌብዓ ፥ መለከትን ÷ በራማ ፥ እንቢልታን ፥ ንፋና ፥ — ብንያም ፥ ሆይ ÷ ከእንተ ፥ በኋላ ፥ እያላችሁ ፥ በቤትአዌን ፥ ላይ ፥ እረ ፥ በሉ ። ኤፍሬም ፥ በዘለፋ ፥ ቀን ፥ የፈረሰ ፥ ይሆናል ። በእስራኤል ፥ ነገሮች ፥ ዘንድ ፥ በእርግጥ ፥ የሚሆነውን ፥ ነገር ፥ ገልጫለሁ ። የይሁዳ ፥ አለቆች ፥ ድምበርን ፥ እንደሚነቅሉ ፥ ሆነዋል ፤ እኔም ፥ መዓቴን ፥ እንደ ፥ ውኃ ፥ አፈስስባቸዋለሁ ። ኤፍሬም ፥ ከትእዛዝ ፥ በኋላ ፥ መሄድን ፥ ወድዶአልና ፥ የተገፋና ፥ በፍርድ ፥ የተጐሳ ፥ ሆኖአል ። እኔም ፥ ለኤፍሬም ፥ እንደ ፥ ብል ÷ ለይሁዳም ፥ ቤት ፥ እንደ ፥ ነቀዝ ፥ ሆኜአለሁ ። ኤፍሬምም ፥ ደዌውን ÷ ይሁዳም ፥ ቍስሉን ፥ በየ ፥ ጊዜ ፥ ኤፍሬም ፥ ወደ ፥ አሦር ፥ ሄደ ፥ ወደ ፥ ንጉሡም ፥ ወደ ፥ ኢያሪም ፥ መልእክተኛን ፥ ላከ ፤ እርሱ ፥ ግን ፥ ይፈውሳችሁ ፥ ዘንድ ÷ ከቍስላችሁም ፥ ያድናችሁ ፥ ዘንድ ፥ አልቻለም ። እኔም ፥ ለኤፍሬም ፥ እንደ ፥ አንበሳ ÷ ለይሁዳም ፥ ቤት ፥ እንደ ፥ አንበሳ ፥ ደቦል ፤ እሠናለሁና ፥ እኔም ፥ ነጥቄ ፥ እሄዳለሁ ፥ እወስድማለሁ ÷ የሚያድንም ፥ አይገኝም ። በደላቸውንም ፥ እስኪያውቁ ፥ ድረስ ÷ ፊቴንም ፥ እስኪሹ ፥ ድረስ ፥ ሄጄ ፥ ወደ ፥ ስፍራዬ ፥ እመለሳለሁ ፥ በመከራቸው ፥ ጊዜ ፥ እጅግ ፥ አድርገው ፥ ፈቴን ፥ ይፈልጋሉ ።

ምዕራፍ ፮ ።

ኑ ÷ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ እንመለስ ፥ እርሱ ፥ ሰብሮናልና ÷ እርሱም ፥ ይፈውሰናል ፥ እርሱ ፥ መትቶናል ÷ እርሱም ፥ ይጠግነናል ። ከሁለት ፥ ቀን ፥ በኋላ ፥ ያድነናል ፥ በሦስተኛውም ፥ ቀን ፥ ያስነሣናል ÷ በፊቱም ፥ በሕይወት ፥ እንኖራለን ። እንወቅ ፥ እናውቀውም ፥ ፈንድ ፥ እግዚአብሔርን ፥ እንከተል ፥ እንደ ፥ ወገግታም ፥ ተዘጋጅቶ ፥ እናገኘዋለን ፥ እንደ ፥ ዝናብም ፥ ምድርንም ፥ እንደሚያጠጣ ፥ እንደ ፥ መጨረሻ ፥ ዝናብ ፥ ይመጣል ።

ምሕረታችሁ ፥ እንደ ፥ ማለዳ ፥ ደመና ÷ በማለዳም ፥ እንደሚያልፍ ፥ ጠል ፥ ነውና ፥ ኤፍሬም ፥ ሆይ ÷ ምን ፥ ላድርግልህ ? ይሁዳ ፥ ሆይ ÷ ምን ፥ ላድርግልህ ? ስለዚህ ፥ በነቢያት ፥ እጅ ፥ ቈረጥኋቸው ÷ በአፌም ፥ ቃል ፥ ገደልኋቸው ፥ ፍርዴም ፥ እንደ ፥ ብርሃን ፥ ይወጣል ። ከመሥዋዕት ፥ ይልቅ ፥ ምሕረትን ÷ ከሚቃጠልም ፥ መሥዋዕት ፥ ይልቅ ፥ እግዚአብሔርን ፥ ማወቅ ፥ እወድዳለሁና ። እነርሱ ፥ ግን ፥ እንደ ፥ አዳም ፥ ቃል ፥ ኪዳንን ፥ ተላልፈዋል ፥ በዚያም ፥ ላይ ፥ ወንጀለውኛል ። ገለዓድ ፥ ኃጢአትን ፥ የሚሠሩ ፥ ሰዎች ፥ ከተማ ÷ በደምም ፥ የተቀባ ፥ ነው ። ለሰውም ፥ እንደሚያደቡ ፥ ወንበዴዎች ÷ እንዲሁ ፥ የካህናት ፥ ወገኖች ፥ በሴኬም ፥ መንገድ ፥ ላይ ፥ ይገድላሉ ፥ ሴሰኝነትንም ፥ ያደርጋሉ ።

በእስራኤል ፥ ቤት ፥ የሚያስፈራን ፥ ነገር ፥ አይቻለሁ ፥ በዚያ ፥ በኤፍሬም ፥ ውስጥ ፥ ግልሙትና ፥ ተገኘ ÷ እስራኤልም ፥ ረክሶአል ። ይሁዳ ፥ ሆይ ÷ የሕዝቤን ፥ ምርኮ ፥ በምመልስበት ፥ ጊዜ ፥ ለእንተ ፥ ደግሞ ፥ መከር ፥ ተወስኖልሃል ።

ምዕራፍ ፯ ።

በሐሰት ፥ አድርገዋልና ÷ ሴባም ፥ ገብቶአልና ÷ በውጭም ፥ ወንበዴዎች ፥ ቀምተዋልና ፥ አስራኤልን ፥ እፈውስ ፥ ዘንድ ፥ በወደድሁ ፥ ጊዜ ፥ የኤፍሬም ፥ ኃጢአትና ፥ የሰማርያ ፥ ክፋት ፥ ተገለጠ ። እኔም ፥ ክፋታቸውን ፥ ሁሉ ፥ እንዳሰብሁ ፥ በልባቸው ፥ አያስቡም ፥ አሁንም ፥ ሥራቸው ፥ ከብባቸዋለች ÷ በፊቴም ፥ አለች ። ንጉሡን ፥ በክፋታቸው ÷ አለቆቹንም ፥ በሐሰታቸው ፥ ደስ ፥ አሰኝተዋል ። ሁሉም ፥ አመንዝራዎች ፥ ናቸው ፥ ጋጋሪ ፥ እንደሚያነድዱበት ፥ እንደ ፥ ምድጃ ፥ ናቸው ፥ ሁሉ ፥ እስኪበስ ፥ ድረስ ፥ እሳትን ፥ መቄስቄስና ፥ እርሾን ፥ መለወስ ፥ ይቆያል ። በንጉሣችን ፥ ቀን ፥ አለቆች ፥ ከወይን ፥ ጠጅ ፥ መቀት ፥ የተነሣ ፥ ታመሙ ፥ እርሱም ፥ ከባዘኞች ፥ ጋር ፥ እጁን ፥ ዘረጋ ። እያደቡ ፥ ልባቸውን ፥ እንደ ፥ ምድጃ ፥ አዘጋጅተዋል ፥ አበዛቸውም ፥ ሴሲቴን ፥ ሁሉ ፥ እንቀላፋ ፥ በጠባም ፥ ጊዜ ፥ እንደ ፥ እሳት ፥ ነበልባል ፥ ይነድዳል ። ሁሉም ፥ እንደ ፥ ምድጃ ፥ ግለዋል ÷ ፈራጆቻቸውንም ፥ በሉ ፥ ነገሥታቶቻቸውም ፥ ሁሉ ፥ ወደቁ ፥ ከእነርሱም ፥ ወደ ፥ እኔ ፥ የሚጮኽ ፥ የለም ።

ኤፍሬም ፥ ከአሕዛብ ፥ ጋር ፥ ተደበላለቀ ፥ ኤፍሬም ፥ እንዳልተገላበጠ ፥ ቂጣ ፥ ነው ። እንግዶች ፥ ኮልበቱን ፥ በሉት ÷ እርሱም ፥ አላወቀም ፥ ሽበትም ፥ ወጣበት ÷ እርሱም ፥ አላወቀም ። የእስራኤልም ፥ ትዕቢት ፥ በፊቱ ፥ መሰከረ ፥ ወደ ፥ አምላካቸው ፥ ወደ ፥ እግዚአብሔር ፥ ግን ፥ አልተመለሱም ÷ በዚህም ፥ ሁሉ ፥ አልፈለጉትም ። ኤፍሬምም ፥ እእምሮ ፥ እንደሌላት ፥ እንደ ፥ ሰነፍ ፥ ርግብ ፥ ነው ፥ ግብጽን ፥ ጠሩ ÷ ወደ ፥ አሦርም ፥ ሄዱ ። ሲሄዱ ፥ አሽክላዬን ፥ እዘረጋባቸዋለሁ ፥ እንደ ፥ ሰማይ ፥ ወፎች ፥ አወርዳቸዋለሁ ፥ መከራቸውን ፥ ሲሰሙ ፥ እገሥጻቸዋለሁ ። ከእኔ ፥ ፈቀቅ ፥ ብለዋልና ፥ ወዮላቸው ! በእኔም ፥ ላይ ፥ ሠሩወልኝ ፥ ዋፋት ፥ ያምጣባቸው ! እኔ ፥ ልታደጋቸው ፥ ወደድሁ ÷ እነርሱ ፥ ግን ፥ በሐሰት ፥ ተናገሩብኝ ። በመኝታቸው ፥ ላይ ፥ ሆነው ፥ ያለቅሱ ፥ ነበር ፥ እንጂ ፥ በልባቸው ፥ ወደ ፥ እኔ ፥ አልጮኹም ፥ ስለ ፥ እህልና ፥ ስለ ፥ ወይን ፥ ጠጅ ፥ ይሰበሰቡ ፥ ነበር ፥ በእኔም ፥ ላይ ፥ ዐመፁ ። እኔም ፥ ከንዳቸውን ፥ አስተማርሁና ፥ አጸናሁ ፥ እነርሱ ፥ ግን ፥ ክፉ ፥ ነገርን ፥ መከሩብኝ ። ወደ ፥ ከንቱ ፥ ነገር ፥ ተመለሱ ፥ እንደ ፥ ተንኰለኛ ፥ ቀስት ፥ ሆኑ ፥ አለቆቻቸው ፥ ከምላሳቸው ፥ ቍጣ ፥ የተነሣ ፥ በሰይፍ ፥ ይወድቃሉ ፥ ይህ ፥ በግብጽ ፥ ምድር ፥ ውስጥ ፥ መሳለቂያ ፥ ይሆንባቸዋል ።

ምዕራፍ ፰ ።

መለከትን ፥ ወደ ፥ አፍህ ፥ አቅርብ ፥ ቃል ፥ ኪዳኔን ፥ ተላልፈዋልና ÷ በሕጌም ፥ ላይ ፥ ዐምፀዋልና ፤ በእግዚአብሔር ፥ ቤት ፥ ላይ ፥ እንደ ፥ ንስር ፥ ይመጣል ። እነርሱም ፥ — አምላክ ፥ ሆይ ÷ እኛ ፥ እስራኤል ፥ አውቅንህ ፥ ብለው ፥ ወደ ፥ እኔ ፥ ይጮኻሉ ። እስራኤል ፥ ደግነትን ፥ ጥሎአል ፥ ጠላትም ፥ ያሳድዱታል ። ለራሳቸው ፥ ነገሥታትን ፥ አነገሡ ÷ ከእኔም ፥ ዘንድ ፥ አይደለም ፥ አለቆችንም ፥ አደረጉ ÷ እኔም ፥ አላወቅሁም ፥ ለጥፋታቸውም ፥ ከብራቸውና ፥ ከወርቃቸው ፥ ጣዖታትን ፥ ለራሳቸው ፥ አደረጉ ። ሰማርያ ፥ ሆይ ÷ እምቦሳህን ፥ ጥሎአል ፥ ቍጣዬ ፥ በላያቸው ፥ ነድዶአል ፤ እስከ ፥ መቼ ፥ ድረስ ፥ ንጹሕ ፥ ሊሆኑ ፥ አይችሉም ? ይህ ፥ ደግሞ ፥ ከእስራኤል ፥ ዘንድ ፥ ነው ፥ ሠራተኛ ፥ ሠራው ÷ እርሱም ፥ አምላክ ፥ አይደለም ፥ የሰማርያም ፥ እምቦሳ ፥ ይቄራረጣል ። ነፋስን ፥ ዘርተዋል ÷ ዐውሎ ፥ ነፋስንም ፥ ያጭዳሉ ፥ አገዳ ፥ የለውም ÷ ከነፍሯውም ፥ ዱቄት ፥ አይገኝም ፥ ቢገኝም ፥ እንግዶች ፥ ይበሉታል ።

እስራኤል ፥ ተውጦአል ÷ በአሕዛብም ፥ መከክል ፥ ዛሬ ፥ እንደ ፥ ረከሰ ፥ ዕቃ ፥ ሆኖአል ። ለብቻውም ፥ እንደሚቀመጥ ፥ እንደ ፥ ምድረ ፥ በዳ ፥ አህያ ፥ ወደ ፥ አሦር ፥ ወጥተዋል ። ኤፍሬምም ፥ ወዳጆቹን ፥ በእጅ ፥ መንሻ ፥ ገዛ ። ነገር ፥ ግን ፥ ለአሕዛብ ፥ እጅ ፥ መንሻ ፥ ቢሰጡ ፥ እኔ ፥ አሁን ፥ እሰበስባቸዋለሁ ፥ ከንጉሥና ፥ ከአለቆችም ፥ ሸክም ፥ የተነሣ ፥ ይደክማሉ ።

ኤፍሬም ፥ ኃጢአትን ፥ ለመሥራት ፥ መሠዊያ ፥ አብዝቶአልና ፥ መሠዊያ ፥ ለኃጢአት ፥ ይሆንለታል ። የሕጌን ፥ ብዛት ፥ ጽፌለታለሁ ፥ እነርሱ ፥ ግን ፥ እንደ ፥ እንግዳ ፥ ነገር ፥ ቈጥረውታል ። መሥዋዕቴን ፥ ያቀርባሉ ÷ ሥጋንም ፥ ያርዳሉ ÷ ይበላሉም ፥ እግዚአብሔር ፥ ግን ፥ አይቀባቸውም ፥ በደላቸውንም ፥ ያስባል ÷ ኃጢአታቸውንም ፥ ይቀጣል ፥ እነርሱም ፥ ወደ ፥ ግብጽ ፥ ይመለሳሉ ። እስራኤል ፥ ፈጣሪውን ፥ ረስቶአል ÷ መስገጃዎችንም ፥ ሠርቶአል ፥ ይሁዳም ፥ የተመሸጉትን ፥ ከተሞች ፥ አብዝቶአል ፤ እኔ ፥ ግን ፥ በከተሞች ፥ ላይ ፥ እሳትን ፥ እሰድዳለሁ ÷ አዳራሾችንም ፥ ትበላለች ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ እስራኤል ፡ ሆይ ÷ ከአምላክህ ፡ ተለይተህ ፡ አመንዝረሃልና ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ደስ ፡ አይበልህ ÷ ሐሴትንም ፡ አታድርግ ፤ በአህሉ ፡ አውድማ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የግልሙትናን ፡ ዋጋ ፡ ወድ
፪ ደሃል ። አውድማውና ፡ መጥመቂያው ፡ አይመግባቸውም ÷ ጉሽ ፡ ጠጅም ፡ ይጐድልባታል ።
፫ በእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አይቀመጡም ፤ ኤፍሬምም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳል ÷ በአሦ
፬ ርም ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ይበላሉ ። ለእግዚአብሔር ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡ ቍርባን ፡ አያፈስሱም ÷ መሥዋዕታቸውም ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ። የኀዘንም ፡ እንጀራ ፡ ይሆንላቸዋል ÷ የሚበላውም ፡ ሁሉ ፡ ይረክሳል ። እንጀራቸውም ፡ ለሰውነታቸው ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
፭ ቤት ፡ አይገባም ። በዓመት ፡ በዓል ፡ ቀንና ፡ በእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ታደርጋላችሁ ? እነሆ ÷ ከጥፋት ፡ ሸሽተው ፡ ሄዱ ÷
፮ ግብጽም ፡ ትሰበስባቸዋለች ÷ ሜምፎስም ፡ ትቀብራቸዋለች ፤ ሰማም ፡ የብራቸውን ፡ ጌጥ ፡ ይወርሰል ÷ እሾህም ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ውስጥ ፡
፯ ይበቅላል ። የበቀል ፡ ወራት ፡ መጥቶአል ÷ የፍዳም ፡ ወራት ፡ ደርሶአል ÷ እስራኤልም ፡ ያውቃል ፤ ከኃጢአትህና ፡ ከጠላትነትህ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ነቢዩ ፡ ሰንፎአል ÷ መንፈስም ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ አብዶአል ። ኤፍሬም ፡ ከአምላኬ ፡ ጋር ፡ ተመልካች ፡ ነበረ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ነቢዩ ፡ በመንገዱ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የወፍ ፡ ወጥመድ ፡ ሆነ ÷ በአምላኩም ፡ ቤት ፡ ጠላትነት ፡ አለ ።
፱ በጊብዓ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ ረከሱ ፡ እርሱም ፡ በደላቸውን ፡ ያስባል ÷ ኃጢአታቸውንም ፡ ይበቀላል ።

፲ እስራኤልን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ወይን ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ፡ አባቶቻቸውንም ፡ ከመጀመሪያዋ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ በለስ ፡ በኩሉት ፡ ሆነው ፡ አየኋቸው ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ብኤልፈጎር ፡ መጡ ÷ ለነውርም ፡ ተለዩ ÷ እንደ ፡ ወደዱ
፲፩ ትም ፡ ርኩስ ፡ ሆኑ ። የኤፍሬምም ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ በርሮ ፡ ይጠፋል ፡ መውለድና ፡
፲፪ መፅነስ ፡ ማርገዝም ፡ አይሆንላቸውም ። ልጆቻቸውንም ፡ ቢያሳድጉ ፡ ሰው ፡ እንዳይቀርላቸው ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡ አደርጋቸዋለሁ ፤ ከእነርሱም ፡ በራቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ወዮላቸው ! እኔ ፡ እንዳየሁ ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ለምርኮ ፡ ተሰጥተዋል ፡ ኤፍሬምም ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ገዳዮች ፡
፲፫ ያወጣል ። አቤቱ ÷ ስጣቸው ፡ ምን ፡ ትሰጣቸዋለህ ? የሚጨነግፍን ፡ ማኅፀን ፡ የደረቀውንም ፡ ጡት ፡ ስጣቸው ። ክፋታቸው ፡ ሁሉ ፡ በጌልገላ ፡ አለ ፤ በዚያ ፡ ጠልቻቸዋለሁ ፤ ስለ ፡ ሥራት ፡ ክፋት ፡ ከቤቴ ፡ አሳድዳቸዋለሁ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አልወድዳቸውም ፡ አለቆቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ዓመፀኞች ፡ ናቸው ።
፲፮ ኤፍሬም ፡ ተመታ ÷ ሥሩም ፡ ደረቀ ÷ ፍሬም ፡ አያፈራም ፤ ደግሞም ፡ ቢወልዱ ፡ የማኅፀናቸውን ፡ ፍሬ ፡ እገድላለሁ ።
፲፯ አልሰሙትምና ፡ አምላኬ ፡ ይጥላቸዋል ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ተቅበዝባዦች ፡ ይሆናሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ እስራኤል ፡ ፍሬው ፡ የበዛለት ፡ የለመለመ ፡ ወይን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ፍሬው ፡ ብዛቱ ፡ መሠዊያውን ፡ አብዝቶአል ፡ እንደ ፡ ምድሩም ፡ ማማር ፡ መጠን ፡ ሐውልቶችን ፡ እያሳመሩ ፡ ሠርተዋል ።
፪ ልባቸው ፡ ተከፈለ ፡ አሁንም ፡ በደላቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ እርሱ ፡ መሠዊያቸውን ፡ ያፈርሰል ÷ ሐውልቶቻቸውን ፡ ያጠፋል ። አሁንም ፡—
፫ ንጉሥ ፡ የለንም ÷ እግዚአብሔርን ፡ አልፈራንምና ፤ ንጉሥስ ፡ ምን ፡ ያደርግልናል ? ይላሉ ።
፬ የማይረባውን ፡ ቃል ፡ ይናገራሉ ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ ይምላሉ ፤ ስለዚህ ፡ መርዛም ፡ ሣር ፡ በእርሻ ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ እንደሚበቅል ፡ መቅሠፍት ፡ ይበቅልባቸዋል ።
፭ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ቤትአዌን ፡ እምበሳ ፡ ይፈራሉ ፡ ከብሩም ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቶአልና ፡ ሕዝቡ ፡ ያለቅስለታል ÷ የጣዖቱ ፡ ካህናትም ፡ በጎዘን ፡ ደንተብተባሉ ። ለንጉሡ ፡ ለኢያሬም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አሦር ፡ ይማረካል ፡ ኤፍሬምን ፡ እፍረት ፡ ይይዘዋል ÷ እስራኤልም ፡ በምክሩ ፡ ያፍራል ።
፯ ሰማርያ ፡ ከንጉሥዋ ፡ ጋር ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ አረፋ ፡ ጠፍታለች ።
፰ የእስራኤል ፡ ኃጢአት ፡ የሆኑት ፡ የአዌን ፡ የኮረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ይፈርሳሉ ፤ እሾህና ፡ እሜከላ ፡ በመሠዊያዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይበቅላል ፤ ተራሮችንም ፡— ከደኑን ÷ ኮረብቶችንም ፡— ውደቁብን ፡ ይሉ ፡ አቸዋል ።
፱ እስራኤል ፡ ሆይ ÷ ከጊብዓ ፡ ዘመን ፡ ጀምረህ ፡ ኃጢአትን ፡ ሠርተሃል ፤ በዚያ ፡ ጸንተዋል ፤ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ አይደርስባቸውምን ? በፈቀድሁም ፡ ጊዜ ፡ አገሥጻቸዋለሁ ፡ ስለ ፡ ሁለቱም ፡ ኃጢአታቸው ፡ በታሰሩ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ይሰበሰቡባቸዋል ። ኤፍሬም ፡ ማበራየት ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ ጊደር ፡ ነው ÷ እኔ ፡ ግን ፡ በአንገቱ ፡ ውበት ፡ አሜንበታለሁ ፤ በኤፍሬም ፡ ላይ ፡ አጠምድበታለሁ ÷ ይሁዳም ፡ ያርሰል ÷ ያዕቆብም ፡ አፈሩን ፡ ያለሰልሳል ።
፲፪ እግዚአብሔር ፡ መጥቶ ፡ ጽድቅን ፡ እስኪያዘንባችሁ ፡ ድረስ ፡ እርሱን ፡ የምትሹበት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፡ ለእናንተ ፡ በጽድቅ ፡ ዝሩ ÷ እንደ ፡ ምሕረቱም ፡ መጠን ፡ እጨዱ ÷ ዋኖታችሁንም ፡ እረሱ ። ክፋትን ፡ አርሰችኋል ÷ ኃጢአትንም ፡ አጭዳችኋል ÷ የሐሰትንም ፡ ፍሬ ፡ በልታችኋል ፤ በኃያላንህ ፡ ብዛት ÷ በመንገድህም ፡ ላይ ፡ ታምነሃልና ።
፲፫ በሕዝብህም ፡ መካከል ፡ ሽብር ፡ ይነሣል ፤ እናትም ፡ ከልጆችዋ ፡ ጋር ፡ በተፈጠፈጠች ፡ ጊዜ ፡ ሰልማን ፡ ቤትአርብኤልን ፡ በሰልፍ ፡ ቀን ፡ እንዳፈረሰ ÷

፲፬ አምባዎችህ ፡ ሁሉ ፡ ይፈርሳሉ ። ከኃጢአታችሁም ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ቤቴል ፡ እንዲሁ ፡ ያደርግባችኋል ፡ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ፈጽሞ ፡ ይጠፋል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ እስራኤል ፡ ሕፃን ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ወደድ
፪ ሁት ÷ ልጄንም ፡ ከግብጽ ፡ ጠራሁት ። አብዝቼ ፡ ጠራሁ ፡ ግን ፡ ከፊቴ ፡ ራቁ ፤ ለበአሊምም ፡ ዩሠዉ ፡ ነበር ÷ ለተቀረጹ ፡ ምስ-
፫ ኖችም ፡ ያጥኑ ፡ ነበር ። እኔም ፡ ኤፍሬምን ፡ ክንዱን ፡ ይዤ ፡ በእግሩ ፡ እንዲሄድ ፡ መራሁት ፤ እኔም ፡ እፈውሳቸው ፡ እንደ ፡ ነበርሁ ፡ አላወቁም ። በሰው ፡ ገመድ ፡ በፍቅርም ፡ እስራት ፡
፬ ሳብኋቸው ፡ ለእነርሱም ፡ ቀምበርን ፡ ከላንቃቸው ፡ ላይ ፡ እንደሚያነሣ ፡ ሆንሁ ፡ ድርቆሽም ፡ ጣልሁላቸው ።
፭ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱምና ፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ÷ አሦርም ፡
፮ ንጉሣቸው ፡ ይሆናል ። ከመከሩትም ፡ ምክር ፡ የተነሣ ፡ ሰይፍ ፡ በከተሞቻቸው ፡ ላይ ፡ ይወድ
፯ ቃል ÷ ከበርቴዎችንም ፡ ያጠፋል ። ሕዝቤም ፡ ከእኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፡ ወደ ፡ ላይም ፡ ቢጠሩአቸው ፡ ማንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።
፰ ኤፍሬም ፡ ሆይ ÷ እንዴት ፡ አጥልሃለሁ ? እስራኤል ፡ ሆይ ÷ እንዴትስ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥሃለሁ ? እንዴትስ ፡ እንደ ፡ አዳማ ፡ አጥልሃለሁ ? እንዴትስ ፡ እንደ ፡ ሲባዮ ፡ አደርግሃለሁ ? ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተናውጣለች ÷ ምሕረቴም ፡ ተነሣ
፱ ሥታለች ። እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አይደለሁምና ÷ በመካከልህም ፡ ቅዱሱ ፡ ነኝና ፡ የቍጣዬን ፡ መቅሠፍት ፡ አላደርግም ÷ ኤፍሬምንም ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልመለስም ። በመ
፲ ዓትም ፡ አልመጣም ። እግዚአብሔርን ፡ ይከተላሉ ÷ እርሱም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ያገሣል ፤ ባገሣም ፡ ጊዜ ፡ ልጆች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡
፲፩ ከምዕራብ ፡ ይመጣሉ ። እንደ ፡ ወፍም ፡ ከግብጽ ፡ እንደ ፡ ርግብም ፡ ከአሦር ፡ ምድር ፡ እየ ተንቀጠቀጡ ፡ ይመጣሉ ፤ በዚአቸውም ፡ አኖራቸዋለሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ኤፍሬም ፡ በሐሰት ÷ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ በተንኰል ፡ ከበበኝ ፡ ይሁዳም ፡ ከታመነው ፡ ቅዱሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ አይጸናም ።
፪ ኤፍሬም ፡ ነፋስን ፡ ይበላል ÷ የምሥራቅንም ፡ ነፋስ ፡ ይከተላል ፡ ውልጊዜም ፡ ሐሰትንና ፡ ተንኰልን ፡ ያበዛል ፡ ከአሦር ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያደርጋሉ ÷ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳሉ ።
፫ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋር ፡ ክር ክር ፡ አለው ÷ ያዕቆብንም ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ይቀጣል ፡ እንደ ፡ ሥራውም ፡ ይመልስለታል ።
፬ በማኅፀን ፡ ውስጥ ፡ ወንድሙን ፡ በተረከዙ ፡ ያዘው ÷ በጕልማስነቱም ፡ ጊዜ ፡ ከአምላክ ፡ ጋር ፡ ታገለ ፡ ከመልአኩም ፡ ጋር ፡ ታግሎ ፡ አሸነፈ ። አልቅሶም ፡ ለመነው ። በቤቴልም ፡ አገኘው ÷ በዚያም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ።
፭ እርሱም ፡ የሠራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የመታሰቢያው ፡ ስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ አምላክህ ፡ ተመለስ ፤
፮ ምሕረትንና ፡ ፍርድን ፡ ጠብቅ ÷ ዘወትርም ፡ በአምላክህ ፡ ታመን ።
፯ ከነጋዴን ፡ ወገን ፡ ነው ፡ በእጁ ፡ የተንኰል ፡ ሚዛን ፡ አለ ÷ ሽንገላንም ፡ ይወድዳል ። ኤፍሬ-
፰ ምም ፡— ባለ ፡ ጠጋ ፡ ሆኜአለሁ ፡ ብለትንም ፡ አግኝቻለሁ ÷ በድካሜም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ የሚሆን ፡ በደል ፡ አይገኝብኝም ፡ አለ ። እኔም ፡ ከግብጽ ፡ ጀምሬ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ እንደ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በድንኳን ፡ እንድትኖር ፡ እደርግሃለሁ ። ለነቢያትም ፡ ተናግሬአለሁ ÷ ራእይንም ፡ አብዝቻለሁ ፡ በነቢያትም ፡ እጅ ፡ ምሳሌዎችን ፡ አውጥቻለሁ ። ኃጢአት ፡ በገለዓድ ፡ አለ ፡ ፈጽመው ፡
፲፩ ከንቱ ፡ ናቸው ። ወይፈኖች ፡ በጌልገላ ፡ ይሠዋሉ ÷ መሠዊያዎቻቸውም ፡ በእርሻ ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ይሆናሉ ። ያዕቆብ ፡
፲፪ ወደ ፡ ሶርያ ፡ አገር ፡ ሸሸ ÷ እስራኤልም ፡ ስለ ፡ ሚስት ፡ አገለገለ ÷ ስለ ፡ ሚስትም ፡ ጠባቂ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔርም ፡ በነቢይ ፡ እጅ ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣ ÷ በነቢይም ፡ እጅ ፡ ጠበቀው ። ኤፍሬም ፡ አስመርሮ ፡ አስቈጣው ፡
፲፫ ስለዚህ ፡ ደሙ ፡ በላዩ ፡ ነው ፡ ጌታውም ፡ ስድቡን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያመልሰል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ኤፍሬም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሃት ፡ ነበረ ÷ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ታበየ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በአልን ፡ በማምለክ ፡ በበደለ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ።
፪ አሁንም ፡ ኃጢአትን ፡ ይሥሩ ፡ ዘንድ ፡ ጨመሩ ፡ በብራቸውም ፡ ለራሳቸው ፡ ቀልጠ ፡ የተሠራ ፡ ምስልን ÷ እንደ ፡ ጥበባቸውም ፡ ጣዖታትን ፡ ሠርተዋል ፡ ሁሉም ፡ የሠራተኛ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ እነርሱም ፡— የሚሠዉ ፡ ሰዎች ፡ እምቦሰውን ፡ ይሳሙ ፡ ይላሉ ። ስለዚህም ፡
፫ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ደመና ÷ በጥዋትም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ጠል ÷ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ከአውድማ ፡ እንደሚበተን ፡ እብቅ ÷ ከመስኮትም ፡ እንደ ፡ ሚወጣ ፡ ጢስ ፡ ይሆናሉ ።
፬ እኔ ፡ ግን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ጀምሬ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታውቅም ÷ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መድኀኒት ፡ የለም ። በምድረ ፡ በዳ ÷ እጅግ ፡
፭ በደረቀ ፡ ምድር ፡ አውቁህ ፡ ነበር ። ከተሰማሩ ፡
፮ በኋላ ፡ ጠገቡ ÷ በጠገቡም ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ታበየ ፡ ስለዚህ ፡ ረሱኝ ። ስለዚህም ፡ እኔ ፡
፯ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ሆንሁባቸው ÷ እንደ ፡ ነብርም ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ እደባባቸዋለሁ ፡ ልጅዋ ፡
፰

እንደ፣ ተነጠቀበት ፡ ድብ ፣ እገዋማቸዋለሁ ÷ የልባቸውንም ፡ ስብ ፣ እቀድዳለሁ ፡ በዚያም ፡ እንደ ፡ አንበሳ፡ እበላቸዋለሁ ÷ የምድረ ፡ በዳም ፡ አውሬ ፣ ይነጣጠቃቸዋል ።

፱ እስራኤል ፡ ሆይ ÷ በእኔ ፣ በረዳትህ ፡ ላይ ፡
፲ በመነሣትህ ፡ ጥፋትህ ፡ ነው ። በየከተማህ ፡ ሁሉ ፡ ያድንህ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥህ ፡ ወዴት ፡ አለ ? ስለ፡ እነርሱም ፡— ንጉሥንና ፡ አለቆችን ፡ ስጠኝ ፡ ብለህ ፡ የተናገርኸው ፡ መሳፍንቶችህ ፡ ወዴት ፡
፲፩ አሉ ? በቍጣዬ ፡ ንጉሥን ፡ ሰጠሁህ ÷ በመዓ
፲፪ ቴም ፡ ሻርሁት ። የኤፍሬም ፡ በደል ፡ ታስሮ
፲፫ አል ÷ ኃጢአቱም ፡ ተከማችቶአል ። ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ጭንቅ ፡ ይመጣበታል ፤ በሚወለድበት ፡ ጊዜ ፡ በማኅፀን ፡ አፍ ፡ ቀጥ ብሎ ፡ አይወጣምና ፡ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡
፲፬ ነው ። ከሲኦል ፡ እጅ ፡ እታደጋቸዋለሁ ÷ ከሞ ትም ፡ እቤዣቸዋለሁ ፤ ሞት ፡ ሆይ ÷ ቸነፈርህ ፡ ወዴት ፡ አለ ? ሲኦል ፡ ሆይ ÷ ማጥፋትህ ፡ ወዴት ፡ አለ ? ርኅራኄ ፡ ከዓይኔ ፡ ተሰወረች ።
፲፭ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ፍሬያማ ፡ ቢሆን ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ይመጣል ÷ የእግዚአብሔር ፡ ነፋስ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ይመጣል ፡ ምንጩንም ፡ ያደርቃል ÷ ፈሳሹንም ፡ ያጠፋል ÷ የተከበሩ ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ያሉበትን ፡ መዝገብ ፡ ይበዘብ
፲፮ ዛል ። ሰማርያ ፡ በአምላክዋ ፡ ላይ ፡ ሀያባለ ችና ፡ በደልዋን ፡ ትሸከማለች ፤ በሰይፍ ፡ ይወ ድቃሉ ÷ ሕፃኖቻቸውም ፡ ይፈጠፈጣሉ ÷ እር ጉዞቻቸውም ፡ ይቀደዳሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩ እስራኤል ፡ ሆይ ÷ በኃጢአትህ ፡ ወድቀሃ ልና ፡ ወደ ፡ አምላክህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለስ ። ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ቃልን ፡ ውሰዱ ÷ ፪ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተመልሳችሁ ፡— ኃጢ አትን ፡ ሁሉ ፡ አስወግድ ÷ በቸርነትም ፡ ተቀበ ለን ÷ በወይፈንም ፡ ፋንታ ፡ የከንፈራችንን ፡ ፍሬ ፡ እንሰጣለን ። ፫ አሦር ፡ አያድነንም ፤ በፈ ረስ ፡ ላይ ፡ እንቀመጥም ፤ ድሀ ፡ አደጉም ፡ በአ ንተ ፡ ዘንድ ፡ ምሕረትን ፡ ያገኛልና ፡ ከእንግ ዲህወዲህ ፡ ለእጆቻችን ፡ ሥራ ፡— አምላኮቻ ችን ፡ ናችሁ፡ አንላቸውም ፡ በሉት ።

፬ ቍጣዬ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶአልና ፤ ዓመፃቸውን ፡ እፈውሳለሁ ÷ በገዛ ፈቃዴ ፤ እወ ድዳቸዋለሁ ። ለእስራኤልም ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ እሆ ነዋለሁ ፤ እንደ ፡ አበባም ፡ ያብባል ÷ እንደ ፡ ሊባ ኖስም ፡ ሥሩን ፡ ይሰድዳል ። ቅርንጫፎቹም ፡ ፮ ይዘረጋሉ ÷ ውበቱም ፡ እንደ ፡ ወይራ ÷ ሽታ ውም ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ይሆናል ። ከጥላውም ፡ ፯ በታች ፡ የሚቀመጡ ፡ ይመለሳሉ ፤ ከእህሉም ፡ የተነሣ ፡ ይጠግባሉ ፤ እንደ ፡ ወይንም ፡ አረግ ፡ ያብባሉ ፡ መታሰቢያውም ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይሆናል ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ፰ ጣዖት ፡ ለኤፍሬም ፡ ምንጩን ፡ ሰም ቼዋለሁ ÷ ወደ ፡ እርሱም ፡ እመለከታለሁ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ለመለመ ፡ ዋድ ፡ ነኝ ፤ ፍሬህ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ።

፱ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚያስተውል ፡ ጠቢብ ÷ የሚ ያውቃትም ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ነው ? የእግዚ አብሔር ፡ መንገድ ፡ ቅን ፡ ነው ÷ ጻድቃንም ፡ ይሄዱበታል ፤ ተላላፊዎች ፡ ግን ፡ ይወድቁበ ታል ።

ትንቢተ ፡ አሞጽ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በቴቁሔ ፡ ከላም ፡ ጠቦቂዎች ፡ መካከል ፡ የነ በረ ፡ አሞጽ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በያዝያን ፡ ዘመን ÷ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በዮአስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ዘመን ÷ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ከሆነበቱ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ እስ ራኤል ፡ ያየው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ እንዲህም ፡ አለ ፡— እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ሆኖ ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ይጮኻል ÷ በኢ የሩሳሌምም ፡ ሆኖ ፡ ቃሉን ፡ ይሰጣል ፤ የእረኞ ችም ፡ ማሰማርያዎች ፡ ያለቅሳሉ ÷ የቀርሜሎ ስም ፡ ራስ ፡ ይደርቃል ።

፫ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ገለዓድን ፡ በብረት ፡ መንኰራኵር ፡ አሂዶአልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የደማስቆ ፡ ኃጢ አት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ። በአዛሄል ፡ ቤት ፡ እሳትን ፡ እሰድዳለሁ ÷ የወ ፬ ልደ ፡ አዴርንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ። የደ ፭ ማስቆንም ፡ መወርወሪያ ፡ እሰብራለሁ ÷ ተቀማ ጮችንም ፡ ከአቄን ፡ ሸለቆ ፡ አጠፋለሁ ÷ በትር ፡ የያዘውንም ፡ ከዔደን ፡ ቤት ፡ አጠፋለሁ ፤ የሶ ርያም ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ቂር ፡ ይማረካል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ለኤዶም ፮ ያስ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡአቸው ፡ ዘንድ ፡ ምር ከኞችን ፡ ሁሉ ፡ ማርከዋልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የጋዛ ፡ ኃጢአት ፡ መቅሠ ፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ። በጋዛ ፡ ቅጥር ፯ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰድዳለሁ ÷ አዳራሾችዋንም ፡ ትበላለች ። ተቀማጮችን ፡ ከአዛጦን ፡ አጠፋ ፰ ለሁ ÷ በትር ፡ የያዘውንም ፡ ከአስቀሎና ፡ አጠ ፋለሁ ፤ እጄንም ፡ በአቃሮን ፡ ላይ ፡ እመልሳ ለሁ ÷ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ የቀሩት ፡ ይጠ

ፋሉ ÷ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

፱ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ምርኮኞ ችን ፡ ሁሉ ፡ ለኤዶምያስ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጥተዋ ልና ÷ የወንድሞችንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አላሰቡ ምና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የጢ ሮስ ፡ ኃጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አል ፲ መለስም ። በጢሮስ ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰድዳለሁ ÷ አዳራሾችዋንም ፡ ትበላለች ።

፲፩ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ወንድ ሙን ፡ በሰይፍ ፡ አሳድዶታልና ÷ ርኅራኄንም ፡ ሁሉ ፡ ጥሎአልና ÷ ቍጣውም ፡ ሁልጊዜ ፡ ቀድ ዶአልና ÷ መዓቱንም ፡ ለዘላለም ፡ ጠብቆአልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የኤዶምያስ ፡ ኃጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለ ፲፪ ስም ። በቴማን ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰድዳለሁ ÷ የቦሶራንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

፲፫ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ዳርቻቸ ውን ፡ ያሰፉ ፡ ዘንድ ፡ የገለዓድን ፡ እርጉዞች ፡ ቀድደዋልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የአሞን ፡ ልጆች ፡ ኃጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማ ፲፬ ድረግ ፡ አልመለስም ። በረባት ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ አነድዳለሁ ፡ በሰልፍም ፡ ቀን ፡ በፈጴ ኽት ፡ በወዑሎ ፡ ነፋስም ፡ ቀን ፡ በሡዕት ፡ አዳ ፲፭ ራሾችዋን ፡ ትበላለች ፤ ንጉሣቸውም ፡ ከአለ ቆቹ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ይማረካል ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የኤዶም ያስን ፡ ንጉሥ ፡ አጥንት ፡ አመድ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ አቃጥሎታልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራ ት ፡ የሞዓብ ፡ ኃጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ፪ ከማድረግ ፡ አልመለስም ። በሞዓብ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰድዳለሁ ÷ የቂርዮትንም ፡ አዳራ ሾች ፡ ትበላለች ፤ ሞዓብም ፡ በውካታና ፡ በፉጩ ፫ ኽት ፡ ዘመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ይሞታል ፤ ፈራ ጅንም ፡ ከመካከልዋ ፡ አጠፋለሁ ÷ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አለቆችዋን ፡ ሁሉ ፡ እገድላለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

፬ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የእግ ዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ጥለዋልና ÷ ትእዛዙንም ፡ አልጠበቁምና ÷ አባቶቻቸውም ፡ የተከተሉት ፡ ሐሰታቸው ፡ አስቶአቸዋልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የይሁዳ ፡ ኃጢአት ፡ መቅ ፭ ሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ። በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰድዳለሁ ÷ የኢየሩሳሌምንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

፮ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ጻድቁን ፡ ስለ ፡ ብር ÷ ችጋረኛውንም ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጥንድ ፡ ጫማ ፡ ሸጠውታልና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የእስራኤል ፡ ኃጢአት ፡ መቅ ፯ ሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ። የደሀ ችን ፡ ራስ ፡ በምድር ፡ ትቢያ ፡ ላይ ፡ ይረግጣሉ ÷ የትሑታንንም ፡ መንገድ ፡ ያጣምማሉ ፡ ቅዱሱ ንም ፡ ስሜን ፡ ያረክሱ ፡ ዘንድ ፡ አባትና ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ይገባሉ ፡ በመሠዊያ ፰ ውም ፡ ሁሉ ፡ አጠገብ ፡ ለመያዣነት ፡ በተወሰ ደው ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ ፡ በአምላካቸ ውም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በከሣ ፡ የተወሰደውን ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣሉ ። እኔ ፡ ግን ፡ ቁመቱ ፡ ፱ እንደ ፡ ዝግባ ፡ ቁመት ÷ ብርታቱም ፡ እንደ ፡ ከምበል ፡ ዛፍ ፡ የነበረውን ፡ አሞራዊውን ፡ ከፊታቸው ፡ አጠፋሁ ፡ ፍሬውንም ፡ ከላዩ ÷ ሥሩንም ፡ ከታቹ ፡ አጠፋሁ ። የአሞራዊውንም ፡ ምድር ፡ ተወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣኋችሁ ÷ በምድረ ፡ በዳም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ መራኋችሁ ። ከወንድ ፡ ልጆቻችሁም ፡ ነቢያ ፲፩ ትን ÷ ከጕበዛዝቶቻችሁም ፡ ናዝራውያንን ፡ አስነሣሁ ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ÷ ይህ ፡ እንደዚህ ፡ አይደለምን ? ይላል ፡ እግዚአ ብሔር ። እናንተ ፡ ግን ፡ ናዝራውያኑን ፡ የወ ፲፪ ይን ፡ ጠጅ ፡ አጠጣችኋቸው ፡ ነቢያቱንም ፡— ትንቢት ፡ አትናገሩ ፡ ብላችሁ ፡ አዘዛችኋቸው ። እነሆ ÷ ነዶ ፡ የተሞላች ፡ ሰረገላ ፡ እንደምትደ ፲፫ ቀድቅ ፡ እንዲሁ ፡ አደቀድቃችኋለሁ ። ከርዋ ጨል ፡ ሽሽት ፡ ይጠፋል ÷ ብርቱውም ፡ በብር ታቱ ፡ አይበረታም ÷ ኃያሉም ፡ ነፍሱን ፡ አያ ድንም ፡ ቀስተኛውም ፡ አይቆምም ÷ ፈጣኑም ፡ ፲፬ አይድንም ÷ ፈረሰኛውም ፡ ነፍሱን ፡ አያድንም ፤ በኃያላኑም ፡ መካከል ፡ ልበ ፡ ሙሉው ፡ በዚያ ፲፭ ቀን ፡ ዕራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ ይሸሻል ÷ ይላል ፡ እግዚ አብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ÷ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጣሁት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ እንዲሀም ፡ ብሎአል ፡— እኔ ፡ ከምድር ፡ ወገን ፡ ፪ ሁሉ ፡ እናንተን ፡ ብቻችሁን ፡ አውቀአችኋለሁ ፡ ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ ሁሉ ፡ እበቀላች ኋለሁ ። በውኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሳይስማሙ ፡ ፫ በእንድነት ፡ ይሄዳሉን ? ወይስ ፡ አንበሳ ፡ የሚ ፬ ነጥቀው ፡ ነገር ፡ ሳያገኝ ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ያገ ሣልን ? ወይስ ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ አንዳች ፡ ሳይዝ ፡ በመደቡ ፡ ሆኖ ፡ ይጮኻልን ? ወይስ ፡ ፭ ወፍ ፡ አጥሣኝ ፡ ከሌለው ÷ በምድር ፡ ላይ ፡ በወ ጥመድ ፡ ይያዝልን ? ወይስ ፡ ወስፈንጠር ፡ አን ዳች ፡ ሳይዝ ፡ ከምድር ፡ ይፈንጠራልን ? ወይስ ፮ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ መለከት ፡ ሲነፋ ፡ ሕዝቡ ፡ አይፈራምን ? ወይስ ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ በከተማ ፡ ላይ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያደረገው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አይደለምን ? በእውነት ፡ ጌታ ፡ እግዚ ፯ አብሔር ፡ ምሥጢሩን ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ለነቢያት ፡ ከልነገረ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አያደርግም ። እንበ ፰ ሳው ፡ አንሣ ፡ የማይፈራ ፡ ማን ፡ ነው ? ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረ ፡ ትንቢት ፡ የማይናገር ፡ ማን ፡ ነው ?

በአዛጦን ፡ አዳራሾችና ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ፱

አዳራሾች ፥ አውሩና ፦— በሰማርያ ፥ ተራሮች ፥ ላይ ፥ ተሰብሰቡ ÷ በውስጥዋም ፥ የሆነውን ፥ ታላቁን ፥ ውካታ ÷ በመካከልዋም ፥ ያለውን ፥
፲ ግፍ ፥ ተመልከቱ ፤ በሉ ። ግፍንና ፥ ቅሚያን ፥ በአዳራሾቻቸው ፥ የሚያከማቹት ፥ ቅን ፥ ነገርን ፥ ያደርጉ ፥ ዘንድ ፥ አያውቁም ÷ ይላል ፥ እግዚአ
፲፩ ብሔር ። ስለዚህ ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ እን ዲህ ፥ ይላል ፦— በምድሪቱ ፥ ዙሪያ ፥ ጠላት ፥ ይመጣል ፥ ብርታትሽንም ፥ ከእንቺ ፥ ያወርዳል ÷
፲፪ አዳራሾችሽም ፥ ይበዘበዛሉ ። እግዚአብሔር ፥ እንዲህ ፥ ይላል ፦— እረኛ ፥ ከእንበሳ ፥ አፍ ፥ ሁለት ፥ እግርን ፥ ወይም ፥ የጆሮን ፥ ጫፍ ፥ እን ደሚያድን ÷ እንዲሁ ፥ በሰማርያ ፥ በአልጋ ፥ ማዕዘን ÷ በደማስቆም ፥ በምንጣፍ ፥ ላይ ፥ የተ
፲፫ ቀመጡት ፥ የእስራኤል ፥ ልጆች ፥ ይድናሉ ።
፲፬ ስሙ ÷ በያዕቆብም ፥ ቤት ፥ ላይ ፥ መስክሩ ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ አምላክ ፥ ጌታ ፥ እግዚአብ
፲፭ ሔር ። እስራኤልን ፥ ስለ ፥ ኃጢአቱ ፥ በምበቀ ልበት ፥ ቀን ፥ የቤቴልን ፥ መሠዊያዎች ፥ ደግሞ ፥ እበቀላለሁ ፥ የመሠዊያው ፥ ቀንዶች ፥ ይሰበ
፲፮ ራሉ ÷ ወደ ፥ ምድርም ፥ ይወድቃሉ ። የክረ ምቱንና ፥ የበጋውን ፥ ቤት ፥ እመታለሁ ፥ በገዘ ንም ፥ ጥርስ ፥ የተለበጡት ፥ ቤቶች ፥ ይጠፋሉ ÷ ታላላቆችም ፥ ቤቶች ፥ ይፈርሳሉ ÷ ይላል ፥ እግ ዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፥ ፬ ።

፩ በሰማርያ ፥ ተራራ ፥ የምትኖሩ ÷ ድሆችንም ፥ የምትበድሉ ÷ ችገረኞችንም ፥ የምታስጨ ንቁ ÷ ጌቶቻቸውንም ፦— አምጡ ፥ እንጠጣ ፥ የምትሉ ፥ እናንተ ፥ የባሳን ፥ላሞች ፥ ሆይ ÷
፪ ይህን ፥ ቃል ፥ ስሙ ። ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፦— እናንተን ፥ በሰልፍ ፥ ዕቃ ÷ ቅሬታችሁንም ፥ በመቃጥን ፥ የሚወስዱበት ፥ ቀን ÷ እነሆ ÷ በላ ያችሁ ፥ይመጣል ፥ብሎ ፥ በቅዱስነቱ ፥ምሎአል ።
፫ እያንዳንዳችሁ ፥በየፊታችሁ ፥ በተነደለ ፥ስፍራ ፥ ትወጣላችሁ ፥ በረማንም ፥ትጣላላችሁ ÷ይላል ፥ እግዚአብሔር ።
፬ የእስራኤል ፥ልጆች ፥ ሆይ ÷ ይህን ፥ ወድዳ ችኋልና ፥ወደ ፥ቤቴል ፥ኑና ፥ኃጢአትን ፥ሥሩ ፥ ወደ ፥ጌልገላ ፥ኑና ፥ኃጢአትን ፥አብዙ ፥ በየማ ለዳውም ፥ መሥዋዕታችሁን ÷በየሦስተኛውም ፥
፭ ቀን ፥አሥራታችሁን ፥አቅርቡ ፥ እርሾ ፥ ከለበ ትም ፥ የምስጋናውን ፥ መሥዋዕት ፥ አቅርቡ ÷ በፈቃዳችሁም ፥ የምታቀርቡትን ፥ አውጁና ፥ አውሩ ÷ ይላል ፥ጌታ ፥ እግዚአብሔር ።
፮ በከተማችሁ ፥ሁሉ ፥ጥርስን ፥ማጥራት ÷ በስ ፍራችሁም ፥ሁሉ ፥እንጀራን ፥ ማጣት ፥ ሰጠኋ ችሁ ፥ እናንተ ፥ግን ፥ወደ ፥ እኔ ፥ አልተመለሳ ችሁም ÷ ይላል ፥ እግዚአብሔር ። መከር ፥ሳይ ደርስ ፥ገና ፥ከሦስት ፥ወር ፥በፊት ፥ዝናብ ፥ከለ ከልኋችሁ ፥በአንድም ፥ከተማ ፥ላይ ፥አዘነብሁ ÷ በሌላውም ፥ከተማ ፥ላይ ፥ እንዳይዘንብ ፥አደረ ግሁ ፤ በአንድ ፥ወገን ፥ዘነበ ÷ ያልዘነበበትም ፥ ወገን ፥ደረቀ ። የሁለት ፥ወይም ፥የሦስት ፥ከተ ሞች ፥ሰዎች ፥ወደ ፥ አንዲት ፥ከተማ ፥ውኃ ፥ ይጠጡ ፥ዘንድ ፥ሄዱ ÷ነገር ፥ግን ፥አልረኩም ፤ እናንተ ፥ ግን ፥ወደ ፥እኔ ፥ አልተመለሳችሁም ÷ ይላል ፥እግዚአብሔር ። በዋግና ፥በአረማሞ ፥ መታኋችሁ ፥የአታክልቶቻችሁንም ፥ብዛት ፥ ወይኖቻችሁንም ፥ በለሰቻችሁንም ፥ወይራዎ ቻችሁንም ፥ተምች ፥በልቶአል ፥እናንተ ፥ግን ፥ ወደ ፥እኔ ፥ አልተመለሳችሁም ÷ ይላል ፥እግዚ አብሔር ። በግብጽ ፥እንደ ፥ነበረው ፥ቸነፈርን ፥ ሰደድኩባችሁ ፥ጕበዛዝቶቻችሁን ፥ በሰይፍ ፥ ገደልሁ ÷ ፈረሶቻችሁንም ፥ አስማረክሁ ፥ የሰ ፈራችሁንም ፥ግማት ፥ወደ ፥አፍንጫችሁ ፥አወ ጣሁ ፥እናንተ ፥ግን ፥ወደ ፥ እኔ ፥ አልተመለሳ ችሁም ÷ ይላል ፥ እግዚአብሔር ። ሰዶምንና ፥ ገሞራን ፥እግዚአብሔር ፥እንደ ፥ገለበጣቸው ÷ እንዲሁ ፥ገለበጥኋችሁ ÷ እናንተም ፥ ከእሳት ፥ ውስጥ ፥እንደ ፥ተነጠቀ ፥ትንታግ ፥ሆናችሁ ፤ ነገር ፥ግን ፥ወደ ፥እኔ ፥አልተመለሳችሁም ÷ ይላል ፥እግዚአብሔር ።

ስለዚህ ÷እስራኤል ፥ሆይ ÷እንደዚህ ፥አደር ግብሃለሁ ፤እስራኤልም ፥ሆይ ÷እንደዚህ ፥ስለ ማደርግብህ ፥ አምላክህን ፥ ለመገናኘት ፥ተዘ ጋጅ ። እነሆ ÷ ተራሮችን ፥የሠራ ÷ነፋስንም ፥ የፈጠረ ÷ የልቡንም ፥ አሳብ ፥ ለሰው ፥ የሚነ ግር ÷ ንጋትን ፥ጨለማ ፥የሚያደርግ ÷ በምድ ርም ፥ ከፍታዎች ፥ ላይ ፥ የሚረግጥ ÷ ስሙ ፥ የሠራዊት ፥ አምላክ ፥ እግዚአብሔር ፥ነው ።

ምዕራፍ ፥ ፭ ።

፩ የእስራኤል ፥ቤት ፥ ሆይ ÷ በእናንተ ፥ላይ ፥ ለሙሾ ፥የማነሣውን ፥ይህን ፥ ቃል ፥ስሙ ።
፪ የእስራኤል ፥ ድንግል ፥ ወደቀች ÷ ከእንግዲ ህም ፥ ወዲህ ፥ አትነሣም ፤ በምድርዋ ፥ላይ ፥ ተጣለች ÷ የሚያስነሣትም ፥የለም ። ጌታ ፥እግ
፫ ዚአብሔርም ፥እንዲህ ፥ይላልና ፦— ሺህ ፥ከሚ ወጣባት ፥ከተማ ፥መቶ ፥ይቀርላታል ÷ መቶም ፥ ከሚወጣባት ፥ከተማ ፥ለእስራኤል ፥ ቤት ፥ አሥር ፥ይቀርላታል ።
፬ እግዚአብሔርም ፥ለእስራኤል ፥ ቤት ፥እን ዲህ ፥ይላልና ፦— እኔን ፥ፈልጉ ÷ በሕይወትም ፥ትኖራላችሁ ፥ነገር ፥ግን ፥ ጌልገላ ፥ ፈጽሞ ፥ ትማረካለችና ÷ ቤቴልም ፥ከንቱ ፥ትሆናለችና ፥ ቤቴልን ፥አትፈልጉ ÷ ወደ ፥ ጌልገላም ፥ አት ግቡ ÷ ወደ ፥ ቤርሳቤህም ፥ አትለፉ ። በዮሴፍ ፥ ቤት ፥አሳት ፥ እንዳትቃጠል ÷ በቤቴል ፥ የሚ ያጠፋትም ፥ ሳይኖር ፥ እንዳትበላ ÷ እግዚአብ ሔርን ፥ፈልጉ ÷ በሕይወትም ፥ ትኖራላችሁ ። ሰጠኋ ፍርድን ፥ወደ ፥እሬት ፥የምትለውጡ ÷ጽድቅ ንም ፥ በምድር ፥ላይ ፥የምትጥሉ ፥እናንተ ፥ ሆይ ÷ ሰባቱን ፥ከዋክብትና ፥ አሬዮን ፥የተ ባለውን ፥ ከክብ ፥የፈጠረውን ÷ የሞትን ፥ ጥላ ፥ወደ ፥ንጋት ፥የሚለውጠውን ÷ ቀኑንም ፥ በሌሊት ፥ የሚያጨልመውን ÷ የባሕሩንም ፥ ውኖች ፥ጠርቶ ፥በምድር ፥ፊት ፥ላይ ፥ የሚያ ፈስሳቸውን ÷ አምባውም ፥እንዲፈርስ ፥ በብ ርቱ ፥ላይ ፥ የድንገት ፥ጥፋት ፥የሚያመጣውን ፥ ፈልጉ ፥ስሙ ፥እግዚአብሔር ፥ነው ።
፯ በበሩ ፥አደባባይ ፥ የሚገሥጸውን ፥ጠሉ ÷
፲፩ እውነትም ፥ የሚናገረውን ፥ተጸየፉ ። ድሀው ንም ፥ደብድባችኋልና ÷ የስንዴውንም ፥ቀረጥ ፥ ከእርሱ ፥ወስዳችኋልና ፥ከተጠረበ ፥ድንጋይ ፥ ቤቶችን ፥ሠርታችኋል ÷ ነገር ፥ግን ፥አትቀመ ጡባቸውም ፥ያማሩ ፥የወይን ፥ጠጆች ፥ተክ ላችኋል ÷ ነገር ፥ግን ፥ ከወይን ፥ጠጃቸው ፥
፲፪ አትጠጡም ። ጻድቁን ፥ የምታስጨንቁ ÷ጉቦ ንም ፥ የምትቀበሉ ÷ በበሩም ፥ አደባባይ ፥ የች ጋረኛውን ፥ ፍርድ ፥ የምታጣምሙ ፥እናንተ ፥ ሆይ ÷ በደላችሁ ፥እንዴት ፥እንደ ፥በዛ ÷ኃጢ አታችሁም ፥እንዴት ፥እንደ ፥ጸና ፥እኔ ፥አው ቃለሁና ። ስለዚህ ፥ክፉ ፥ዘመን ፥ነውና ፥በዚያ ፥ ዘመን ፥አስተዋይ ፥ የሚሆን ፥ዝም ፥ይላል ።
፲፫ በሕይወት ፥ትኖሩ ፥ዘንድ ፥መልካሙን ፥እንጂ ፥ ክፉውን ፥ አትፈልጉ ፤ እንዲሁም ፥እናንተ ፥ እንደ ፥ተናገራችሁ ፥የሠራዊት ፥አምላክ ፥እግዚ
፲፬ አብሔር ፥ከእናንተ ፥ጋር ፥ይሆናል ። ክፋውን ፥ ጥሉ ÷ መልካሙንም ፥ውደዱ ÷ በበሩም ፥ አደ ባባይ ፥ ፍርድን ፥ አጽኑ ፥ ምናልባት ፥ የሠራ ዊት ፥ አምላክ ፥ እግዚአብሔር ፥ ለዮሴፍ ፥ ቅሬታ ፥ይራራ ፥ይሆናል ።
፲፭ ስለዚህ ፥ጌታ ፥የሠራዊት ፥አምላክ ፥እግዚ አብሔር ፥ እንዲህ ፥ይላል ፦— በየአደባባዩ ፥ ሁሉ ፥ላይ ፥ዋይታ ፥ይሆናል ፥በየመንገዱም ፥ ሁሉ ፥ላይ ፥ወዮ ፥ወዮ ፥ይባላል ፥ገበሬዎቹም ፥ ወደ ፥ ልቅሶ ÷ አልቃሾቹም ፥ ወደ ፥ዋይታ ፥ ይጠራሉ ። በመካከልህ ፥ አልፋለሁና ፥ በወ ይኑ ፥በታ ፥ሁሉ ፥ልቅሶ ፥ይሆናል ÷ይላል ፥ እግዚአብሔር ።
፲፯ የእግዚአብሔርን ፥ቀን ፥ለምትፈልጉ ፥ወዮ ላችሁ ! የእግዚአብሔርን ፥ቀን ፥ለምን ፥ትፈ ልጋላችሁ ? ጨለማ ፥ነው ፥እንጂ ፥ ብርሃን ፥ አይደለም ። ከአንበሳ ፥ፊት ፥እንደ ፥ሸሸ ፥ ድብም ፥እንዳገኘው ፥ሰው ÷ ወይም ፥ወደ ፥ ቤት ፥ገብቶ ፥እጁን ፥በግድግዳ ፥ላይ ፥እንዳስ ደገፈና ፥እባብ ፥እንደ ፥ነደፈው ፥ሰው ፥ነው ።
፲፰ የእግዚአብሔር ፥ቀን ፥ብርሃን ፥ሳይሆን ፥ጨለማ ፥ አይደለምን ? ፀዳል ፥የሌለውም ፥ድቅድቅ ፥ ጨለማ ፥አይደለምን ?
፲፱ ዓመት ፥በዓላችሁን ፥ጠልቼዋለሁ ፥ተጸየፌ ውማለሁ ፥የተቀደሰውም ፥ጉባኤአችሁ ፥ደስ ፥ አያሰኘኝም ። የሚቃጠለውን ፥መሥዋዕታች ሁና ፥የእህሉን ፥ቍርባናችሁን ፥ብታቀርቡል ኝም ፥እንኳ ፥አልቀበለውም ፥ለምስጋና ፥መሥ ዋዕት ፥የምታቀርቡልኝን ፥የሰቡትን ፥እንስ ሶች ፥አልመለከትም ። የዝማሬህንም ፥ጩኸት ፥ ከእኔ ፥ዘንድ ፥አርቅ ፤ የመሰንቆህንም ፥ዜማ ፥ አላደምጥም ። ነገር ፥ግን ፥ፍርድ ፥እንደ ፥ውኃ ÷ ጽድቅም ፥እንደማይደርቅ ፥ፈሳሽ ፥ይፍሰስ ።

፳ የእስራኤል ፥ቤት ፥ሆይ ÷ በውኑ ፥በምድረ በዳ ፥አርባ ፥ዓመት ፥ ሙሉ ፥ መሥዋዕትንና ፥ ቍርባንን ፥አቅርባችሁልኛልን ? ለራሳችሁም ፥ የሠራችኋቸውን ፥ምስሎች ÷ የሞሎክን ፥ድን ኳንና ፥የአምላካችሁን ፥የሬፋን ፥ከዋክብ ፥አነሣ ችሁ ። ስለዚህ ፥ከደማስቆ ፥ወደዚያ ፥አስማርካ ችኋለሁ ÷ ይላል ፥ስሙ ፥የሠራዊት ፥አምላክ ፥ የተባለ ፥እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፥ ፮ ።

፩ በጽዮን ፥ላሉ ፥ዓለመኞች ÷ በሰማርያም ፥ ተራራ ፥ላይ ፥ ተዘልለው ፥ለተቀመጡ ÷ የእስ ራኤልም ፥ቤት ፥ወደ ፥እነርሱ ፥ለመጡባቸው ፥ ለአሕዛብ ፥አለቆች ፥ወሮላቸው ! ወደ ፥ካልኔ ፪ አልፋችሁ ፥ተመልከቱ ፥ከዚያም ፥ወደ ፥ታላ ቂቱ ፥ሐማት ፥ሂዱ ፥ከዚያም ፥ወደ ፥ፍልስጥ ኤም ፥ጌት ፥ውረዱ ፥እነርሱ ፥ከእነዚህ ፥መን ግሥታት ፥ይሻላሉን ? ወይስ ፥ድንበራቸው ፥ ከድንበራችሁ ፥ይሰፋልን ? ክፉውን ፥ቀን ፫ ፥ከእናንተ ፥ለምታርቁ ÷ የግፍንም ፥ወንበር ፥ ለምታቀርቡ ÷ ከገዘቦን ፥ጥርስ ፥በተሠራ ፬ አልጋ ፥ላይ ፥ለምትተኙ ÷ በምንጣፋችሁም ፥ ላይ ፥ተደላደላችሁ ፥ለምትቀመጡ ÷ከበጎችም ፥ መንጋ ፥ጠቦትን ፥ዝንጉርም ፥ውስጥ ፥ጥጃን ፥ ለምትበሉ ÷ በመሰንቆም ፥ድምፅ ፥ለምትን ፭ ጫጩ ÷እንደ ፥ ዳዊትም ፥ የዜማን ፥ ዕቃ ፥ ለምታዘጋጁ ÷ በፋጋ ፥የወይን ፥ጠጅ ፥ለምት ፮ ጠጡ ÷ እጅግ ፥ባማረ ፥ ሽቱም ፥ለምትቀቡ ÷ ስለ ፥ዮሴፍ ፥መከራ ፥ግን ፥ለማታዝኑ ፥ለእና ንተ ፥ወዮላችሁ !
፯ ስለዚህ ፥በምርኮ ፥መጀመሪያ ፥ይማረካሉ ÷ ተደላደልው ፥ከተቀመጡትም ፥ዘንድ ፥ዘፈን ፥ ይርቃል ። ጌታ ፥እግዚአብሔር ፦— የያዕቆብን ፰ ትዕቢት ፥ተጸየፈአለሁ ÷ አዳራሾቹንም ፥ጠል ቻለሁ ፥ ስለዚህ ፥ከተማይቱንና ፥ የሚኖሩባ ትን ፥ሁሉ ፥አሳልፌ ፥እሰጣለሁ ፥ብሎ ፥በራሱ ፥ምሎአል ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥አምላክ ፥እግ ዚአብሔር ። እንዲህም ፥ይሆናል ፥አሥር ፱ ሰዎች ፥በአንድ ፥ቤት ፥ውስጥ ፥ቢቀሩ ፥እን ርሱ ፥ይሞታሉ ። አጥንቱንም ፥ከቤቱ ፥ያወጡ ፲ ዘንድ ፥ የሰው ፥ዘመድና ፥አቃጣዩ ፥ባኑሩ ፥ ጊዜ ÷ በቤቱም ፥ውስጥ ፥ያለውን ፦— እስከ ፥አሁን ፥ድረስ ፥ገና ፥ሰው ፥በእንተ ፥ዘንድ ፥ አለን ? ባለው ፥ጊዜ ÷ እርሱም ፦— ማንም ፥የለም ፥ባለ ፥ጊዜ ፥ያን ፥ጊዜ ፦— የእግዚአብ ሔርን ፥ስም ፥እንጠራ ፥ዘንድ ፥አይገበንምና ፥ ዝም ፥በል ፥ይለዋል ። እነሆም ÷ እግዚአብ ሔር ፲፩ ፥ያዝዛል ፥ ታላቁንም ፥ቤት ፥በማፍረስ ÷ ታናሹንም ፥ቤት ፥በመሰባበር ፥ይመታል ። ፲፪ ፲፫ ፍርድን ፥ወደ ፥ሐሞት ÷ የጽድቅንም ፥ፍሬ ፥ወደ ፥እሬት ፥የለወጣችሁ ÷ በከንቱም ፥ነገር ፥ ደስ ፥የሚላችሁ ፦— በኃይላችን ፥ቀንድ ፥የወ ሰድን ፥አይደለምን?የምትሉ ÷እናንተ ፥ሆይ ÷ በውኑ ፥ፈረሶች ፥በጭንጫ ፥ላይ ፥ይጋልቡትን ?

ወይስ ፣ በፈዖች ፣ በዚያ ፣ ላይ ፣ ያርሳሉን ?
፲፬ የእስራኤል ፣ ቤት ፣ ሆይ ÷ እነሆ ÷ እኔ ፣ ሕዝብን ፣ አስነሣበችኋለሁ ÷ ይላል ፣ የሠራዊት ፣ አምላክ ፣ እግዚአብሔር ፣ እነርሱም ፣ ከሐማት ፣ መግቢያ ፣ ጀምረው ፣ እስከ ፣ ዓረባ ፣ ወንዝ ፣ ድረስ ፣ ያስጨንቋችኋል ።

ምዕራፍ ፣ ፯ ።

፩ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ አሳየኝ ፣ እነሆም ÷ የኋለኛው ፣ ጣር ፣ በሚበቅልበት ፣ መጀመሪያ ፣ ላይ ፣ እንበጣን ፣ ፈጠረ ፣ እነሆም ÷ ከንጉሡ ፣ እጨዳ ፣ በኋላ ፣ የበቀለ ፣ የገበ ፣ ነበረ ።
፪ የምድሩንም ፣ ጣር ፣ በልተው ፣ ከጨረሱ ፣ በኋላ ÷ እኔ ፦ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ ሆይ ÷ ይቅር ፣ እንድትል ፣ እለምንሃለሁ ፣ ያዕቆብ ፣ ታናሽ ፣
፫ ነውና ፣ እንዴት ፣ ይቆማል ? አልሁ ። እግዚአብሔርም ፣ ስለዚህ ፣ ነገር ፣ ተጸጸተ ፣ ይህ ፣ ደግሞ ፣ አይሆንም ÷ ይላል ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ።

፬ እንዲህም ፣ አሳየኝ ፣ እነሆም ÷ ጌታ ፣ ቱንቢውን ፣ ይዞ ፣ በቱንቢ ፣ በተሠራ ፣ ቅጥር ፣ ላይ ፣
፭ ቆሞ ፣ ነበር ። እግዚአብሔርም ፦ አሞጽ ፣ ሆይ ÷ የምታየው ፣ ምንድር ፣ ነው ? አለኝ ። እኔም ፦ ቱንቢ ፣ ነው ፣ አልሁ ። ጌታም ፦ እነሆ ÷ በሕዝቤ ፣ በእስራኤል ፣ መካከል ፣ ቱንቢ ፣ አደርጋለሁ ፣ ከእንግዲህም ፣ ወዲህ ፣ ደግሞ ፣ አላ
፰ ልፋቸውም ፣ የይሁሐቅም ፣ የከረብታው ፣ መስገጃዎች ፣ ያፈርሳሉ ÷ የእስራኤልም ፣ መቅደሶች ፣ በድማ ፣ ይሆናሉ ፣ በኢዮርብዓምም ፣ ቤት ፣ ላይ ፣ በሰይፍ ፣ እነሣለሁ ፣ አለ ።

፱ ፣ ፲፩ የቤቴልም ፣ ካህን ፣ አሜስያስ ፣ ወደ ፣ እስራኤል ፣ ንጉሥ ፣ ወደ ፣ ኢዮርብዓም ፣ ልከ ፦ አሞጽ ፣ ኢዮርብዓም ፣ በሰይፍ ፣ ይሞታል ÷ እስራኤልም ፣ ከአገሩ ፣ ተማርከ ፣ ይሄዳል ፣ ብሎ ፣ አልኖ ፣ አሞጽ ፣ በእስራኤል ፣ ቤት ፣ መካከል ፣ ሀምያብሃል ፣ ምድሪቱም ፣ ቃሉን ፣ ሁሉ ፣ ልት
፲፪ ሸከም ፣ ኣትችልም ፣ አለ ። አሜስያስም ፣ አሞጽን ፦ ባለ ፣ ራእዩ ፣ ሆይ ÷ ሂድ ፣ ወደ ፣ ይሁዳም ፣ ምድር ፣ ሽሽ ÷ በዚያም ፣ እንጀራን ፣ ብላ ÷
፲፫ በዚያም ፣ ትንቢትን ፣ ተናገር ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ቤቴል ፣ የንጉሥ ፣ መቅደስና ፣ የመንግሥት ፣ ቤት ፣ ናትና ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ በዚህ ፣ ደግሞ ፣ ትንቢት ፣ አትናገር ፣ አለው ።

፲፬ አሞጽም ፣ መልሶ ፣ አሜስያስን ፣ አለው ፦ — እኔ ፣ ላም ፣ ጠበቂና ፣ ወርክ ፣ ለቃሚ ፣ ነኝ ፣ እንጂ ፣ ነቢይ ፣ ወይም ፣ የነቢይ ፣ ልጅ ፣ አይደለሁም ፤ እግዚአብሔርም ፣ በጎቼን ፣ ከመከተል ፣ ወሰ
፲፭ ደኝ ÷ እግዚአብሔርም ፦ — ሂድ ÷ ለሕዝቤም ፣ ለእስራኤል ፣ ትንቢት ፣ ተናገር ፣ አለኝ ። አሁንም ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ቃል ፣ ስማ ፣ አንተ ፦ — በእስራኤል ፣ ላይ ፣ ትንቢት ፣ አትናገር ÷ በይስሐቅም ፣ ቤት ፣ ላይ ፣ አትስበክ ፣ ብለሃል ፣ ስለ
፲፮ ዚህ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ ይላል ፦ — ሚስትህ ፣ በከተማይቱ ፣ ውስጥ ፣ ጋለሞታ ፣ ትሆናለች ÷ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ልጆችህም ፣ በሰይፍ ፣ ይወድቃሉ ÷ ምድርህም ፣ በገመድ ፣ ትከፈላለች ፣ አንተም ፣ በረከሰች ፣ ምድር ፣ ትሞታለህ ፤ እስራኤልም ፣ ከምድሩ ፣ ተማርኮ ፣ ይሄዳል ።

ምዕራፍ ፣ ፰ ።

፩ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እንዲህ ፣ አሳየኝ ፣ እነሆም ÷ የቃርሚያ ፣ ሩሬ ፣ የሞላበት ፣ ዕንቅብ ፣
፪ ነበረ ። እርሱም ፦ — አሞጽ ፣ ሆይ ÷ የምታየው ፣ ምንድር ፣ ነው ? አለኝ ። እኔም ፦ — የቃርሚያ ፣ ሩሬ ፣ የሞላበት ፣ ዕንቅብ ፣ ነው ፣ አልሁት ። እግዚአብሔርም ፣ አለኝ ፦ — ፍጻሜ ፣ ቤሕዝቤ ፣ በእስራኤል ፣ ላይ ፣ መጥቶአል ፤ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ይግሞ ፣ አላልፋቸውም ። የመቅደሱ ፣
፫ ዝማሬ ፣ በዚያ ፣ ቀን ፣ ዋይታ ፣ ይሆናል ÷ ይላል ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ የሰምቾም ፣ ሬሳ ፣ ይበዛል ÷ በስፍራውም ፣ ሁሉ ፣ በዝምታ ፣ ይጣላል ።

፬ ችጋረኛውን ፣ የምትውጡ ÷ የአገሩንም ፣
፭ ድሀ ፣ የምታጠፉ ፣ እናንተ ፣ ሆይ ፦ እህልን ፣ እንሸጥ ፣ ዘንድ ፣ መባቻው ፣ መቼ ፣ ያልፋል ? የሉና ፣ መስፈሪያውንም ፣ እያሳነስን ÷ ሰቅሉንም ፣ እያጸበን ÷ በሐሰተኛም ፣ ሚዛን ፣ እያታለልን ÷ ድሀውን ፣ በብር ፣ ችጋረኛውንም ፣ በአንድ ፣ ጥንድ ፣ ጫማ ፣ እንገዛ ፣ ዘንድ ÷ የስንዴውንም ፣ ግርድ ፣ እንሸጥ ፣ ዘንድ ፣ ስንዴውን ፣
፮ እንድንሸምት ፣ ሰንበት ፣ መቼ ፣ ያልፋል ? የምትሉ ፣ እናንተ ፣ ሆይ ÷ ይህን ፣ ስሙ ። እግዚአብሔር ፣ በያዕቆብ ፣ ክብር ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ ምሎአል ፦ — ሥራቸውን ፣ ሁሉ ፣ ለዘላለም ፣ ምንም ፣ አልረሳም ። በውኑ ፣ ምድሪቱ ፣ ስለዚህ ፣ ነገር ፣
፰ አትናወጥምን ? በእርስዋም ፣ የሚኖር ፣ ሁሉ ፣ አያለቅስምን ? ሙላዋም ፣ እንደ ፣ ወንዙ ፣ ትነሣለች ፣ እንደ ፣ ግብጽ ፣ ወንዝ ፣ ትነሣለች ፣ ደግሞም ፣ ትወርዳለች ። በዚያም ፣ ቀን ፣ ፀሐይ ፣
፱ በቀትር ፣ እንድትገባ ፣ አደርጋለሁ ÷ ይላል ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ በብርሃንም ፣ ቀን ፣ ምድሩን ፣ አጨልማለሁ ። ዓመት ፣ በዓላችሁንም ፣
፲ ወደ ፣ ልቅሶ ÷ ዝማሬአችሁንም ፣ ወደ ፣ ዋይታ ፣ አለውጣለሁ ፣ ማቅንም ፣ በወገብ ፣ ሁሉ ÷ ራስ ፣ መንጨትንም ፣ በሁሉ ፣ ላይ ፣ አመጣለሁ ፣ እንደ ፣ አንድያ ፣ ልጅም ፣ ልቅሶ ÷ ፍጻሜውንም ፣ እንደ ፣ መራራ ፣ ቀን ፣ አደርገዋለሁ ።

፲፩ እነሆ ÷ በምድር ፣ ላይ ፣ ራብን ፣ የምሰድድ ፣ በት ፣ ዘመን ፣ ይመጣል ÷ ይላል ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ እርሱም ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ቃል ፣ ከመ
፲፪ ስማት ፣ እንጂ ፣ እንጀራን ፣ ከመራብና ፣ ውኃን ፣ ከመጠማት ፣ አይደለም ። ከባሕርም ፣ እስከ ፣ ባሕር ፣ ድረስ ÷ ከሰሜንም ፣ እስከ ፣ ምሥራቅ ፣ ድረስ ፣ ይቅበዘበዛሉ ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ቃል ፣
፲፫ ለመሻት ፣ ይርመሰመሳሉ ÷ አያገኙትምም ። በዚያ ፣ ቀን ፣ መልከከሚቾች ፣ ደናግል ፣ ጕበዛዝትም ፣ በጥም ፣ ይዝላሉ ። በሰማርያ ፣ ኃጢአት ፣ የሚምሉና ፦ — ዳን ፣ ሆይ ÷ ሕያው ፣ አምላክህ ፣ ነው ! ደግሞ ፦ — ሕያው ፣ የቤርሳቤህን ፣ መንገድ ! ብለው ፣ የሚሉ ÷ እነርሱ ፣ ይወድቃሉ ÷ ደግሞም ፣ አይነሡም ።

ምዕራፍ ፣ ፱ ።

፩ ጌታን ፣ በመሠዊያው ፣ አጠገብ ፣ ቆሞ ፣ አየሁት ፣ እርሱም ፣ እንዲህ ፣ አለ ፦ — መድረክቹ ፣ ይናወጡ ፣ ዘንድ ፣ ጕልላቶቹን ፣ ምታ ÷ በራሳቸውም ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣ ሰበብራቸው ፣ እኔም ፣ ከእነርሱ ፣ የቀሩትን ፣ በሰይፍ ፣ እገድላለሁ ፣ የሚሸሽ ፣ አያመልጥም ÷ የሚያመልጥም ፣ አይድንም ። ወደ ፣ ሲኦል ፣ ቢወርዱ ፣ እጄ ፣ ከዚያ ፣
፪ ታወጣቸዋለች ፣ ወደ ፣ ሰማይም ፣ ቢወጡ ፣ ከዚያ ፣ አወርዳቸዋለሁ ። በቀርሜሎስም ፣ ራስ ፣ ውስጥ ፣ ቢሸሸጉ ፣ ፈልጌ ፣ ከዚያ ፣ አወጣቸዋለሁ ፣ በጥልቅ ፣ በሕርም ፣ ውስጥ ፣ ከዓይኔ ፣ ቢደበቁ ፣ ከዚያ ፣ እባቡን ፣ አዝዘለሁ ÷ እርሱም ፣
፬ ይነድፋቸዋል ። በጠላቶቻቸውም ፣ ፊት ፣ ተማርከው ፣ ቢሄዱ ፣ ከዚያ ፣ ሰይፍን ፣ አዝዘለሁ ÷ እርሱም ፣ ይገድላቸዋል ፣ ዓይኔንም ፣ በእነርሱ ፣ ላይ ፣ ለክፋት ፣ እንጂ ፣ ለመልካም ፣ አላደርግም ።
፭ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔር ፣ ምድርን ፣ ይዳስሳል ፣ እርስዋም ፣ ትቀልጣለች ÷ የሚኖሩባትም ፣ ሁሉ ፣ ያለቅሳሉ ፣ ሙላዋም ፣ እንደ ፣ ግብጽ ፣ ወንዝ ፣ ትነሣለች ÷ ደግሞም ፣ እንደ ፣
፮ ግብጽ ፣ ወንዝ ፣ ትወርዳለች ። አዳራሹን ፣ በሰማይ ፣ የሠራ ÷ ጠፈሩንም ፣ በምድር ፣ ላይ ፣ የመሠረተ ÷ የባሕርንም ፣ ውኃ ፣ ጠርቶ ፣ በምድር ፣ ፊት ፣ ላይ ፣ የሚያፈስሰው ፣ እርሱ ፣ ነው ፣ ስሙም ፣ እግዚአብሔር ፣ ነው ።

የእስራኤል ፣ ልጆች ፣ ሆይ ÷ እናንተ ፣ ለእኔ ፣
፯ እንደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ልጆች ፣ አይደላችሁምን ? ይላል ፣ እግዚአብሔር ። እስራኤልን ፣ ከግብጽ ፣ ምድር ÷ ፍልስጥኤማውያንንም ፣ ከክሬቴ ÷ ሶርያውያንንም ፣ ከቂር ፣ አላወጣሁምን ? እነሆ ÷ የጌታ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ዓይኖች ፣ በኃጢአተኛ ፣ መንግሥት ፣ ላይ ፣ ናቸው ÷ ከምድርም ፣ ፊት ፣ አጠፋታለሁ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ የያዕቆብን ፣ ቤት ፣ ፈጽሜ ፣ አላጠፋም ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ።
፰ እነሆ ÷ እገዛለሁ ÷ እህልም ፣ በወንፊት ፣ እንደ ፣ ይንቀጠቀጣል ፣ ቤት ፣ በአሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ መካከል ፣ እንፋለሁ ፣ ነገር ፣ ግን ፣ እንዲት ፣ ቅንጣት ፣ በምድር ፣ ላይ ፣ አትወድቅም ። ክፉው ፣ ነገር ፣ አይደርስብንም ÷ እያለ
፱ ኘንምም ፣ የሚሉ ፣ የሕዝቤ ፣ ኃጢአተኞች ፣ ሁሉ ፣ በሰይፍ ፣ ይሞታሉ ።

በዚያ ፣ ቀን ፣ የወደቀችውን ፣ የዳዊትን ፣ ድንኳን ፣ አነሣለሁ ÷ የተናደውንም ፣ ቅጥርዋን ፣ አጠግናለሁ ፣ የፈረሰውንም ፣ አድሳለሁ ÷ እንደ ፣
፲፩ ቀደመውም ፣ ዘመን ፣ እሠራታለሁ ፣ ይኸውም ፣ የኤዶምያስን ፣ ቅሬታ ÷ ስሜም ፣ የተጠራበቸውን ፣ አሕዛብን ፣ ሁሉ ፣ ይወርሱ ፣ ዘንድ ፣ ነው ÷ ይላል ፣ ይህን ፣ የሚያደርግ ፣ እግዚአብሔር ።
፲፪ እነሆ ÷ አራሹ ፣ አጫጁን ÷ ወይን ፣ ጠማቂው ፣ ዘሪውን ፣ የሚያገኝበት ፣ ወራት ፣ ይመጣል ÷ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ ተራሮችም ፣ በተወውን ፣ የወይን ፣ ጠጅ ፣ ያንጠባጥባሉ ÷ ኮረብቶችም ፣ ሁሉ ፣ ይቀልጣሉ ። የሕዝቤን ፣
፲፬ የእስራኤልን ፣ ምርከ ፣ እመልሳለሁ ÷ የፈረሱትንም ፣ ከተሞች ፣ ሠርተው ፣ ይቀመጡባቸዋል ፣ ወይንንም ፣ ይተክላሉ ÷ የወይን ፣ ጠጁንም ፣ ይጠጣሉ ፣ አትክልትንም ፣ ያበጃሉ ÷ ፍሬውንም ፣ ይበላሉ ። በምድራቸውም ፣ አተክላቸዋለሁ ÷ ከእንግዲህም ፣ ወዲህ ፣ ከሰጠኋቸው ፣ ከምድራቸው ፣ አይነቀሉም ÷ ይላል ፣ አምላክህ ፣ እግዚአብሔር ፣ ነው ።

ትንቢተ ሚክያስ ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ።

፩ በይሁዳ ፣ ነገሥታት ፣ በአያአታምና ፣ በአካዝ ፣ በሕዝቅያስም ፣ ዘመን ፣ ወደ ፣ ሞሬታዊው ፣ ወደ ፣ ሚክያስ ፣ የመጣው ÷ ስለ ፣ ሰማርያና ፣ ስለ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ ያየው ÷ የእግዚአብሔር ፣ ቃል ፣ ይህ ፣ ነው ። እናንተ ፣ አሕዛብ ፣ ሁሉ ÷ ስሙ ፣ ምድርም ፣ ሙላዋም ፣ ታዘዙም ፣ ጌታ ፣ እግዚአብሔርም ÷ እርሱም ፣ በቅዱስ ፣ መቅደሱ ፣ የሆነ ፣ ጌታ ፣ ይመስክርባችሁ ።
፫ እነሆ ÷ እግዚአብሔር ፣ ከስፍራው ፣ ይወጣል ÷ ወርዶም ፣ በምድር ፣ ከፍታዎች ፣ ላይ ፣ ይረግ
፬ ጣል ። ተራሮችም ፣ በእሳት ፣ ፊት ፣ እንዳለ ፣ ሰም ÷ በገደልም ፣ ውርዶ ፣ እንደሚፈስስ ፣ ውኃ ÷ በበታቹ ፣ ይቀልጣሉ ÷ ሸለቆችም ፣ ይሰነጠቃሉ ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ ስለ ፣ ያዕቆብ ፣ በደልና ፣ ስለ ፣ እስራኤል ፣ ቤት ፣ ኃጢአት ፣ ነው ።
፭ የያዕቆብም ፣ በደል ፣ ምንድር ፣ ነው ? ሰማርያ ፣ አይደለችምን ? የይሁዳስ ፣ የከረብታው ፣ መስገጃ ፣ ምንድር ፣ ነው ? ኢየሩሳሌም ፣ አይደለች ምን ? ስለዚህ ፣ ሰማርያን ፣ በሜዳ ፣ እንደሚገኝ ፣ የድንጋይ ፣ ክምር ÷ ወይን ፣ እንደሚተከልበትም ፣ ስፍራ ፣ አደርጋታለሁ ፣ ድንጋጮችዋንም ፣ ወደ ፣ ሸለቆ ፣ እወረውራለሁ ÷ መሠረቶ

፮ ችዋንም፡እገልጣለሁ ። የተቀረጹትም ፡ምስሎ
ችዋ፡ይደቅቃሉ ÷ በግልሙትና ፡ያገኘችው ፡
ዋጋ ፡ሁሉ ፡በእሳት ፡ይቃጠላል ÷ ጣዖታትዋ
ንም ፡ሁሉ ፡አጠፋለሁ ፤ በግልሙትና ፡ዋጋ ፡
ሰበሰበቻቸው ÷ ወደ ፡ግልሙትናም ፡ዋጋ ፡
፯ ይመለሳሉና ። ስለዚህ ፡ነገር ፡ዋይ ፡ብላ ፡ታለ
ቅሳለች ÷ ባዶ ፡እግርዋንና ፡ዕራቁትዋን ፡ሆና ፡
ትሄዳለች ፤ እንደ ፡ቀበሮ ፡ታለቅሳለች ÷ እንደ ፡
፰ ሰጉንም ፡ዋይ ፡ትላለች ፤ ቍስልዋ ፡የማይፈ
ወስ ፡ነውና ፤ እስከ ፡ይሁዳም ፡ደርሶአልና ÷
ወደ ፡ሕዝቤም ፡በር ፡ወደ ፡ኢየሩሳሌም ፡ቀር
፱ ቦአልና ። በጌት ፡ላይ ፡አታውሩ ፤ በአክ ፡ላይ ፡
እንባን ፡አታድርጉ ፤ በቤትዓፍራ ፡በትቢያ ፡
፲ ላይ ፡ተንከባለሉ ። በሻፊር ፡የምትቀመጪ ፡
ሆይ ÷ በዕራቁትነትሽና ፡በእፍረት ፡እለፊ ፤
በጸዓንን ፡የምትቀመጠው ፡አልወጣችም ፤ የቤ
ትኤጼል ፡ልቅሶ ፡ከእናንተ ፡ዘንድ ፡መኖርያ
፲፩ ውን ፡ይወስዳል ። ክፋ ፡ነገር ፡ከእግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡እስከ ፡ኢየሩሳሌም ፡በር ፡ድረስ ፡ወር
ዶአልና ፤ በማሮት ፡የምትቀመጠው ፡በጎነትን ፡
፲፪ ትጠብቃለች ። በለኪሶ ፡የምትቀመጪ ፡ሆይ ÷
ሰረገላውን ፡ለፈረስ ፡አሰሪ ፤ እርስዋ ፡ሰጽዮን ፡
ሴት ፡ልጅ ፡የኃጢአት ፡መጀመሪያ ፡ነበረች ፤
የእስራኤል ፡በደል ፡በእንቺ ፡ዘንድ ፡ተገኝቶ
፲፫ አልና ። ስለዚህ ፡ትሎት ፡ለሞሬሼትጌት ፡ትሰ
ጪ.አለሽ ፤ የአክዚብ ፡ቤቶች ፡ለእስራኤል ፡
፲፬ ነገሥታት ፡አታላይ ፡ይሆናሉ ። በመረሳ ፡የም
ትቀመጪ ፡ሆይ ÷ ወራሽ ፡አመጣብሻለሁ ፡የእ
ስራኤል ፡ክብር ፡ወደ ፡ዓዶላም ፡ይመጣል ።
፲፭ ተማርከው ፡ከእንቺ ፡ዘንድ ፡ወጥተዋልና ፡
ስለ ፡ተድላሽ ፡ልጆች ፡ራስሽን ፡ንጪ ÷ ጠጕ
ርሽንም ፡ተቈረጪ ፤ ቡሃነትሽንም ፡እንደ ፡
ንስር ፡አስፊ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ በመኝታቸው ፡ላይ ፡በደልን ፡ለሚያስቡ ፡
ክፋትንም ፡ለሚያደርጉ ፡ወዮላቸው ! ኃይል ፡
በእጃቸው ፡ነውና ፡ሲነጋ ፡ይፈጽሙታል ።
፪ በእርሻው ፡ላይ ፡ይመኛሉ ÷ በግዴታም ፡ይይ
ዙታል ፤ በቤቶችም ፡ላይ ፡ይመኛሉ ÷ ይወስ
ዱአቸውማል ፤ ሰውንና ፡ቤቱን ÷ ሰውንና ፡
፫ ርስቱንም ፡ይነጥቃሉ ። ስለዚህ ፡እግዚአብ
ሔር ፡እንዲህ ፡ይላል ፦ እነሆ ÷ በዚህ ፡ወገን ፡
ላይ ፡በክፋ ፡አስባለሁ ÷ ከዚያም ፡አንገታች
ሁን ፡አታነሡም ፤ ዘመኑም ፡ክፋ ፡ነውና ፡ቀጥ ፡
፬ ብላችሁ ፡አትሄዱም ። በዚያ ፡ቀን ፡በምሳሌ ፡
ይመስሉብችኋል ÷ በጽኑ ፡ልቅሶም ፡ያለቅሱላ
ችኋል ፤ እነርሱም ፦ ፈጽመን ፡ጠፍተናል ፤
የሕዝቤን ፡እድል ፡ፈንታ ፡ይሰፍራል ÷ እርሱ
ንም ፡የሚከለክል ፡የለም ፤ እርሻችንን ፡ለኃመ
፭ ፀሮች ፡ይከፍላል ፡ይላሉ ። ስለዚህ ፡በእግዚ
አብሔር ፡ጉባኤ ፡መከከል ፡በዕጣ ፡ገመድ ፡
የሚጥል ፡አይኖርህም ።
፮ ትንቢት ፡አትናገሩ ፡ብለው ፡ይናገራሉ ፤
በእነዚህ ፡ላይ ፡ትንቢት ፡አይናገሩም ÷ ስድ
ብም ፡አይርቅም ። ፯ የያዕቆብ ፡ቤት ፡የተባልህ ፡
ሆይ ÷ በውኑ ፡የእግዚአብሔር ፡መንፈስ ፡የማ
ይታገሥ ፡ነውን ? ወይስ ፡ሥራው ፡እንደዚህ ፡
ናትን ? ቃሌስ ፡በቅን ፡ለሚሄድ ፡በጎነት ፡አያ
ደርግምን ? ነገር ፡ግን ፡ከቅርብ ፡ጊዜ ፡ጀምሮ ፡
፰ ሕዝቤ ፡እንደ ፡ጠላት ፡ሆኖ ፡ተነሥቶአል ፤
ቀሚስንና ፡መጐናጸፊያን ፡ገፈፋችሁ ፤ ሳያፈ
ሩም ፡የሚያልፉትን ፡ከሰልፍ ፡እንደሚመለሱ ፡
አደረጋችኋቸው ። ፱ የሕዝቤንም ፡ሴቶች ፡ከተ
ሸለሙ ፡ቤቶቻቸው ፡አሳደዳችኋቸው ፤ ከሕፃ
ናቶቻቸውም ፡ክብሬን ፡ለዘላለም ፡ወሰዳችሁ ።
፲ በዚህ ፡ዕረፍት ፡የላችሁምና ፡ተነሥታችሁ ፡
ሂዱ ፤ በርኵሰት ፡ምክንያት ፡ክፉ ፡ጥፋት ፡
፲፩ ታጠፋችኋለች ። ነፋስንም ፡ተከትሎ ፦ ስለ ፡
ወይን ፡ጠጅና ፡ስለ ፡ስካር ፡ትንቢት ፡እናገር ፡
ልሃለሁ ፡ብሎ ፡ሐሰትን ፡የሚናገር ፡ሰው ፡
ቢኖር ፡እርሱ ፡ለዚህ ፡ሕዝብ ፡ነቢይ ፡ይሆናል ።
፲፪ ያዕቆብ ፡ሆይ ÷ ሁለንተናህን ፡ፈጽሞ ፡እሰበ
ስባለሁ ÷ የእስራኤልንም ፡ቅሬታ ፡ፈጽሞ ፡
አከማቻለሁ ፤ እንደ ፡በሶራ ፡በጎችና ፡እንደ ፡
መንጋ ፡በማሰማርያቸው ፡ውስጥ ፡በአንድነት ፡
አኖራቸዋለሁ ፤ ከሰው ፡ብዛት ፡የተነሣ ፡ድም
፲፫ ፃቸውን ፡ያሰማሉ ። ሰባሪው ፡በፊታቸው ፡
ወጥቶአል ፤ እነርሱም ፡ሰብረው ፡ወደ ፡በሩ ፡
አልፈዋል ÷ በእርሱም ፡በኩል ፡ወጥተዋል ፤
ንጉሣቸውም ፡በፊታቸው ፡አልፎአል ÷ እግዚ
አብሔርም ፡በራሳቸው ፡ላይ ፡ነው ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ እንዲህም ፡አልሁ ፦ የያዕቆብ ፡አለቆችና ፡
የእስራኤል ፡ቤት ፡ገዦች ፡ሆይ ÷ እባክችሁ ፡
ስሙኝ ፤ ፍርድን ፡ታውቁ ፡ዘንድ ፡አይገባች
ሁምን ? ፪ መልካሙን ፡ጠልታችኋል ÷ ክፉው
ንም ፡ወድዳችኋል ፤ ቁርበታቸውን ፡ገፍፋችኋ
ቸዋል ÷ ሥጋቸውንም ፡ከአጥንታቸው ፡ለያይ
፫ ታችኋል ! የሕዝቤን ፡ሥጋ ፡በልታችኋል ÷
ቁርበታቸውንም ፡ገፍፋችኋቸዋል ÷ አጥንታ
ቸውንም ፡ሰብራችኋል ! ለእፍላል ፡እንደሚ
ሆን ፡ሥጋ ፡ለድስትም ፡እንደሚሆን ፡መዳ ፡
፬ ቈራረጣችኋቸው ። የዚያን ፡ጊዜ ፡ወደ ፡እግ
ዚአብሔር ፡ይጮኻሉ ÷ እርሱም ፡አይሰማች
ውም ፤ ሥራቸውንም ፡ክፉ ፡አድርገዋልና ፡
በዚያን ፡ጊዜ ፡ፊቱን ፡ከእነርሱ ፡ይሰውራል ።
፭ እግዚአብሔር ፡ሕዝቤን ፡ስለሚያስቱ ፡ነቢ
ያት ፡እንዲህ ፡ይላል ፤ በጥርሶቸው ፡ሲነክሱ ፡
በሰላም ፡ይሰብካሉ ፤ በአፋቸው ፡ግን ፡አንዳች ፡
በማይሰጥ ፡ሰው ፡ላይ ፡ሰልፍን ፡ያስቡበታል ።
፮ ስለዚህ ፡ሌሊት ፡ይሆንባችኋል ፤ እንጂ ፡ራእይ ፡
አይሆንላችሁም ፤ ጨለማም ፡ይሆንባችኋል ፤
እንጂ ፡አታምዋርቱም ፤ ፀሐይም ፡በነቢያት ፡
ላይ ፡ትገባለች ÷ ቀኑም ፡ይጠቍርባቸዋል ።
፯ ከእግዚአብሔርም ፡ዘንድ ፡መልስ ፡የለምና ፡
ባለ ፡ራእዮቹ ፡ያፍራሉ ÷ ምዋርተኞችም ፡ይዋ

ረዳሉ ፤ ሁሉም ፡ከንፈራቸውን ፡ይሸፍናሉ ።
፰ እኔ ፡ግን ፡በይሉን ፡ለያዕቆብ ÷ ኃጢአቱንም ፡
ለእስራኤል ፡እነግር ፡ዘንድ ፡በእግዚአብሔር ፡
መንፈስ ፡ኃይልንና ፡ፍርድን ፡ብርታትንም ፡
ተሞልቻለሁ ።
፱ ፍርድን ፡የምትጠሉ ፡ቅን ፡ነገርንም ፡ሁሉ ፡
የምታጣምሙ ፡እናንተ ፡የያዕቆብ ፡ቤት ፡አለ
ቆችና ፡የእስራኤል ፡ቤት ፡ገዦች ፡ሆይ ÷
፲ እባክችሁ ፡ይህን ፡ስሙ ። ጽዮንን ፡በደም ÷
፲፩ ኢየሩሳሌምንም ፡በኃጢአት ፡ይሠራሉ ። አለ
ቆችዋ ፡በጉቦ ፡ይፈርዳሉ ፥ ካህናቶችዋም ፡
በዋጋ ፡ያስተምራሉ ÷ ነቢያቶችዋም ፡በገን
ዘብ ፡ያምዋርታሉ ፤ ከዚህም ፡ጋር ፦ እግዚአ
ብሔር ፡በመካከላችን ፡አይደለምን ? ክፋ ፡
ነገር ፡ምንም ፡አይመጣብንም ፡እያሉ ፡በእግ
፲፪ ዚአብሔር ፡ይታመናሉ ። ስለዚህ ፡በእናንተ ፡
ምክንያት ፡ጽዮን ፡እንደ ፡እርሻ ፡ትታረሰለች ÷
ኢየሩሳሌምም ፡የድንጋይ ፡ክምር ፡ትሆናለች ÷
የቤቱም ፡ተራራ ፡እንደ ፡ዱር ፡ከፍታ ፡ይሆ
ናል ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ በመጨረሻውም ፡ዘመን ፡የእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ተራራ ፡በተራሮች ፡ራስ ፡ላይ ፡ጸንቶ ፡ይቆ
ማል ÷ ከከረብቶችም ፡በላይ ፡ከፍ ፡ከፍ ፡ይላል ፤
፪ አሕዛብም ፡ወደ ፡እርሱ ፡ይጐርፋሉ ። ከጽ
ዮን ፡ሕግ ÷ ከኢየሩሳሌምም ፡የእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ይወጣልና ፡ብዙዎች ፡አሕዛብ ፡ሄደው ፡—
ኑ ÷ ወደ ፡እግዚአብሔር ፡ተራራ ÷ ወደ ፡ያዕ
ቆብ ፡አምላክ ፡ቤት ፡እንውጣ ፤ እርሱም ፡መን
ገዱን ፡ያስተምረናል ÷ በፍለጋውም ፡እንሄዳ
፫ ለን ፡ይላሉ ። በብዙዎችም ፡አሕዛብ ፡መከከል ፡
ይፈርዳል ÷ በሩቅም ፡ባሉ ፡በብርቱዎች ፡አሕ
ዛብ ፡ላይ ፡ይበይናል ፤ ሰይፋቸውንም ፡ማረሻ ÷
ጦራቸውንም ፡ማጭድ ፡ለማድረግ ፡ይቀጠቅ
ጣሉ ፤ ሕዝብም ፡በሕዝብ ፡ላይ ፡ሰይፍ ፡አያነ
ሣም ፡ከእንግዲህም ፡ወዲህ ፡ሰልፍ ፡አይማ
፬ ሩም ። የሠራዊት ፡ጌታ ፡የእግዚአብሔር ፡
አፍም ፡ተናግሮአልና ፡ሰው ፡እያንዳንዱ ፡ከወ
ይኑና ፡ከበለሱ ፡በታች ፡ይቀመጣል ÷ የሚያ
፭ ስፈራውም ፡የለም ። ሕዝብም ፡ሁሉ ፡እያንዳ
ንዱ ፡በየአምላኩ ፡ስም ፡ይሄዳል ÷ እኛም ፡
በአምላካችን ፡በእግዚአብሔር ፡ስም ፡ለዘላ
ለም ፡እንሄዳለን ።
፮ በዚያ ፡ቀን ፡አንካሳይቱን ፡እሰበስባለሁ ÷
ይላል ፡እግዚአብሔር ÷ የባከነችውንና ፡ያስ
፯ ጨነቅኋትንም ፡አከማቻለሁ ፤ አንካሳይቱንም ፡
ለቅሬታ ÷ ወደ ፡ሩቅም ፡የተጣለችውን ፡ለብ
ርቱ ፡ሕዝብ ፡አደርጋታለሁ ፤ ከዚያም ፡ወዲያ ፡
እስከ ፡ዘላለም ፡ድረስ ፡እግዚአብሔር ፡በጽ
፰ ዮን ፡ተራራ ፡በእነርሱ ፡ላይ ፡ይነግሣል ። አን
ተም ፡የመንጋ ፡ግንብ ፡ሆይ ÷ የጽዮን ፡ሴት ፡
ልጅ ፡አምባ ፡ወደ ፡አንተ ፡ትመጣለች ፤ የቀ
ደመችው ፡ግዛት ÷ የኢየሩሳሌም ፡ሴት ፡ልጅ ፡
መንግሥት ፡ትደርሰለች ።
፱ አሁንስ ፡ለምን ፡ትጮኺአለሽ ? እንደምት
ወልድ ፡ሴት ፡ምጥ ፡የደረሰብሽ ÷ ንጉሥ ፡ስለ
ሌለሽ ፡ነውን ? ወይስ ፡መካሪ ፡ስለ ፡ጠፋብሽ ፡
ነውን ? የጽዮን ፡ልጅ ፡ሆይ ÷ እንደምትወ
፲ ልድ ፡ሴት ፡አምጠሽ ፡ውለጂ ፤ አሁን ፡ከከ
ተማ ፡ትወጪአለሽና ÷ በሜዳም ፡ትቀመጪአለሽ ÷
ወደ ፡በቢሎንም ፡ትደርሻለሽ ፤ በዚያም ፡ያድ
ንሻል ÷ በዚያም ፡እግዚአብሔር ፡ከጠላቶችሽ ፡
እጅ ፡ይቤዥሻል ።
፲፩ አሁንም ፡— ርኩስ ፡ትሁን ፡ዓይናችንም ፡
በጽዮን ፡ላይ ፡ይይ ፡የሚሉ ፡ብዙ ፡አሕዛብ ፡
በአንቺ ፡ላይ ፡ተሰብስበዋል ። ነገር ፡ግን ፡የእ
፲፪ ግዚአብሔርን ፡አሳብ ፡አያውቁም ፡ምክሩ
ንም ፡አያስተውሉም ፤ እንደ ፡ነዶ ፡ወደ ፡አው
ድማ ፡አከማችቶአቸዋልና ። የጽዮን ፡ልጅ ፡
፲፫ ሆይ ÷ ቀንድሽን ፡ብረት ÷ ጥፍርሽንም ፡ናስ ፡
አደርጋለሁና ፡ተነሺ ፡አሂጂ ፤ ብዙ ፡አሕዛብ
ንም ፡ታደቅቂአለሽ ፤ ትርፋቸውንም ፡ለእግዚ
አብሔር ÷ ሀብታቸውንም ፡ለምድር ፡ሁሉ ፡
ጌታ ፡ትቀድሻለሽ ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩ የጭፍሮች ፡ሴት ፡ልጅ ፡ሆይ ÷ ጭፍሮችሽን ፡
አሁን ፡ሰብስቢ ፤ ከብበ ፡አስጨንቆናል ፤ የእስራ
ኤልን ፡ፈራጅ ፡ጉንጩን ፡በበትር ፡ይመታሉ ።
፪ አንቺም ፡ቤተ ፡ልሔም ፡ኤፍራታ ፡ሆይ ÷
አንቺ ፡በይሁዳ ፡አእላፋት ፡መካከል ፡ትሆኚ ፡
ዘንድ ፡ታናሽ ፡ነሽ ፤ ከአንቺ ፡ግን ፡አወጣጡ ፡
ከቀድሞ ፡ጀምሮ ፡ከዘላለም ፡የሆነ ÷ በእስራ
ኤልም ፡ላይ ፡ገዥ ፡የሚሆን ፡ይወጣልኛል ።
፫ ስለዚህ ፡ወላጂቱ ፡እስከምትወልድበት ፡ጊዜ ፡
ድረስ ፡አሳልፎ ፡ይሰጣቸዋል ፤ የቀሩትም ፡
ወንድሞቹ ፡ወደ ፡እስራኤል ፡ልጆች ፡ይመ
ለሳሉ ። እርሱም ፡ይቆማል ÷ በእግዚአብሔ
፬ ርም ፡ኃይል ፡በአምላኩ ፡በእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ግርማ ፡መንጋውን ፡ይጠብቃል ፤ እነር
ሱም ፡ይኖራሉ ፤ እርሱ ፡አሁን ፡እስከ ፡ምድር ፡
ዳርቻ ፡ድረስ ፡ታላቅ ፡ይሆናልና ። ፭ ይህም ፡
ሰላማም ፡ይሆናል ፤ አሦራዊውም ፡ወደ ፡አገራ
ችን ፡በገባ ፡ጊዜ ÷ ምድራችንንም ፡በረገጠ ፡
ጊዜ ፡ሰባት ፡እረኞችና ፡ስምንት ፡አለቆች ፡
እናስነሣበታለን ። ፮ የአሦርንም ፡አገር ፡በሰይፍ÷
የናምሩድንም ፡አገር ፡በመግቢያው ፡ውስጥ ፡
ያፈርሰሉ ፤ አሦራዊውም ፡ወደ ፡አገራችን ፡
በገባ ፡ጊዜ ÷ ዳርቻዎቻችንንም ፡በረገጠ ፡ጊዜ ፡
እርሱ ፡ይታደገናል ። የያዕቆብም ፡ቅሬታ ፡
፯ በብዙ ፡አሕዛብ ፡መካከል ፡ከእግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡እንደሚወርድ ፡ጠል ÷ በሣር ፡ላይ ፡እን
ደሚወርድ ፡ካፊያ ፡ሰውንም ፡እንደማይጠብቅ÷
የሰውንም ፡ልጆች ፡ተስፋ ፡እንደማያደርግ ፡
ይሆናል ። ፰ በዱር ፡አራዊትም ፡መካከል ፡እን
ዳለ ፡አንበሳ ÷ በበጎች ፡መንጋም ፡መካከል ፡
አልፎ ፡እንደሚረግጥ፡የሚታደግም ፡ሳይኖር፡

እንደሚነጥቅ ፣ እንደ ፣ አንበሳ ፣ ይበል ÷ እን
ዲሁ ፣ የያዕቆብ፣ ቅሬታ ፣ በአሕዛብና ፣ በብዙ ፡
፰፡ ወገኖች ፣ መካከል ፣ ይሆናል ። እጅህ ፣ በጠላ
ቶችህ ፣ ላይ ፣ ከፍ ፣ ከፍ ፣ ትበል ÷ ጠላቶችህም ፣
ሁሉ ፣ ይጥፉ ።
፱፡ በዚያም ፣ ቀን ፣ ፈረሶችህን ፣ ከመካከልህ ፣
አጠፋለሁ ÷ ሰረገሎችህንም ፣ አስብራለሁ ÷
፲፩፡ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ የምድርህንም ፣ ከተ
ሞች ፣ አጠፋለሁ ÷ ምሽጎችህንም ፣ ሁሉ ፣ አፈ
፲፪፡ ርሳለሁ ፣ መተትንም ፣ ከእጅህ ፣ አጠፋለሁ ÷
ምዋርተኞችም ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ አይሆኑ
፲፫፡ ልህም ፣ የተቀረጹትን ፣ ምስሎችህንና ፣ ሐውል
ቶችህን ፣ ከመካከልህ ፣ አጠፋለሁ ፣ ለእጅህም ፡
ሥራ ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ አትሰግድም ፣
፲፬፡ የማምለክ፣ ፀፀዶችህንም ፣ ከመካከልህ ፣ እን
፲፭፡ ቅላለሁ ÷ ከተሞችህንም ፣ አፈርሳለሁ ። በልሰ
ሙም ፣ አሕዛብ ፣ ላይ ፣ በቍጣና ፣ በመዓት ፣
እበቀላለሁ ።

ምዕራፍ ፣ ፮ ።

፩፡ አሁን ፦ ተነሣ ÷ በተራሮችም ፣ ፊት ፣ ተፋ
ረድ ÷ ኮረብቶችም ፣ ቃልህን ፣ ይስሙ ፣ ብሎ ፡
፪፡ እግዚአብሔር ፣ የሚለውን ፣ ስሙ ። ተራሮች ፡
ሆይ ÷ ጠንካሮች ፣ የምድር ፣ መሠረቶችም ፡
ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፣ ከሕዝቡ ፣ ጋር ፣ ክርክር ፡
አለውና ÷ ከእስራኤልም ፣ ጋር ፣ ይፋረዳልና ፡
፫፡ የእግዚአብሔርን ፣ ክርክር ፣ ስሙ ። ሕዝቤ ፡
ሆይ ÷ ምን ፣ አድርጌሃለሁ ? በምንስ ፣ አድክሜሃ
፬፡ ለሁ ? መስክርብኝ ። ከግብጽ ፣ ምድር ፣ አውጥቼ
ሃለሁ ÷ ከባርነት ፣ ቤትም ፣ ተቤዣቸሃለሁ ፤ በፊ
ትህም ፡ ሙሴንና ፣ አሮንን ፣ ማርያምንም ፣ ልኬ
፭፡ ልህ ፣ ነበር ። ሕዝቤ ፣ ሆይ ÷ የሞዓብ ፣ ንጉሥ ፡
በላቅ ፣ የመከረውን ÷ የቢዖርም ፣ ልጅ ፣ በለዓም ፡
የመለሰለትን ፣ አሁን ፣ አስብ ፣ የእግዚአብሔር
ንም ፣ የጽድቅ ፣ ሥራ ፣ ታውቅ ፣ ዘንድ ፣ ከሰ
ጢም ፣ ጀምሮ ፣ እስከ ፣ ጌልገላ ፣ ድረስ ፣ አስብ ።
፮፡ ምን ፣ ይዤ ፣ ወደ ፣ እግዚአብሔር ፣ ፊት ፣
ልምጣና ፣ በልዑል ፣ አምላክ ፣ ፊት ፣ ልስገድ ?
የሚቃጠለውን ፣ መሥዋዕትና ፣ የአንዳን ፡
፯፡ ዓመት ፣ ጥጃ ፣ ይዤ ፣ በፊቱ ፣ ልምጣን ? እግዚ
አብሔርስ ፣ በሺህ ፣ አውራ ፣ በጎች ፣ ወይስ ፣ በአ
ልና ፣ የዘይት ፣ ፈሳሾች ፣ ደስ ፣ ይለዋልን ?
ወይስ ፣ የበኵር ፣ ልጄን ፣ ስለ ፣ በደሌ ፣ የሆዴ
ንም ፡ ፍሬ ፣ ስለ ፣ ነፍሴ ፣ ኃጢአት ፣ አሰጣለሁን ?
፰፡ ሰው ፣ ሆይ ÷ መልካሙን ፣ ነግሮሃል ፣ እግዚአብ
ሔርም ፣ ከአንተ ፣ ዘንድ ፣ የሚሻው ፡ ምንድር ፡
ነው ? ፍርድን ፡ ታደርግ ፣ ዘንድ ÷ ምሕረትንም ፡
ትወድድ ፣ ዘንድ ÷ ከአምላክህም ፣ ጋር ፣ በትሕ
ትና ፡ ትሄድ ፣ ዘንድ ፡ አይደለምን ?
፱፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ከተማይቱን ፡ ይጠ
ራታል ፡ ስምህን ፡ መፍራት ፡ ጥበብ ፡ ነው ፡ የመ
ቅሠፍትን ፣ በትር ÷ እርሱንም ፡ ያዘጋጀ ፡ ማን ፡
፲፡ እንደ ፣ ሆነ ፡ ስሙ ። በውኑ ፡ በኃጢአተኛ ፡
ቤት ፣ የኃጢአት ፣ መዝገብ ÷ የተጸየፈም ፡
ሙሽተኛ ፡ መስፈሪያ ፡ ገና ፡ አለ ፡ ይሆን ? በአ
፲፩፡ ባይ ፡ ሚዛንና ፡ በነረጢት ፡ ባለ ፡ በተንኰል ፡
መመዘኛ ፡ ንጹሕ ፡ እሆናለሁን ? ባለ ፡ ጠጎቸዋን ፡
፲፪፡ ግፍ ፡ ሞልቶበቸዋል ፡ በእርስዋም ፡ የሚኖሩ ፡
በሐሰት ፡ ተናግረዋል ÷ ምላሳቸውም ፡ በአፋ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ ተንኰለኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እኔ ፡
፲፫፡ ደግሞ ፡ በክፋ ፡ ቀስል ፡ መታሁህ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
አትህም ፡ አፈረስሁህ ። ትበላለህ ÷ ነገር ፡ ግን ፡
፲፬፡ አትጠግብም ÷ ችጋርህም ፡ በመካከልህ ፡ ይሆ
ናል ፡ ትወስዳለህ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አታድንም ፡
የምታድነውንም ፡ ለሰይፍ ፡ እሰጣለሁ ። ትዘራ
፲፭፡ ለህ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አታጭድም ፡ ወይራውንም ፡
ትጨነዋለህ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ዘይቱን ፡ አትቀ
ባም ፡ ወይኑንም ፡ ትጨመቃለህ ÷ ነገር ፡ ግን ፡
የወይን ፡ ጠጁን ፡ አትጠጣም ። አንተን ፡ ለጥ
፲፮፡ ፋት ÷ በእርስዋም ፡ የሚኖሩትን ፡ ለማፍዋጫ ፡
እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የዘንበሪን ፡ ሥርዓትና ፡ የአክዓ
ብን ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጠብቃችኋል ÷ በም
ክራቸውም ፡ ሄዳችኋል ፡ የሕዝቤንም ፡ ስድብ ፡
ትሸከማላችሁ ።

ምዕራፍ ፣ ፯ ።

፩፡ የዛፍ ፡ ፍሬና ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ ከተለቀሙ ፡
በኋላ ፡ እንደ ፡ ቀረው ፡ ቃርሚያ ፡ ሆኛለሁና ፡
ወዮልኝ ! መብል ፡ የሚሆን ፡ ዘለላ ÷ ነፍሴም ፡
የተመኘችው ፡ በመጀመሪያ ፡ የበሰለው ፡ በለስ ፡
፪፡ የለም ። ደግ ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ ጠፍቶአል ÷
በሰውም ፡ መካከል ፡ ቅን ፡ የለም ፡ ሁሉ ፡ ደምን ፡
ለማፍሰስ ፡ ያደባሉ ÷ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ወንድ
ሙን ፡ በመረብ ፡ ለመያዝ ፡ ይከታተላሉ ።
፫፡ እጆቻቸውን ፡ ለክፋት ፡ ያነጣሉ ፤ አለቃውና ፡
ፈራጁ ፡ ጉቦን ፡ ይፈልጋሉ ÷ ትልቁም ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ምኞት ፡ ይናገራል ፡ እንዲሁም ፡
ከፋትን ፡ ይጐነጉናሉ ። ከእነርሱም ፡ ሁሉ ፡
፬፡ የተሻለው ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ እሜከላ ፡ ነው ÷
ከሁሉም ፡ ቅን ፡ የሆነው ፡ እንደ ፡ ሦርኒንችት ፡
ነው ፡ ጠባቆችህ ፡ የሚጐበኙበት ፡ ቀን ፡ መጥ
ቶአል ፡ አሁን ፡ ይሸበራሉ ። በልጁራን ፡ አት
መኑ ÷ በወዳጅም ፡ አትታመኑ ፡ የአናህን ፡
፭፡ ደጅ ፡ በብብትህ ፡ ከምትተኛው ፡ ጠብቅ ።
ወንድ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ይንቃልና ፡ ሴት ፡
ልጅ ፡ በእናትዋ ፡ ላይ ፡ ምራቲቱም ፡ በአማ
ትዋ ፡ ላይ ፡ ትነሣለችና ÷ የሰው ፡ ጠላቶች ፡
የቤቱ ፡ ሰዎች ፡ ናቸውና ።
፮፡ እኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመለከታ
ለሁ ÷ የመድኀኒቴንም ፡ አምላክ ፡ ተስፋ ፡ አደ
ርጋለሁ ፤ አምላኬም ፡ ይሰማኛል ። ጠላቴ ፡
፯፡ ሆይ ÷ ብወድቅ ፡ እነሣለሁና ÷ በጨለማም ፡ ብቀ
መጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ይሆንልኛልና ፡
በእኔ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አይበልሽ ። በእግዚአብሔር ፡
፰፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቻለሁና ፡ እስኪ ፡ ምዋገትልኝ ፡
ድረስ ÷ ፍርድን ፡ ለእኔ ፡ እስኪ ያደርግ ፡ ድረስ ፡
ቍጣው ፡ እታገሣለሁ ። ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወ
ጣኛል ÷ ጽድቅንም ፡ እያለሁ ። ጠላቴም ፡ ታያ
፲፩፡

ለች ፡ እንጉም ፦ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡
ወዲት ፡ ነሙ ? ያለች ፡ በእኅረት ፡ ትከደናለች ።
፲፩፡ ዓይኖቼ ፡ ይመለከቱአታል ፡ አሁን ፡ እንደ ፡ መን
ገድ ፡ ጭቃ ፡ ትረገጣለች ። ቅጥርሽ ፡ በሚሠራ
በት ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ድንበርሽ ፡ ትስፋፋለች ።
፲፪፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከአሦርና ፡ ከግብጽ ፡ ከተሞች ÷ ከግ
ብጽ ፡ እስከ ፡ ወንዙ ÷ ከባሕርም ፡ እስከ ፡ ባሕር ÷
ከተራራም ፡ እስከ ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡
ይመጣሉ ። ምድሪቱ ፡ ግን ፡ በሚኖሩባት ፡ በሥ
ራቸው ፡ ፍሬ ፡ ምክንያት ፡ በድማ ፡ ትሆናለች ።
፲፫፡ በቀርሜሎስ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ዱር ፡ ብቻ
ቸውን ፡ የተቀመጡት ፡ ሰዎችህ ÷ የርስትህን ፡
በጎች ÷ በብትርህ ፡ እግድ ፡ እንደ ፡ ቀደመውም ፡
፲፬፡ ዘመን ፡ በባሳንና ፡ በገለዓድ ፡ ይሰማሩ ። ከግ
ብጽ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ወጣህበት ፡ ዘመን ፡ ተአ
፲፭፡ ምራትን ፡ አሳያቸዋለሁ ። አሕዛብ ፡ አይተው ፡
በኮልበታቸው ፡ ሁሉ ፡ ያፍራሉ ፡ እጃቸውን ፡
በአፋቸው ፡ ላይ ፡ ያኖራሉ ÷ ጆሮአቸውም ፡
ትደነቍራለች ፡ እንደ ፡ እባብም ፡ መሬት ፡ ይል
፲፯፡ ሳሉ ÷ እንደ ፡ ምድርም ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ እየ
ተንቀጠቀጡ ፡ ከግንባቸው ፡ ይመጣሉ ፡ ፈሪተ
ሙም ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይመጣሉ ÷ ስለ ፡ አንተም ፡ ይፈራሉ ።
፲፰፡ በደልን ፡ ይቅር ፡ የሚል ÷ የርስቱንም ፡ ቅሬታ ፡
ዓመፅ ፡ የሚያልፍና ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ አም
ላክ ፡ ማን ፡ ነው ? ምሕረትን ፡ ይወድዳልና ፡
ቍጣውን ፡ ለዘላለም ፡ አይጠብቅም ። ተመልሶ ፡
፲፱፡ ይምረናል ፡ ከፋታችንንም ፡ ይጠቀጥቃል ÷
ኃጢአታችንንም ፡ በባሕሩ ፡ ጥልቅ ፡ ይጥለ
ዋል ። ከተደሞ ፡ ዘመን ፡ ጀምረህ ፡ ለአበቶቹ ፡
፳፡ ችን ፡ የማልህላቸውን ፡ እውነት ፡ ለያዕቆብ ÷
ምሕረትንም ፡ ለአብርሃም ፡ ታደርጋለህ ።

ትንቢተ ኢዩኤል ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ።

፩፡ ወደ ፡ ባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዩኤል ፡ የመ
ጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።
፪፡ እናንተ ፡ ሽማግሌዎች ÷ ይህን ፡ ስሙ ፡ በምድ
ርም ፡ የምትኖሩ ፡ ሁሉ ÷ አድምጡ ። ይህ ፡ በዘ
መናችሁ ፡ ወይስ ፡ በአበቶቻችሁ ፡ ዘመን ፡ ሆኖ ፡
፫፡ ነበርን ? ይህን ፡ ለልጆቻችሁ ፡ ንገሩ ፡ ልጆቻች
ሁም ፡ ለልጆቻቸው ÷ ልጆቻቸውም ፡ ለኋለ
፬፡ ኛው ፡ ትውልድ ፡ ይንገሩ ። ከተምች ፡ የቀረ
ውን ፡ አንበጣ ፡ በላው ፡ ከአንበጣም ፡ የቀረ
ውን ፡ ደንብያ ፡ በላው ፡ ከደንብያም ፡ የቀረውን ፡
ኩብኩብ ፡ በላው ።
፭፡ በተፃ ፡ ወይን ፡ ጠጪችሁ ፡ ከአፋችሁ ፡ ተው
ገፍአልና ፡ እናንተ ፡ ሰካራሞች ÷ ኑክታችሁ ፡
አልቅሱ ፡ እናንተም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የምት
፮፡ ጠጡ ፡ ሁሉ ÷ ዋይ ፡ በሉ ። ቍጥሩም ፡ የሌለው ፡
ብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ በምድሬ ፡ ላይ ፡ ወጥቶአልና ፡
ጥርሶቹ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጥርስ ፡ ናቸውን ፡
ቸውም ፡ እንደ ፡ እንስቲቱ ፡ አንበሳ ፡ መንጋጋ ፡
፯፡ ነው ። ወይኔን ፡ በዶ ፡ ምድር ፡ አደረገው ÷ በለ
ሰንም ፡ ሰበረው ፡ ባዶም ፡ አደረገው ÷ ጣለውም ፡
ቅርንጫፎቹም ፡ ነጡ ።
፰፡ ለቅንጦርኖ ፡ ባል ፡ ማቅ ፡ ለብሳ ፡ እንደምታ
፱፡ ለቅስ ፡ ድንግል ፡ አልቅሺ ። የእህሉ ፡ ቍርባ
ንና ፡ የመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ተወግዶአል ፡ የእግዚአብሔርም ፡ አገል
ጋዮች ፡ ካህናቱ ፡ አለቀሱ ። እህሉ ፡ ጠፍቶአ
ልና ÷ ወይኑም ፡ ደርቆአልና ÷ ዘይቱም ፡ ጉድ
ለኣልና ፡ እርሻው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆኖአል ÷
፲፡ ምድሪቱም ፡ አልቅሳለች ። መከሩ ፡ ከእርሻችው ፡
ጠፍቶአልና ፡ ገበሬዎች ፡ ስለ ፡ ስንዴውና ፡ ስለ ፡
ገብሱ ፡ አፈሩ ፡ የወይን ፡ አትክልተኞችም ፡
አለቀሱ ። ወይኑ ፡ ደርቆአል ÷ በለሱም ፡ ጠው
፲፪፡ ልእል ፡ ሮማኑና ፡ ተምሩ ፡ እንኩዋሮም ፡ የምድ
ርም ፡ ዛፎች ፡ ሁሉ ፡ ደርቀዋል ፡ ደስታም ፡
ከሰው ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ርቆአል ።
፲፫፡ የእህሉ ፡ ቍርባንና ፡ የመጠጡ ፡ ቍርባን ፡
ከእምላካችሁ ፡ ቤት ፡ ቀርቶአልና ፡ እናንተ ፡ ካህ
ናት ÷ ማቅ ፡ ታዋታላችሁ ፡ አልቅሱ ፡ እናንተም ፡
የመሠዊያ ፡ አገልጋዮች ÷ ዋይ ፡ በሉ ፡ እናንተ ፡
የአምላክ ፡ አገልጋዮች ÷ ኑ ÷ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡
በማቅ ፡ ላይ ፡ ተኙ ። ጾምን ፡ ቀድሱ ÷ ጉባኤው
፲፬፡ ንም ፡ አውጁ ። ሽማግሌዎችንና ፡ በምድር ፡ የሚ
ኖሩትን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሰብስቡ ÷ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔርም ፡ ጩኹ ።
፲፭፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርቦአልና ፡ ለቀኑ ፡
ወዮ ! እርሱም ፡ ሁሉን ፡ ከሚችል ፡ ከአምላክ ፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጥፋት ፡ ይመጣል ። ከሃይኖችን ፡
፲፮፡ ፈት ፡ ምግብ ፡ ከአምላካችንም ፡ ቤት ፡ ደስታና ፡
አልልታ ፡ የጠፋ ፡ አይደለምን ? ዘሩ ፡ በምድር ፡
፲፯፡ ውስጥ ፡ በሰበሰ ፡ እህሉ ፡ ደርቆአልና ፡ ጎተራ
ዎቹ ፡ ባዶ ፡ ናቸው ÷ ጎታዎቹም ፡ ፈርሰዋል ።
እንስሶች ፡ እይ ፡ ጮኹ ፡ የላምም ፡ መንጎች ፡
፲፰፡ ማሰማርያ ፡ የላቸውምና ፡ ተጠራጠሩ ፡ የበግም ፡
መንጎች ፡ ጠፍተዋል ። አቤቱ ÷ እሳት ፡ የም
፲፱፡ ድረ ፡ በዳውን ፡ ማሰማርያ ፡ በልቶአልና ÷ ነበ
ልባሉም ፡ የዱሩን ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ አቃጥሎአ
ልና ፡ ወይ ፡ አንተ ፡ እጮኻለሁ ። ፈሳሹ ፡ ውኃ ፡
፳፡ ደርቆአልና ÷ እሳቱም ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡
ማሰማርያ ፡ በልቶአልና ፡ የምድር ፡ አራዊት ፡
ወደ ፡ አንተ ፡ አለ ኸለኹ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ መጥቶአልና ÷ እር
ሱም ፡ ቀርቦአልና ፡ በጽዮን ፡ መለከትን ፡ ንፋ ÷
በቅዱሱም ፡ ተራራዬ ፡ ላይ ፡ አሪ ፡ በሉ ፡ በም
ድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ይንቀጥቀጡ ፡ የእግ
፪ ዚአብሔር ፡ ቀን ፡ መጥቶአልና ፡ የጨለማና ፡
የጭጋግ ፡ ቀን÷የደመናና ፡ የድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡
ቀን ፡ ነው ፡ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ በተራሮች ፡
ላይ ፡ እንደ ፡ ወገግታ ፡ ተዘርግቶአል ። ከዘላለ
ምም ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ያለ ፡ አልነበ
ረም ÷ ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ትው
ልድ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ያለ ፡ ከእንግዲህ ፡
፫ ወዲህ ፡ አይሆንም ። እሳት ፡ በፊታቸው ፡ ትባ
ላለች ÷ በኋላቸውም ፡ ነበልባል ፡ ታቃጥላለች ፡
ምድሪቱ ፡ በፊታቸው ፡ እንደ ፡ ዔድን ፡ ገነት ÷
በኋላቸውም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ በረሃ ፡ ናት ፡ ከእ
ነርሱም ፡ የሚያመልጥ ፡ የለም ።

፬ መልክቸው ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ መልክ ፡ ነው ÷
፭ እንደ ፡ ፈረሰኞም ፡ ይሮጣሉ ። በተራራ ፡ ላይ ፡
እንዳሉ ፡ ሰረገሎች ፡ ድምፅ ÷ ገለባውንም ፡ እን
ደሚበላ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ድምፅ ÷
ለሰልፍም ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡
፮ ሕዝብ ፡ ያኰበኵባሉ ። ከፊታቸው ፡ አሕዛብ ፡
ይንቀጠቀጣሉ ፡ የሰውም ፡ ፊት ፡ ሁሉ ፡ ይጠቍ
፯ ራል ። እንደ ፡ ኃያላን ፡ ይሮጣሉ ÷ እንደ ፡ ሰል
ፈኞችም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፡ እያንዳ
ንዱም ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ይራመዳል ÷ ከእርስ
፰ ኛቸውም ፡ አያፈገፍጉም ። አንዱ ፡ ከንዱ ፡ ጋር ፡
አይጋፋም ÷ እያንዳንዱም ፡ መንገዱን ፡ ይጠበ
ጥባል ። በሰልፉ ፡ መከከል ፡ ያልፋሉ ÷ እነር
፱ ሱም ፡ አይቁስሉም ። በከተማም ፡ ያኰበኵባሉ ÷
በቅጥሩም ፡ ላይ ፡ ይሮጣሉ ፡ ወደ ፡ ቤቶችም ፡
ይወጣሉ ÷ እንደ ፡ ሌባም ፡ በመስኮቶች ፡ ይገ
፲ ባሉ ። ምድሪቱም ፡ ከፊታቸው ፡ ትናወጣለች ÷
ሰማያትም ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፡ ፀሐይና ፡ ጨረ
ቃም ፡ ይጨልማሉ ÷ ከዋክብትም ፡ ብርሃናቸ
፲፩ ውን ፡ ይሰውራሉ ። እግዚአብሔርም ፡ በሥራ
ዊቱ ፡ ፊት ፡ ድምፁን ፡ ይሰጣል ፡ ሰፈሩ ፡ እጅግ ፡
ብዙ ፡ ነውና ÷ ቃሉንም ፡ የሚያደርግ ፡ እርሱ ፡
ኃያል ፡ ነውና ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቀን ፡ ታላ
ቅና ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነውና ፡ ማንስ ፡ ይች
ለዋል ?

፲፪ አሁንስ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ በፍጹም ፡
ልባችሁ ÷ በጾምም ÷ በልቅሶና ፡ በዋይታ ፡
፲፫ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ። ልባችሁን ፡ እንጂ ፡ ልብ
ሳችሁን ፡ አትቅደዱ ፡ አምላካችሁም ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ቸርና ፡ መሐሪ ÷ ቍጣው ፡ የዘገየ ÷ ምሕ
ረቱም ፡ የበዛ ÷ ለክፋትም ፡ የተጸጸተ ፡ ነውና ፡ ወደ ፡
፲፬ እርሱ ፡ ተመለሱ ። የሚመለስና ፡ የሚጸጸት ፡
እንደ ፡ ሆነ ÷ ለአምላካችሁም ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የእህልና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርበን ፡ የሚሆነ
ውን ፡ በረከት ፡ የሚያተርፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡
ያውቃል ?

በጽዮን ፡ መለከትን ፡ ንፋ ÷ ጾምንም ፡ ቀድሱ ÷ ፲፭ ፡
ጉባኤውንም ፡ አውጁ ÷ ሕዝቡንም ፡ አከማቹ ÷ ፲፮ ፡
ማኅበሩንም ፡ ቀድሱ ÷ ሽማግሌዎቹንም ፡ ሰብ
ስቡ ÷ ሕፃናቱንና ፡ ጡት ፡ የሚጠቡትን ፡ አከ
ማቹ ፡ ሙሽራው ፡ ከአልጫኑ ÷ ሙሽራይቱም ፡
ከመጋኃላዋ ፡ ይውጡ ። የእግዚአብሔርም ፡ አገል ፲፯ ፡
ጋዮች ፡ ካህናት ፡ ከወለሉና ፡ ከመሠዊያው ፡ መካ
ከል ፡ እያለቀሱ ፡— አቤቱ ÷ ለሕዝብህ ፡ ራራ ÷
አሕዛብም ፡ እንዳያነቅፉአቸው ፡ ርስትህን ፡ ለማ
ላገጫ ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጥ ፡ ከአሕዛብ ፡ መካ
ከል ፡— አምላካቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ? ስለ ፡ ምን ፡
ይላሉ ? ይበሉ ።

እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ምድሩ ፡ ቀና ÷ ለሕ ፲፰ ፡
ዝቡም ፡ ራራለት ። እግዚአብሔርም ፡ መልሶ ፲፱ ፡
ሕዝቡን ፡— እነሆ ÷ እህልንና ፡ ወይንን ፡ ዘይ
ትንም ፡ እሰድድላችኋለሁ ÷ እናንተም ፡ በእ
ርሱ ፡ ትጠግባላችሁ ፡ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡
በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ መሰደቢያ ፡ አላደርጋች
ሁም ። የሰሜንንም ፡ ሠራዊት ፡ ከእናንተ ፡ ፳ ፡
ዘንድ ፡ እርቃለሁ ÷ ወደ ፡ በረሃና ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡
በዳ ÷ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ምሥራቁ ፡ ባሕር ፡ ጀርባ
ውንም ፡ ወደ ፡ ምዕራቡ ፡ ባሕር ፡ አድርጌ ፡ አሳ
ድደዋለሁ ፡ እርሱም ፡ ትዕቢትን ፡ አድርጎአልና ፡
ግማቱ ፡ ይወጣል ÷ ክርፋቱም ፡ ይነሣል ፡ አለ ።
ምድር ፡ ሆይ ÷ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፳፩ ፡
አድርጎአልና ፡ አትፍሪ ÷ ደስም ፡ ይበልሽ ÷
እልልም ፡ በዪ ። እናንተ ፡ የምድር ፡ እንስሶች ፳፪ ፡
ሆይ ÷ የምድረ ፡ በዳው ፡ ማሰማርያ ፡ ለምልሞ
አልና ÷ ዛፉም ፡ ፍሬውን ፡ አፍርቶአልና ÷ በለ
ሱና ፡ ወይኑም ፡ ኃይላቸውን ፡ ሰጥተዋልና ፡
አትፍሩ ። እናንተ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ÷ አምላ ፳፫ ፡
ካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈተኛውን ፡ ዝናብ ፡
በጽድቅ ፡ ሰጥቶአችኋልና ÷ እንደ ፡ ቀድሞ
ውም ፡ የፈተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ ዝናብ ፡
አዝንቦላችኋልና ፡ በእርሱ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ÷
ለእርሱም ፡ እልል ፡ በሉ ። አውድማዎችም ፡ ፳፬ ፡
እህል ፡ ይሞላሉ ÷ መጥመቂያዎችም ፡ የወይን ፡
ጠጅንና ፡ ዘይትን ፡ አትረፍርፈው ፡ ያፈስሳሉ ።
የሰደድሁባችሁ ፡ ታላቁ ፡ ሠራዊቴ ፡ አንበጣና ፳፭ ፡
ደጎብያ ፡ ኩብኩባና ፡ ተምች ፡ የበላቸውን ፡
ዓመታት ፡ እመልስላችኋለሁ ። ብዙ ፡ መብል ፡ ፳፮ ፡
ትበላላችሁ ÷ ትጠግቡማላችሁ ፡ ከእናንተም ፡
ጋር ፡ ተአምራትን ፡ የሠራውን ፡ የአምላካችሁን ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ታመሰግናላችሁ ፤ ፳፯ ፡
ሕዝቤም ፡ ለዘላለም ፡ አያፍርም ። እኔም ፡ በእ
ስራኤል ፡ መከከል ፡ እንዳለሁ ÷ እኔም ፡ አምላ
ካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ÷ ከእ
ኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ ታው
ቃላችሁ ፡ ሕዝቤም ፡ ለዘላለም ፡ አያፍርም ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ መንፈ ፳፰ ፡
ሴን ፡ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ÷ አፈስሰዋለሁ ፤
ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁም ፡ ትንቢት ፡
ይናገራሉ ÷ ሽማግሌዎቻችሁም ፡ ሕልምን ፡
ያልማሉ ÷ ጕበዞቻችሁም ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፤

ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በወንዶችና ፡ በሴ
ቶች ፡ ባሪያዎች ፡ ላይ ፡ መንፈሴን ፡ አፈስሳለሁ ።
፴ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ድንቆችን ፡ አሳያለሁ ÷ በታች ፡
በምድርም ፡ ደምና ፡ እሳት ፡ የጢስም ፡ ጭጋግ ።
፴፩ ታላቁና ፡ የሚያስፈራው ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ÷ ጨረ
ቃም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ይለወጣል ። እንዲህም ፡
ይሆናል ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡
ሁሉ ፡ ይድናል ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተና
ገረ ÷ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መድ
፴፪ ኀኒት ፡ ይገኛል ። ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡
የጠራቸው ÷ የምስራች ፡ የሚሰበክላቸው ፡ ይገ
ኛሉ ።

ምዕራፍ ፫ ።

እነሆም ÷ በዚያ ፡ ወራትና ፡ በዚያ ፡ ዘመን ÷ ፫
የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ምርኮ ፡ በምመ
ልስበት ፡ ጊዜ ÷ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቤ ፡
ወደ ፡ ኢዮሣፍጥ ፡ ሸለቆ ፡ አወርዳቸዋለሁ ፡
በዚያም ፡ ስለ ፡ ሕዝቤና ፡ ስለ ፡ ርስቴ ፡ ስለ ፡
እስራኤል ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ የበተኑአቸ
ው ፡ ምድሬንም ፡ የተካፈሉአትን ፡ እፋረድባ
ቸዋለሁ ። በሕዝቤም ፡ ላይ ፡ ሰሚ ፡ ተጣጣሉ ፡
ወንድ ፡ ልጅን ፡ ለጋለሞታ ፡ ዋጋ ፡ ሰጡ ÷ ሴት ፡
ልጅን ፡ ለወይን ፡ ጠጅ ፡ ሸጡ ÷ ጠጡም ።
ጢሮስና ፡ ሲዶና ፡ የፍልስጥኤምም ፡ ግዛት ፡
ሁሉ ፡ ሆይ ÷ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ለእኔ ፡ ምን ፡
አለኝ ? በውኑ ፡ ብድራትን ፡ ትመልሱልኛላ
ችሁን ? ብድራትን ፡ ብትመልሱልኝ ፡ ፈጥኜ ፡
በችኰላ ፡ ብድራታችሁን ፡ በራሳችሁ ፡ ላይ ፡
እመልሳለሁ ። ብሬንና ፡ ወርቄን ፡ ወስዳችኋ
ልና ÷ የተወደደውንም ፡ መልካሙን ፡ ዕቃዬን ፡
ወደ ፡ መቅደሳችሁ ፡ አግብታችኋልና ÷ ከዳር
ቻቸውም ፡ ታርቁአቸው ፡ ዘንድ ፡ የይሁዳንና ፡
የኢየሩሳሌምን ፡ ልጆች ፡ ለግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ሸጣ
ችኋልና ÷ እነሆ ÷ እነርሱን ፡ ከሸጣችሁበት ፡
ስፍራ ፡ አስነሣቸዋለሁ ÷ ብድራታችሁንም ፡
በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ እመልሳለሁ ። እግዚአብሔር ፡
ተናግሮአልና ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻች
ሁን ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ እሸጣለሁ ÷ እነ
ርሱም ፡ ለሩቆቹ ፡ ሕዝብ ፡ ለሳባ ፡ ሰዎች ፡ ይሸ
ጡአችኋል ።

ይሁን ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አውጁ ፡ ለሰ ፬ ፡
ልፍ ፡ ተዘጋጁ ፡ ኃያላንን ፡ አስነሡ ፡ ሰልፈኞች ፡
ሁሉ ፡ ይቅረቡ ፡ ይውጡም ። መረሻችሁን ፭ ፡
ሰይፍ ÷ ማጭዳችሁንም ፡ ጦር ፡ ለማድረግ ፡
ቀጥቅጡ ፡ ደከማውም ፡— እኔ ፡ ብርቴ ፡ ነኝ ፡
ይበል ። እናንተ ፡ በዙሪያ ፡ ያላችሁ ፡ አሕዛብ ፡ ፮ ፡
ሁሉ ÷ ቸኰላችሁ ፡ ኑ ÷ ተሰብሰቡ ፡ አቤቱ ÷
ኃያላኖችህን ፡ ወደዚያ ፡ አውርድ ። አሕዛብ ፡ ፯ ፡
ይነሡ ÷ ወደ ፡ ኢዮሣፍጥ ፡ ሸለቆም ፡ ይውጡ ፡
በዙሪያ ፡ በሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እፈርድ ፡
ዘንድ ፡ በዚያ ፡ እቀመጣለሁና ። መከሩ ፡ ደርሶ ፰ ፡
አልና ፡ ማጭድ ፡ ስደዱ ፡ መጥመቂያውም ፡
ሞልቶአልና ፡ ጕ ፡ እርገጡ ፡ ክፋታቸውም ፡
በዝቶአልና ፡ መጥመቂያ ፡ ሁሉ ፡ ፈስሶአል ።
የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በሩርድ ፡ ሸለቆ ፡ ቀር ፲፬ ፡
ቦአልና ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ውካታ ፡ በፍ
ርድ ፡ ሸለቆ ፡ አለ ። ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ጨል ፲፭ ፡
መዋል ÷ ከዋክብትም ፡ ብርሃናቸውን ፡ ሰውረ
ዋል ። እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ሆኖ ፡ ድም ፲፮ ፡
ፁን ፡ ከሩ ፡ አድርጎ ፡ ይጮኻል ÷ በኢየሩሳሌ
ምም ፡ ሆኖ ፡ ቃሉን ፡ ይሰጣል ፡ ሰማይና ፡ ምድ
ርም ፡ ይናወጣሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለሕ
ዝቡ ፡ መሸሸጊያ ÷ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
መጠጊያ ፡ ይሆናል ። እኔም ፡ በተቀደሰው ፡ ፲፯ ፡
ተራራዬ ፡ በጽዮን ፡ የምቀመጥ ፡ እግላክቹ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታውቃላችሁ ፡
የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የተቀደሰች ፡
ትሆናለች ÷ እንግዶችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
አያልፉባትም ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ ተራሮች ፡ ፲፰ ፡
በተሃ ፡ ጠጅ ፡ ያንጠባጥባሉ ÷ ኮረብቶችም ፡
ወተትን ፡ ያፈስሳሉ ÷ በይሁዳም ፡ ያሉት ፡ ፈፋ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ ውኃን ፡ ያጕርፋሉ ፡ ከእግዚአብ
ሔርም ፡ ቤት ፡ ምንጭ ፡ ትፈልቃለች ÷ የሰጢ
ምንም ፡ ሸለቆ ፡ ታጠጣለች ። በእገራቸው ፡ ንጹ ፲፱ ፡
ሑን ፡ ደም ፡ አፍስሰዋልና ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡
ላይ ፡ ስላደረጉት ፡ ግፍ ፡ ግብጽ ፡ ምድረ ፡ በዳ ÷
ኤዶምያስም ፡ በረሃ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ፳ ፡
ይሁዳ ፡ ለዘላለም ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ለልጅ ፡
ልጅ ፡ መኖሪያ ፡ ይሆናል ። እኔም ፡ ንጹሕ ፡ ያላ ፳፩ ፡
ደረግሁትን ፡ ደማቸውን ፡ ንጹሕ ፡ አደርገዋ
ለሁ ÷ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ያድራል ።

ትንቢተ ፡ አብድዩ ።

የአብድዩ ፡ ራእይ ።
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ ሰም ፡
ተናል ፤ መልእክተኛ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ተልኮ ፡—
ተነሡ ÷ በላይዋም ፡ በሰልፍ ፡ እንነሣ ፡ ብሎ ፩ ፡
አል ። እነሆ ÷ በአሕዛብ ፡ ዛንድ ፡ ታናሽ ፡ አድ
ርጌሃለሁ ፡ አንተ ፡ እጅግ ፡ ተንቀሃል ። በተሰነ ፪ ፡
ጠቀ ፡ ዓለት ፡ ውስጥ ፡ የምትኖር ÷ ማደሪያህ
ንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግህ ÷ በልብህም ፡— ፫ ፡
ወደ ፡ ምድር ፡ የሚያወርደኝ ፡ ማን ፡ ነው ? ያም
ትል ፡ አንተ ፡ ሆይ ÷ የልብህ ፡ ትዕቢት ፡ አታል
ሎሃል ። እንደ ፡ ንስር ፡ መጥቀህ ፡ ብትወጣ ÷ ፬ ፡

ነፍሴ ፡ በዛለችብኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አሰብሁት ፡
ጸሎቴም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስህ ፡ ገባች ።
ከንቱነትንና ፡ ሐሰትን ፡ የሚጠብቁ ፡ ምሕረታቸውን ፡ ትተዋል ።
እኔ ፡ ግን ፡ በምስጋና ፡ ቃል ፡ እሠዋልሃለሁ ፡ የተሳልሁትንም ፡ እከፍላለሁ ።
ደኅንነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
እግዚአብሔርም ፡ ዓሣውን ፡ አዘዘው ፡ አርሱም ፡ ዮናስን ፡ በየብስ ፡ ላይ ፡ ተፋው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ሁለተኛ ፡ ወደ ፡ ዮናስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ተነሥተህ ፡ ወደዚያች ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ሂድ ፡ ÷ የምነግርህንም ፡ ስብክት ፡ ስበክላት ፡ አለው ። ዮናስም ፡ ተነሥቶ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ሄደ ፡ ነነዌም ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያህል ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ነበረች ። ዮናስም ፡ የአንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊገባ ፡ ጀመረ ፡ ጮኸም ፡— በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነነዌ ፡ ትገለበጣለች ፡ አለ ።

የነነዌም ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመኑ ፡ ለጾም ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ÷ ከታላቁም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታናሹ ፡ ድረስ ፡ ማቅ ፡ ለበሱ ። ወሬውም ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ንጉሥ ፡ ደረሰ ፡ እርሱም ፡ ከዙፋኑ ፡ ተነሥቶ ፡ መጐናጸፊያውን ፡ አወለቀ ፡ ማቅም ፡ ለበሰ ÷ በአመድም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። አዋጅም ፡ አስነገረ ÷ በነነዌም ፡ ውስጥ ፡ የንጉሡንና ፡ የመኳንንቱን ፡ ትእዛዝ ፡ አሳወጀ ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡— ሰዎችና ፡ እንስሶች ፡ ላሞችና ፡ በጎች ፡ አንዳችን ፡ አይቅመሱ ፡ አይሰማሩም ፡ ውኃንም ፡ አይጠጡ ፤ ሰዎችና ፡ እንስሶችም ፡ በማቅ ፡ ይከደኑ ÷ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በብርቱ ፡ ይጩኹ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸውና ፡ በእጃቸው ፡ ከለው ፡ ግፍ ፡ ይመለሱ ። እኛ ፡ እንዳንጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሶ ፡ ይጸጸት ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ ከጽኑ ፡ ቍጣውም ፡ ይመለስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡ ያውቃል ? እግዚአብሔርም ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ሥራቸውን ፡ አየ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ በተናገረው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተጸጸቶ ፡ አላደረገውም ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ይህም ፡ ዮናስን ፡ ከቶ ፡ ደስ ፡ አላሰኘውም ÷ እርሱም ፡ ተቈጣ ። ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየና ፡— አቤቱ ÷ እለምንሃለሁ ፡ በአገሬ ፡ ሳለሁ ፡ የተናገርሁት ፡ ይህ ፡ አልነበረምን ? አንተ ፡ ቸርና ፡ ይቅር ፡ ባይ ÷ ታጋሽም ÷ ምሕረተህም ፡ የበዛ ÷ ከክፋት ፡ ነገርም ፡ የተነሣ ፡ የምትጸጸት ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ አውቄ ፡ ነበርና ፡

ወዴት ፡ ነው ? ወይስ ፡ ከማን ፡ ወገን ፡ ነህ ? አሉት ። እርሱም ፡— እኔ ፡ ዕብራዊ ፡ ነኝ ፡ ባሕሩንና ፡ የብሱን ፡ የፈጠረውን ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመልካለሁ ፡ አላቸው ።
እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ኰበለለ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፡ አውቀዋልና ፡ እጅግ ፡ ፈርተው ፡— ይህ ፡ ያደረግኸው ፡ ምን ድር ፡ ነው ? አሉት ።
ባሕሩንም ፡ ሞገዱ ፡ አጥብቆ ፡ ያናውጠው ፡ ነበርና ፡— ባሕሩ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ጸጥ ፡ እንዲል ፡ ምን ፡ እናድርግብህ ? አሉት ። እርሱም ፡— ይህ ፡ ታላቅ ፡ ማዕበል ፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኛችሁ ፡ አውቃለሁና ፡ እንሥታችሁ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉኝ ÷ ባሕሩም ፡ ጸጥ ፡ ይልላችኋል ፡ አላቸው ። ሰዎቹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ሊመለሱ ፡ አጥብቀው ፡ ቀዘፉ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ባሕሩ ፡ እጅግ ፡ አብዝቶ ፡ ይናወጥባቸው ፡ ነበርና ፡ አልቻሉም ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፡— አቤቱ ÷ እንደ ፡ ወደድህ ፡ አድርገሃልና ፡ እንለምንሃለን ፡ አቤቱ ÷ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ እንዳንጠፋ ፡ ንጹሕም ፡ ደም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ እንዳታደርግ ፡ እንለምንሃለን ፡ አሉ ። ዮናስንም ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ጣሉት ። ባሕሩም ፡ ከመናወጡ ፡ ጸጥ ፡ አለ ። ሰዎችም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ÷ ለእግዚአብሔርም ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረቡ ÷ ስእለትንም ፡ ተሳሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

እግዚአብሔርም ፡ ዮናስን ፡ የሚውጥ ፡ ታላቅ ፡ ዓሣ ፡ አሰናዳ ፡ ዮናስም ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በዓሣው ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ። ዮናስም ፡ በዓሣው ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡—
በመከራዬ ፡ ሳለሁ ፡ ወደ ፡ አምላኬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽሁ ÷
እርሱም ፡ ሰማኝ ፤
በሲኤልም ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ሆኜ ፡ ጮኽሁ ÷ ቃሌንም ፡ አዳመጥህ ።
ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ጣል ፡ ሽኝ ÷
ፈሳሾችም ፡ በዙሪያዬ ፡ ነበሩ ፤
ማዕበልህና ፡ ሞገድህ ፡ ሁሉ ፡ በላዬ ፡ አለፉ ።
እኔም ፡— ከዓይንህ ፡ ፊት ፡ ተጣልሁ ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስህ ፡ ደግሞ ፡ እመለከታለሁ ፡ አልሁ ።
ውኖችም ፡ እስከ ፡ ነፍሴ ፡ ድረስ ፡ ከበቡኝ ፡ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ በዙሪያዬ ፡ ነበረ ፤
የባሕሩ ፡ ሣር ፡ በራሴ ፡ ተጠመጠመ ፡ ነበር ።
ወደ ፡ ተራሮች ፡ መሠረት ፡ ወረድሁ ፡ በምድርና ፡ በመወርወሪያዎችዋ ፡ ለዘላለም ፡ ተዘጋሁ ፡
አንተ ፡ ግን ÷ አቤቱ ፡ አምላኬ ÷ ሕይወቴን ፡ ከጕድጓዱ ፡ አወጣህ ።

ቤትህም ፡ በነዋክብት ፡ መካከል ፡ ቢሆን ÷ ከዚያ ፡ አወርድሃለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
ሴቦች ፡ ቢመጡብህ ፡ ወይም ፡ ወንበይኖች ፡ በሌሊት ፡ ቢመጡ ÷ የሚበቃቸውን ፡ የሚሰርቁ ፡ አይደሉምን ? ወይንኝም ፡ የሚቄርጡ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ቢመጡ ፡ ቃርሚያ ፡ አያስቀሩ ፡ ምን ? አንተ ፡ ግን ፡ ምንኛ ፡ ጠፋህ ! ዔሳው ፡ ምንኛ ፡ ተመረመረ ! የተሸሸገበት ፡ ነገር ፡ ምንኛ ፡ ተፈለገ ! የተማማልንቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ዳርቻህ ፡ ሰደዱህ ፡ የታመንህቸው ፡ ሰዎች ፡ አታለሉህ ÷ አሸነፉህም ፡ በዘታችህም ፡ አሸክላ ፡ ዘረጉብህ ÷ አነርሱም ፡ ማስ ተዋል ፡ የላቸውም ። በዚያ ፡ ቀን ፡ ከኤዶም ያስ ፡ ጥበበኞችን ÷ ከዔሳውም ፡ ተራራ ፡ ማስተዋልን ፡ አላጠፋምን ? ይላል ፡ እግዚአብሔር ።
ቴማን ፡ ሆይ ÷ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዔሳው ፡ ተራራ ፡ በመገደል ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ኃያላንህ ፡ ይደነግጣሉ ።
በወንድምህ ፡ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ግፍ ፡ እፍረት ፡ ይከድንሃል ÷ ለዘላለምም ፡ ትጠፋለህ ። በፊቱ ፡ አንጻር ፡ በቆምህ ፡ ቀን ÷ አሕዛብ ፡ ጭፍሮቹን ፡ በማረኩበት ÷ እንግዶችም ፡ በበሩ ፡ በገቡበት ÷ በኢየሩሳሌምም ፡ ዕጣ ፡ በተጣጣሉበት ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእነርሱ ፡ አንደ ፡ አንዱ ፡ ነበርህ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመከራው ፡ ቀን ፡ ወንድምህን ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ÷ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይልህ ፡ ዘንድ ÷ በጭንቅትም ፡ ቀን ፡ በትዕቢት ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ አይገባህም ፡ ነበር ።
በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በሕዝቤ ፡ በር ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ÷ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ መከራቸውን ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ÷ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በሀብታቸው ፡ ላይ ፡ እጅህን ፡ ትዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ አይገባህም ፡ ነበር ።
የሸሹትንም ፡ ለመግደል ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ትቆም ፡ ዘንድ ÷ በጭንቅትም ፡ ቀን ፡ ከእርሱ ፡ የቀሩትን ፡ አሳልፈህ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አይገባህም ፡ ነበር ።
የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቀርቦአልና ፡ አንተ ፡ እንዳደረግኸው ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግብሃል ÷ ፍዳህም ፡ በራስህ ፡ ላይ ፡ ይመለሳል ።
በቅዱሱ ፡ ተራራዬ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጠጣችሁ ፡ እንዲሁ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ዘወትር ፡ ይጠጣሉ ፡ አዎን ፡ ይጠጣሉ ÷ ይጨልጡማል ÷ እንዳልሆኑም ፡ ይሆናሉ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የሚያመልጡ ፡ ይሆናሉ ÷ እርሱም ፡ ቅዱስ ፡ ይሆናል ፡ የያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ ርስታቸውን ፡ ይወርሳሉ ።
እግዚአብሔርም ፡ ተናግሮአልና ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ እሳት ÷ የዮሴፍ ፡ ቤት ፡ ነበል ፡ ባል ÷ የዔሳው ፡ ቤት ፡ ገለባ ፡ ይሆናሉ ፡ እነርሱንም ፡ ያቃጥሉአቸዋል ፡ ይበሉአቸውማል ፡ ከዔሳውም ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ የለውም ።
የደቡብም ፡ ሰዎች ፡ የዔሳውን ፡ ተራራ ÷ የቈላውም ፡ ሰዎች ፡ ፍልስጥዔማውያንን ፡ ይወርሳሉ ፡ የኤፍሬምንም ፡ አገር ፡ የሰማርያንም ፡ አገር ፡ ይወርሳሉ ፡ ብንያምም ፡ ገለዓድን ፡ ይወርሳል ።
ይህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የጭፍራቸው ፡ ምርኮ ፡ የከነዓንን ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ሰራፅታ ፡ ድረስ ፡ ይወርሳል ፡ በስፋራድም ፡ የሚኖሩ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ምርኮኞች ፡ የደቡብን ፡ ከተሞች ፡ ይወርሳሉ ።
በዓሳውም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ አዳኞች ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፡ መንግሥቱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሆናል ።

ትንቢተ ፡ ዮናስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ አማቴ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮናስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ተነሥተህ ፡ ወደዚያች ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ሂድ ÷ ክፋታቸውም ፡ ወደ ፡ ፊቴ ፡ ወጥቶአልና ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ስበክ ። ዮናስ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ይኰበልል ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴም ፡ ወረደ ÷ ወደ ፡ ተርሴስም ፡ የምትልፍ ፡ መርከብ ፡ አገኘ ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ኰብልሎ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ገባ ።
እግዚአብሔርም ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ነፋስን ፡ አመጣ ÷ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ማዕበል ፡ ሆነ ÷ መርከቢቱም ፡ ልትሰበር ፡ ቀረበች ።
መርከበኞቹም ፡ ፈሩ ÷ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ጮኸ ፡ መርከቢቱም ፡ እንድትቀልልላቸው ፡ በውስጥዋ ፡ የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉት ፡ ዮናስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መርከቡ ፡ ውስጠኛው ፡ ክፍል ፡ ወርዶ ፡ ነበር ÷ በከባድ ፡ እንቅልፍም ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ። የመርከቡንም ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀርቦ ፡— ምነው ፡ ተኝተሃል ? እንዳንጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስበን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተነሥተህ ፡ አምላክህን ፡ ጥራ ፡ አለው ። እርስ ፡ በእርሳቸውም ፡— ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በማን ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ÷ ዕጣ ፡ እንጣጣል ፡ ተብለው ፡ ዕጣም ፡ ተጣጣሉ ÷ ዕጣውም ፡ በዮናስ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።
የዚያን ፡ ጊዜም ፡— ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በማን ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘን ፡ እባክህ ፡ ንገረን ፡ ሥራህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ከወዴትስ ፡ መጣህ ? አገርህስ ፡

ስለዚህ፡ ወደ፡ ተርሴስ፡ ለመኰብለል፡ ፈጥኜ፡
፫፡ ነበር ። አሁንም ÷ አቤቱ ÷ ከሕይወት፡ ሞት፡
ይሻለኛልና፡ እበክህ ÷ ነፍሴን፡ ከእኔ፡ ውሰድ፡
፬፡ አለው ። እግዚአብሔርም ፡— በውኑ፡ ትቈጣ፡
ዘንድ፡ ይገባሃልን ? አለ ።
፭፡ ዮናስም ፡ ከከተማይቱ ፡ ወጣ ÷ ከከተማይ
ቱም፡ በስተ፡ ምሥራቅ፡ በኩል፡ ተቀመጠ፡ ከተ
ማይቱንም፡ የሚያሳኝትን፡ እስኪያይ፡ ድረስ፡
በዚያ፡ ለራሱ፡ ዳስ፡ ሠርቶ፡ ከጥላው፡ በታች፡
፮፡ ተቀመጠ ። እግዚአብሔር፡ አምላክም፡ ቅል፡
አዘጋጀ÷ከሥጉንቀቱም፡ ታድነው፡ ዘንድ፡ በራሱ፡
ላይ፡ ጥላ፡ እንድትሆን፡ በዮናስ፡ ላይ፡ ከፍ፡
ከፍ፡ አደረጋት፡ ዮናስም፡ ስለ፡ ቅሏቴ፡ እጅግ፡
፯፡ ደስ፡ አለው ። በነጋው፡ ግን፡ ወገግ፡ ብለ፡ ጊዜ፡
እግዚአብሔር፡ ትልን፡ አዘጋጀ ÷ አርስዋም፡
፰፡ ቅሏቱን፡ አስከትደርቅ፡ ድረስ፡ መታቻት ። ወሐ
ይም፡ በወጣች፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ትኩስ፡
የምሥራቅ፡ ነፋስ፡ አዘጋጀ፡ ዮናስ፡ እስኪ፡ ዝል፡
ድረስም፡ ወሐይ፡ ራሱን፡ መታው፡ ለራሱም፡
ሞትን፡ ፈለገና ፡— ከሕይወት፡ ሞት፡ ይሻለ
ኛል፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፡ ዮናስን ፡— ፱፡
በውኑ፡ ስለዚች፡ ቅል፡ ትቈጣ፡ ዘንድ፡ ይገባሃ
ልን ? አለው ። እርሱም ፡— እስከ፡ ሞት፡ ድረስ፡
እቈጣ፡ ዘንድ፡ ይገባኛል፡ አለ ። እግዚአብሔ
ርም ፡— አንተ፡ ትበቅል፡ ዘንድ፡ ላልደከምህ ፲፡
ባት፡ ላላሳደግሃትም ÷ በአንድ፡ ሌሊት፡ ለበቀ
ለች ÷ በአንድ፡ ሌሊትም፡ ለደረቀችው፡ ቅል፡
አገነባህ ። እኔስ ፡ ቀኛቸውንና ፡ ግራቸውን ፡ ፲፩፡
የማይለዩ፡ ከመቶ፡ ሺያ ፡ ሺህ ፡ የሚበልጡ፡ ሰም
ትና ፡ ብዙ ፡ እንስሶች ፡ ላሉባት ፡ ለታላቂቱ ፡
ከተማ ፡ ለእንዌ ፡ አላዝንምን ? አለው ።

ትንቢተ፡ናሆም።

ምዕራፍ፡ ፩ ።

፩፡ ስለ፡ ነነዌ ፡ የተነገረ፡ ሸክም ፡ የኤልቀዊሢው፡
የናሆም ፡ የራእዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፪፡ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛና ፡ ተበቃይ ፡ አም
ላክ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ተበቃይና ፡ መዓትን፡
የተሞላ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃዋሚዎ
ቹን ፡ ይበቀላል ÷ ለጠላቶቹም ፡ ቍጣውን ፡
፫፡ ይጠብቃል ። እግዚአብሔር ፡ ትዕግሥተኛ ÷
ኃይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ÷ በደለኛውንም ፡—
ንጹሕ ፡ ነህ ፡ አይልም ፡ እግዚአብሔር ፡ በወጀ
ብና ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ፡ አለው ÷
፬፡ ደመናም፡ የእግሩ ፡ ትቢያ ፡ ነው ። ባሕሩንም ፡
ይገሥጻታል ÷ ያደርቃትማል ÷ ወንዞችንም ፡
ሁሉ ፡ ያደርቃል ፡ ባሳንና ፡ ቀርሜሎስም ፡ ላል
ተዋል ÷ የሊባኖስም ፡ አበባ ፡ ጠውልጎአል ።
፭፡ ተራሮችም ፡ ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ ታወኩ ÷ ኮረብ
ቶችም ፡ ቀለጡ ፡ ምድርና ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩብ
፮፡ ትም ፡ ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ ተናወጡ ። በቍጣው ፡
ፊት ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ? የቍጣውንስ ፡
ትዕሳት ፡ ማን ፡ ይታገሣል ? መዓቱ ፡ እንደ ፡
እሳት ፡ ይፈስሳል ÷ ከእርሱም ፡ የተነሣ ፡ ዓለ
፯፡ ቶች ፡ ተሰነጠቁ ። እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡
ነው ÷ በመከራ ፡ ቀንም ፡ መሸሸጊያ ፡ ነው ፡ በእ
፰፡ ርሱ ፡ የሚታመኑትንም ፡ ያውቃል ። ስፍራዋን ፡
ግን ፡ በሚያጥለቀልቅ ፡ ጎርፍ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋ
ታል ÷ ጠላቶቹንም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ያሳድዳ
ቸዋል ።
፱፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የምታስቡት ፡ ምን
ድር ፡ ነው ? እርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋል ÷ መከ
፲፡ ራም ፡ ሁለተኛ ፡ አያነሣም ። እርስ ፡ በእርሳ
ቸው ፡ እንደ ፡ ተመሰቃቀለ ፡ እሾህ ፡ ቢሆኑ ÷
በመጠጣቸውም ፡ ቢሰክሩ ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡
ገለባ ፡ ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ። በእግዚአብሔር ፲፩፡
ላይ ፡ በክፋ ፡ የሚያስብ ÷ክፋትን ፡ የሚመክር ÷
ከእንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቶአል ። እግዚአብሔር ፲፪፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— ኃይለኞችና ፡ ብዙዎች ፡
ቢሆኑ ፡ እንዲሁ ፡ ይቈረጣሉ ÷ እርሱም ፡ ያል
ቃል ። አንሁ ፡ አስጨንቂሃለሁ ÷ ነገር ፡ ግን ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስጨንቅህም ። አሁ ፲፫፡
ንም ፡ ቀንበሩን ፡ ከአንተ ፡ አሰብራለሁ ÷ አስራ
ትህንም ፡ አበጥሳለሁ ።
እግዚአብሔርም ፡ ከስምህ ፡ ማንም ፡ ከእንግ ፲፬፡
ዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይዘራ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ አገዘ
አል ፡ ከአምላክህ ፡ ቤት ፡ የተቀረጸውንና ፡
ቀልጠ ፡ የተሠራውን ፡ ምስል ፡ አጠፋለሁ ፡
አንተም ፡ የተጠላህ ፡ ነህና ፡ መቃብርህን ፡
እምሳለሁ ።
እነሆ ÷ የምስራችን ፡ የሚያመጣ ፡ ሰላምንም ፡ ፲፭፡
የሚያወራ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ በተራሮች ፡ ላይ ፡
ነው ! ይሁዳ ፡ ሆይ ÷ አጥፊው ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፍ
ቶአልና ÷ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ በእንተ ፡
ዘንድ ፡ አያልፍምና ፡ ዓመት ፡ በዓሎችህን ፡
አድርግ ÷ ስእለቶችህን ፡ ክፈል ።

ምዕራፍ፡ ፪ ።

የሚቀጠቅጥ ፡ በእንተ ፡ ላይ ፡ ወጥቶአል ፡ ፩፡
ምሽግን ፡ ጠብቅ ÷ መንገድንም ፡ ሰልል ፡ ወገ
ብህን ፡ አጽና ÷ ኃይልህንም ፡ እጅግ ፡ አበርታ ።
፪፡ ዘራፊዎች ፡ ዘርፈዋቸዋልና ÷ የወይናቸውንም ፡
አረግ ፡ አጥፍተዋልና ፡ እግዚአብሔር ፡ የያዕ
ቆብን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ክብር ፡ ይመ
ልሳል ። የኃያላኑ ፡ ጋሻ ፡ ቀልቶአል ÷ጽኑዓንም ፡
፫፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ። እርሱም ፡ በሚያዘጋ

ጅበት ፡ ቀን ፡ ሰረገሎች ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይንበገ
፬፡ በጋሉ ፤ የጦሩም ፡ ሰመያ ፡ ይወዛወዛል ። ሰረገ
ሎች ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ይነጉዳሉ ÷ አደባባ
ይም ፡ ይጋጫሉ ፤ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ፋና ፡
፭፡ ነው ÷ እንደ ፡ መብረቅም ፡ ይከንፋሉ ። መሰ
ናንቱን ፡ ያስባል ፤ በእረማመዳቸው ፡ ይሰናከ
ላሉ ፤ ፈጥነው ፡ በቅጥርዋ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ÷
፮፡ መጠጊያም ፡ ተዘጋጀለት ። የወንዞቹም ፡ መዝ
ጊያዎች ፡ ተከፈቱ ÷ የንጉሡ ፡ ቤትም ፡ ቀለ
፯፡ ጠች ። ንግሥት ፡ ተገለጠች ÷ ተማረከችም ÷
ሴቶች ፡ በሪያዎችዋም ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ እየጮ
ኹና ፡ ደረታቸውን ፡ እየመቱ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡
ይላሉ ።
፰፡ ነነዌ ፡ ግን ፡ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ ጀምራ ፡ እንደ ፡
ተከማቸ ፡ ውኃ ፡ ነበረች ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ይሸ
ሻሉ ፤ እነርሱም ፡— ቁሙ ÷ ቁሙ ፡ ይላሉ ÷
፱፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚመለስ ፡ የለም ። መዝገብዋ ፡
መጨረሻ ፡ የለውምና ÷ የከበረውም ፡ የዕቃዋ ፡
ሁሉ ፡ ብዛት ፡ አይቈጠርምና ፡ ብሩን ፡ በገብዙ ፡
፲፡ ወርቁንም ፡ በገብዙ ። በዶና ፡ በድማ ፡ ምድረ ፡
በዳም ፡ ሆናለች ፤ ልብ ፡ ቀልጦአል ÷ ጕልበቶ
ችም ፡ ተብረክርከዋል ፤ በወገብም ፡ ሁሉ ፡
ሕማም ፡ አለ ÷ የሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ጠቍሮ
፲፩፡ አል ። የአንበሶችም ፡ መደብ ÷ የአንበሶችም ፡
ደቦል ፡ የሚሰማራበት ÷ አንበሳውና ፡ አንበ
ሳይቱ ፡ ግልገሉም ፡ ሳይፈሩ ፡ የሚሄዱት ፡
፲፪፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ? አንበሳው ፡ ለልጆቹ ፡
የሚበቃውን ፡ ነጠቀ ÷ ለአንስቶቹም ፡ ሰበረላ
ቸው ፡ ዋሻውን ፡ በንጥቂያ ÷ መደቡንም ፡ በቅ
፲፫፡ ሚያ ፡ ሞልቶታል ። እነሆ ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ÷
ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ሰረገ
ሎችዋንም ፡ አቃጥሎ ፡ አጨሳለሁ ÷ ሰይፍም ፡
የአንበሳ ፡ ደቦሎችሽን ፡ ይበላቸዋል ፤ ንጥቂያሽ
ንም ፡ ከምድር ፡ አጠፋለሁ ÷ የመልክተኞች
ሽን ፡ ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሰማም ።

ምዕራፍ፡ ፫ ።

ለደም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት ! በሁለንተናዋ ፡
፩፡ ሐሰትና ፡ ቅሚያ ፡ ሞልቶባታል ፤ ንጥቂያ ፡ ከአ
ርስዋ ፡ አያልቅም ። የአለንጋ ፡ ድምፅ ÷ የመን
፪፡ ኰራኵርም ፡ ድምፅ ÷ የፈረሶችም ፡ ኮቴ ÷ የፈ
ጣን ፡ ሰረገላም ፡ ጩኸት ፡ ተሰምቶአል ፤ ፈረሰ
፫፡ ኛው ፡ ይጋልባል ÷ ሰይፍም ፡ ይንበገበጋል ÷
ጦርም ፡ ይብለጨለጫል ፤ የተገደሉትም ፡ ይበ
ዛሉ ÷ በድኖችም ፡ በክምር ፡ ይከመራሉ ÷ሬሳ
ቸውም ፡ አይቈጠርም ፤ በሬሳቸውም ፡ ይሰናከ
፬፡ ላሉ ። ስለ ፡ ተዋበችው ፡ ጋለሞታ ፡ ግልሙ
ትና ፡ ብዛት ፡ ይህ ፡ ሆኖአል ፤ እርስዋም ፡ በመ
ተትዋ ፡ እጅግ ፡ በለጠች ÷ አሕዛብንም ፡ በግል
ሙትናዋ ÷ ወገኖችንም ፡ በመተትዋ ፡ ሸጠች ።
እነሆ ÷ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ፭፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ÷ ልብስሽን ፡ በፊትሽ ፡ እገ
ልጣለሁ ፤ ኀፍረት ፡ ሥጋሽንም ፡ ለሕዝብ ÷
ነውርሽንም ፡ ለመንግሥታት ፡ አሳያለሁ ። ርኵ ፮፡
ሰትንም ፡ በላይሽ ፡ እጥላለሁ ÷ እንቅሽማለሁ ÷
ማላገጫም ፡ አደርግሻለሁ ። የሚያይሽም ፡ ሁሉ ፡ ፯፡
ከአንቺ ፡ ሸሽቶ ፡— ነነዌ ፡ ባድማ ፡ ሆናለች ፤
የሚያለቅስላትስ ፡ ማን ፡ ነው ? የሚያጽናና
ንስ ፡ ከወዴት ፡ እፈልጋለሁ ? ይላል ።
አንቺ ፡ በመስሮች ፡ መከከል ፡ ከተቀመጠ ፰፡
ችው ÷ ውኃም ፡ በዙሪያዋ ፡ ከነበራት ÷ ምሽግ
ዋም ፡ ባሕር ፡ ከነበረ ÷ ቅጥርዋም ፡ በባሕር ፡
ውስጥ ፡ ከነበረ ፡ ከኖእ ፡ አሞን ፡ ትበልጫለሽን ?
ኢትዮጵያና ፡ ግብጽ ፡ የማይቈጠር ፡ ኀይልዋ ፡ ፱፡
ነበሩ ፤ ፉጥና ፡ ልብያ ፡ ረዳቶችዋ ፡ ነበሩ ። እር ፲፡
ስዋ ፡ ግን ፡ ተማርካ ፡ ፈለሰች ፤ ሕፃናቶችዋ ፡
በመንገድ ፡ ሁሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተፈጠፈጡ ፤ በከ
በርቴዎችዋም ፡ ላይ ፡ ሰጣ ፡ ተጣጣሉ ÷ ታላላ
ቆችዋም ፡ ሁሉ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሰሩ ። አንቺም ፡ ፲፩፡
ትሰክሪአለሽ ፡ ወራዳም ፡ ትሆኛለሽ ፤ አንቺ ፡
ደግሞ ፡ ከጠላት ፡ የተነሣ ፡ መጠጊያን ፡ ትፈል
ጊአለሽ ። አምባሽ ፡ ሁሉ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ፲፪፡
የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ በለስ ፡ ዛፎች ፡
ነው ፤ ቢወዛወዝ ፡ በሚበላው ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡
ይወድቃል ። እነሆ ÷ በመካከልሽ ፡ ያሉ ፡ ሕዝ ፲፫፡
ብሽ ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ፤ የአገርሽ ፡ በሮች ፡ ለጠ
ላቶችሽ ፡ ፈጽሞ ፡ ተከፍተዋል ÷ እሳትም ፡ መወ
ርወሪያዎችህን ፡ በልቶአል ። ከብበው ፡ ያስ ፲፬፡
ጨንቁሽልና ፡ ውኃን ፡ ቅጂ ፤ አምባሽን ፡ አጠ
ንክረ ፤ ወደ ፡ ጭቃ ፡ ገብተሽ ፡ እርገጪ ፤ የጡ
ብን ፡ መሠሪያ ፡ ያገር ። በዚያ ፡ እሳት ፡ ይበላ ፲፭፡
ሻል ÷ ሰይፍ ፡ ያጠፋሻል ÷ እንደ ፡ ደንብያ ፡
ይበላሻል ፤ እንደ ፡ ደንብያ ፡ ብገር ÷ እንደ ፡ አን
በጣም ፡ ተበገር ። ነጋዴዎችሽን ፡ ከሰማይ ፡ ከዋ ፲፮፡
ክብት ፡ ይልቅ ፡ አበዛሽ ፤ ደንብያ ፡ ተዘረጋ ÷
በረረም ። በአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ዘውድ ፡ የጫኑት ፡ ፲፯፡
እንደ ፡ አንበጣ ÷ አለቆችሽም ፡ እንደሚንቀሳ
ቀሱ ፡ ኩብኩባዎች ፡ ናቸው ፤ በብርድ ፡ ቀን ፡
በቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ÷ ፀሐይም ፡ በወ
ጣች ፡ ጊዜ ፡ ያኰብኵባሉ ፤ ስፍራቸው ፡ በየት ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ አይታወቅም ። የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፰፡
ሆይ ÷ እረኞችህ ፡ አንቀላፍተዋል ፤ መኳንንት
ችህም ፡ ወርፈዋል ፤ ሕዝብህም ፡ በተራሮች ፡
ላይ ፡ ተበትኖአል ÷ የሚሰበስበውም ፡ የለም ።
ስብራትህ ፡ አይፈወስም ÷ ቍስልህም ፡ ክፉ ፡ ፲፱፡
ነው ፤ ወሬህንም ፡ የሚሰሙ ፡ ሁሉ ፡ እጃቸውን ፡
በአንተ ፡ ላይ ፡ ያጨበጭባሉ ፤ ክፋትህ ፡ ሁል
ጊዜ ፡ ያላለፈችበት ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነውና ?

ት ን ቢ ተ ፡ ዕ ን ባ ቆ ም ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ነቢዩ ፡ ዕንባቆም ፡ ያየው ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።
፪ አቤቱ ÷ እኔ ፡ ስጮኽ ፡ የማትሰማው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? ስለ ፡ ግፍ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እጮኻለሁ ÷ አንተም ፡ አታድንም ።
፫ በደልንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አሳየኸኝ ? ጠማምነትንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትመለከታለህ ? ጥፋትና ፡ ግፍ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ይነሣሉ ።
፬ ስለዚህ ፡ ሕግ ፡ ላልቶአል ÷ ፍርድም ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አይወጣም ፤ ኃጢአተኛ ፡ ጻድቅን ፡ ይከብባልና ፡ ስለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ጠማማ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ።
፭ እናንተ ፡ የምትንቁ ፡ ሆይ ÷ አንድ ፡ ቢተርክላችሁ ፡ ስንኳ ፡ የማታምኑትን ፡ ሥራ ፡ በዘመናችሁ ፡ እሠራለሁና ፡ እዩ ÷ ተመልከቱ ÷ ተደነቁ ። እነሆ ÷ የእነርሱ ፡ ያልሆነውን ፡ መኖሪያ ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ስፋት ፡ ላይ ፡ የሚሄዱትን ፡ ሠራዊቶችንና ፡ ፈጣኖችን ፡ ሕዝብ ፡ ከለዳውያንን ፡ አስነሣለሁ ። እነርሱ ፡ የሚያስፈሩና ፡ የሚያስደነግጡ ፡ ናቸው ፡ ፍርዳቸውና ፡ ክብራቸው ፡ ከራሳቸው ፡ ይወጣል ።
፰ ፈረሶቻቸውም ፡ ከነብር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ÷ ከማታም ፡ ተኩላ ፡ ይልቅ ፡ ጨካኞች ፡ ናቸው ፡ ፈረሰኞቻቸውም ፡ ይንሰፈሰፉ ÷ ከሩቅም ፡ ይመጣሉ ÷ ለመብልም ፡ እንደሚቸኵል ፡ ንስር ፡ ይበርራሉ ።
፱ ሁሉም ፡ ለግፍ ፡ ሥራ ፡ ይመጣሉ ÷ ፊታቸውንም ፡ እንደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ያቀናሉ ፡ ምርኮኞችንም ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ ይሰበስባሉ ።
፲ በነገሥታት ፡ ላይ ፡ ያላግጣሉ ÷ መሳፍንትም ፡ ዋዛ ፡ ሆነውላቸዋል ፤ በምሽጉ ፡ ሁሉ ፡ ይስቃሉ ÷ አፈራንም ፡ ከምረው ፡ ይወስዱታል ።
፲፩ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ አልፎ ፡ ይሄዳል ÷ ይበድላሉ ፡ ኃይሉንም ፡ አምላክ ፡ ያደርገዋል ።
፲፪ አቤቱ ÷ የተቀደስህ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡ ከዘላለም ፡ ጀምሮ ፡ አልነበርህምን ? እኛ ፡ አንሞትም ። አቤቱ ÷ ለፍረድ ፡ ሠርተኸዋል ÷ ለተግሣጽም ፡ አድርገኸዋል ። ዓይኖችህ ፡ ክፉ ፡ እንዳያዩ ፡ ንጹሐን ፡ ኖሮው ÷ ጠማምነትንም ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ፡ አታላዮችንስ ፡ ለምን ፡ ትመለከታለህ ? ኃጢአተኛውስ ፡ ከአርሱ ፡ ይልቅ ፡ ጻድቅ ፡ የሆነውን ፡ ሲውጠው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ትላለህ ? ሰዎችንም ፡ እንደ ፡ በሕር ፡ ዓሣዎች ÷ አለ ፡ ገዥ ፡ እንደሌላቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ለምን ፡ ታደርጋቸዋለህ ? ሁሉን ፡ በመቃጥን ፡ ያወጣል ÷ በመረቡም ፡ ይይዛቸዋል ÷ በእኸክላውም ፡ ውስጥ ፡ ያከማቻቸዋል ፡ ስለዚህ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ እልል ፡ ይላል ። እድል ፡ ፈንታው ፡ በእነርሱ ፡ ሰብታለችና ÷ መብሉም ፡ በዝቶአልና ፡ ስለዚህ ፡ ለመረቡ ፡ ይሠዋል ÷ ለእኸክላውም ፡ ያጥናል ። ስለዚህ ፡ መረቡን ፡ ይጥላልን ? አሕዛብንም ፡ ዘወትር ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ አይራራምን ?

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ በመጠበቂያዬ ፡ ላይ ፡ አቆማለሁ ÷ በአምባ ፡ ላይም ፡ እወጣለሁ ፤ የሚናገረኝንም ÷ ስለ ፡ ክርክራም ፡ የምመልሰውን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ እመለከታለሁ ። እግዚአብሔርም ፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ አንበቢው ፡ ይፈጥን ፡ ዘንድ ፡ ራእዩን ፡ ጻፍ ÷ በጽላትም ፡ ላይ ፡ ግለጠው ።
፪ ራእዩ ፡ ገና ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ነው ÷ ወደ ፡ ፍጻሜውም ፡ ይቸኵላል ÷ አርሱም ፡ አይዋሽም ። ቢዘገይም ፡ በእርግጥ ፡ ይመጣልና ፡ ታገሠው ፤ እርሱ ፡ አይዘገይም ።
፫ እነሆ ÷ ነፍሱ ፡ ኰርታለች ÷ በውስጡም ፡ ቅን ፡ አይደለችም ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ በእምነቱ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።
፬ እርሱ ፡ አታላይና ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በስኖራው ፡ ሀርፎ ፡ አይቀመጥም ፡ ስስቱን ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ ያሰፋል ÷ እርሱም ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ አይጠግብም ፤ አሕዛብንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ይሰበስባል ÷ ወገኖቹንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ያከማቻል ።
፭ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱ ፡ ያልሆነውን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ለሚሰበስብ ፡ መያዣውንም ፡ ለራሱ ፡ የሚያበዛ ፡ ወዮለት ! እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? እያሉ ፡ ምሳሌ ፡ አይመስሉበትምን ? ተረትም ፡ አይተርቱበትምን ? የሚነክሱህ ፡ ድንገት ፡ አይነሡብህምን ? የሚያስጨንቁህም ፡ ድንገት ፡ አይነሡብህምን ? የሚያስጨንቁህም ፡ እንዲህ ፡ ነውና ።
፮ ብዙ ፡ ያገኘ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱ ፡ አይደለምን ? ሰውን ፡ ደም ፡ ስላፈሰሰህ ÷ በምድሪቱና ፡ በከተማይቱም ፡ በእርስዋም ፡ በሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ስላደረግኸው ፡ ግፍ ÷ አንተ ፡ ብዙ ፡ ዎችን ፡ አሕዛብን ፡ በዝብዘሃልና ፡ ከአሕዛብ ፡ የቀሩት ፡ ሁሉ ፡ ይበዝብዙሃል ።
፯ ከክፉ ፡ እንዲድን ፡ ጐጆውን ፡ በክፍታ ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለቤቱ ፡ ክፉ ፡ ትርፍን ፡ ለሚሰበስብ ፡ ወዮለት ! ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አዋፍተሃልና ፡ ለቤትህ ፡ እፍረትን ፡ መክረሃል ÷ በነፍስህም ፡ ላይ ፡ ኃጢአትን ፡ አድርገሃል ። ድንጋይም ፡ ከግንብ ፡ ውስጥ ፡ ይጮኻል ÷ እንጨትም ፡ ከውቅር ፡ ውስጥ ፡ ይመልስለታል ።
፰ ከተማን ፡ በደም ፡ ለሚሠራ ÷ ከተማንም ፡ በኃጢአት ፡ ለሚመሠርት ፡ ወዮለት ! እነሆ ÷ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ እሳት ፡ እንዲሠሩ ÷ ወገኖችም ፡ ስለ ፡ ከንቱነት ፡ እንዲደክሙ ፡ ከሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሆነ ፡ አይደለምን ?
፱ ውኃ ፡ በሕርን ፡ እንደሚከድን ፡ ምድር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ በማወቅ ፡ ትሞላለችና ።
፲ ኀፍረት ፡ ሥጋውን ፡ ለማየት ፡ በልጁራውን ፡ ለሚያጠጣ ÷ ክፉንም ፡ ለሚጨምርበት ÷ ለሚያሰክረውም ፡ ወዮለት ! በክብር ፡ ፋንታ ፡ እፍረት ፡ ሞልቶብሃል ። አንተ ፡ ደግሞ ፡ ጠጥተህ ፡ ተንገዳገድ ። የእግዚአብሔር ፡ የቀኙ ፡ ጽዋ ፡ ይመለስብሃል ÷ እፍረትም ፡ በክብርህ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።
፲፩ የሰውንም ፡ ደም ፡ ስላፈሰስህ ÷ በምድሪቱና ፡ በከተማይቱም ፡ በእርስዋም ፡ በሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ስላደረግኸው ፡ ግፍ ÷ በሊባኖስ ፡ ላይ ፡ የሠራኸው ፡ ግፍ ፡ ይከድንሃል ፤ የአራዊትም ፡ አደጋ ፡ ያስፈራራሃል ።
፲፪ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ሠረው ፡ የቀረጸው ፡ ለምን ፡ ጥቅም ፡ ነው ? ዳዳንም ፡ ጣዖት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሠረው ፡ የታመነበት ÷ ሐሰትን ፡ የሚያስተምር ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ?
፲፫ እንጨቱን ፦ንቃ ÷ ዲዳውንም ፡ ድንጋይ ፦ተነሣ ፡ ለሚለው ፡ ወዮለት ! በውኑ ፡ ይህ ፡ ያስተምራልን ? እነሆ ÷ በወርቅና ፡ በብር ፡ ተለብጦአል እንጂ ፡ በውስጡ ፡ የለበትም ።
፲፬ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በተቀደሰ ፡ መቅደሱ ፡ አለ ፤ ምድርም ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ዝም ፡ ትበል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ የነቢዩ ፡ የዕንባቆም ፡ ጸሎት ፡ በመዝሙር ።
፪ አቤቱ ÷ ዝናህን ፡ ሰምቼ ፡ ፈራሁ ። አቤቱ ÷ በዓመታት ፡ መካከል ፡ ሥራህን ፡ ፈጽም ፤ በዓመታት ፡ መካከል ፡ ትታወቅ ፤ በመዓት ፡ ጊዜ ፡ ምሕረትን ፡ አስብ ።
፫ እግዚአብሔር ፡ ከቴማን ÷ ቅዱሱም ፡ ከፋራን ፡ ተራራ ፡ ይመጣል ። ክብሩ ፡ ሰማያትን ፡ ከደኖአል ÷ ምስጋናውም ፡ ምድርን ፡ ሞልቶአል ።
፬ ፀዳሉም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ ጨረር ፡ ከእጁ ፡ ወጥቶአል ፤ ኃይሉም ፡ በዚያ ፡ ተሰውሮአል ።
፭ ቸነፈር ፡ በፊቱ ፡ ይሄዳል ÷ የአሳትም ፡ ነበልባል ፡ ከእግሩ ፡ ይወጣል ።
፮ ቆመ ÷ ምድርንም ፡ አወከት ፤ ተመለከተ ÷ አሕዛብንም ፡ አናወጠ ፤ የዘላለምም ፡ ተራሮች ፡ ተቀጠቀጡ ÷ የዘላለምም ፡ ኮረብቶች ፡ ቀለጡ ፤ መንገዱ ፡ ከዘላለም ፡ ነው ።
፯ የኢትዮጵያ ፡ ድንኳኖች ፡ ሲጨነቁ ፡ አየሁ ፤ የምድያም ፡ አገር ፡ መጋረጃዎች ፡ ተንቀጠቀጡ ።
፰ በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወንዞች ፡ ላይ ፡ ተቈጥቶአልን ? ቍጣህ ፡ በወንዞች ፡ ላይ ÷ መዓትህም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ነውን ? በፈረሶችህና ፡ በማዳንህ ፡ ሰረገሎች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠሃልና ።
፱ በቃልህ ፡ እንደ ፡ ማልህ ፡ መቅሠፍትህን ፡ አወጣህ ፤ ቀስትህንም ፡ ገተርህ ፤ ምድርን ፡ ሰንጥቀህ ፡ ፈሳሾችን ፡ አወጣህ ።
፲ ተራሮች ፡ አንተን ፡ አይተው ፡ ተጨነቁ ፤ የውኃ ፡ ሞገድ ፡ አልፎአል ፤ ቀላይም ፡ ድምፁን ፡ ሰጥቶአል ÷ እጁንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥቶአል ።
፲፩ ፀሓይና ፡ ጨረቃ ፡ በመኖሪያቸው ፡ ቆሙ ። በምድር ፡ ላይ ፡ በመዓት ፡ ተራመድህ ፤ አሕዛብን ፡ በቍጣ ፡ አሄድሃቸው ።
፲፪ ሕዝብህን ፡ ለመታደግ ÷ የቀባኸውንም ፡ ለማዳን ፡ ወጣህ ፤ የኃጢአተኛውን ፡ ቤት ፡ ራስ ፡ ቀጠቀጥህ ፤ መሠረቱን ፡ እስከ ፡ አንገቱ ፡ ድረስ ፡ ገለጥህ ።
፲፫ የአለቆችን ፡ ራስ ፡ በገዛ ፡ በትራቸው ፡ ወጋህ ፤ እኔን ፡ ይበትኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ መጡ ፤ ችግረኛውን ፡ በስውር ፡ ለመዋጥ ፡ ደስታቸው ፡ ነው ።
፲፬ ፈረሶችህን ፡ በባሕር ÷ በብዙ ፡ ውኖችም ፡ ላይ ፡ አስረገጥህ ።
፲፭ እኔ ፡ ሰምቻለሁ ÷ ልቤም ፡ ደነገጠብኝ ፤ ከድምፁ ፡ የተነሣ ፡ ከንፈሮቼ ፡ ተንቀጠቀጡ ፤ መንቀጥቀጥ ፡ ወደ ፡ አጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፤ በስፍራዬ ፡ ሆኜ ፡ ተናወጥሁ ፤ በሚያስጨንቀን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የመከራን ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ እጠብቃለሁ ።
፲፮ ምንም ፡ እንኳ ፡ በለስም ፡ በታፈራ ÷ በወይንም ፡ ሐረግ ፡ ፍሬ ፡ ባይገኝ ÷ የወይራ ፡ ሥራ ፡ ቢጐድል ÷ እርሻችም ፡ መብልን ፡ ባይሰጡ ÷ በጎች ፡ ከበረቱ ፡ ቢጠፉ ÷ ላሞችም ፡ በጋጡ ፡ ውስጥ ፡ ባይገኙ ÷
፲፯ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ በመድኃኒቴ ፡ አምላክ ፡ ሐሤት ፡ አደርጋለሁ ።
፲፰ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሌ ፡ ነው ፤ እግሮቼን ፡ እንደ ፡ ዋላ ፡ እግሮች ፡ ያደርጋል ፤ በከፍታዎችም ፡ ላይ ፡ ያስሄደኛል ።

ትንቢተ ሶፎንያስ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ በይሁዳ ንጉሥ በአሞጽ ልጅ በኢዮ
ያስ ዘመን ወደ ሕዝቅያስ ልጅ ወደ
አማርያ ልጅ ወደ ጎዶልያስ ልጅ ወደ
ኩሲ ልጅ ወደ ሶፎንያስ የመጣ የእግዚ
አብሔር ቃል ይህ ነው ።

፪ ነገርን ሁሉ ከምድር ፊት ፈጽሜ አጠ
፫ፋለሁ ይላል እግዚአብሔር ። ሰውንና
እንስሳን አጠፋለሁ ፤ የሰማይን ወፎችና
የባሕርን ዓሣዎች ፣ ማሰናከያንም ከኃጢ
አተኞች ጋር አጠፋለሁ ፤ ሰውንም ከም
ድር ፊት እቈርጣለሁ ፥ ይላል እግዚአብ
፬ሔር ። እጄንም በይሁዳ ላይ በኢየሩሳሌ
ምም በሚኖሩት ሁሉ ላይ እዘረጋለሁ ፤
ከዚህም ስፍራ የበአልን ቅሬታና የማያ
፭ታቱን ከህናት ስም አጠፋለሁ ፤ በሰገነትም
ላይ ለሰማይ ሠራዊት የሚሰግዱትን ÷ በእ
ግዚአብሔርና በንጉሣቸው በሚልኮም
፮ ምለው የሚሰግዱትን ÷ እግዚአብሔርንም
ከመከተል የተመለሱትን ÷ እግዚአብሔር
ንም ያልፈለጉትንና ያልጠየቁትን አጠፋ
ለሁ ።

፯ የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና ÷ እግዚአ
ብሔር መሥዋዕትን አዘጋጅቶአልና ÷ የጠ
ራቸውንም ቀድሶአልና በጌታ በእግዚአብ
፰ሔር ፊት ዝም በሉ ። በእግዚአብሔርም
መሥዋዕት ቀን አለቆችንና የንጉሥን
ልጆች እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም
፱ሁሉ እቀጣለሁ ። በዚያም ቀን በመድረኩ
ላይ የሚዘልሉትን ÷ የጌታቸውን ቤት ዓመ
ፃንና ሽንገላን የሚሞሉትን እቀጣለሁ ።

፲ በዚያ ቀን ÷ ይላል እግዚአብሔር ÷ ከዓ
ሣው በር የጩኸት ድምፅ ÷ ከከተማውም
በሁለተኛው ከፍል ውከታ ÷ ከኮረብቶቹም
፲፩ ታላቅ ሽብር ይሆናል ። እናንተ በመከቴሽ
የምትኖሩ ሆይ ÷ የከነዓን ሕዝብ ሁሉ
ጠፍተዋልና ÷ ብርም የተሸከሙ ሁሉ ተቈ
፲፪ርጠዋልና አልቅሱ ። በዚያም ዘመን ኢየ
ሩሳሌምን በመብራት እመረምራለሁ ፤ በአ
ተላቸውም ላይ የሚቀመጡትን ÷ በልባቸ
ውም — እግዚአብሔር መልካምን አያደር
ግም ÷ክፉም አያደርግም የሚሉትን ሰዎች
፲፫ እቀጣለሁ ። ብልጥግናቸውም ለምርኮ ይሆ
ናል ÷ ቤቶቻቸውም ይፈርሰሉ ፤ ቤቶችንም
ይሠራሉ ÷ ነገር ግን አይቀመጡባቸውም ፤
ወይንንም ይተክላሉ ÷ የወይን ጠጁን ግን
አይጠጡም ።

፲፬ ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአል ፤
የእግዚአብሔር ቀን ድምፅ ቀርቦአል ፤ እጅ
ግም ፈጥኖአል ፤ ኃያሉም በዚያ በመራራ
ልቅሶ ይጮኻል ። ያ ቀን የመዓት ቀን ÷ ፲፭
የመከራና የጭንቀት ቀን ÷ የመፍረስና የመ
ጥፋት ቀን ÷ የጨለማና የጭጋግ ቀን ÷ የደ
መናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ÷ በተመሸጉ ፲፮
ከተሞችና በረዘሙ ግንቦች ላይ የመለከ
ትና የሰልፍ ጩኸት ቀን ነው ። በእግዚ ፲፯
አብሔርም ላይ ኃጢአት ሠርተዋልና
እንደ ዕውር እስኪሄዱ ድረስ ሰዎችን
እስጨንቃለሁ ፤ ደማቸውም እንደ ትቢያ ÷
ሥጋቸውም እንደ ጕድፍ ይፈሰሳል ። በእ ፲፰
ግዚአብሔርም ቍጣ ቀን ብራቸውና ወር
ቃቸው ሊያድናቸው አይችልም ፤ እርሱም
በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ፈጥኖ ይጨርሰ
ዋልና ። ምድር ሁሉ በቅንዓቱ እሳት
ትበላለች ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩፪ እናንተ እፍረት የሌላችሁ ሕዝብ ሆይ ÷
ትእዛዝ ሳይወጣ ÷ ቀኑም እንደ ገለባ ሳያ
ልፍ ÷ የእግዚአብሔርም ቍጣ ትኵሳት
ሳይመጣባችሁ ÷ የእግዚአብሔርም ቍጣ
ቀን ሳይደርስባችሁ ተሰብሰቡ ÷ ተከማቹም ።
፫ እናንተ ፍርዱን የጠበቃችሁ የምድር
ትሑታን ሁሉ ÷ እግዚአብሔርን ፈልጉ ፤
ጽድቅንም ፈልጉ ÷ ትሕትናንም ፈልጉ ፤
ምናልባት በእግዚአብሔር ቍጣ ቀን ትሰ
ወሩ ይሆናል ።

፬ ጋዛ ትበረበራለች ÷ አስቀሎናም በድማ ፤
ትሆናለች ፤ አዛጦንንም በቀትር ወደ ውጭ ፥
፭ ያሰድዱአታል ÷ አቃሮንም ትነቀላለች ። በባ
ሕር ዳር ለሚኖሩ ለከሊታውያን ሕዝብ
ወዮላቸው ! የፍልስጥኤማውያን ምድር ፥
ከነዓን ሆይ ÷ የእግዚአብሔር ቃል በእንተ
ላይ ነው ÷ የሚቀመጥብህም ሰው እንዳይኖር ፤
አጠፋሃለሁ ። ቀርጤስም የእረኞች መኖሪያና ፮
የመንጎች በረት ይሆናል ። የባሕሩም ዳር ፯
ለይሁዳ ቤት ቅሬታ ይሆናል ÷ በዚያም
ይሰማራሉ ፤ አምላካቸው እግዚአብሔር ይጐ
በኛቸዋልና ÷ ምርኮአቸውንም ይመልሳልና ፤
በአስቀሎና ቤቶች ውስጥ ማታ ይተኛሉ ።

፰ በሕዝቤም ላይ ያላገጡባትን ÷ በድንበራ
ቸውም ላይ እየታበዩ የተናገሩባትን የሞ
ዓብን ማላገጥና የአሞንን ልጆች ስድብ
ሰምቻለሁ ። ስለዚህ የእስራኤል አምላክ ፱
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል — እኔ ሕያው ነኝና በእርግጥ ሞዓብ
እንደ ሰዶም ÷ የአሞንም ልጆች እንደ ገሞራ ÷
የሰማ ስፍራና የጨው ጕድጓድ ለዘላለ
ምም ምድረ በዳ ሆነው ፤ የናራሉ ፤ የሕዝ ፲
ቤም ቅሬታ ፤ በዘብዛቸዋል ÷ ከወገኔም
የተረፉት ይወርሱአቸዋል ። በሠራዊት ጌታ ፲፩
በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አላግጠዋልና ÷
እየታበዩም ተናግረዋልና ፤ ይህ ስለ ትዕቢታ
ቸው ፤ ያገኛቸዋል ። እግዚአብሔር በእነርሱ ፲፪
ላይ የተፈራ ይሆናልና ÷ የምድርንም አማል
ክት ሁሉ ያከሳቸዋል ፤ በአሕዛብም ፥ ደሴ
ቶች ሁሉ ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በስ
ፍራቸው ሆነው ለእርሱ ይሰግዳሉ ።

፲፫ እናንተም ኢትዮጵያውያን ደግሞ ÷ በሰ
፲፬ይፈ ትገደላላችሁ ። እርሱም በሰሜን ላይ
እጁን ይዘረጋል ÷ አሦርንም ያጠፋል ፤ ነነዌ
ንም በድማ ÷ እንደ በረሃም ደረቅ ያደርጋ
፲፭ታል ። መንጎችም የምድርም አራዊት
ሁሉ በውስጥዋ ይመሰጋሉ ፤ ይብራና ጃርት
በዓምዶችዋ መካከል ያድራሉ ፤ ድምፃቸው
በመስኮቶችዋ ይጮኻል ፤ የዝግባም እን
ጨት ሥራ ይገለጣልና በመድረኮችዋ
፲፮ ላይ ጥፋት ይሆናል ። ተዘልላ የተቀመጠች ÷
በልብዋም — እኔ ነኝ ÷ ከእኔም በቀር ሌላ
የለም ያለች ደስተኛይቱ ከተማ ይህች
ናት ፤ አራዊት የሚመሰገባት በድማ እን
ዴት ሆነች ! በእርስዋ በኩል የሚያልፈው
ሁሉ እጁን እያወዛወዘ ያፍዋጫል ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ ለዓመፀኛይቱና ለረከሰች ለእስጨናቂይ
፪ ቱም ከተማ ወዮላት ! ድምፅን አልሰማ
ችም ÷ ተግሣጽንም አልተቀበለችም ፤ በእግ
ዚአብሔርም አልታመነችም ÷ ወደ አምላክ
፫ዋም አልቀረበችም ። በውስጥዋ ያሉ አለ
ቆችዋ እንደሚያገሡ አንበሶች ናቸው ፤
ፈራጆችዋም እስከ ነገ ድረስ ምንም እን
ደማያስቀሩ እንደ ማታ ተኵላዎች ናቸው ።
፬ ነቢያቶችዋ ቅሌታሞችና ተንኰለኞች ፤
ሰዎች ናቸው ፤ ካህናቶችዋም መቅደሱን
አርክሰዋል ÷ በሕግም ላይ ግፍ ሠርተዋል ።
፭ እግዚአብሔር በውስጥዋ ጻድቅ ነው ፤ ክፋ
ትን አያደርግም ፤ ፍርዱን በየማለዳው ወደ
ብርሃን ያወጣል ÷ ሳያወጣውም ፥ አይቀርም ፤
፮ ዓመፀኛው ግን እፍረትን አያውቅም ። አሕ
ዛብን አጥፍቻለሁ ፤ ግንቦቻቸው ሁሉ ፈር
ሰዋል ፤ መንገዳቸውን ማንም እንዳያልፍ
በት ምድረ በዳ አድርጌአለሁ ÷ ከተሞቻ
ቸውም ማንም እንዳይኖርባቸው ÷ አን
ድስ እንኳ እንዳይቀመጥባቸው ፈርሰዋል ።
፯ እኔም — ይፈሩኛል ÷ ተግሣጽንም ይቀበላሉ ፤
ከዘገሩትም ሁሉ ከዓይንዋ ምንም አይጠ
ፋም ብዩ ፥ ነበር ፤ እነርሱ ግን በማለዳ ተነ
ሡተው ድርጊታቸውን ሁሉ አረከሱ ።

፰ መዓቴንና የቍጣዬን ትኵሳት ሁሉ አፈ
ስስባቸው ዘንድ ፍርዴ አሕዛብን ለመሰብ
ሰብ ÷ መንግሥታትንም ለማከማቸት ነውና ÷
ምድርም ሁሉ በቅንዓቴ እሳት ትበላለ
ችና ስለዚህ ለመበዝበዝ እስከምነሣበት
ቀን ድረስ ጠብቂኝ ÷ ይላል እግዚአብሔር ።

፱ በዚያን ጊዜም አሕዛብ ሁሉ አንድ
ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉት ዘንድ
ስሙን እንዲጠሩ ንጹሕን ልሳን እመልስ
ላቸዋለሁ ። ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚ
፲ ማልዱኝ ÷ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ÷ ቍር
ባኔን ያመጡልኛል ። በዚያን ጊዜ እየታ
፲፩ በዩ የሚፎክሩትን ከመካከልሽ አወጣለሁና ÷
እንቺም በቅዱስ ተራራዬ ዳግመኛ አትኰ
ሪምና በዚያ ቀን በእኔ ላይ ተላልፈሽ
በሠራሽው ሥራ ሁሉ አታፍሪም ። በመካ
፲፪ ከልሽም የዋህና ትሑት ሕዝብን እስቀ
ራለሁ ፤ በእግዚአብሔርም ስም ይታመናሉ ።
፲፫ የእስራኤል ቅሬታ ኃጢአትን አይሠሩም ÷
ሐሰትንም አይናገሩም ÷ በአፋቸውም ውስጥ
ተንኰለኛ ምላስ አይገኝም ፤ እነርሱም ይሰ
ማራሉ ÷ ይመሰጉማል ÷ የሚያስፈራቸውም
የለም ።

፲፬ የጽዮን ልጅ ሆይ ÷ ዘምሪ ፤ እስራኤል
ሆይ ÷ አልል በል ፤ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ ÷
በፍጹም ልብሽ ሐሤት አድርጊ ፤ ደስም
ይበልሽ ። እግዚአብሔር ፍርድሽን ÷ አስወ
፲፭ገዶአል ÷ ጠላትሽንም ጥሎአል ፤ የእስራ
ኤል ንጉሥ እግዚአብሔር በመካከልሽ ፤
አለ ÷ ከእንግዲህም ወዲህ ክፋ ነገርን
አታዪም ። በዚያን ቀን ለኢየሩሳሌም ፦ ፲፮
ጽዮን ሆይ ÷ አትፍሪ ÷ እጆችሽም አይዛሉ ።
አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ፤ ታዳጊ ፲፯
ኃያል ነው ። በደስታ በእንቺ ደስ ይለዋል ÷
በፍቅሩም ያርፋል ÷ በእልልታም በእንቺ
ደስ ይለዋል ይባላል ። ከጉባኤው ርቀው ፲፰
የሚያዝኑትን ÷ ከእንቺም የሆኑትን እሰበስ
ባለሁ ፤ ስድብ እንደ ሸክም ከብዶባቸው ፥
ነበር ። በዚያ ዘመን እነሆ ÷ በስጨነቋቸው ፲፱
ሁሉ ላይ ፤ አደርግባቸዋለሁ ፤ አንካሳይቱንም
አድናለሁ ÷ የቀጣለችውንም እሰበስባታለሁ ፤
በፈሩባትም ምድር ሁሉ ላይ ለምስጋናና ፥
ለከበረ ስም አደርጋቸዋለሁ ። በዚያ ዘመን ፳
አስገባችኋለሁ ÷ በዚያም ዘመን እሰበስባች
ኋለሁ ፤ ምርኮአችሁንም በዓይናችሁ ፊት ፥
በመለስሁ ጊዜ በምድር አሕዛብ ሁሉ ፥
መካከል ለከበረ ስምና ለምስጋና አደርጋ
ችኋለሁ ÷ ይላል እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሐጌ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በንጉሡ ፡ በዳርዮስ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ አጅ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዘሩባቤል ÷ ወደ ፡ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ወደ ፡ ኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡
፪ ኢያሱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ ዘመኑ ፡ አልደረሰም ÷ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ዘመን ፡ አልደረሰም ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተና
፫ ገረ ። የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡
፬ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ በውኑ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ሳለ ፡ እናንተ ፡ ራሳችሁ ፡ በተሸለሙ ፡ ቤቶቻችሁ ፡ ለመኖር ፡ ጊዜው ፡ ነውን ?
፭ አሁንም ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልባችሁን ፡ በመንገዳችሁ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ። ብዙ ፡ ዘራችሁ ÷ ጥቂትም ፡ አገባችሁ ፤ በላችሁ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አልጠገባችሁም ፤ ጠጣችሁ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አልረካችሁም ፤ ለበሳችሁ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ አልሞቃችሁም ፤ ደመወዙን ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ በቀዳዳ ፡ ከረጢት ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ደመወዙን ፡ ተቀበለ ።
፮ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልባችሁን ፡ በመንገዳችሁ ፡ ላይ ፡ አድ
፯ ርጉ ። ወደ ፡ ተራራው ፡ ውጡ ÷ እንጨትንም ፡ አምጡ ÷ ቤቱንም ፡ ሥሩ ፤ እኔም ፡ በእርሱ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ÷ እኔም ፡ እመሰገናለሁ ÷ ይላል ፡
፰ እግዚአብሔር ። እናንተ ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ተስፋ ፡ አደረጋችሁ ÷ እነሆም ÷ ጥቂት ፡ ሆነ ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ባገባችሁት ፡ ጊዜ ፡ እፍ ፡ አልሁበት ። ይህ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። እናንተ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እየቤታችሁ ፡ እየሮጣችሁ ፡ የእኔ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ
፱ ስለ ፡ ተቀመጠ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰማያት ፡ በላያችሁ ፡ ጠልን ፡ ከልከለዋል ÷ ምድሪቱም ፡ ፍሬ
፲፩ ዋን ፡ ከልክላለች ። እኔም ፡ በምድርና ፡ በተራሮች ÷ በእህልና ፡ በወይንም ፡ በዘይትና ፡ ምድርም ፡ በምታበቅለው ፡ ላይ ÷ በሰዎችና ፡ በእንስሶችም ፡ ላይ ÷ እጅም ፡ በሚደክምበት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ድርቅን ፡ ጠርቻለሁ ።
፲፪ የሰላትያልም ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ÷ ታላቁም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ÷ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ የነቢዩንም ፡ የሐጌን ፡ ቃል ÷ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ሁሉ ፡ ሰሙ ፤ ሕዝቡም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፈሩ ።
፲፫ የእግዚአብሔርም ፡ መልእክተኛ ፡ ሐጌ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልእክት ፡ ሕዝቡን ፦ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ነኝ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።
፲፬ እግዚአብሔርም ፡ የይሁዳን ፡ የይሁዳን ፡ አለቃ ፡ የሰላትያልን ፡ ልጅ ፡ የዘሩባቤልን ፡ መንፈስ ÷ የታላቁንም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅን ፡ ልጅ ፡ የኢያሱን ፡ መንፈስ ÷ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ አስነሣ ፤ በንጉሡም ፡ በዳርዮስ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በሀያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ መጡ ÷ የአምላካቸውንም ፡ የሠራዊትን ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሠሩ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በሀያ ፡ አንደኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡
፪ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ ለይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ለሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ለዘሩባቤል ÷ ለታላቁም ፡ ካህን ፡ ለኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ለኢያሱ ÷ ለቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ተናገር ፦
፫ በቀድሞ ፡ ክብሩ ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ያየ ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ የቀረ ፡ ማን ፡ ነው ? ዛሬስ ፡ እንዴት ፡ ሆኖ ፡ አያችሁት ? በዓይናችሁ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ አይደለምን ? አሁን ፡ ግን ÷ ዘሩባቤል ፡
፬ ሆይ ÷ በርታ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ታላቁም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሆይ ÷ በርታ ÷ እናንተም ፡ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ÷ በርቱና ፡ ሥሩ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ነኝና ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። መንፈሴም ፡ በመካከላችሁ ፡
፭ ይኖራልና ፡ አትፍሩ ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ገና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ እኔ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንና ፡ የብስንም ፡ እናውጣለሁ ።
፮ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ እናውጣለሁ ÷ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የተመረጠውም ፡ ዕቃ ፡ ይመጣል ። ይህንም ፡ ቤት ፡ በክብር ፡ እሞላዋለሁ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ብሩ ፡ የእኔ ፡
፰ ነው ÷ ወርቁም ፡ የእኔ ፡ ነው ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡
፱ የዚህ ፡ የሁለተኛው ፡ ቤት ፡ ክብር ፡ ይበልጣል ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ሰላምን ፡ አሰጣለሁ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።
፲ በዳርዮስም ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በሀያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡
፲፩ ሲል ፡ መጣ ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ካህናቱን ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡
፲፪ ጠይቅ ። አንድ ፡ ሰው ፡ የተቀደሰ ፡ ሥጋ ፡ በልብሱ ፡ ዘርፍ ፡ ቢይዝ ÷ በዘርፉም ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ ወጥ ÷ ወይም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ÷ ወይም ፡ ዘይት ÷ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ መብል ፡ ቢነካ ፡ ያ ፡ የተነካው ፡ በውኑ ፡ ይቀደሳልን ? ብለህ ፡
፲፫ ካህናቱን ፡ ጠይቃቸው ። ካህናቱም ፦ አይሆንም ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ሐጌም ፦ በሬሳ ፡ የረከሰ ፡ ሰው ፡ ከእነዚህ ፡ አንዱን ፡ ቢነካ ፡ ያ ፡ የተነካው ፡ በውኑ ፡ ይረክሳልን ? አለ ። ካህናቱም ፦
፲፬ አዎን ፡ ይረክሳል ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ሐጌም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ሕዝብና ፡ ይህ ፡ ወገን ፡ በፊቴ ፡ እንዲህ ፡ ነው ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ በዚያም ፡ ያቀረቡት ፡ ነገር ፡ ርኩስ ፡ ነው ።
፲፭ አሁንም ፡ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ሳይነባበር ÷ ከዛሬ ፡ ጀምራችሁ ፡ ወዳለፈው ፡ ዘመን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።
፲፮ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሀያ ፡ መስፈሪያ ፡ ወዳለበት ፡ ምርት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ÷ የተገኘው ፡ አሥር ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አምላ ፡ ማድጋም ፡ ይቀዳ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መጥመቂያው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ÷ የተገኘው ፡ ሀያ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
፲፯ በእጃችሁ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በዋግና ፡ በአረማሞ ፡ በበረዶም ፡ መታኋችሁ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችሁም ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ከዛሬው ፡ ከዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ከሀያ ፡
፲፰ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ጀምራችሁ ፡ የሚመጣውን ፡ ዘመን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ መሠረት ፡ ከተተከለበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ። ዘር ፡ በጎተራ ፡ ገና ፡ ይኖራልን ? ወይንና ፡ በለስ ፡ ሮማንና ፡ ወይራ ፡ አላፈሩም ፤ ከዚህች ፡ ቀን ፡ ጀምሬ ፡ እባርክሻለሁ ።
፲፱ በወሩ ፡ በሀያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሁለተኛ ፡ ወደ ፡ ሐጌ ፡ እንዲህ ፡
፳ ሲል ፡ መጣ ፦ ለይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ለዘሩባቤል ፡
፳፩ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ አናውጣለሁ ፤ የመንግሥታትንም ፡ ዙፋን ፡ እገለብጣለሁ ÷ የአሕዛብንም ፡ መንግሥታት ፡ ኃይል ፡ አጠፋለሁ ፤ ሰረገሎችንና ፡ የሚቀመጡባቸውንም ፡ እገለብጣለሁ ፤ ፈረሰኛና ፡ ፈረሰኞቻቸውም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በወንድማቸው ፡ ሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ። ባሪያዬ ፡ የሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፡ ሆይ ÷ በዚያ ፡ ቀን ፡ እወስድሃለሁ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ መርጬሃለሁና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ÷ እንደ ፡ ቀለበት ፡ ማተሚያ ፡ አደርግሃለሁ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በዳርዮስ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ አዶ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ በራክዩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡
፪ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ እግዚአብሔር ፡ በአባቶቻችሁ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡
፫ ነበር ። ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ÷ እኔም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመለሳለሁ ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። የቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ ለአባቶቻችሁ ፡
፬ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሰብከዋል ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከክፉ ፡ መንገዳችሁና ፡ ከክፉ ፡ ሥራችሁ ፡ ተመለሱ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አልሰሙም ÷ እኔንም ፡ አላደመጡም ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ አትሁኑ ÷ ይላል ፡ እግ
፭ ዚአብሔር ። አባቶቻችሁ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ? ነቢያትስ ፡ ለዘላለም ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉን ?
፮ ለባሪያዎቼስ ፡ ለነቢያት ፡ ያዘዝኋቸው ፡ ቃሎቼና ፡ ሥርዓቴ ፡ በአባቶቻችሁ ፡ ላይ ፡ አልደረሱምን ? እነርሱም ፡ ተመልሰው ፡ ፦ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንገዳችንና ፡ በሥራችን ፡ መጠን ፡ ያደርግብን ፡ ዘንድ ፡ እንዳሰበ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጎብናል ፡ አሉ ።
፯ በዓርዮስ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ሳቡዋ ፡ በሚባል ፡ በአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡ በሀያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ አዶ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ በራክዩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡
፰ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦ እኔ ፡ ሌሊት ፡ አየሁ ÷ እርሱም ፡ በቀይ ፡ ፈረስ ፡ ሆኖ ÷ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በስተ ፡ ኋላውም ፡ መጋለና ፡ ሐመር ፡ አንበሳ ፡ ም ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ። እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ? አልሁ ። ከእኔም ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አሳይሃለሁ ፡ አለኝ ። በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከልም ፡ ቆሞ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፦ እነዚህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የላካቸው ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከልም ፡ ቆሞ ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፦ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለስን ÷ እነሆም ÷ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ዐርፋ ፡ ተቀምጣለች ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።
፲፪ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ መልሶ ፦ አቤቱ ÷ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ÷ እነዚህ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ የተቈጣሃቸውን ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ የይ

ሁዳን፡ከተሞች፡የማትምራቸው፡እስከ፡መቼ፡
፲፫፡ ነው ? አለ ። እግዚአብሔርም ፡ መልሶ ፡ ከእኔ ፡
ጋር ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረው ፡ መልአክ ፡ በመልካ
፲፬፡ ምና ፡ በሚያጽናና ፡ ቃል ፡ ተናገረው ። ስለዚ
ህም ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መል
አክ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡— ስበክ ፡ እንዲህም ፡
በል ፡— የሥራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፡— እኔ ፡ በታላቅ ፡ ቅንዓት ፡ በኢየ
፲፭፡ ሩሳሌምና ፡ በጽዮን ፡ ቀንቻለሁ ። እኔ ፡ ጥቂት ፡
ብቻ ፡ ተቈጥቼ ፡ ሳለሁ ፡ እነርሱ ፡ ክፋትን ፡ ስላገ
ዙት ፡ ባልተቈጠሩት ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡
፲፮፡ ተቈጥቻለሁ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን
ዲህ ፡ ይላል ፡— ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በምሕረት ፡
ተመልሻለሁ ፤ ቤቴ ፡ ይሠራበታል ፤ በኢየሩሳ
ሌምም ፡ ላይ ፡ ገመድ ፡ ይዘረጋበታል ፡ ይልላ ፡
፲፯፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ደግሞም ፡ እን
ዲህ ፡ ስትል ፡ ስበክ ፡— የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ከተሞቼ ፡ ደግሞ ፡
በበጎ ፡ ነገር ፡ ይረክሉ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡
ጽዮንን ፡ ያጽናናል ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ ደግሞ ፡
ይመርጣል ።
፲፰፡ ዓይኖቼንም ፡ አንሥቼ ፡ እነሆ ፡ አራት ፡ ቀን
፲፱፡ ዶች ፡ አየሁ ። ከእኔም ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነበረ
ውን ፡ መልአክ ፡— እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው?
አልሁት ። እርሱም ፡— እነዚህ ፡ ይሁዳንና ፡ እስ
ራኤልን ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ የበተኑ ፡ ቀንዶች ፡
፳፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ። እግዚአብሔርም ፡
፳፩፡ አራት ፡ ጠራቢዎች ፡ አሳየኝ ። እኔም ፡— እነ
ዚህ ፡ የመጡት ፡ ምን ፡ ሊሠሩ ፡ ነው ? አልሁ ።
እርሱም ፡— እንድ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ እስከማያ
ነሣ ፡ ድረስ ፡ እነዚህ ፡ ቀንዶች ፡ ይሁዳን ፡ የበ
ተኑ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ግን ፡ ሊያስፈራሩአ
ቸው ፡ የይሁዳንም ፡ አገር ፡ ይበትኑ ፡ ዘንድ ፡
ቀንዳቸውን ፡ ያነሡትን ፡ የአሕዛብን ፡ ቀንዶች ፡
ሊጥሉ ፡ መጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩፡ ዓይኖቼንም ፡ አነሣሁ ፤ እነሆም ፡ በእጁ ፡
የመለኪያ ፡ ገመድ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ አየሁ ።
፪፡ እኔም ፡— እንተ ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ? አልሁ ።
እርሱም ፡— የኢየሩሳሌምን ፡ ወርድና ፡ ርዝ
መት ፡ ስንት ፡ መሆኑን ፡ ሰፍሬ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እሄ
፫፡ ዳለሁ ፡ አለኝ ። እነሆም ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይነጋ
ገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ወጣ ፡ ሌላም ፡ መል
፬፡ አክ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡—
ሩጥ ፡ ይህንም ፡ ጕልማሳ ፡ እንዲህ ፡ በለው ፡—
ኢየሩሳሌም ፡ በውስጥዋ ፡ ካሉት ፡ ሰዎችና ፡
እንስሶች ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ቅጥር ፡ እንደሌላ
፭፡ ቸው ፡ መንደሮች ፡ ሆና ፡ ትኖራለች ። እኔ ፡ በዙ
ሪያዋ ፡ የእሳት ፡ ቅጥር ፡ እሆንላታለሁ ፡ በውስ
ጥዋም ፡ ክብርን ፡ እሆናለሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአ
ብሔር ።
፮፡ እናንተ ፡ ሆይ ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ሽሹ ፡
ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንደ ፡ አራቱ ፡ የሰ
ማይ ፡ ነፋሳት ፡ በትኖች ችኋለሁና ፡ ይላል ፡ እግዚ
አብሔር ። አንቺ ፡ ከባቢሎን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡
፯፡ ጋር ፡ የምትኖሪ ፡ ጽዮን ፡ ሆይ ፡ ኰብልዩ ።
፰፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላልና ፡— ከክብሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ በዘበዙአ
ችሁ ፡ አሕዛብ ፡ ልከኛል ፤ የሚነክችሁ ፡ የዓይ
ኑን ፡ ብሌን ፡ የሚነካ ፡ ነውና ። እነሆ ፡ እጄን ፡
፱፡ በላያቸው ፡ አወዛውዛለሁ ፡ ተገዢዎቻው ፡ ለነበ
ሩት ፡ ብዝበዛ ፡ ይሆናሉ ፤ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችሁ ።
፲፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ መጥቼ ፡ በመካ
ከልሽ ፡ እኖራለሁና ፡ ዘምሪ ፡ ደስም ፡ ይበልሽ ፡
፲፩፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡
አሕዛብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠጋሉ ፡ ሕዝ
ብም ፡ ይሆኑኛል ፤ በመካከልሽም ፡ እኖራለሁ ፡
የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡
፲፪፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቂአለሽ ። እግዚአብሔርም ፡
ይሁዳን ፡ እድል ፡ ፈንታው ፡ አድርጎ ፡ በተቀደ
ሰችው ፡ ምድር ፡ ይወርሰዋል ፡ ኢየሩሳሌምን
፲፫፡ ንም ፡ ዳግመኛ ፡ ይመርጣል ። እግዚአብሔር ፡
ከተቀደሰ ፡ ማደሪያው ፡ ነቅቶአልና ፡ ሥጋ ፡
ለባሽ ፡ ሁሉ ፡ ሆይ ፡ በፊቱ ፡ ዝም ፡ በል ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩፡ እርሱም ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ኢያሱን ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ አሳየኝ ፡
ሰይጣንም ፡ ይከስሰው ፡ ዘንድ ፡ በስተ ፡ ቀኙ ፡
፪፡ ቆሞ ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፡—
ሰይጣን ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይገሥጽህ ፤ ኢየ
ሩሳሌምን ፡ የመረጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይገሥ
ጽህ ፤ በውኑ ፡ ይህ ፡ ከእሳት ፡ የተነጠቀ ፡ ትን
፫፡ ታግ ፡ አይደለምን ? አለው ። ኢያሱም ፡ እድ
ፋም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ በመልአኩ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡
፬፡ ነበር ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ በፊቱ ፡ የቆሙትን ፡—
እድፋሙን ፡ ልብስ ፡ ከእርሱ ፡ ላይ ፡ አውልቁ ፡
አላቸው ። እርሱንም ፡— እነሆ ፡ አበሳህን ፡ ከአ
ንተ ፡ አርቄአለሁ ፡ ዋሩ ፡ ልብስም ፡ አለብስሃ
፭፡ ለሁ ፡ አለው ። ደግሞ ፡— ንጹሕ ፡ ጥምጥም ፡
በራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ በራሱ ፡
ላይ ፡ ንጹሕ ፡ ጥምጥም ፡ አደረጉ ፡ ልብስንም ፡
አለበሱት ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በአ
ጠገቡ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።
፮፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በኢያሱ ፡ እን
፯፡ ዲህ ፡ ሲል ፡ አዳንበት ፡— የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በመንገዴ ፡
ብትሄድ ፡ ትእዛዜንም ፡ ብትጠብቅ ፡ በቤቴ ፡
ላይ ፡ ትፈርዳለህ ፡ አደባባዮቼንም ፡ ትጠብቃ
ለህ ፡ በዚህም ፡ ከቆሙት ፡ ከእነዚህ ፡ ጋር ፡ መግ
፰፡ ባትን ፡ እሰጥሃለሁ ። ታላቁ ፡ ካህን ፡ ኢያሱ ፡
ሆይ ፡ ስማ ፤ በፊትህም ፡ የሚቀመጡት ፡ ባል
ንጀሮችህ ፡ ለምልክት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ናቸ
ውና ፡ ይስሙ ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ ባሪያዬን ፡ ቍጥ
፱፡ ቋጥ ፡ አወጣለሁ ። በኢያሱ ፡ ፊት ፡ ያኖርሁት ፡
ድንጋይ ፡ እነሆ ፡ አለ ፤ በአንዱ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡

ሰባት ፡ ዓይኖች ፡ አሉ ፤ እነሆ ፡ ቅርጹን ፡ እቀር
ጻለሁ ፡ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የዚያችንም ፡ ምድር ፡ በደል ፡ በአንድ ፡
፲፡ ቀን ፡ አስወግዳለሁ ። በዚያ ፡ ቀን ፡ ይላል ፡
የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያንዳንዱ ፡
ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ በልንጀራ
ውን ፡ ይጠራል ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መል
አክ ፡ ተመልሶ ፡ ከእንቅልፉ ፡ እንደሚነቃ ፡
፪፡ ሰው ፡ አነቃኝ ። እርሱም ፡— የምታየው ፡ ምን
ድር ፡ ነው ? አለኝ ። እኔም ፡— እነሆ ፡ ሁሉንም
ናው ፡ ወርቅ ፡ የሆነውን ፡ መቅረዝ ፡ አየሁ ፤
የዘይትም ፡ ማሰሮ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፡ ሰባ
ትም ፡ መብራቶች ፡ ነበሩበት ፤ ጠራሱም ፡ ላይ ፡
፫፡ ለነበሩት ፡ መብራቶች ፡ ሰባት ፡ ቧምቧዎች ፡
ነበሩ ፡ አትም ፡ የወይራ ፡ ዛፎች ፡ አንዱ ፡
በማሰሮው ፡ በስተ ፡ ቀኝ ፡ አንዱም ፡ በስተ ፡
ግራው ፡ ሆነው ፡ በአጠገቡ ፡ ነበሩ ፡ አልሁ ።
፬፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረውም ፡ መልአክ ፡
መልሼ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እነዚህ ፡ ምንድር ፡
፭፡ ናቸው ? አልሁት ። ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነ
በረው ፡ መልአክ ፡ መልሶ ፡— እነዚህ ፡ ምን ፡
እንደ ፡ ሆኑ ፡ አታውቅምን ? አለኝ ። እኔም ፡—
፮፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አላውቅም ፡ አልሁ ። መልሶም ፡—
ለዘሩባቤል ፡ የተባለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ይህ ፡ ነው ፡— በመንፈሴ ፡ እንጂ ፡ በኃይልና ፡
በብርታት ፡ አይደለም ፡ ይላል ፡ የሠራዊት ፡
፯፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፡
አንተ ፡ ምንድር ፡ ነህ ? በዘሩባቤል ፡ ፊት ፡ ደል
ዳላ ፡ ሜዳ ፡ ትሆናለህ ፤ ሰዎችም ፡— ሞገስ ፡
ሞገስ ፡ ይሁንለት ፡ ብለው ፡ እየጮኹ ፡ እርሱ ፡
መደምደሚያውን ፡ ድንጋይ ፡ ያወጣል ፡ ብሎ ፡
ተናገረኝ ።
፰፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን
፱፡ ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የዘሩባቤል ፡ እጆች ፡
ይህን ፡ ቤት ፡ መሥረቱ ፡ የእርሱም ፡ እጆች ፡
ይፈጽሙታል ፤ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔርም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃ
፲፡ ላችሁ ። የዋቂቱን ፡ ነገር ፡ ቀን ፡ የናቀ ፡ ማን ፡
ነው ? እነዚህ ፡ ሰባቱ ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ በዘ
ሩባቤል ፡ እጅ ፡ ቱንቢውን ፡ ያያሉ ፤ እነዚህም ፡
በምድር ፡ ሁሉ ፡ የሚዘዋወሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ዓይኖች ፡ ናቸው ።
፲፩፡ እኔም ፡ መልሼ ፡— በመቅረዙ ፡ በስተ ፡ ቀኝና ፡
በስተ ፡ ግራ ፡ ያሉ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የወይራ ፡
፲፪፡ ዛፎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ? አልሁት ። ሁለተ
ኛም ፡ መልሼ ፡— በሁለቱ ፡ የወርቅ ፡ ቧምቧ
ዎች ፡ አጠገብ ፡ ሆነው ፡ የወርቁን ፡ ዘይት ፡ የሚ
ያፈስሱ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የወይራ ፡ ቅርንጫፎች ፡
፲፫፡ ምንድር ፡ ናቸው ? አልሁት ። እርሱም ፡ መልሶ ፡—
እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አታውቅምን ?
አለኝ ። እኔም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አላውቅም ፡
፲፬፡ አልሁት ። እርሱም ፡— በምድር ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡
አጠገብ ፡ የቆሙት ፡ ሁለቱ ፡ የተቀቡት ፡ እን
ዚህ ፡ ናቸው ፡ አለኝ ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩፡ ተመልሼም ፡ ዓይኖቼን ፡ አነሣሁ ፡ እነሆም ፡
አንድ ፡ በራሪ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ አየሁ ።
፪፡ እርሱም ፡— የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለኝ ።
እኔም ፡— በራሪ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ አያለሁ ፤
ርዝመቱ ፡ ሀያ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ አሥር ፡ ክንድ ፡
፫፡ ነው ፡ አልሁ ። እንዲህም ፡ አለኝ ፡— ይህ ፡ በም
ድር ፡ ፊት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚወጣው ፡ እርግማን ፡
ነው ፤ የሚሰርቅ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡
በኩል ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል ፡ ከሐ
፬፡ ሰት ፡ የሚምል ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡
በኩል ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል ።
እኔ ፡ አስወጣዋለሁ ፡ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡
፭፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰርቅው ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሐሰ
ትም ፡ በስሜ ፡ ወደሚምለው ፡ ቤት ፡ ይገባል ፤
በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል ፡ እርሱንም ፡ እን
ጨቱንና ፡ ድንጋዩን ፡ ይበላል ።
፮፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡
ወጥቶ ፡— ዓይኖችህን ፡ አንሣ ፡ ይህችም ፡ የም
ትወጣው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አይ ፡ አለኝ ።
፯፡ እኔም ፡— ምንድር ፡ ናት ? አልሁ ። እርሱም ፡—
ይህች ፡ የምትወጣው ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ናት ፡
አለኝ ። ደግሞም ፡— በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡
በደላቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ። እነሆም ፡ የእርሳ
፰፡ ሱን ፡ መክሊት ፡ አነሡት ፤ እነሆም ፡ በኢፍ ፡
መስፈሪያው ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ተቀ
ምጣ ፡ ነበር ። እርሱም ፡— ይህች ፡ ክፋት ፡ ናት ፡
፱፡ አለኝ ፤ በኢፍ ፡ መስፈሪያው ፡ ውስጥ ፡ ጣላት ፡
የእርሳሱንም ፡ ጠጋራ ፡ በመስፈሪያ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡
፲፡ ጣለ ። ዓይኖቼንም ፡ አንሥቼ ፡ አየሁ ፡ እነሆም ፡
ሁለት ፡ ሴቶች ፡ ወጡ ፡ ነፋስም ፡ በክንፎቻ
ቸው ፡ ነበረ ፤ ክንፎቻቸውም ፡ እንደ ፡ ሽመላ ፡
ክንፎች ፡ ነበሩ ፤ የኢፍ ፡ መስፈሪያውንም ፡
በምድርና ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ አነሡት ። ከእ
፲፩፡ ኔም ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውን ፡ መልአክ ፡—
እነዚህ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያውን ፡ ወዴት ፡ ይወ
፲፪፡ ስዱታል ? አልሁት ። እርሱም ፡— በሰናዖር ፡
ምድር ፡ ቤት ፡ ይሠሩለት ፡ ዘንድ ፡ ይወስዱታል ፤
በተዘጋጀም ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ በስፍራው ፡ ይኖ
ራል ፡ አለኝ ።

ምዕራፍ ፮ ።

፩፡ ተመልሼም ፡ ዓይኖቼን ፡ አነሣሁ ፡ እነሆም ፡
አራት ፡ ሰረገሎች ፡ ከሁለት ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡
ሲወጡ ፡ አየሁ ፤ ተራሮቹም ፡ የናስ ፡ ተራሮች ፡
፪፡ ነበሩ ። በፊተኛው ፡ ሰረገላ ፡ መጋላ ፡ ፈረሶች ፡
በሁለተኛውም ፡ ሰረገላ ፡ ዱሪ ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ፡
፫፡ በሦስተኛውም ፡ ሰረገላ ፡ አምባላይ ፡ ፈረሶች ፡
በአራተኛውም ፡ ሰረገላ ፡ ቀዋልጣል ፡ ፈረሶች ፡
፬፡ ነበሩ ። ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረውም ፡

መልአክ ፡ መልሼ ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ÷ እነዚህ ፡
፮ ምንድር ፡ ናቸው ? አልሁት ። መልአኩም ፡
መልሶ ፡— እነዚህ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡
ከቆሙበት ፡ ስፍራ ፡ የሚወጡ ፡ አራቱ ፡ የሰ
፯ ማይ ፡ ነፋሳት ፡ ናቸው ። ዱሪ ፡ ፈረሶች ፡ ያሉ
በት ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይወጣል ፤ አምበላዮቹም ፡
ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ ይወጣሉ ÷ ቀዋልጣሮችም ፡
፰ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይወጣሉ ፡ አለኝ ። መጋላዎቹም ፡
ደግሞ ፡ ወጡ ፡ በምድርም ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡
ለመኔድ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡— ሂዱ ÷
በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለሱ ፡ አለ ። እነርሱም ፡
፱ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለሱ ። ጮኽም ፡— እነሆ ÷
ወደ ፡ ሰሜን ፡ ምድር ፡ የሚወጡት ፡ እነርሱ ፡
መንፈሴን ፡ በሰሜን ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አሳርፈ
ዋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

፲ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን
፲፩ ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ከበቢሎን ፡ ከመጡት ፡
ምርከኞች ፡ ከሒልዳዩና ፡ ከጦብያ ፡ ከዮዳኤም ፡
ውሰድ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ መጥተህ ፡ ወደ ፡ ሶፎ
ንያስ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ቤት ፡ ግባ ።
፲፪ ብርንና ፡ ወርቅን ፡ ከእነርሱ ፡ ውሰድ ÷ አክሊሎ
ችንም ፡ ሥራ ፤ በታላቁም ፡ ካህን ፡ በኢዮሴ
ዴቅ ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ድፋቸው ÷
፲፫ እንዲህም ፡ በለው ፡— የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷ ስሙ ፡
ቀጥቃጥ ፡ የሚበል ፡ ሰው ፡ በስፍራው ፡ ይበቅ
ላል ÷ የእግዚአብሔርንም ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ።
፲፫ እርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ÷
ክብርንም ፡ ይሸከማል ÷ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ ይነግሣል ፤ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ካህን ፡ ይሆ
ናል ÷ የሰላምም ፡ ምክር ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡
፲፬ ይሆናል ። አክሊሎችም ፡ ለሔሌምና ፡ ለጦብያ ፡
ለዮዳኤም ፡ ለሶፎንያስም ፡ ልጅ ፡ ለሔን ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለመታሰቢያ ፡
፲፭ ይሆናሉ ። በሩቅም ፡ ያሉት ፡ መጥተው ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ይሠራሉ ፤ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡
ላከኝ ፡ ታውቃላችሁ ። የአምላካችሁንም ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አጥብቃችሁ ፡ ብትሰሙ ፡
ይህ ፡ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ በንጉሡም ፡ በዳርዮስ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡
ከሰሉ ፡ በሚባል ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በአራተ
ኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዘካ
፪ ርያስ ፡ መጣ ። የቤቴልም ፡ ሰዎች ፡ ሰራሳርንና ፡
ሬጌሜሌክን ፡ ሰዎቻቸውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡
፫ ፊት ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ÷ ለሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ካህናት ፡ ለነቢያቶችም ፡— በለ
ሩት ፡ ዓመታት ፡ እንዳደረግሁት ፡ በአምስተ
ኛው ፡ ወር ፡ መለየትና ፡ ማልቀስ ፡ ይገባኛልን ?
ብለው ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ልከአቸው ፡ ነበር ።
፬ የሠራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
፭ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— ለምድሩ ፡
ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ለካህናትም ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡
ተናገራቸው ፡— በዚህ ፡ በሰባው ፡ ዓመት ፡ በአ
ምስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በጾማችሁና ፡
በለቀሳችሁ ፡ ጊዜ ÷ በውኑ ፡ ለእኔ ፡ ጾም ፡ ጾማ
፮ ችሁልኝ ? በምትበሉበትና ፡ በምትጠጡበትስ ፡
፯ ጊዜ ÷ ለራሳችሁ ፡ የምትበሉና ፡ የምትጠጡ ፡
አይደላችሁምን ? ኢየሩሳሌምና ፡ በዙሪያዋ ፡
፰ ያሉ ፡ ከተሞች ፡ ገና ፡ ሰዎች ፡ በሰባቸው ፡ ጊዜ ÷
በምቾትም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ÷ ደቡቡና ፡ ቈላ
ውም ፡ ሰዎች ፡ በሰባቸው ፡ ጊዜ ÷ እግዚአብ
ሔር ፡ በቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ እጅ ፡ የተናገረ
፱ ውን ፡ ቃል ፡ መስማት ፡ አይገባችሁምን ?

፲ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዘከርያስ ፡
፲፩ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮአል ፡— እው
ነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤ ቸርነትንና ፡ ምሕ
ረትን ፡ ሁላችሁ ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ አድርጉ ፤
፲፪ መበለቲቱንና ፡ ድሀ ፡ አደጉን ÷ መጻተኛውንና ፡
ችግረኛውን ፡ አትበድሉ ፤ ከእናንተም ፡ ማንም ፡
በወንድሙ ፡ ላይ ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡
፲፫ አያስብ ። እነርሱ ፡ ግን ፡ ደንደሰኛውን ፡ አዘሩ ፡
እንጂ ፡ መስማትን ፡ እምቢ ፡ አሉ ፤ እንዳይሰ
ሙም ፡ ጆሮአቸውን ፡ አደነቁሩ ። የሠራዊትም ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀደሙት ፡ ነቢያት ፡
እጅ ፡ በመንፈሱ ፡ የላከውን ፡ ሕጉንና ፡ ቃሉን ፡
እንዳይሰሙ ፡ ልባቸውን ፡ እንደ ፡ አልማዝ ፡
አጠነከሩ ፡ ስለዚህ ፡ ከሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ቍጣ ፡ መጣ ። እኔ ፡ በጠ
ራው ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ እንዳልሰሙኝ ÷ እንዲሁ ፡
እነርሱ ፡ በሚጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አልሰማም ÷
ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ወደ
፲፬ ማያውቁአቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በወሎሙ ፡
ነፋስ ፡ በተንኗቸው ። እንዲሁ ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡
ምድሪቱ ፡ በድማ ፡ ሆናለች ÷ የሚተላለፍበትና ፡
የማይላለስበትም ፡ አልነበረም ፤ ያማረችው
ንም ፡ ምድር ፡ በድማ ፡ አደረጉአት ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ የሠራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
፪ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ስለ ፡
ጽዮን ፡ ታላቅ ፡ ቅንዓት ፡ ቀንቻለሁ ÷ በታላቅም ፡
፫ ቍጣ ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ቀንቻለሁ ። እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— ወደ ፡ ጽዮን ፡ ተመልሻለሁ ÷
በኢየሩሳሌምም ፡ መካከል ፡ እኖራለሁ ፤ ኢየሩ
ሳሌምም ፡ የእውነት ፡ ከተማ ፡ ትባላለች ፤ የሠ
ራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ የተ
፬ ቀደሰ ፡ ተራራ ፡ ይባላል ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ዳግመኛ ፡
ሽማግሌዎችና ፡ ባልቴቶች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደ
በባይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከዕድሜው ፡
፭ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምርኩዝ ፡ በእጁ ፡ ይይዛል ።
የከተማይቱም ፡ አደባባዮች ፡ በእነዚያ ፡ በሚጫ
፮ ወቱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይሞላሉ ።

፯ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— በዚህ ፡ ወራት ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቀሪታ ፡
ዓይን ፡ ዘንድ ፡ ድንቅ ፡ ቢሆን ÷ በውኑ ፡ በእኔ ፡
ዓይን ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ድንቅ ፡ ይሆናልን ? ይላል ፡
፰ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ÷
ሕዝቤን ፡ ከምሥራቅ ፡ ምድርና ፡ ከምዕራብ ፡
፱ ምድር ፡ አድነዋለሁ ፤ አመጣቸዋለሁም ÷ በኢ
የሩሳሌምም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፤ እነርሱም ፡
ሕዝብ ፡ ይሆኑኛል ÷ እኔም ፡ በእውነትና ፡ በጽ
ድቅ ፡ አምላክ ፡ እሆናቸዋለሁ ።

፲ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— መቅደሱ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከተመሠረተበት ፡
ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከነቢያት ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡
፲፩ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሰማችሁ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ÷ እጃ
ችሁን ፡ አበርቱ ። ከዚያ ፡ ወራት ፡ አስቀድሞ ፡
ለሰውና ፡ ለእንስሳ ፡ ዋጋ ፡ አልነበረምና ፤ እኔም ፡
ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ አስነሥቼ ፡
ነበርና ፡ ከአስጨናቂው ፡ የተነሣ ፡ ለሚገባውና ፡
፲፪ ለሚወጣው ፡ ሰላም ፡ አልነበረም ። አሁን ፡ ግን ፡
እንደ ፡ ቀደመው ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡
ቀሪታ ፡ ላይ ፡ አልሆንም ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡
፲፫ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰላምን ፡ እዘ
ራለሁ ፤ ወይኑ ፡ ፍሬውን ፡ ይሰጣል ÷ ምድርም ፡
አዝመራዋን ፡ ታወጣለች ÷ ሰማያትም ፡ ጠላቸ
ውን ፡ ይሰጣሉ ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ቀሪታ ፡
፲፬ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አወርሳለሁ ። የይሁዳ ፡
ቤትና ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፡ በእሕዝብ ፡
ዘንድ ፡ እርግማን ፡ እንደ ፡ ነበራችሁ ÷ እንዲሁ ፡
አድናችኋለሁ ÷ በረከትም ፡ ትሆናላችሁ ፤ አት
ፍሩ ÷ እጃችሁንም ፡ አበርቱ ።

፲፭ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላልና ፡— አባቶቻችሁ ፡ እጅግ ፡ ባስቈጡኝ ፡
ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ እንዳሰብሁ ÷ እንዲሁ ፡
ተጸጸትሁም ÷ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚ
፲፮ አብሔር ÷ እንዲሁ ፡ ዳግመኛ ፡ ለኢየሩሳሌ
ምና ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ በጎነትን ፡
፲፯ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ አስቤአለሁ ፡ አትፍሩ ። የምት
ሠሩት ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እያንዳንዳችሁ ፡ ከባ
ልንጀራችሁ ፡ ጋር ፡ እውነትን ፡ ተነጋገሩ ፤ በበር ፡
አደበባያችሁም ፡ የእውነትንና ፡ የሰላምን ፡
፲፱ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤ ሁላችሁም ፡ በባልንጀራችሁ ፡
ላይ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ በልባችሁ ፡ አታስቡ ፤ የሐ
ሰትንም ፡ መሐላ ፡ አትውደዱ ፤ ይህን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ እጠላለሁና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

፳ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
፳፩ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የሠራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የአራ
ተኛው ፡ ወር ፡ ጾም ፡ የአምስተኛውም ፡ የሰባተ
ኛውም ፡ የአሥረኛውም ፡ ወር ፡ ጾም ፡ ለይሁዳ ፡
ቤት ፡ ደስታና ፡ ተድላ ፡ የሐሤትም ፡ በዓላት ፡
ይሆናል ፡ ስለዚህም ፡ እውነትንና ፡ ሰላምን ፡
፳፪ ውደዱ ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— በብዙ ፡ ከተሞች ፡ የሚቀ
መጡ ፡ አሕዛብ ፡ ገና ፡ ይመጣሉ ፤ በእንዲትም ፡ ፳፪
ከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡— እግዚአብሔርን ፡
እንለምን ፡ ዘንድ ÷ የሠራዊትንም ፡ ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ እንፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ እንሂድ ፤
እኔም ፡ እሄዳለሁ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ከተማ ፡
ይሄዳሉ ። ብዙ ፡ ወገኖችና ፡ ኃይለኞች ፡ አሕ ፳፪
ዛብ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሠራዊትን ፡ ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ÷ እግዚአብሔ
ርንም ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣሉ ። የሠራዊ ፳፫
ትም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከአሕዛብ ፡ ቋንቋ ፡ ሁሉ ፡ አሥር ፡
ሰዎች ፡ የእንዱን ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡
ዘርፍ ፡ ይዘው ፡— እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡
ጋር ፡ እንዳለ ፡ ሰምተናልና ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡
እንሂድ ፡ ይላሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ በሐድራክ ፡ ፩
ምድር ፡ ላይ ፡ ነው ÷ በደማስቆም ፡ ላይ ፡ ያር
ፍል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዓይን ፡ ወደ ፡ ሰውና ፡
ወደ ፡ እስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤
፪ ደግሞም ፡ በዳርቻዋ ፡ ባለችው ፡ በሐማት ፡ ፪
ላይ ÷ እጅግ ፡ ጠቢበኞች ፡ በሆኑ ፡ በጢሮስና ፡
በሲዶና ፡ ላይ ፡ ነው ። ጢሮስም ፡ ምሽግን ፡ ፫
ለራስዋ ፡ ሠርታለች ÷ ብሩንም ፡ እንደ ፡ አፈር ፡
ዋሩውንም ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ መንገድ ፡ ጭቃ ፡
አከማችታለች ። እነሆ ÷ ጌታ ፡ ይገፍፋታል ÷ ፬
በባሕርም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ብርታትዋን ፡ ይመ
ታታል ፤ እርስዋም ፡ በእሳት ፡ ትበላለች ። አስቀ ፭
ሎና ፡ አይታ ፡ ትፈራለች ፤ ጋዛ ፡ ደግሞ ፡ አይታ ፡
እጅግ ፡ ትታመማለች ፤ አቃሮንም ፡ እንዲሁ ÷
ተስፋዋ ፡ ይቄረጣልና ፤ ንጉሡም ፡ ከጋዛ ፡ ይጠ
ፋል ÷ በአስቀሎናም ፡ የሚቀመጥ ፡ አይገኝም ። ፮
የተደበለቀ ፡ ወገን ፡ በአዛጦን ፡ ይቀመጣል ÷ ፯
የፍልስጥኤማውያንንም ፡ ትዕቢት ፡ አጠፋለሁ ።
ደሙንም ፡ ከአፉ ፡ ውስጥ ፡ ርኩሱንም ፡ ነገር ፡ ፯
ከጥርሱ ፡ መካከል ፡ አስወግዳለሁ ፤ እርሱም ፡
ደግሞ ፡ ለአምላካችን ፡ ቀሪታ ፡ ይሆናል ፤ በይ
ሁዳም ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ይሆናል ÷ አቃሮንም ፡
እንደ ፡ ኢያቡሰዊ ፡ ይሆናል ። እኔም ፡ ማንም ፡ ፰
እንዳይሄድና ፡ እንዳይመለስ ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡
ጦር ፡ ሆኖ ፡ በቤቴ ፡ ዙሪያ ፡ ሰፈር ፡ አደር ፡ጋለሁ ፤
አሁንም ፡ በዓይኔ ፡ አይቻለሁና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
አስጨናቂ ፡ አያልፍባቸውም ።

አንቺ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ እጅግ ፡ ደስ ፡ ፱
ይበልሽ ፤ አንቺ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷
እልል ፡ በዪ ፤ እነሆ ÷ ንጉሥሽ ፡ ጻድቅና ፡ አዳኝ ፡
ነው ፤ ትሑትም ፡ ሆኖ ፡ በአህያም ÷ በአህያይቱ ፡
ግልገል ፡ በውርንጫይቱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡
ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣል ። ሰረገላውንም ፡ ከኤ ፲
ፍሬም ፡ ፈረሱንም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አጠፋለሁ ፤
የሰልፉም ፡ ቀስት ፡ ይሰበራል ÷ ለአሕዛብም ፡
ሰላምን ፡ ይናገራል ፤ ግዛቱም ፡ ከባሕር ፡ እስከ ፡

ባሕር ÷ ከወንዙም ፥ እስከ ፥ ምድር ፡ ዳርቻ ፥ ድረስ ፡ ይሆናል ።

፲፩ ለእንቺም ፥ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ቃል ፡ ኪዳንሽ ፡ ደም ÷ እስሮችሽን ፡ ውኃ ፡ ከሌለበት ፡ ጕድጓድ ፡

፲፪ አውጥቻለሁ ። እናንተ ፡ በተስፋ ፡ የምትኖሩ ፡ እስሮች ፡ ሆይ ÷ ወደ ፡ ጽኑ ፡ አምባ ፡ ተመ ለሱ ። ሁለት ፡ እጥፍ ፡ አድርጌ ፡ እንድመልስ

፲፫ ልሽ ፡ ዛሬ ፡ እነግርሻለሁ ። ይሁዳን ፡ ለእኔ ፡ ገት ሬአለሁ ፤ ቀስቱን ፡ በኤፍሬም ፡ ሞልቼአለሁ ፤ ጽዮን ፡ ሆይ ÷ ልጆችሽን ፡ በግሪክ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አስነሣለሁ ÷ አንቺንም ፡ እንደ ፡ ኃያል ፡

፲፬ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ አደርግሻለሁ ። እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ÷ ፍላጻውም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ይወጣል ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ መለከትን ፡ ይነፋል ÷ በደቡብም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡

፲፭ ይሄዳል ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቃቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ይበሉአቸዋል ÷ የወንጭፉንም ፡ ድንጋዮች ፡ ይረግጣሉ ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ጠጅም ፡ ይጠጡአቸዋል ÷ እንደ ፡ ጥዋ ምችም ፡ እንደ ፡ መሠዊያም ፡ ማዕዘኖች ፡ የተ

፲፮ ሞሉ ፡ ይሆናሉ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ መንጋ ፡ ያድና ቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ለአክሊል ፡ እንደሚሆኑ ፡ እንደ ፡ ከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ይሆናሉ ÷ በምድ

፲፯ ሩም ፡ ላይ ፡ ይብለጨለጫሉ ። በጎነቱ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ ውበቱስ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው ! እህል ፡ ጕበዛዝቱን ÷ ጕሽ ፡ ጠጅም ፡ ቄነ ጃጅቱን ፡ ያለመልማል ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ በኋለኛው ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዝናቡን ፡ ለምኑ ፤ እግዚአብሔር ፡ መብ ረቅ ፡ ያደርጋል ፤ እርሱም ፡ የበልግ ፡ ዝናብን ፡ ለእያንዳንዱም ፡ በሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ሣርን ፡ ይሰ

፪ ጣል ። ተራፊም ፡ ከንቱነትን ፡ ተናግረዋልና ÷ ምዋርተኞችም ፡ ውሸትን ፡ አይተዋልና ፤ ሕል ምንም ፡ የሚያዩ ፡ በሐሰት ፡ ተናግረዋል ÷ በከ ንቱም ፡ ያጽናናሉ ፤ እረኛም ፡ የላቸውምና ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ ተቅበዝብዘዋል ፡ ተጨንቀውማል ።

፫ ቍጣዬ ፡ በእረኞች ፡ ላይ ፡ ነድዶአል ÷ አውራ ፡ ፍየሎችንም ፡ እቀጣለሁ ፤ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ መንጋውን ፡ ጐብኝቶአል ÷ በሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡

፬ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ፈረስ ፡ ያደርጋቸዋል ። ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የማዕዘኑ ፡ ድንጋይ ÷ ከእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ችንካሩ ÷ ከእርሱም ፡ ዘንድ ፡ የሰልፉ ፡ ቀስት ÷ ከእርሱም ፡ ዘንድ ፡ አስገባሪው ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡

፭ ላይ ፡ ይመጣሉ ። በሰልፍም ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ በመንገድ ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚረ ግጡ ፡ ኃያላን ፡ ይሆናሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ ይዋጋሉ ÷ ፈረሰኞችም ፡

፮ ያፍራሉ ። ወድጃቸዋለሁና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ አበረታለሁ ÷ የዮሴፍንም ፡ ቤት ፡ አድናለሁ ፤ አደላድላቸዋለሁም ፤ እመልሳትዋለሁ ፤ እኔም ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ÷ እኔም ፡ እሰማቸዋለሁና ፡ እንዳልጣልኋቸው ፡ ይሆናሉ ።

፯ የኤፍሬምም ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኃያላን ፡ ይሆ ናሉ ÷ ልባቸውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ ጠጣ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ልጆቻቸውም ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ÷ ልባቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ።

፰ ተቤዣቸዋለሁና ፡ በፉጨት ፡ ጠርቼ ፡ እሰበ ስባቸዋለሁ ፤ ቀድሞም ፡ በዝተው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ይበዛሉ ። በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ብዘራቸው ፡

፱ እንኳ ፡ በሩቅ ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ ያስቡኛል ÷ ከልጆ ቻቸውም ፡ ጋር ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፡ ይመ ለሱማል ። ከግብጽም ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋ ለሁ ÷ ከአሦርም ፡ እሰበስባቸዋለሁ ፤ ወደ ፡ ገለዓ ድና ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ምድር ፡ አመጣቸዋለሁ ÷ የሚበቃም ፡ ቦታ ፡ አይገኝላቸውም ። እርሱም ፡

፲ በጭንቅ ፡ ባሕር ፡ ያልፋል ÷ የባሕርንም ፡ ሞገድ ፡ ይመታል ÷ የወንዙም ፡ ጥልቅ ፡ ሁሉ ፡ ይደር ቃል ፤ የአሦርም ፡ ትዕቢት ፡ ይዋረዳል ÷ የግብ ጽም ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ይርቃል ። በእምላክ ቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አበረታቸዋለሁ ÷ በስ ሙም ፡ ይመካሉ ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ ሊባኖስ ፡ ሆይ ÷ ደጆችህን ፡ ክፈት ÷ እሳትም ፡

፪ ዝግባዎችህን ፡ ትብላ ። የጥድ ፡ ዛፍ ፡ ሆይ ÷ ዝግባ ፡ ወድቆአልና ÷ ከበርቴዎችም ፡ ጠፍተዋልና ፡ ዋይ ፡ በል ፤ እናንተም ፡ የባሳን ፡ ዛፎች ፡ ሆይ ÷ ጽኑው ፡ ጫካ ፡ ተቈርጦአልና ፡ ዋይ ፡ በሉ ።

፫ የእረኞች ፡ ክብር ፡ ተዋርዶአልና ፡ የዋይታቸው ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቶአል ፤ የዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ ተዋርዶአልና ፡ የአንበሶች ፡ ግሣት ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቶአል ።

፬ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ አል ፦ ለእርድ ፡ የሚሆኑትን ፡ በጎች ፡ ጠብቅ ።

፭ የገዙአቸው ፡ ያርዱአቸዋል ÷ ራሳቸውንም ፡ እንደ ፡ በደለኞች ፡ አድርገው ፡ አይቈጥሩም ፤ የሸጡአቸውም ፦ በለ ፡ ጠጋ ፡ ሆነናልና ፡ እግዚ አብሔር ፡ ይመስገን ፡ ይላሉ ፤ እረኞቻቸውም ፡ አይራሩላቸውም ። ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በም

፮ ድር ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ አልራራም ÷ ይላል ፡ እግ ዚአብሔር ፤ እነሆም ÷ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በባልን ጀራውና ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ፤ ምድሪቱንም ፡ ይመታሉ ÷ ከእጃቸውም ፡ አላድ ናቸውም ።

፯ እኔም ፡ ለእርድ ፡ የሚሆኑትን ፡ በጎች ÷ የመ ንጋውን ፡ ችግረኞች ፡ ጠበቅሁ ። ሁለት ፡ በት ሮችንም ፡ ወሰድሁ ፤ የአንዲቱን ፡ ስም ፡ ውበት ÷ የሁለተኛይቱንም ፡ ስም ፡ ግሰሬያ ፡ ብዬ ፡ ጠራሁ ፤ መንጋውንም ፡ ጠበቅሁ ። በአንድ ፡ ወርም ፡

፰ ሦስቱን ፡ እረኞች ፡ አጠፋሁ ፤ ነፍሴም ፡ ተሰቀቀቻቸው ÷ ነፍሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ እኔን ፡ ጠላች ። እኔም ፡ — እናንተን ፡ አልጠብቅም ፤ የሚሞ

ተው ፡ ይሙት ÷ የሚጠፋውም ፡ ይጥፋ ፤ የቀ ረውም ፡ እያንዳንዱ ፡ የባልንጀራውን ፡ ሥጋ ፡

፱ ይብላ ፡ አለው ። እኔም ፡ ከሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ የገባሁትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ውበት ፡ የተባለችውን ፡ በትሬን ፡ ወሰጀ ፡ ቈረ ጥሁ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ተሰበረች ፤ እንዲሁም ፡

፲፩ እኔን ፡ የተመለከቱ ፡ የመንጋው ፡ ችግረኞች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አወቁ ።

፲፪ እኔም ፡ — ደስ ፡ ብሎአችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ዬን ፡ ስጡኝ ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ተዉት ፡ አልሁ ። እነርሱም ፡ ለዋጋዬ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ መዘኑ ።

፲፫ እግዚአብሔርም ፡ — የተሰማሙበትን ፡ የከበረ ውን ፡ ዋጋዬን ፡ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አኑ ረው ፡ አለኝ ። እኔም ፡ ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ወሰጀ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በለው ፡ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡

፲፬ ውስጥ ፡ አኖርሁት ። በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ ወንድማማችነት ፡ አሰ ብር ፡ ዘንድ ፡ ማሰሪያ ፡ የተባለችውን ፡ ሁለተኛ ይቱን ፡ በትሬን ፡ ቈረጥሁ ።

፲፭ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳግመ

፲፮ ኛም ፡ የሰነፍን ፡ እረኛ ፡ ዕቃ ፡ ውሰድ ። እነሆ ÷ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ እረኛ ፡ አስነሣለሁ ፤ እርሱም ፡ የጠፋውን ፡ አያስብም ÷ የበዘነውን ፡ አይፈል ግም ÷ የተሰበረውን ፡ አይጠግንም ፤ የጻነው ንም ፡ አይቀልብም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ የሰባውን ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ÷ ሰኰሩውንም ፡ ይቀለጣጥማል ።

፲፯ መንጋውን ፡ ለሚተው ፡ ለምናምንቴ ፡ እረኛ ፡ ወዮለት ! ሰይፍ ፡ በክንዱና ፡ በቀኝ ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፤ ክንዱም ፡ ኣጥብቃ ፡ ትደርቃ ለች ÷ ቀኝ ፡ ዓይኑም ፡ ፈጽማ ፡ ትጨልማለች ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ስለ ፡ እስራኤል ፡ የተነገረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሰማያትን ፡ የዘረጋ ÷ ምድርንም ፡ የመሠረተ ÷ የሰውንም ፡ መንፈስ ፡ በውስጡ ፡ የሠራ ፡ እግዚ

፪ አብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ÷ ኢየሩሳ ሌምን ፡ በዙሪያዋ ፡ ላሉት ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የመንገድገድ ፡ ዋንጫ ፡ አደርጋታለሁ ፤ ደግ ሞም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስትከበብ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡

፫ እንዲሁ ፡ ይሆናል ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢየሩሳ ሌምን ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከባድ ፡ ድንጋይ ፡ አደ ርጋታለሁ ፤ የሚሸከሙአት ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ይቈ ስላሉ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በላይዋ ፡

፬ ላይ ፡ ይከማቻሉ ። በዚያ ፡ ቀን ÷ ይላል ፡ እግ ዚአብሔር ÷ ፈረስን ፡ ሁሉ ፡ በድንጋጤ ÷ ተቀ ማጭንም ፡ በእብድነት ፡ እመታለሁ ፤ ዓይኖቼ ንም ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እከፍታለሁ ÷ የአሕዛብ ንም ፡ ፈረሶች ፡ ሁሉ ፡ በዕውርነት ፡ እመታለሁ ።

፭ የይሁዳም ፡ አለቆች ፡ በልባቸው ፡ — በኢየሩሳ ሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ በአምላካቸው ፡ በሠራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ብርታት ፡ አለ ፡ ይላሉ ።

፮ በዚያ ፡ ቀን ፡ የይሁዳን ፡ አለቆች ፡ በእንጨት ፡ መከከል ፡ እንዳለ ፡ ትንታግ ÷ በነዶችም ፡ መካ

ከል ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ነበልባል ፡ አደርጋ ቸዋለሁ ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ በዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይበላሉ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በስፍራዋ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትኖ

፯ ራለች ። እግዚአብሔርም ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ክብርና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ በይ ሁዳ ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ እንዳይታበይ ፡ የይሁዳን ፡

፰ ድንኳኖች ፡ አስቀድሞ ፡ ያድናል ። በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖ ሩት ፡ ይመክትላቸዋል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከእነ ርሱ ፡ መከከል ፡ ደክማው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ይሆ ናል ፤ የዳዊትም ፡ ቤት ፡ በፊታቸው ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ይሆ

፱ ናል ። በዚያም ፡ ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ የሚመጡትን ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ለማጥፋት ፡ እጋ ደላለሁ ።

፲ በዳዊትም ፡ ቤት ፡ ላይ ÷ በኢየሩሳሌምም ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ÷ የሞገስንና ፡ የልመናን ፡ መን ፈስ ፡ አፈስሳለሁ ፤ ወደ ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ወጉት ፡ ይመለከታሉ ፤ ሰውም ፡ ለአንድያ ፡ ልጁ ፡ እንደ ሚያለቅስ ፡ ያለቅሱለታል ÷ ሰውም ፡ ለበዙር ፡ ልጁ ፡ እንደሚያዝን ፡ በመራራ ፡ ኀዘን ፡ ያዝኑ

፲፩ ለታል ። በዚያ ፡ ቀን ፡ በመጊዶን ፡ ሜዳ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ሐዳድሪሞን ፡ ልቅሶ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይሆናል ። ምድሪቱም ፡

፲፪ ታለቅሳለች ፤ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ÷ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ÷ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የናታን ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ÷ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የሌዊ ፡ ቤት ፡

፲፫ ወገን ፡ ለብቻው ÷ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የሰሜኢ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ÷ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የቀሩት ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ እያንዳ

፲፬ ንዱ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ÷ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻ ቸው ፡ ያለቅሳሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለዳዊት ፡ ቤትና ፡ በኢየሩሳ ሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ ከኃጢአትና ፡ ከርኵሰት ፡ የሚያነጻ ፡ ምንጭ ፡ ይከፈታል ። በዚያ ፡ ቀን ÷

፪ ይላል ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ÷ የጣ ዖታትን ፡ ስም ፡ ከምድር ፡ አጠፋለሁ ÷ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይታሰቡም ፤ ደግሞም ፡ ሐሰተኞችን ፡ ነቢያትና ፡ ርኩስ ፡ መንፈስን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አስ

፫ ወግዳለሁ ። ማንም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ቢናገር ፡ የወለዱት ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፡ — አንተ ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ስም ፡ ሐሰትን ፡ ተናግረሃልና ፡ በሕይ ወት ፡ አትኖርም ፡ ይሉታል ፤ ትንቢትንም ፡ ሲና ገር ፡ የወለዱት ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ይወጉታል ።

፬ በዚያም ፡ ቀን ፡ ነቢያቱ ፡ ሁሉ ፡ ትንቢትን ፡ ሲና ገሩ ፡ እያንዳንዱ ፡ ስለ ፡ ራእዩ ፡ ያፍራል ፤ ያታ ልሉም ፡ ዘንድ ፡ የማቅ ፡ ልብስ ፡ አይለብሱም ።

፭ እርሱ ፡ ግን ፡ — ከታናሽነቴ ፡ ጀምሮ ፡ በሬያ ዞኜ ፡ ነበርሁና ፡ ገበሬ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ነቢይ ፡ አይደለሁም ፡ ይላል ። ሰውም ፡ — ይህ ፡

፮

በእጅህ፥ መካከል፥ ያለ፥ ቀኑስ፥ ምንድር፥ ነው? ይለዋል ። እርሱም ፦— በወዳጆቼ፥ ቤት፥ የቄሰ
ልሁት፥ ቀኑስ፥ ነው፥ ይላል ።
፮ ሰይፍ፥ ሆይ÷ ባልንጀራዬ፥ በሆነው፥ ሰው፥ በእረኛዬ፥ ላይ፥ ንቃ÷ ይላል፥ የሠራዊት፥ ጌታ፥ እግዚአብሔር ፤ እረኛውን፥ ምታ÷ በጎ
ቹም፥ ይበተናሉ ፤ እጄንም፥ በታናናሾች፥ ላይ፥
፯ እመልሳለሁ ። በምድርም፥ ሁሉ፥ ላይ፥ ሁለት፥ ክፍል፥ ተቈርጠው፥ ይሞታሉ÷ ይላል፥ እግ
ዚአብሔር ፤ ሦስተኛውም፥ ክፍል፥ በእርስዋ፥
፰ ውስጥ፥ ይቀራል ። ሦስተኛውንም፥ ክፍል፥ ወደ፥ እሳት፥ አገባለሁ÷ ብርም፥ እንደሚነዋር፥ አነዋራቸዋለሁ÷ ወርቅም፥ እንደሚፈተን፥ እፈ
ትናቸዋለሁ ፤ እነርሱም፥ ስሜን፥ ይጠራሉ÷ እኔም፥ እሰማቸዋለሁ፤ እኔም፦— ይህ፥ ሕዝቤ፥ ነው፥ እላለሁ ፤ እርሱም፦— እግዚአብሔር፥ አምላኬ፥ ነው፥ ይላል ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

፩ እነሆ÷ የእግዚአብሔር፥ ቀን፥ ይመጣል÷
፪ ብዝበዛሽንም፥ በውስጥሽ፥ ይከፈላሉ ። አሕዛ
ብንም፥ ሁሉ፥ በኢየሩሳሌም፥ ላይ፥ ለሰልፍ፥ አሰበስባለሁ ፤ ከተማይቱም፥ ትያዛለች ÷ ቤቶ
ችም፥ ይበዘበዛሉ ÷ ሴቶችም፥ ይነወራሉ ፤ የከተማይቱም፥ እኵሌታ፥ ለምርኮ፥ ይወጣል÷ የቀረው፥ ሕዝብ፥ ግን፥ ከከተማ፥ አይጠፋም ።
፫ እግዚአብሔርም፥ ይወጣል÷ በሰልፍም፥ ቀን፥ እንደ፥ ተዋጋ፥ ከእነዚያ፥ አሕዛብ፥ ጋር፥ ይዋ
፬ ጋል ። በዚያም፥ ቀን፥ እግሮቹ፥ በኢየሩሳሌም፥ ትይዩ፥ በምሥራቅ፥ በኩል፥ ባለው፥ በደብረ፥ ዘይት፥ ላይ፥ ይቆማሉ ፤ ደብረ፥ ዘይትም፥ በመ
ካከል፥ ወደ፥ ምሥራቅና፥ ወደ፥ ምዕራብ፥ ይሰ
ነጠቃል÷ እጅግም፥ ታላቅ፥ ሸለቆ፥ ይሆናል ፤ የተራራውም፥ እኵሌታ፥ ወደ፥ ሰሜን÷ እኵሌ
፭ ታውም፥ ወደ፥ ደቡብ፥ ይርቃል ። የተራሮ
ችም፥ ሸለቆ፥ እስከ፥ አጸል፥ ይደርሳልና፥ በተራሮች፥ ሸለቆ፥ ትሸሻላችሁ ፤ በይሁዳም፥ ንጉሥ፥ በዖዝያን፥ ዘመን፥ ከሆነው፥ ከም
ድር፥ መናወጥ፥ ፊት፥ እንደ፥ ሸሻችሁ፥ ትሸ
ሻላችሁ ። አምላኬ፥ እግዚአብርሃም፥ ከቅ
፮ ዱሳኑ፥ ሁሉ፥ ጋር፥ ይመጣል ። በዚያም፥ ቀን፥ በረዶና፥ ውርጭ፥ እንጂ፥ ብርሃን፥ አይሆንም ።
፯ አንድ፥ ቀንም፥ ይሆናል÷ እርሱም፥ በእግዚአ
ብሔር፥ ዘንድ፥ የታወቀ፥ ይሆናል ፤ ቀንም፥ አይሆንም÷ ሌሊትም፥ አይሆንም ፤ ሲመሽም፥
፰ ብርሃን፥ ይሆናል ። በዚያም፥ ቀን፥ የሕይወት፥ ውኃ፥ ከኢየሩሳሌም፥ ይወጣል ፤ እኵሌታው፥ ወደ፥ ምሥራቁ፥ በሕር÷ እኵሌታውም፥ ወደ፥ ምዕራቡ፥ በሕር፥ ይሄዳል ፤ ይህ፥ በበጋና፥ በክ
ረምት፥ ይሆናል ።
፱ እግዚአብሔርም፥ በምድር፥ ሁሉ፥ ላይ፥ ይነ
ግሣል ። በዚያ፥ ቀን፥ እግዚአብሔር፥ አንድ÷ ስሙም፥ አንድ፥ ይሆናል ። ምድር፥ ሁሉ፥ ከጌባ፡ጀምሮ፡በኢየሩሳሌምም፡ደቡብ፡በኩል፡ አስካለችው፡ አስከ፡ ሬሞን፡ ድረስ፡ ተለውጣ፡ እንደ፡ ዓረባ፡ ትሆናለች ፤ እርስዋም፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ትላለች ÷ ከብንያምም፡ በር፡ ጀምሮ፡ አስከ፡ ፊተኛው፡ በር፡ ስፍራ፡ አስከ፡ ማዕዘኑ፡ በር፡ ድረስ÷ ከሐናንኤልም፡ ግንብ፡ ጀምሮ፡ አስከ፡ ንጉሡ፡ መጥመቂያ፡ ድረስ፡ በስፍራዋ፡ ትኖራለች ። ሰዎችም፡ይኖሩባታል÷ ከዚያም፡ ወዲያ፡ እርግማን፡ አይሆንም ፤ ኢየሩሳሌምም፡ ተዘልላ፡ ትኖራለች ።
፲፪ እግዚአብሔርም፡ ከኢየሩሳሌም፡ ጋር፡ የተ
ዋጉትን፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡ የሚቀሥፍበት፡ ቸነ
ፈር፡ ይህ፡ ነው ። በእግራቸው፡ ሲቆሙ፡ ሥጋ
ቸው፡ ይበሰብሳል ÷ ዓይናቸቸውም፡ በዓይን፡ ስባቸው፡ ውስጥ፡ ይበሰብሳሉ÷ ምላሳቸውም፡ በአፋቸው፡ ውስጥ፡ ይበሰብሳል ። በዚያም፡
፲፫ ቀን፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ታላቅ፡ ሽብር፡ በእነርሱ፡ ላይ፡ ይሆናል ፤ እያንዳንዱም፡ የባ
ልንጀራውን፡ እጅ፡ ይይዛል ÷ እጁም፡ በባል
ንጀራው፡ እጅ፡ ላይ፡ ይነሣል ። ይሁዳም፡
፲፬ ደግሞ፡ በኢየሩሳሌም፡ ውስጥ፡ ሆኖ፡ ይዋ
ጋል ፤ በዙሪያም፡ ያሉት፡ የአሕዛብ፡ ሁሉ፡ ሀብት፡ እጅግ፡ ብዙ፡ ወርቅና፡ ብር፡ ልብስም፡ ይሰበሰባል ። በፈረስና፡ በበቅሎ÷ በግመልና፡ በአህያ÷ በዚያም፡ ሰፈር፡ ባለ፡ እንስሳ፡ ሁሉ፡ ላይ፡ የሆነ፡ ቸነፈር፡ እንደዚያ፡ ያለ፡ ቸነፈር፡ ይሆናል ።
፲፭ በኢየሩሳሌም፡ ላይ፡ ከመጡት፡ ከአሕዛብ፡ ሁሉ፡ የቀሩት፡ ሁሉ፡ ለንጉሡ፡ ለሠራዊት፡ ጌታ፡ ለእግዚአብሔር፡ ይሰግዱ፡ ዘንድ÷ የዳስ፡ በዓልንም፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ በየዓመቱ፡ ይወ
፲፮ ጣሉ ። ከምድርም፡ ወገኖች፡ ሁሉ፡ ለንጉሡ፡ ለሠራዊት፡ ጌታ፡ ለእግዚአብሔር፡ ይሰግዱ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ለማይወጡ፡ ለእነርሱ፡ ዝናብ፡ አይዘንብላቸውም ። የግብጽም፡ ወገን፡
፲፯ ባይወጣ፡ ወደዚያም፡ ባይመጣ÷ እግዚአብሔር፡ የዳስ፡ በዓልን፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ የማይወጡትን፡ አሕዛብ፡ የሚቀሥፍበት፡ ቸነፈር፡ በእርሱ፡ ላይ፡ ይሆናል ። የግብጽ፡ ቅጣት÷ የዳስ፡ በዓ
፲፱ ልንም፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ የማይወጡት፡ የአሕ
ዛብ፡ ሁሉ፡ ቅጣት፡ እንደዚህ፡ ይሆናል ።
፳ በዚያ፡ ቀን፡ በፈረሶች፡ ኅዙራ፡ ላይ፡— ለእግ
ዚአብሔር፡ የተቀደሰ፡ ተብሎ፡ ይጻፋል ፤ በእ
ግዚአብሔርም፡ ቤት፡ ያሉ፡ ምንቸቶች፡ በመ
ሠዊያው፡ ፊት፡ እንዳሉ፡ ዳካዎች፡ ይሆናሉ ።
፳፩ በኢየሩሳሌምና፡ በይሁዳ፡ ያሉ፡ ምንቸቶችም፡ ሁሉ፡ ለሠራዊት፡ ጌታ፡ ለእግዚአብሔር፡ የተ
ቀደሱ፡ ይሆናሉ ፤ የሚሠዉትም፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይመጣሉ ፤ ከእነዚያም፡ ወስደው፡ ይቀቅሉባ
ቸዋል ። በዚያም፡ ቀን፡ በሠራዊት፡ ጌታ፡ በእ
ግዚአብሔር፡ ቤት፡ ከነጋናዊው፡ ከእንግዳህ፡ ወዲያ፡ አይገኝም ።

* * *

ትንቢተ፡ ሚልክያስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በሚልክያስ፡ እጅ፡ ለእስራኤል፡ የሆነ፡ የእ
ግዚአብሔር፡ ቃል፡ ሸክም፡ ይህ፡ ነው ።
፪ ወድኃችኋለሁ÷ ይላል፡ እግዚአብሔር ፤ እና
ንተ፡ ግን፦— በምን፡ ወደድኸን? ብላችኋል ። ዔሳው፡ የያዕቆብ፡ ወንድም፡ አልነበረምን? ይላል፡ እግዚአብሔር ፤ ያዕቆብንም፡ ወደድሁ÷
፫ ዔሳውንም፡ ጠላሁ፡ ተራሮቹንም፡ በረገ፡ አደ
ረግኋቸው÷ ርስቱንም፡ ለምድረ፡ በዳ፡ ቀበ
፬ ሮች፡ አሳልፌ፡ ሰጠኋቸው ። ኤዶምያስ፡ ፦— እኛ፡ ፈርሰናል÷ ነገር፡ ግን፡ የፈረሰውን፡ መልሰን፡ እንሠራለን፡ ቢል÷ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ይላል፡— እነርሱ፡ ይሠራሉ÷ እኔ፡ ግን፡ አፈርሳለሁ፡ በሰዎችም፡ ዘንድ፡— የበደል፡ ዳርቻና፡ እግዚአብሔር፡
፭ ለዘላለም፡ የተቈጣው፡ ሕዝብ፡ ይባላል ። ዓይ
ኖቻችሁም፡ ያያሉ÷ እናንተም፡— እግዚአብ
ሔር፡ ከእስራኤል፡ ዳርቻ፡ ወዲያ፡ ታላቅ፡ ይሁን፡ ትላላችሁ።
፮ እናንተ፡ ስሜን፡ የምታቃልሉ፡ ካህናት፡ ሆይ÷ ልጅ፡ አባቱን÷ ባሪያም፡ ጌታውን፡ ያክ
ብራል ፤ እኔስ፡ አባት፡ ከሆንሁ፡ ክብሬ፡ ወዴት፡ አለ? ጌታስ፡ ከሆንሁ፡ መፈራቴ፡ ወዴት፡ አለ? ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። እና
ንተም፡— ስምህን፡ያቃለልን፡ በምንድር፡ነው?
፯ ብላችኋል ። በመሠዊያዬ፡ ላይ፡ ርኩስ፡ እን
ጀራ፡ ታቀርባላችሁ ። እናንተም፡— ያረከስንህ፡ በምንድር፡ ነው? ብላችኋል ። የእግዚአብሔር፡ ገበታ፡ የተናቀ፡ ነው፡ በማለታችሁ፡ ነው ።
፰ ዕውር፡ መሥዋዕትንም፡ ስታቀርቡ፡ ይህ፡ ክፋ፡ አይደለምን? አንካሳውንና፡ የታመመውን፡ ስታቀርቡ፡ ይህ፡ ክፋ፡ አይደለምን? ያንን፡ ለአለቃህ፡ አቅርብ፤ በውኑ፡ በአንተ፡ ደስ፡ ይል
ዋልን? ወይስ፡ ፊትህን፡ ይቀበላልን? ይላል፡
፱ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። አሁንም፡ ጸጋን፡ ይስጠን፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔርን፡ ለምኑ፤ ይህ፡ ከእጃችሁ፡ የተሰጠ፡ ሲሆን፡ ከቶ፡ ፊታ
፲ ችሁን፡ ይቀበላልን? ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። በመሠዊያዬ፡ ላይ፡ እሳትን፡ በከንቱ፡ እንዳታቃጥሉ፡ ከእናንተ፡ ሆን፡ ደጅ፡ የሚዘጋ፡ ሰው፡ ምነው፡ በተገኘ! በእና
ንተ፡ ደስ፡ አይለኝም÷ ቍርባንንም፡ ከእጃ
ችሁ፡ አልቀበልም÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡
፲፩ እግዚአብሔር ። ከወሐዩ፡ መውጫ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ሠሚይዖ፡ ድረስ፡ ስሜ፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ ታላቅ፡ ይሆናልና፡ በየስፍራውም፡ ለስሜ፡ ዕጣን፡ ያጥናሉ÷ ንጹሕም፡ ቍርባን፡ ያቀርባሉ ፤ ስሜ፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ ታላቅ፡ ይሆናልና÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአ
ብሔር ። እናንተ፡ ግን፦— የእግዚአብሔር፡ ገበታ፡ ርኩስ፡ ነው፡ ፍሬውና፡ መብሉም፡ የተ
፲፪ ናቀ፡ ነው፡ በማለታችሁ፡ አስነቀፋችሁት ።
፲፫ እናንተ፡— እነሆ÷ ይህ፡ ድክም፡ ነው፡ ብላ
ችሁ፡ ጠቀ፡ አላችሁበት÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። በቅሚያ፡ የያዛችሁት
ንም፡ እንከሳውንም፡ የታመመውንም፡ አቅር
ባችኋል ፤ እንዲሁ፡ ቍርባንን፡ ታመጣላችሁ፤
፲፬ በውኑ፡ ከእጃችሁ፡ የሆነ፡ ይህን፡ ልቀበለው? ይላል፡ እግዚአብሔር ። እኔ፡ ታላቅ፡ ንጉሥ፡ ነኝና÷
፲፭ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር÷ ስሜም፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ የተፈራ፡ ነውና፡ በመንጋው፡ ውስጥ፡ ተባት፡ እያለው፡ ለጌታ፡ ተስሎ፡ ነውረኛውን፡ የሚሠዋ፡ ሸንጋይ፡ ሰው፡ ርጉም፡ ይሁን ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ አሁንም፡ እናንተ፡ ካህናት፡ ሆይ÷ ይህ፡ ትእ
፪ ዛዝ፡ ለእናንተ፡ ነው ። ለስሜ፡ ክብር፡ ትሰጡ፡ ዘንድ፡ በትሰሙ÷ በልባችሁም፡ በታደርጉት÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር÷ እር
ግማን፡ አሰድድባችኋለሁ÷ በረከታችሁንም፡ እረግማታለሁ፡ አውንም፡ በልባችሁ፡ አላደረጋ
፫ ችሁትምና፡ እኔ፡ ረግሜአታለሁ ። እነሆ÷ ክን
ዳችሁን፡ እገሥዳለሁ÷ የመሥዋዕታችሁንም፡ ፋንድያ፡ በፊታችሁ፡ ላይ፡ እበትናለሁ፡ ከእር
ሱም፡ ጋር፡ በእንድነት፡ ትወሰዳላችሁ ።
፬ ቃል፡ ኪዳኔ፡ ከሌዊ፡ ጋር፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ይህን፡ ትእ
ዛዝ፡ እንደ፡ ሰደድሁላችሁ፡ ታውቃላችሁ÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። ቃል፡
፭ ኪዳኔ፡ ከእርሱ፡ ጋር፡ የሕይወትና፡ የሰላም፡ ቃል፡ ኪዳን፡ ነበረ፤ ይፈራ፡ ዘንድም፡ እንር
ሱን፡ ሰጠሁት፡ እርሱም፡ ፈራኝ÷ ከስሜም፡ የተነሣ፡ ደነገጠ ። የእውነት፡ ሕግ፡ በአፉ፡
፮ ውስጥ፡ ነበረች÷ በከንፈሩም፡ ውስጥ፡ በደል፡ አልተገኘበትም ፤ ከእኔም፡ ጋር፡ በሰላምና፡ በቅንነት፡ ሄደ÷ ብዙ፡ ሰዎችንም፡ ከኃጢአት፡ መለሰ ። ካህኑ፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ የእግዚአብ
፯ ሔር፡ መልእክተኛ፡ ነውና፡ ከንፈሮቹ፡ እውቀ
ትን፡ ይጠብቁ፡ ዘንድ፡ ይገባቸዋል÷ ሰዎችም፡ ሕግን፡ ከእሱ፡ ይፈልጉ፡ ዘንድ፡ ይገባቸዋል ። እናንተ፡ ግን፡ ከመንገዱ፡ ፈቀቅ፡ ብላችኋል ፤
፰ በሕግም፡ ብዙ፡ ሰዎችን፡ አሰናክላችኋል ፤ የሌ
ዊንም፡ ቃል፡ ኪዳን፡ አስነውራችኋል÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ፡ መን
፱ ገዴን፡ እንዳልጠበቃችሁ÷ በሕግም፡ ለሰው፡ ፊት፡ እንዳዳላችሁ፡ መጠን÷ እኔ፡ ደግሞ፡ በሕዝብ፡ ሁሉ፡ ፊት፡ የተናቃችሁና፡ የተዋረ
ዳችሁ፡ አድርጌአችኋለሁ ።
፲ ለሁላችን፡ አንድ፡ አባት፡ ያለን፡ አይደለምን? ብሔር ። እናንተ፡ ግን፦— የእግዚአብሔር፡ ገበታ፡ ርኩስ፡ ነው፡ ፍሬውና፡ መብሉም፡ የተ
፲፪ ናቀ፡ ነው፡ በማለታችሁ፡ አስነቀፋችሁት ።
፲፫ እናንተ፡— እነሆ÷ ይህ፡ ድክም፡ ነው፡ ብላ
ችሁ፡ ጠቀ፡ አላችሁበት÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። በቅሚያ፡ የያዛችሁት
ንም፡ እንከሳውንም፡ የታመመውንም፡ አቅር
ባችኋል ፤ እንዲሁ፡ ቍርባንን፡ ታመጣላችሁ፤
፲፬ በውኑ፡ ከእጃችሁ፡ የሆነ፡ ይህን፡ ልቀበለው? ይላል፡ እግዚአብሔር ። እኔ፡ ታላቅ፡ ንጉሥ፡ ነኝና÷
፲፭ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር÷ ስሜም፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ የተፈራ፡ ነውና፡ በመንጋው፡ ውስጥ፡ ተባት፡ እያለው፡ ለጌታ፡ ተስሎ፡ ነውረኛውን፡ የሚሠዋ፡ ሸንጋይ፡ ሰው፡ ርጉም፡ ይሁን ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ አሁንም፡ እናንተ፡ ካህናት፡ ሆይ÷ ይህ፡ ትእ
፪ ዛዝ፡ ለእናንተ፡ ነው ። ለስሜ፡ ክብር፡ ትሰጡ፡ ዘንድ፡ በትሰሙ÷ በልባችሁም፡ በታደርጉት÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር÷ እር
ግማን፡ አሰድድባችኋለሁ÷ በረከታችሁንም፡ እረግማታለሁ፡ አውንም፡ በልባችሁ፡ አላደረጋ
፫ ችሁትምና፡ እኔ፡ ረግሜአታለሁ ። እነሆ÷ ክን
ዳችሁን፡ እገሥዳለሁ÷ የመሥዋዕታችሁንም፡ ፋንድያ፡ በፊታችሁ፡ ላይ፡ እበትናለሁ፡ ከእር
ሱም፡ ጋር፡ በእንድነት፡ ትወሰዳላችሁ ።
፬ ቃል፡ ኪዳኔ፡ ከሌዊ፡ ጋር፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ይህን፡ ትእ
ዛዝ፡ እንደ፡ ሰደድሁላችሁ፡ ታውቃላችሁ÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። ቃል፡
፭ ኪዳኔ፡ ከእርሱ፡ ጋር፡ የሕይወትና፡ የሰላም፡ ቃል፡ ኪዳን፡ ነበረ፤ ይፈራ፡ ዘንድም፡ እንር
ሱን፡ ሰጠሁት፡ እርሱም፡ ፈራኝ÷ ከስሜም፡ የተነሣ፡ ደነገጠ ። የእውነት፡ ሕግ፡ በአፉ፡
፮ ውስጥ፡ ነበረች÷ በከንፈሩም፡ ውስጥ፡ በደል፡ አልተገኘበትም ፤ ከእኔም፡ ጋር፡ በሰላምና፡ በቅንነት፡ ሄደ÷ ብዙ፡ ሰዎችንም፡ ከኃጢአት፡ መለሰ ። ካህኑ፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ የእግዚአብ
፯ ሔር፡ መልእክተኛ፡ ነውና፡ ከንፈሮቹ፡ እውቀ
ትን፡ ይጠብቁ፡ ዘንድ፡ ይገባቸዋል÷ ሰዎችም፡ ሕግን፡ ከእሱ፡ ይፈልጉ፡ ዘንድ፡ ይገባቸዋል ። እናንተ፡ ግን፡ ከመንገዱ፡ ፈቀቅ፡ ብላችኋል ፤
፰ በሕግም፡ ብዙ፡ ሰዎችን፡ አሰናክላችኋል ፤ የሌ
ዊንም፡ ቃል፡ ኪዳን፡ አስነውራችኋል÷ ይላል፡ የሠራዊት፡ ጌታ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ፡ መን
፱ ገዴን፡ እንዳልጠበቃችሁ÷ በሕግም፡ ለሰው፡ ፊት፡ እንዳዳላችሁ፡ መጠን÷ እኔ፡ ደግሞ፡ በሕዝብ፡ ሁሉ፡ ፊት፡ የተናቃችሁና፡ የተዋረ
ዳችሁ፡ አድርጌአችኋለሁ ።
፲ ለሁላችን፡ አንድ፡ አባት፡ ያለን፡ አይደለምን?

አንድ ፥ አምላክስ ፥ የፈጠረን ፥ አይደለምን ? የአባቶቻችንን ፥ ቃል ፥ ኪዳን ፥ ለማስነቀፍ ፥ እኛ ፥ እያንዳንዳችን ፥ ወንድማችንን ፥ ስለ ፤
፲፩ ምን ፥ አታለልን ? እግዚአብሔር ፥ የወደደውን ፥ መቅደስ ፥ ይሁዳ ፥ እርክሰአልና ÷ የእንግዳውንም ፥ አምላክ ፥ ልጅ ፥ ሚስት ፥ አድርጎ ፥ አግብቶአልና ፥ ይሁዳ ፥ አታልሎአል ÷ በእስራኤልና ፥ በኢየሩሳሌም ፥ ውስጥ ፥ ርኵሰት ፥ ተሠር
፲፪ ቶአል ። ይህን ፥ ከሚያደርግ ፥ ሰው ÷ እግዚአብሔር ፥ የሚጠራውንና ፥ የሚመልሰውን ፥ ለሠራዊትም ፥ ጌታ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ቍርበን ፥ የሚያቀርበውን ፥ ከያዕቆብ ፥ ድንኳን ፥ ያጠፋል ።
፲፫ ይህንም ፥ ደግሞ ፥ አድርጋችኋል ፤ እግዚአብሔር ፥ ቍርባኑን ፥ ዳግመኛ ፥ እንዳይመለከት ÷ ከእጃችሁም ፥ በደስታ ፥ እንዳይቀበለው ፥ መሠዊያውን ፥ በእንባና ፥ በልቅሶ ፥ በኀዘንም ፥ ትከድና
፲፬ ላችሁ ። እናንተም ፦ ስለ ፥ ምንድር ፥ ነው ? ብላ ችኋል ። ሚስትህ ፥ በልጃገረድህና ፥ የቃል ፥ ኪዳንህ ፥ ሚስት ፥ ሆና ፥ ሳለች ፥ እርስዋን ፥ አታልለሃታልና ፥ እግዚአብሔር ፥ በእንተና ፥ በልጅነት ፥ ሚስትህ ፥ መካከል ፥ ምስክር ፥ ስለ ፥ ሆነ ፥ ነው ።
፲፭ እግዚአብሔር ፥ የሕይወትን ፥ መንፈስ ፥ አንድ ፥ አድርጎ ፥ ጠብቆልን ፥ የለምን ? እርሱም ፥ የሚፈልገው ፥ ምንድር ፥ ነው ? ዘር ፥ አይደለምን ? ስለዚህ ፥ መንፈሳችሁን ፥ ጠብቁ ÷ ማንም ፥ የል
፲፮ ጅነት ፥ ሚስቱን ፥ አያታልል ። መፋታትን ፥ እጠላለሁ ÷ ይላል ፥ የእስራኤል ፥ አምላክ ፥ እግዚአብሔር ÷ ልብሱንም ፥ በግፍ ፥ ሥራ ፥ የሚከደነውን ፥ ሰው ፥ እጠላለሁ ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ ስለዚህ ፥ እንዳታታልሉ ፥ መንፈሳችሁን ፥ ጠብቁ ።
፲፯ እግዚአብሔርን ፥ በቃላችሁ ፥ አታክታችኋል ። እናንተም ፦ ያታክትነው ፥ በምንድር ፥ ነው ? ብላችኋል ። ክፉን ፥ የሚያደርግ ፥ ሁሉ ፥ በእግዚአብሔር ፥ ዘንድ ፥ መልካም ፥ ነው ÷ እርሱም ፥ በእነርሱ ፥ ደስ ፥ ይለዋል ፤ ወይስ ፦ የፍርድ ፥ አምላክ ፥ ወዴት ፥ አለ ? በማለታችሁ ፥ ነው ።

ምዕራፍ ፥ ፫ ።

፩ እነሆ ÷ መልእክተኛዬን ፥ እልክለሁ ÷ መንገድንም ፥ በፊቴ ፥ ያስተካክላል ፤ እናንተም ፥ የም ትፈልጉት ፥ ጌታ ፥ በድንገት ፥ ወደ ፥ መቅደሱ ፥ ይመጣል ፤ የምትወድዱትም ፥ የቃል ፥ ኪዳን ፥ መልእክተኛ ÷ እነሆ ÷ ይመጣል ÷ ይላል ፥ የሠራ
፪ ዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ። ነገር ፥ ግን ፥ እርሱ ፥ እንደ ፥ እንጥረኛ ፥ እሳትና ፥ እንደ ፥ አጣቢ ፥ ሳሙና ፥ ነውና ፥ የሚመጣበትን ፥ ቀን ፥ መታገሥ ፥ የሚችል ፥ ማን ፥ ነው ? እርሱስ ፥ በተገለጠ ፥ ጊዜ ፥ የሚቆም ፥ ማን ፥ ነው ? እርሱም ፥
፫ ብርን ፥ እንደሚያነጥርና ፥ እንደሚያጠራ ፥ ሰው ፥ ይቀመጣል ÷ የሌዊንም ፥ ልጆች ፥ ያጠራል ÷ እንደ ፥ ወርቅና ፥ እንደ ፥ ብርም ፥ ያነጥራቸዋል ፤ እነርሱም ፥ ለእግዚአብሔር ፥ በጽድቅ ፥ ቍርባንን ፥ የሚያቀርቡ ፥ ይሆናሉ ። እግዚአብሔርም ፥ እንደ ፥ ዳሮው ፥ ዘመንና ፥ እንደ ፥ ቀደሙት ፥ ዓመታት ፥ በይሁዳና ፥ በኢየሩሳሌም ፥ ቍርባን ፥ ደስ ፥ ይለዋል ። ለፍርድ ፥ ወደ ፥ እናንተ ፥ እቀርባለሁ ፤ በመተተኞችና ፥ በአመንዝሮች ÷ በሐሰትም ፥ በሚምሉ ÷ የምንደኛውን ፥ ደመወዝ ፥ በሚከለክሉ ÷ መበለቲቱንና ፥ ድሀ ፥ አደጉን ፥ በሚያስጨንቁ ÷ የመጻተኛውንም ፥ ፍርድ ፥ በሚያጣምሙ ÷ እኔንም ፥ በማይፈሩ ፥ ላይ ፥ ፈጣን ፥ ምስክር ፥ እሆንባቸዋለሁ ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ። እኔ ፥ እግዚአብሔር ፥ አልለወጥም ፤ እናንተ ፥ የያዕቆብ ፥ ልጆች ፥ ሆይ ÷ ስለዚህ ፥ የጠፋችሁ ፥ አይደላችሁም ።
፯ ከአባቶቻችሁ ፥ ዘመን ፥ ጀምሮ ፥ ከሥርዓቴ ፥ ፈቀቅ ፥ ብላችኋል ÷ አርስዋንም ፥ አልጠበቃችሁም ። ወደ ፥ እኔ ፥ ተመለሱ ÷ እኔም ፥ ወደ ፥ እናንተ ፥ እመለሳለሁ ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ። እናንተ ፥ ግን ፦ ምንመለሰው ፥ በምንድር ፥ ነው ? ብላችኋል ። ሰው ፥ እግዚአብሔርን ፥ ይሰርቃልን ? እናንተ ፥ ግን ፥ እኔን ፥ ሰርቃችኋል ። እናንተም ፦ የሰረቅንህ ፥ በምንድር ፥ ነው ? ብላችኋል ። በአሥራትና ፥ በበኵራት ፥ ነው ። እናንተ ÷ ይህ ፥ ሕዝብ ፥ ሁሉ ÷ እኔን ፥ ሰርቃችኋልና ፥ በእርግማን ፥ ርገሞት ፥ ናችሁ ። በቤቴ ፥ ውስጥ ፥ መብል ፥ እንዲሆን ፥ አሥራቱን ፥ ሁሉ ፥ ወደ ፥ ጎተራ ፥ አግቡ ፤ የሰማይንም ፥ መስኮት ፥ በልከፍትላችሁ ÷ በረከትንም ፥ አትረፍርፌ ፥ ባላፈስስላችሁ ፥ በዚህ ፥ ፈትኑኝ ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ። ስለ ፥ እናንተ ፥ ነቀዙን ፥ አገሥጻለሁ ÷ የምድራችሁንም ፥ ፍሬ ፥ አያጠፋም ፤ በእርሻችሁም ፥ ያለው ፥ ወይን ፥ ፍሬውን ፥ አያረግፍም ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ። የተድላ ፥ ምድር ፥ ትሆናላችሁና ፥ አሕዛብ ፥ ሁሉ ፥ ብፁዓን ፥ ብለው ፥ ይጠሩአችኋል ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ።
፲፫ ቃላችሁ ፥ በእኔ ፥ ላይ ፥ ድፍረት ፥ ሆኖአል ÷ ይላል ፥ እግዚአብሔር ። እናንተ ፥ ግን ፦ በእንተ ፥ ላይ ፥ ደፍረን ፥ የተናገርነው ፥ በምንድር ፥ ነው ? ብላችኋል ። እናንተም ፦ እግዚአብሔርን ፥ ማገልገል ፥ ከንቱ ፥ ነው ፤ ትእዛዙንስ ፥ በመጠበቅ ÷ በሠራዊት ፥ ጌታ ፥ በእግዚአብሔር ፥ ፊት ፥ ኀዘንተኞች ፥ ሆነን ፥ በመሄድ ፥ ምን ፥ ይረባናል ? አሁንም ፥ የሚታበዩትን ፥ ሰዎች ፥ ብፁዓን ፥ ብለን ፥ እንጠራቸዋለን ፤ ክፉንም ፥ የሚሠሩ ፥ ጸንተዋል ፥ እግዚአብሔርንም ፥ ይፈታተናሉ ÷ ያመልጣሉም ፥ ብላችኋል ።
፲፮ የዚያን ፥ ጊዜ ፥ እግዚአብሔርን ፥ የሚፈሩ ፥ እርስ ፥ በእርሳቸው ፥ ተነጋገሩ ፤ እግዚአብሔርም ፥ አደመጠ ÷ ሰማም ÷ እግዚአብሔርንም ፥ ለሚፈሩ ፥ ስሙንም ፥ ለሚያስቡ ፥ የመታሰቢያ ፥ መጽሐፍ ፥ በፊቱ ፥ ተጻፈ ። እኔ ፥ በምሠራበት ፥ ቀን ፥ እነርሱ ፥ የእኔ ፥ ገንዘብ ፥ ይሆናሉ ÷ ይላል ፥

የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ፥ ሰውም ፥ የሚያገለግለውን ፥ ልጁን ፥ እንደሚምር ÷ እንዲሁ ፥
፲፰ እምራቸዋለሁ ። ተመልሳችሁም ፥ በጻድቁና ፥ በኃጢአተኛው ፥ መካከል ÷ ለእግዚአብሔር ፥ በሚገዛውና ፥ በማይገዛው ፥ መካከል ፥ ትለያላችሁ ።

ምዕራፍ ፥ ፬ ።

፩ እነሆ ÷ እንደ ፥ ምድጃ ፥ እሳት ፥ የሚነድድ ፥ ቀን ፥ ይመጣል ፤ ትዕቢተኞችና ፥ ኃጢአትን ፥ የሚሠሩ ፥ ሁሉ ፥ ገለባ ፥ ይሆናሉ ፤ የሚመጣውም ፥ ቀን ፥ ያቃጥላቸዋል ÷ ሥርንና ፥ ቅርንጫፍንም ፥ አይተውላቸውም ÷ ይላል ፥ የሠ
፪ ራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ። ነገር ፥ ግን ፥ ስሜን ፥ ለምትፈሩት ፥ ለእናንተ ፥ የጽድቅ ፥ ፀሐይ ፥ ትወጣላችኋለች ÷ ፈውስም ፥ በክንፎችዋ ፥ ውስጥ ፥ ይሆናል ፤ እናንተም ፥ ትወጣላችሁ ÷ እንደ ፥ ሰባም ፥ እምቦሳ ፥ ትፈነጫላችሁ ።
፫ በምሠራበት ፥ ቀን ፥ በደለኞች ፥ ከእግራችሁ ፥ ጫማ ፥ በታች ፥ አመድ ፥ ይሆናሉና ፥ እናንተ ፥ ትረግጡአቸዋላችሁ ÷ ይላል ፥ የሠራዊት ፥ ጌታ ፥ እግዚአብሔር ።
፬ ለእስራኤል ፥ ሁሉ ፥ ሥርዓትንና ፥ ፍርድን ፥ አድርጌ ፥ በኮሬብ ፥ ያዘዝሁትን ፥ የባሪያዬን ፥ የሙሴን ፥ ሕግ ፥ አስቡ ። እነሆ ÷ ታላቁና ፥ የሚ
፭ ያስፈራው ፥ የእግዚአብሔር ፥ ቀን ፥ ሳይመጣ ፥ ነቢዩን ፥ ኤልያስን ፥ እልክላችኋለሁ ። መጥቼም ፥ ምድርን ፥ በእርግማን ፥ እንዳልመታ ፥ አርሱ ፥ የአባቶችን ፥ ልብ ፥ ወደ ፥ ልጆች ÷ የልጆችንም ፥ ልብ ፥ ወደ ፥ አባቶች ፥ ይመልሳል ።